የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች
የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት
ዓመታዊ ሪፖርት

ጥረዝ 1

ግንቦት/2007

አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ 1
2. ኦዲት በተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተገኙ
   ዋና ዋና ግኝቶች የተጠቃለለ ሪፖርት /Summery Report 4
3. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በዘርፍ የተጠቃለለ
   ኦዲት ሪፖርት
   3.1 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን 40
   3.2 የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች 110
   3.3 የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች 133
   3.4 የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤቶች 179
   3.5 የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች 257

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የልዩ ልዩ የመንግስት መ/ቤቶች

የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

ዓመታዊ ሪፖርት

I. መግቢያ

የዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስተ አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጡት ሕጎች፣ በአስፈጻሚው አካል በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የፋይናንስና ህጋዊነት፣ የክዋኔና የአካባቢ ጥበቃ፣ ኦዲቶች እና ልዩ ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳበ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ/ስታንዳርድ/ ማውጣትና ተግባሪዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጐማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፡
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አሰፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥትና የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል አስፈላጊውንም ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣

ይህንኑ ስልጣን መሰረት በማድረግ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ለፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በእንጌጅሜንት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በ4 ዘርፍ በተደረጁ የኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፡- የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፤ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፤ የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች እና የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች እና በ2 የክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፤ እንዲሁም በክልል መንግስታት የተከናወነው የመሰረትዊ አገልገሎቶች ከለላ ድጋፍ /PBS/ ተከታታይ ኦዲት ለማከናወን በ1 የድጋፍና ድጎማ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በመደራጀት የኦዲቱ ስራ ተከናውኗል፡፡

ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በሪፖርት ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፣ ኦዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን፣ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም በተከታታይ ኦዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የኦዲት ሥራ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉ ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የፌዴራል መ/ቤትና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡

መ/ቤታችን በሚከተለው የኦዲት ጊዜ አቆጣጠር ከጥር1/2006 እስከ ታህሣሥ 30/2007 ዓ.ም የ133 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ በመከናወን የኦዲት ሪፖርቶቹ ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶችና ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል።

II. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

ኦዲት በተደረገ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉድለቶች በዚሁ ጥራዝ ከገጽ 39 ጀምሮ በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አንጻር የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

1.1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ4 መ/ቤቶች ብር 79,241.55 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንደሚገኝ ተውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 6 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል የሚታይ ልዩነት በ7 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 490,647.11 በማነስ የሚታይ ሲሆን ፣ በአንድ መ/ቤት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን /ክሬዲት የሚታይ መሆኑ ታውቋል ፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 7 እና 8 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነትም ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ

(ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ20 መ/ቤቶችና ለተለያዩ መ/ቤቶች ተጠሪ የሆኑ በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ- 8/ሀ - ሰ ተመልክቷል፡፡/ ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያየዝ ጉድለቶች፤

- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከር መሆኑ፤
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ/የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ተደርጓል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ መሆኑ፤
- በባንክ ሂሣብ ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች የገቢ ደረሰኝ አለማዘጋጀትና አለመመዝገብ፤
- የተሰበሰበውን ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ አለማድረግ፤የተለያዩ ቼኮችና ባንክ በሒሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ እና በሌጀር ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- ለልዩ ልዩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ያለማስፈቀድ እና ከተፈቀደውም በላይ በሳጥን ማስቀመጥ ወይም በግዥ ሠራተኞች እጅ እንዲያዝ መደረጉ፤
- በካዝና እንዲቀመጥ ከተፈቀደው የጥሬ ገንዘብ በላይ ከፍተኛ ገንዘብ በሳጥን የሚያስቀምጡ መ/ቤቶች መኖራቸው ፣
- የተለያዩ ቼኮችና ባንክ በሒሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ እና በሌጀር ላይ ያልመዘገቡ፤
- በ8 መ/ቤቶች ብር 14,920,449.76 ከክፍያ መመሪያ ውጪ በመመሪያው ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ ያደረጉ መሆኑ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ

ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፤ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ፤ እንዲሁም በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1. በደንቡ መሰረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኘባቸው መ/ቤቶች

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ78 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 2,025,166,722.71 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /በዝርዝሩ በአባሪ-9 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	687,904,623.73
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		866,529,560.55
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		267,354,369.34
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		203,378,169.09
ጠ/ድምር	ብር	2,025,166,722.71

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት፤ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 666,440,245.66፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 433,466,219.10፣ የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ማስተባበሪያ ብር 174,399,737.92 ፤የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 144,266,244.06፤

ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 102,154,467.22፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 77,514,902.99፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 64,943,966.34፣ የግብርና ሚ/ር ብር 64,408,202.66፤ እና ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 39,294,784.18 ይገኙበታል፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2. በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- ለተሰብሳቢ ሂሳብ ሌጀር ያልተዘጋ በ3 መ/ቤቶች ብር 111,803,250.27 መገኘቱ ፣
- ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው በ4 መ/ቤቶችና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 6,414,090.56 መሆኑ፣
- በ3 መ/ቤቶች እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤትና 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 11,819,456.35 ከማን እንደሚሰበሰብ መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ በመሆኑ፣ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣

- በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው አላግባብ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘ በ4 መ/ቤቶች ብር 70,399,565.48 መገኘቱ፣
- ያልተሰበሰበ የቅድሚያ ክፍያ በ2 መ/ቤቶች ብር 4,977,146.17 መገኘቱ፣
- በ1 መ/ቤት በሪፖርት በብልጫ የተያዘ ቅድሚያ ክፍያ (የሂሳብ መደብ 4253) ብር 1,361,719.89 መገኘቱ
  ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ዝርዝራቸው በአባሪ-10 ሀ እስከ ሰ ተመልክቷል።

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ/እንዲሰበሰቡ፤ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግለቸው፤ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

3.1 <u>በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ ተገኘ ሂሳብ</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ25 መ/ቤቶችና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ አስራ አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 176,939,859.99 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-12 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	148,034,104.83
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		10,680,464.83
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		18,212,198.44
ድምር	ብር	176,939,859.99

በአዋጁ ደንብና መመሪያው በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ብር 118,073,560.67 ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 17,332,974.61፣በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 9,960,926.18 ፣ በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት ብር 7,633,367.06 እና በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት ብር 7,507,248.72 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Coustom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖሪት የመጫኛ ማራገፊና ኢንሹራንስ ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግበር እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች ወሳኝ ስለሆነ፤ ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ሕግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበው ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልገሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስሩ ባሉ ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች 12 መ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ፣ቅጣት እና ከውዝፍ የዱቤ ሽያጭ መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 1,039,493,043.58 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-11 ተመልክቷል/

ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 354,731,428.16 (ከተወረሱ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ ከጅንአድና አዲስ ፋና ያልተሰበሰበ)፣ በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ብር 194,121,340.97፣ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 160,697,495.76 ፣ በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት ብር 44,990,059.02 እና በመቐለ ዩኒቨርሲቲ ብር 43,092,521.89 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በውዝፍ የሚታየው ገቢም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው፣ ህንፃዎች በውላቸው ላይ በተገለፀው የግዜ ገደብ ባለመጠናቀቃቸው ላደረሱት የጉዳት ካሳ እና ውዝፍ የቤት ኪራይ ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቅሬታ ሰሚ ውሳኔ ሰጥቶባቸው ለበርካታ ዓመታት ያልተሰበሰበ ውዝፍ ግብር እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ መሆኑ ተውቋል ፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢ እርምጃ በመውሰድ የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለየመ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ አራት ቅ/ጽ/ቤቶች፣ 1 ተጠሪ ጽ/ቤት እና በ12 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 265,302,012.62 እና በሌሎች 8 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የገቢ ሂሳብ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ የትራንስፖርት ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት መካተት እንዳለበት በተደነገገው ከጅቡቲ ወደብ እስከ ቅ/ጽ/ቤቱ ደረቅ ወደብ ድረስ ለተጓጓዙበት የተከፈለውን ሂሳብ የሚያሳይ የትራንስፖርት ደረሰኝ(Inland freight invoice) ከዲክላራሲዎኑ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑና ተፈላጊ መረጃዎች በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ በመሆኑ፤ብዛት ያላቸው ከፋዮች ባንክ ገቢ ያደረጉት ገንዘብ በጥቅል በአንድ ቅጠል የገቢ ደረሰኝ የሚዘጋጅለት መሆኑና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነተ ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-13 ሀ እና ለ ተመልክቷል/

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 የውስጥ ገቢን ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሒሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 72,072,130.37 ባቀረቡት

ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /የዝርዝሩ በአባሪ-15 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች ብር		28,178,903.75
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		43,893,226.62
በድምር	**ብር**	**72,072,130.37**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ በሁለት መ/ቤቶች ስር የሚገኑ አራት ቅ/ጽ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለፀ ከዋናው መ/ቤት ለሚላክለቸው ገንዘብ የገቢ ደረሰኝ የማያዘጋጁ መሆኑ ታውቋል። በተጨማሪም አንድ መ/ቤት/ መቐለ ዩኒቨርሲቲ ያለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፍቃድ የገቢ ደረሰኝ በማሳተም ብር 12,879,067.34 ገቢ የሰበሰበ መሆኑ ተውቋል። /ዝርዝሩ በአባሪ-14 እና 14/1 እና 15 ተመልክቷል/

ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣፋ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስበቸውን ገቢ ሕገዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም እንዲሰበስቡና የገቢን ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች

በመንግሥት ሥም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜው

ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ በፈሰስ/ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ15 መ/ቤቶች ብር 41,374,483.14 ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ /ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ-16 ተመልክቷል/

በመሆኑም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ ፈስስ መሆን እንዳለበት፤ለወደፊቱም በሚሰበሰቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.6 <u>በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ሰልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

በገቢዎችና ባላስልጣንና ቅጽ/ቤቶች

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፣ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 35 መሠረት ለመንግሥት መ/ቤት በስህተት ገቢ የተደረገ ሂሣብ መኖሩ ሲረጋገጥ ገንዘቡ ለባለመብቱ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

  ይሁን እንጂ በ2006 በጀት ዓመት በናሙና ከታዩት ውስጥ -

  - በከምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ብር 2,630,021.95

- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር1,504,337.85
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 582,757.62
- በመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ብር 635,835.15

በድምሩ ብር 5,352,952.57 በስህተት ተሰብስቦ የነበረ ቀረጥና ታክስ ሂሳብ ተመላሽ ቢደረግም፣ አስቀድሞ በገቢ የተመዘገበና ለከፋዩ ተመላሽ የተደረገው ሂሳብ ማስተካከያ ሳይደረግበት በዘመኑ የተሰበሰበው ትክክለኛ ገቢ ጋር ተዳምሮ እየተመዘገበ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም የመንግስት ገቢ የወጡትን የገቢ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ በገቢው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

- በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እና በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት የጉምሩክ ስነስርአት አፈፃፀምና ፈቃድ አሰጣጥ የተጠቃለለ መመሪያ ቁጥር 86/2005 ንዑስ ክፍል አራት(19) መሰረት የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ከቀረጥ ነፃ ባስገቡት ጥሬ እቃ ላይ ተገቢውን ምርት ለውጪ ገበያ እያቀረቡ ለመሆኑና በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ባላዋሉት ጥሬ እቃ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- የቀረጥ መጠኑ ብር 28,252,497.56 የሆነ ጥሬ እቃ በቫውቸር ስርአት ከቀረፅ ነፃ ገብቶ በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ቢሆንም በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው የቀረጥ መጠን ያልተሰበሰበ መሆኑን፣
- የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋው ብር 2,905,137.04 የሆነ ጥሬ እቃ በቫውቸር ስርአት ከቀረፅ ነፃ ገብቶ በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ቢሆንም በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው የቀረጥ መጠን ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋው ብር 700,946.29 የሆነ ጥሬ እቃ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ ቢሆንም ያልተወራረደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ከቀረጥ ነፃ በገባው ጥሬ እቃ ልክ ምርት ለውጪ ገበያ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

➢ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 አንቀጽ 86 እንዲሁም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/2002 አንቀጽ 26 በአንድ የሂሳብ ግዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ግዜ ሂሳቡን ለታክስ ባለስልጣኑ ማስታወቅ እንዳለበት ደደነግጋል፡፡በዚህ መሰረት ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን እየተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ማጣራት በናሙና ከታዩት ውስጥ፡-

- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል በታክስ ከፋየይነት ተመዝግበው ነገር ግን ከተመዘገቡበት ጊዜ አንስቶ ወደ ታክስ ማዕከሉ መጥተው የማያሳውቁ 329 ግብር ከፋዮች እንዲሁም በተደጋጋሚ ባዶ / Nil / የሚያሳውቁ 88 ግብር ከፋዮች መኖራቸው ፡፡
- በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ለገቢ ግብር፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስና ለተርን ኦቨር ታክስ ተመዝግበዉ ገቢያቸውን በወቅቱ የማያሳዉቁና ግብርም የማይከፍሉ እንዲሁም ገቢያቸውን ማሳወቅ ያቆሙ 6 ግብር ከፋዮች መኖራቸው ፡፡
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ለገቢ ግብር፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስና ለተርን ኦቨር ታክስ ተመዝግበዉ ገቢያቸውን በወቅቱ የማያሳዉቁና ግብርም የማይከፍሉ እንዲሁም ገቢያቸውን ማሳወቅ ያቆሙ 27 ግብር ከፋዮች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው በመንግስት ተቋም ከተቀጠሩ ሰራተኞች የሚፈለግባቸውን የወጪ መጋራት አሰሪው መስሪያ ቤት በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እየሰበሰበ ገቢ እያደረጉ ለመሆኑ የሚከታተልበት ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 43(ሀ) መሰረት ማንኛውም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በማናቸውም ሁኔታ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ የበለጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲይዝ አይፈቀድለትም፡፡ ነገር ግን በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከቢረ ኢንተርፕራይዝ ሀላ/የተ/የግል/ማህ አዋጁ በማይፈቅደው አኳኋን አንድ ግብር ከፋይ ሁለት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በባህር ዳር የቅ/ፅ/ቤት በኩል የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች ያሳወቁት ወርሃዊ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሽያጭ መጠን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ የባህር ዳር ጨርቃ-ጨርቅ ፋብሪካ አ.ማ የሀምሌ እና የነሐሴ ብር 12,098,238.87 እንዲሁም የመስከረም፤ የጥቅምት፤ የህዳር እና የታህሳስ በባለስልጣኑ የታተመ ደረሰኝ የተሰበሰበ ሽያጭ ብር 603,950.43 በጠቅላላው የብር 12,702,189.30- summery report ባለመቅረቡ የሽያጩን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ ሀ-ለ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 ክፍል 7 ንዑስ አንቀጽ 26 ተራ ቁ. 1 ሀ እያንዳንዱ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ግብር ባለስልጣኑ ዘንድ በመቅረብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ ወይም ባለስልጣኑ ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም ማስታወቅ እና ለእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ የተሰጠውን የመጨረሻ ታክስ መክፈያ ጊዜ ገደብ ጠብቆ ለባለስልጣኑ ለወከለው ሰው ከገቢ ማስታወቂያው ጋር በአንድነት ታክሱን መክፈል አለበት በሚለው መሰረት የቅርጫፍ ጽ/ቤቱ የግብር ከፋዮች የ2006 በጀት ዓመት የተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል ማሳወቀቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ቁጥራቸው 21 የሆኑ ድርጅቶች የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ በግብር ከፋዮች

ፋይል ውስጥ ባለመገኘቱ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት አልተቻለም።

- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የሊሙ ሊበን የመጋቢት ወር የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቀና በፋይሉ ውስጥ ያልተገኘ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ቁጥራቸው 9 የሆኑ ድርጅቶች የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ በግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ ባለመገኘቱ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት አልተቻለም፡፡

ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

- በ4 መ/ቤቶች ብር 21,509,145.55 /ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቷል/ ለመንግስት ገቢ መሆን ያለበት ከተቋራጮች ያልተሰበሰበ የመቀጫ ሂሳብ/የጉዳት ካሳ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በ2 መ/ቤቶች ብር 16,727,198.50 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ /ያልተሰበሰበ/ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 31/1 ተመልክቷል/
- የአለርት ማዕከል በ2005 በጀት ዓመት ከግል የህክምና አግልግሎት ከሰበሰበው ገቢ ውስጥ የማዕከሉን ድርሻ 15% ለሆስፒታሉ ገቢም፣ ፈሰስም ያላደረገ ሲሆን፣ በዚህ በጀት ዓመት በተመሳሳይ ሁኔታ የማዕከሉን ድርሻ ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤

- የማዕድን ፍቃድ አውጥተው ማዕድን በማምረት ላይ ከሚገኙ ግብር ከፋዮች ውስጥ የሮያሊቲ ክፍያ 40 ከመቶ የክልሎች ድርሻ ለአፋርና ለኦሮሚያ ክልሎች እንዲሁም ለድሬዳዋ መስተዳደር የሮያሊቲ ድርሻ ክፍያ ሲፈጸም ገንዘቡ ለመድረሱ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 44,614,430.61 ለክልሎቹ የተከፈለው ሂሳብ ለመድረሱ የሚያሳይ ማረጋገጫ (ደረሰኝ) ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

- በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ገንዘብ የማይሰበሰቡ መሆናቸው፣
- የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሉ በበጀት ዓመቱ ከፈጸመው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 1,601,290.49 ላይ የሥራ ግብር ያልቀነስ እንዲሁም ለሆስፒታሉ የጤና ባለሙያዎች ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የተፈቀደው የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ከክፍያው ላይ የገቢ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፤
- ሌሎች 4 መ/ቤቶች የተለያዩ የገቢ አያያዝና አመዘጋገብ ችግር የሚታይባቸው መ/ቤቶች መሆኑ/በ አባሪ-18 ተመልክቷል/

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፤ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣ እንድሁም በገቢ አሰበሰሰብ ላይ የሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

4.1 <u>ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ20 መ/ቤቶች ብር 4,304,357,755.21 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገባና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 21 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	12,350,459.20
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		**155,026,185.24**
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች		1,871,866.24
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		4,135,109,244.53
ድምር	ብር	4,304,357,755.21

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው ዋናኛው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚሊተሪ ደመወዝና አበል የተከፈለ ብር 3,830,887,814.87፣ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር ብር 27,350,502.50 እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 273,845,378.34 ፣ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ብር 110,930,205.38፣ መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,443,824.20፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 11,599,720.78 እና ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ ብር 10,440,712.55 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የደመወዝ ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ በዝውውር የመጡ በጡረታ የተገለሉ እና በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሠራዊት አባላት ስም ዝርዝር ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ መ/ቤቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሠራዊት ደመወዝ ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ፤ ሌሎቹ የወጪ ሂሣቦች ለምሳሌ የመኪና ጥገና የነዳጅ ለማጣራት የመኪኖች ታርጋ የስልክ ቁጥሮችና የመሳሰሉት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል በኦዲት ወቅት መገለፁና የሌሎች መ/ቤቶችም ክፍያ የተፈጸመባቸው ደጋፊ የክፍያ ሰነዶችና ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላክው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰዉ የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር

ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በየመ/ቤቶቹ ተጠያቂነትን ከመስፈን አንጻር የማስረጃዎቹ ሚስጥራዊት በመንግስት ታምኖበት የትኞቹ እንደሆኑ በግልፅ ተለይቶ በሚስጢር እንዲያዙና ቀሪዎቹን የሂሳብ ማስረጃዎችን በአግባቡ በመያዝ ለኦዲት ሊያቀርቡ ይገባል።

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ29 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 368,002,429.66 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 20 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	1,930.20
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		35,979,753.81
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		95,445,380.45
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		236,579,225.60
ድምር		368,002,429.66

ሆኖ ተገኝቷል ።

ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣የቀረቡት

ደረሰኞች የገዥውን ማንነት እንዲሁም ቀኑንና ነዳጁ የተሞላላቸውን እጥበትና ግሪስ የተደረገለትን መኪና ሰሌዳ ቁጥሩን የማይገልጽ፣ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጉላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና የልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውንና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

4.3 <u>ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣በ47 መ/ቤቶችና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 53,360,272.59 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-22 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	1,049,682.39
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		49,673,916.01
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		2,298,031.22
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		293,642.97
ድምር	ብር	53,360,272.59

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባበ ከተፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 20,309,358.20፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብር 7,183,248.07 ፤ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 6, 864,329.08 ፤ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,971,271.40 ፣ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 3,392,102.00 የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ብር 3,286,245.49 እና የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ብር 3,168,957.57 ሲሆኑ፤ ከምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል

ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ፣ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች አበል ፣ደመወዝና ማበረታቻ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የሃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለዩኒቨርሲቲ የስራ አመራሮች ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት/ ከ1 እስከ 6 ወር/ የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባበ የተከፈለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ11 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 28,175,126.27 እና በ16 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 4,897,884.43 በጠቅላላው ብር 33,073,010.70 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 23 ተመልክቷል/ በተጨማሪም በ5 መ/ቤቶች ብር 37,792,667.88 በብልጫ የተመዘገበ ወጪና በ2 መ/ቤቶች ብር 282,783.78 በድጋሚ የተመዘገበ ወጪ ተገኝቷል።

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ዕደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ በድግሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈል፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰአት፤ለተለየያ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተተመነው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግና በብልጫ መመዝገብ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆንና ምዝገባውም አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.5 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ62 መ/ቤቶችና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 956,702,992.92 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 24 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	10,938,646.93
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		184,600,282.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		755,655,097.77
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		5,508,966.22
ጠ/ድምር	ብር	956,702,992.92

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 743,797,845.69 ፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 95,008,585.46 ፣ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 25,144,748.02 ፤ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 13,641,407.32 እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,791,692.29 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚሁ በተጨማሪ በ4 መ/ቤቶች የብር 9,120,451.76 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆኑ ድርጅቶች የአገልግሎት

ግዥ፤የተፈጸሙ መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩም በአባሪ-24/1 ተመልክቷል፡፡/

ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን የግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸሙ እና የተለያዩ ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ ብቻ መፈጸም የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም/ገቢም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

4.6 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶችና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በብር 6,802,769.45 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-25 እና አባሪ-25/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	1,269.00
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		3,222,404.66
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		2,609,367.38
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		969,728.41
ድምር	ብር	6,802,769.45

ከዚህም ውስጥ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 2,416,905.52 ፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,474,812.23 የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ብር 605,745.67 እና በፌዴራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዘርፍ ብር 499,871.83 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በተጨማሪም በ3 መ/ቤቶች 76,052,521.48 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው እንደሆነ ተውቋል። ከዚህም ውስጥ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 32,128,296.51፣ በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 41,189,738.68፣ እና በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ብር 2,734,486.29 ናቸው፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጠው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጠው ወጪ ተመጣጥኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዘው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.7 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ11 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 241,408,732.29 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 10 /ረ ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	12,126,710.24
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		130,334,104.66
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		98,947,917.39
ድምር	ብር	241,408,732.29

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ብር 129,633,744.23፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 93,820,097.01 ፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,541,896.06 ፤ እና አማኑኤል ሆስፒታል ብር 2,876,348.12 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.8 የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ28 መ/ቤቶችና በሁለት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 32,567,045.57 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 29 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	743,403.47
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		13,100,252.06
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		18,261,471.08
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		461,918.96
ድምር	ብር	32,567,045.57

የወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 11,978,865.61 ፣ የኢንዱስትሪ

ሚኒስቴር ብር 8,912,538.86 ፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ብር 4,520,703.09 እና የፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ብር 3,762,182.75 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.9 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ14 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 12,263,629.77 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2006 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -28 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	10,459,017.77
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		1,745,791.37
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		58,820.63
ድምር	ብር	12,263,629.77

ሲሆን ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 <u>በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ</u>

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና ሌሎች ወጪዎች የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች ብር 107,912,890.55 ከውስጥ ገቢ የተከፈለና የሌሎች ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ/ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-27 ተመልክቷል/

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 <u>በመስክ ላይ ለነበሩ የግንባታ ዕቃዎች (Material on Site) ክፍያ የተፈጸመ ስለመሆኑ</u>፤

በፌዴራል ግዥ አፈጻጸም መመሪያ በሳይት ላይ ያሉ ዕቃዎች በገንዘብ እንዲተካ የማይፈቀድ ቢሆንም በ6 መ/ቤቶች በሳይት ለሚገኙ ዕቃዎች ብር 76,063,137.72 ለተለያዩ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች በገንዘብ አላግባብ እንዲተካ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከዚሁ ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች

በ2 መ/ቤቶች ብር 16,727,198.50 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ/ ያልተሰበሰበ ብድር ሂሳብ እና በውል በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ግንባታውን በማያጠናቅቁት ተቋራጮች ላይ የጉዳት

የካሳ ጥያቄ በውሉ መሰረት በመቅረብ ቅጣት መሰበሰብ ሲገባቸው ይህንን እንደማያደርጉ ተውቋል።

ለግንባታ የቀረቡ ግብዓቶች ስራ ላይ ሳይውሉ ክፍያ መፈጸሙና ተቋራጮች ክፍያ ሲፈጸምላቸው ቀደም ሲል የተሰጠቸው ብድር ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸሙ ከውል በላይ ክፍያ እንዲፈጸም፣ የተሰጠ ብድርም እንዳይሰበሰብ ክፍተት ይፈጥራል።

በመሆኑም ያልተሰበሰበው የግንባታ ግብዓቶች ብድር እንዲሰበሰብ የወሰዱትን ግንባታ በወቅቱ በመያጠናቅቁ ተቀራጮች ተገቢው የጉዳት ካሳ በውሉ መሰረት እንዲጠየቅና የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል።

4.12 <u>በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

በወጪ ተመዘገበቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ4 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 12,037,955.78 እና በ4 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 16,145,008.22 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘቱ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-30 እና 30/1 ተመልክቷል/

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፤ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፤ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ይገኝበታል፡፡

አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገበ አሳስበናል።

5. <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

5.1. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ45 መ/ቤቶችና በሶስት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 973,746,519.63 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-32 / ሀ ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	471,753,684.35
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		107,526,920.03
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		339,929,947.33
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		54,535,967.92
ድምር	ብር	973,746,519.63

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 460,160,937.67 ፣ ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 330,805,868.99 ፤ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 43,306,907.03 ፤የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 71,434,198.75 እና ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,535,123.38 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ አስገዳጅ ሕጎች መሰረት ገቢ ሰብስበው የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ በ15 መ/ቤቶች ብር 41,374,483.14 መኖሩ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-16 ተመልክቷል/ የተከፋይ ሂሳቡ የሠራተኞች የጡረታ መዋጮንና በሌሎች የገቢ መሰብሰብ ግዴታዎች ምክንያት ተሰብስበው ለሚመለከተው አካል ያልተከፈሉትን ሂሳብ ይጨምራል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር የሰራዊት የደመወዝ ተከፋይ ብር 247,264,224.87 በተመለከተ የመከላከያ ሚ/ር ከተሰጠው ተልኮና ግዳጅ መነሻነት ደመወዛቸውን በወቅቱ ቀርበው ያልወሰዱ የሰራዊት አባላት ከተሰጣቸው ግዳጅ ሲመለሱ ያለእንግልት ደመወዛቸውን እንዲወሰዱ በማሰብ የመከላከያ ከፍተኛ ኃላፊዎች ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጋር በመነጋገር ደመወዛቸውን በግዳጅና በተለያየ ምክንያት ያለወሰዱ የሰራዊት አባላትን ደመወዝ ማሰቀመጫ መደቡ D የሆነ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እንዲከፈት ጠይቀው በቀን 09/10/1995 ዓ.ም. በቁጥር አሂመ1/7/47 ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተጻፈ ደብዳቤ ተፈቅዶ መከፈቱን ገልጸዋል፡፡ይሁን እንጂ ገንዘቡን አላግባብ ለሌላ አካል በማበደር

እየተጠቀመበት በመሆኑ ተገቢው ቁጥጥር ካልተደረገ ለግል ጥቅም ሊውል የሚችልበት ሁኔታ የሰፋ ነው፡፡

በሂሳብ መደብ 5021 በተከፋይ ሂሳብ የሚታየው ብር 1,831,070.50 በአየር ሀይል ጠቅላይ መምሪያ ለረጅም ጊዜ በምዝገባ የታየ ሂሳብና ተከፋይ ድርጅቱ ወይም ግለሰቡ ማን እንደሆነ በግልጽ የማያሳይና ገንዘቡም በጠቅላይ መምሪያው የባንክ ሂሳብ ውስጥ የማይገኝ ሲሆን ትክክለኛ የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አወቃቀር (Chart of Accounts) ባለመረዳት የተፈጠረ የምዝገባ ስህተት መሆኑን በመገንዘብ አስፈላጊውን ማጣራት እያደረግና ወደፊት በማጣራት በሂደቱ የምናገኛቸውን የምናሳውቃቹሁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ይህ ሂሣብ በመንግሥት የሂሣብ አሠራር መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጐ ጥያቄው ሲቀርብ የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴርን በመጠየቅ መከፈል ሲገባው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ለዓመታት ሳይከፈል መቀመጡ ገንዘቡም ለምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደተቀመጠ ለማወቅ የማያስችል በመሆኑና ለብክነት እንዲጋለጥ የሚያደርግ መሆኑን በመጥቀስ ሂሣቡ ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ እንዲደረግ፣ ጥያቄው ሲቀርብ ክፍያ እንዲፈጸም አሳስበናል።

የሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2. <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 164,658,370.51 መኖሩ፣
- በተከፋይ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ፤በ5 መ/ቤቶች ብር 42,641,122.73 መገኘቱ፣
- አላግባብ በዕዳ ወይም ተከፋይ ተብሎ የተያዘ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 19,683,605.46 መገኘቱ፣

- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ2 መ/ቤቶች ብር 2,534,141.80 መታየቱ፣
- የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በ3 መ/ቤቶች ብር 19,069,335.68 መኖሩና ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች ከተቀጽላ ሌጀር አዘጋጃጀትና አያያዝ ችግሮች እንደሚታባቸው ተረጋግጧል። /ዝርዝሩ በአባሪ-32 ለ እስከ ረ ተመልክቷል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

6. የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ37 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ በመደበኛ በጀት ብር 232,148,072.37 እና ከፒታል በጀት ብር 3,163,827.82 በድምሩ ብር 235,311,900.19 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	28,749,427.27
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		131,483,352.93
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		69,620,145.66
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		5,458,974.33
ጠ/ድምር	ብር	235,311,900.19

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች ፣ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 31,741,412.73 ፣ ሚዛን -ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 22,712,013.47 ፣ ዲላ ዩንቨርሲቲ ብር 16,422,282.30 ፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 14,825,649.05 እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 14,250,809.51 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ6 መ/ቤቶች ብር 38,473,539.74 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሳይፈቀድ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ ወጪ አድርገው የተጠቀሙ ሲሆን፣ ሌሎችሶስት መ/ቤቶች ብር 129,293,924.35 የበጀት ዝውውር ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ ከተመደበለት አርዕስት ውጭ የተጠቀሙ መ/ቤቶች መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀተ ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀተ እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 ያልተሰራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ99 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 1,027,319,514.59 እና ካፒታል ብር 1,549,338,191.03 በድምሩ ብር 2,576,657,705.62 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	453,820,282.97
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		173,840,330.75
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		738,777,713.43
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		1,210,219,378.47
ድምር	ብር	2,576,657,705.62

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ትምህርት ሚ/ር ብር 588,887,158.78 ፣ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 396,086,596.34 ፣ አርባ ምንጭ ዩ.204,362,089.53፣ የኢፌዲሪ ስፖርት ኮሚሽን ብር 195,186,880.58 ፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 94,374,733.95፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር 97,582,653.71 እና በደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲብር 88,024,688.01 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪም ሁለት መ/ቤቶች ከተፈቀደላቸው ከውስጥ ገቢ በጀት ሥራ ላይ ያልዋለ ብር 24,693,679.88 ተገኝቷል።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል ፣ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	22 መ/ቤቶች
›ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	18 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	11 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ	30 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	31 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	43 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	12 መ/ቤቶች
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	11 መ/ቤቶች
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው	6 ቅ/ጽ/ቤቶች
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ	6 መ/ቤቶች
ዋስትና በሚያስፈልጋቸዉ የስራ መደቦች ላይ የተመደቡ ሰራተኞች ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ ስለመሆኑ	6 መ/ቤቶች
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፤	2 መ/ቤቶች
ከዋናው ግምጃ ቤት በጥቅል ወጪ የሚደረጉ ንብረቶች/መድሓንቶች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር የማያደርጉ መ/ቤቶች	6 መ/ቤቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-34 / ሀ እስከ ቸ ተመልክቷል፡፡/

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አገጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከመችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይተል።

ሌሎች የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው 5 መ/ቤቶች ዝርዝራቸው በአባሪ-30/ሸ የተመለከተ ሲሆን፣ ችግሮቹ በየዘርፍ በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል ።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዘበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንም በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡

ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ20 መ/ቤቶች	192 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ23 መ/ቤቶች	247 ተሽከርካሪዎች
የተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ያልተቋቋመባቸው መ/ቤቶች	በ4 መ/ቤቶች	
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ1 መ/ቤቶች	4 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -35 ሀ እስከ መ ተመልክቷል/ በመሆኑም ም/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልገሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ /እንዲወገዱ፣ ሊብሬ የሌላቸው እንዲወጣላቸውና ሰሌዳ የሌላቸው እንዲወጣላቸው እንዲሁም የተሽከርካሪ ማህደር እንዲቋቋም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8. ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣
በ32 መ/ቤቶች እና 7 ቅ/ጽ/ቤቶች/ ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /ዝርዝሩ በአባሪ-36 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየመ/ቤቶቹና በየዘርፉ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡
በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል።

9. ልዩ ልዩ

9.1 የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት፣

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በዋናው ግቢ ከተማሪዎች ምግብ ቤት የሚሰበሰበው ተረፈ ምግብ አያያዝና አወጋገድ በአካባቢ ጥበቃ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- በመደወላቡ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምግብ ማዘጋጃ ወጥ ቤት እጥብጣቢ እና የተማሪዎች ሽንት ቤት የሚወጣው ፍሳሽ ማስወገጃ በአግባቡ ስለማይሰራ በአባቢው መጥፎ ሽታ እያመጣ መሆኑ፣
- በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ እንደ የሽንኩርትና የድንች ልጣጭ ያለና ከተማሪዎች ካፍቴሪያ የሚወጣ ትርፍራፊ ምግብ በመመገቢያ አዳራሽ አቅራቢያ በአግባቡ ባልተሰራ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦይ ውስጥ እየተደፋ በመሆኑ በአካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን እየፈጠረ መሆኑ፣ እንዲሁም የተማሪዎች ካፍቴሪያ የምግብ ማብሰያ አዳራሽ በአግባቡ የማይጸዳ መሆኑና ይህም በተማሪዎችና በሰራተኞች ላይ የጤና ችግር ሊያስከትል እንደሚችል፣

9.2 በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራቦርድ የተሸጡ የመንግስት ድርጅቶች የተጠቃለለ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ የማይዘጋጅ በመሆኑ የድርጅቶችን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ በመሆኑ መ/ቤቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በባለፉት በጀት ዓመታት በተከታታይ ኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በ2006 በጀት ዓመትም እርምጃ ያልተወሰደ በመሆኑ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በተደጋጋሚ የሚነሱትን የሰው ሃይልና

ሌሎች ችግሮች ለሚመለከተው አካል በመጠየቅና በማስፈቀድ ሥራው በማከናወን ዓመታዊ ሪፖርት ሊያዘጋጅ እንደሚገባ በላክነው የኦዲት ሪፖርት በድጋሚ አሳስበላል።

በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ስር በተለያዩ መጋዘኖች ከ18 ድርጅቶች ከተወረሱ ንብረቶች ውስጥ በናሙና ከታዩት መጋዘኖች ውስጥ 617 ዓይነት እቃዎች የሚገኙ መሆኑና በአብዛኛው ጣቃዎች፣ የተሰፉ ቱታዎች፣ ጥቅል ክሮች ፣ ሹራቦች፣ ጥቅል እና ብትን ጥጦች፣ የተለያየ ስፔር ፓርቶች እንዲሁም በጣም የተከማቹ ኬሚካሎች፣ መስሪያ ማሽኖች እና የመሳሰሉት የሚገኙ እና ሳይሸጡ ወይም ሳይወገዱ ለብዙ ዓመታት የቆዩ በመሆናቸው ጨርቆቹ በአይጥ ከመበላታቸው በተጨማሪ ኬሚካሎች በጸሀይ ደርቀው እና ተበላሽተው የሚገኙ መሆኑ፣ በሰነድ አስተዳደር እና ሰራተኛ ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ከሚፈርሱ ድርጅቶች የተረከባቸው የሰራተኞችን የግል ማህደሮች፣ የሂሳብ ሰነዶች፣ የመዝገብ ቤት ፋይሎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ ማንዋሎች እና የመሳሰሉት በ6 መጋዘኖች በመረከብ ለይቶ በመያዝ እና በማደራጀት ለተገልጋዮች ግልጋሎት እየሰጠ የሚገኝ ቢሆንም በኦዲት በታዩት 4 መጋዘኖች በተለይም በስላሴ መጋዘን የሚገኙት ሰነዶች መደርደሪያ ቢኖርም በቂ ባለመሆኑ እና ፋይሎች በመበታተናቸው በጎርፍ ሳቢያ፣እንዲሁም በንጽህና ጉድለት ምክንያት ተመልካች በማጣታቸው ብዙዎችም መደርደሪያቸው ተዛሞ ሊወድቅ በመድረሱ ከጥቅም ውጭ እየሆኑ መሆኑ እና በሌሎችም መጋዘኖች ተመሳሳይ ችግር ያላቸው ከመሆኑም በላይ በመጋዘን እጦት በየጆንያ ውስጥ ታስረው የሚገኙ በመሆኑ ለችግሮቹ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

የ2006 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 መሰረት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የ2006 በጀት ዓመት ሂሣብ በተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዋና መ/ቤት ፣ የአስራ ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶችንና የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

በዚህም መሰረት የባለስልጣን መስሪያ ቤቱን፣ 12 ቅ/ጽ/ቤቶችን (ማለትም የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የመቀሌ፣ የምስራቅ አዲስ አበባ፣ የሞያሌ፤ የድሬዳዋ፤ የከምቦልቻ፤ የአዋሳ፤ የባህርዳር፤ የአዳማ፣ የጂማ፤ የሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ እና የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤትን) እንዲሁም የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተጠቃለለ የ2006 በጀት አመት የሂሳብ እንቅስቃሴ ኦዲት ተደርጓል፡፡

በኦዲቱም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋና መ/ቤትና የ12 ቅ/ጽቤቶች እንዲሁም የ2006 በጀት ዓመት የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የጉምሩክ ገቢ ሂሳብ

1.1 የጉምሩክ ቀረጥና ታክስን በተመለከተ

ሀ) ትክክለኛው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ባለመወሰዱ ምክንያት ብር 1,516,976.97 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት አዘገጃጀትና ስርጭት አጠቃቀምን አስመልክቶ በወጣው መመሪያ ቁጥር 10/1996 (ከጥር 15/2006 በፊት ለተስተናገዱ ሰነዶች) መሰረት የገቢ ዕቃዎች ዋጋ ከጉምሩክ ሪከርድ መነሻ ዋጋ እና ማነጻጸሪያ ዋጋ አንፃር ተመሳክሮ ቀረጥና ታክስ መሰብሰብ እንዳለበት

ይደነግጋል። ከዚህ አንፃር ስራ ላይ ባለው የሲዲ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክሰ ባለመሰላቱ ምክንያት ምክንያት፡-

- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በከል ብር 764,615.85 እንዲሁም
- በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በአራት ዲ/ዮኖች ላይ ብር 752,361.12 ከሁለቱም

ቅ/ፅ/ቤቶች በድምሩ 1,516,976.97 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

<u>ስጋት</u>

መንግስት ከገቢ እቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበሰብ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በትክክለኛው የቀረጥ ማስከፊያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክሱ ባለመሰብሰቡ ምክንያት ያልተሰበሰበው ሂሣብ ብር **1,516,976.97** ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም በመመሪያው መሰረት ገቢ እቃዎች በትክክለኛው የቀረጥ ማስከፊያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክሱ የተሰላ ለመሆኑ የሚመለከታቸው ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትና የሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኦዲት ግኝቱ መሰረት ቀሪ ሂሳቡ መሰብሰብ ያለበት ስለሆነ እንዲሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ለ) <u>የትራንስፖርት ወጪና ሌሎች ወጪዎች በትክክል ባለመወሰዳቸው ምክንያት ብር 280,761.52 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ.</u>

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 39(1) መሠረት ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ እቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፊያ ዋጋ ሲወሰን ለእቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ላይ እቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ ክልል የመጀመሪያ

መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና፣ የኢንሹራንስ ወጪ መደመር እንዳለበት ይደነግጋል፡፡እንዲሁም ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በቁጥር 3.1.0/856 በ20/የካቲት/2006 በተላከው የመመሪያ ቁጥር 94/2006 አፈጻፀም ማብራሪያ መሰረት ከጅቡቲ እና ከሌሎች ክልሎች መግቢያ ወደቦች ተጓጉዞ ለሚመጡ እቃዎች ከመግቢያ ወደቦች እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው መግቢያ በር ድረስ እስከ መድረሻ የጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤቶች ወይም ደረቅ ወደቦች ያለውን ርቀት መሰረት በማድረግ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ መካተት ያለበትን የትራንስፖርት ወጪ ተሰልቶ መካተት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የትራንስፖርት ወጪ በትክክል በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ ባለመካተቱ ምክንያት፡-

- በኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ብር 188,171.56
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 35,615.44
- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 34,146
- በሞጆ ቅፅ/ቤት በኩል ብር 22,828.47 ባጠቃላይ ትክክለኛው የትራንስፖርት ወጪ እንዲሁም የኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ለቀረጥ ማስከፈያነት በትክክል ያልተካተቱ በመሆናቸው ምክንያት በድምሩ 280,761.52 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

ለቀረጥ ማስከፈያነት መካተት ያለበት ወጪ በትክክል የማይካተት ከሆነ መንግስት ከገቢ እቃዎች ሊሰበስብ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

በተፈጠረው ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበው የቀረጥ መጠን ብር 280,761.52 ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ትራንስፖርት እና ሌሎች ወጪዎች በትክክል የተካተተ ለመሆኑ የሚመለከታቸው የቅርንጫፍ ፅ/ቤት ሰራተኞች ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ብር 5,171.21 የተሰበሰበ መሆኑና ነገር ግን ያልተሰበሰበው ቀሪ ቀረጥና ታክስ ወደፊት ለግብር ከፋዮቹ ማስታወቂያ በማውጣት የሚሰበስቡ መሆኑን፣
- የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት እና የመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት የተጠየቀው ቀሪ ሂሳብ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የሚፈለገው ቀሪ ሂሳብ እንዲሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሐ) **<u>እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥርና የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ ባለመመደባቸው ምክንያት ብር 602,547.95 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ</u>**

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2009 አንቀጽ 45 (1) መሠረት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሠነው ምጣኔ መሠረት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ለዚህም እቃዎች በሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት መመደብ ያለባቸው ቢሆንም ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.code) እና በትክክለኛዉ የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ (CPC) ባለመመደባቸው ምክንያት፡-

- በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ብር 148,966.12
- በሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 101,956.05
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.code) ባለመመደባቸው ምክንያት ብር 2,401.24 እንዲሁም መለዋወጫዎችና አላቂ እቃዎች በትክክለኛው ጉምሩክ ስነስርአት ኮድ(CPC) ባለመስተናገዳቸው ምክንያት ብር 351,625.78 ባጠቃላይ እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥርና የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ መሰረት ባለመስተናገዳቸው ምክንያት ብር 602,547.95 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

መንግስት ከገቢ እቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር እና ጉምሩክ ስነስርአት ኮድ(CPC) ባለመመደባቸው ምክንያት ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ሂሳብ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም እቃዎች በሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት የተመደቡ ለመሆኑ የሚመለከታቸው ሰራተኞች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

የስራ አመራሩ ምላሽ

- የከምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ስራ አመራር ከሚፈለገው ቀሪ ሂሳብ ውስጥ ብር 109,135.83 የሰበሰቡ መሆኑን ፡፡
- የሞያሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ስራ አመራር የተገኘው ልዩነት ትክክል ስለሆነ ቀጣይ የዕቅዳቸው አካል አድርገው የሚሰበስቡ መሆኑን ፡፡
- የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር በቀረበው ግኝት መሰረት በዲ/ዮኖቹ ላይ የቀረበው ቀሪ ሂሳብ እንዲጣራ ለድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን በውስጥ ማስታወሻ ደብዳቤ የተላከ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

መ) **ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 214,071,013.16 መኖሩ**

ግኝት

በጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀጽ 6/1 እና 2 መሰረት የገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች አያያዝ ቡድን በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን በኩል የተጠየቁ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳቸውን ተከታትሎ እያስከፈለ ስለመሆኑና ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆኑ አስመጪዎችን ዝርዝር በመያዝ የንብረት መያዝ ስነ-ስርዓት እንዲፈጸም ለሚመለከተው የስራ ሂደት እያሳወቀ መሆኑንና ተጨማሪ የግብር ውሳኔውም በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል የቀሪ ሂሳብ የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣ ከ3(ሶስት) ወር እስከ 27 (ሀያ ሰባት) ወር የሆነው ሂሳብ በድምሩ ብር **7,672,325.68** ፡፡
- በመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል የቀሪ ሂሳብ የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ በአጠቃላይ ከ 3(ከሶስት) ወር እስከ 36 (ሰላሳ ስድስት) ወር የሆነው ያልተሰበሰበ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ብር **11,457,448.72**
- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣ ከሰባት ወር እስከ አስራ አንድ ወራት የሆነው ያልተሰበሰበ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ብር 6,596,606.57
- በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የቀሪ ቀረጥና ታክስ የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣ ከአንድ አመት ባላይ የሆነው በድምሩ ብር 400,980.88
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት በኩል እ.ኤ.አ.ከ2002 እስከ 2013 የተመዘገቡ ከአንድ ዓመት እስከ አስራ ሁለት ዓመት ያስቆጠሩ በድምሩ ብር 160,697,495.76
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የቀሪ ቀረጥና ታክስ የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣ ከስድስት ወር በላይ የሆነው በድምሩ ብር 10,077,794.24
- በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት በኩል የቀሪ ቀረጥና ታክስ የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣ ከ2 ዓመት በላይ የሆነው ሂሳብ ብር 8,518,532.06
- በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣ ከአምስት ወር እስከ ሃያ ሦስት ወራት ያስቆጠሩ ብር 8,649,829.25

በድምሩ ብር 214,071,013.16 የሚገኝ ሂሳብ መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

የገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን ውሳኔ መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ያለባቸውን አስመጪዎች ዝርዝር

በመያዝ ዕዳቸውን እንዲከፍሉ የማይከታተል ከሆነና የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በውሳኔው መሰረት ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑ አስመጪዎች ላይ በመመሪያ 69/2004 አንቀጽ 7/1 መሰረት የንብረት መያዝ ስነ-ስርዓቱ ተፈጻሚ እንዲሆን ዝርዝሩን ለንብረት ያዥ ኮሚቴ በማስተላለፍ ያልተሰበሰበው ግብር ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- በከምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ብር 1,290,778.65፣ በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት ብር 254,553.96፣ በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ብር 402,267.16 እና፣ የባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ብር 1,368,314.95 ተሰብስቦ ገቢ የተደረገ መሆኑን፣
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከሚፈለገው ሂሳብ ውስጥ ብር 85,031.18 የተሰበሰበ መሆኑ፤የብር 71,194.36 እዳ የተሻረ መሆኑ፤የብር 216543.60 እዳ ወደ ብር 15,562.20 የተሸሻለ መሆኑን ገልፀው ለቀሪው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ወደ ዓቃቢ ህግ ለማስተላለፍ በሂደት ላይ እንደሆኑ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
- የመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ግኝቱን በተመለከተ በርካታ ውዝፍ ዕዳ ባለባቸው ላይ የእግድ ትህዛዝ በማስተላለፍ በክትትል ላይ ሲሆን፣ በተጨማሪም ዕቃዎችን ገቢና ወጪ እንዳያደርጉ ሲስተም ላይ እንዲዘጋ የተደረገ መሆኑንና ክትትሉም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን
- የሞያሌ ቅ/ፅ/ ቤት ስራ አመራር ጉዳዩ በዋናው መስሪያ ቤት በክርክር ላይ ያለ በመሆኑ በወቅቱ ሊሰበሰብ አለመቻሉን በሰጡት ምላሽ የገለፁ ቢሆንም ነገር ግን ጉዳዩ በዋናው መስሪያ ቤት ደረጃ በክርክር ላይ ለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ ግን ሊቀርብ አልቻለም ፡፡
- የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ንብረታቸው እንዲያዝ ለኢንተለጀንስ ቡድን የተላለፈ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል ፡፡

ሠ) **<u>የትራንስፖርት ወጪ በትክክል ለቀረጥ ማስከፈያነት የተወሰደ ለመሆኑ ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ሰነዶች መኖራቸው</u>**

<u>ግኝት</u>

የገቢ እቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 94/2006ን አፈፃፀም ማብራሪያ መሰረት በመልቲ ሞዳል ስርአት ተጓጉዘው ወደ ሀገር ዉስጥ ለሚገቡ እቃዎች ከጅቡቲ እና ሌሎች የመግቢያ ወደቦች እስከ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤቶችና ደረቅ ወደቦች ላለው ርቀት የሚከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ተጠቃሎ የሚከፈል በመሆኑ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ መካተት ያለበት ከመግቢያ ወደቦች እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው መግቢያ በር ድረስ እና ከመግቢያ በር እስከ መዳረሻ የጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤቶች ወይም ደረቅ ወደቦች ያለውን ርቀት መሰረት በማድረግ የትራንስፖርት ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት መካተት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት የትራንስፖርት ወጪ በትክክል ለቀረጥ ማስከፈያነት የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከጅቡቲ ወደብ እስከ ቅ/ጽ/ቤቱ ደረቅ ወደብ ድረስ ለተጓጓዙበት የተከፈለውን ሂሳብ የሚያሳይ የትራንስፖርት ደረሰኝ(Inland freight invoice) ከዲክላራሲዮኑ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ፡-

- በመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል በሰነዶቹ የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር 11,235,761.48
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል በሰነዶቹ የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር 45,543,541.8
- በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በሰነዶቹ የተሰበሰበውን ብር 6,511,979.23 ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም ፡፡

<u>ስጋት</u>

የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋውን ለመወሰን መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች ሳይቀርቡ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ መንግስት ከገቢ እቃዎች ሊሰበስብ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ሊያደርገው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

ያልቀረበው መረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ያልተሰበሰበ የመንግስት ቀረጥና ታክስ ካለ እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- የመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኦዲት ግኝቱ ከተጠቀሱት ሰነዶች ውስጥ ሁለቱ ማለትም ዲ/ዮን ቁጥር C-90/14 እና C-148/14 መመሪያው ከመውጣቱ በፊት የገቡ ስለሆነ የተሰጠው አስተያየት በድጋሚ ቢታይ በቀሪዎቹ ሰነዶች ላይ የ inland freight ደረሰኝ እንዲያቀርቡ የሚጠይቁ መሆኑንና ማቅረብ ካልተቻለ ግን በመመሪያ ቁጥር 94/2006 አንቀፅ 14(3) መሰረት ቀሪ ሂሳቡን የሚሰበስቡ መሆኑን
- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ልዩነት የተገኘባቸውን ሰነዶች በማጥራት ብር 205,826.36 ተጨማሪ ሂሳብ የተሰበሰበ መሆኑን ፡፡
- በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ድርጅቱ መረጃዎችን እንዲያቀርብ ተጠይቆ ማቅረብ ያልቻለ መሆኑን በመውጫ ውይይት ወቅት ገልፀዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

የመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በዲ/ዮን ቁጥር C-90/14 እና C-148/14 ለተስተናገዱት ሰነዶች መመሪያው ከመውጣቱ በፊት የገቡ እቃዎች በመሆናቸው ግኝቱ እንደማይመለከታቸው የተገለፀ ቢሆንም ሰነዱ የተከፈተው(registration date) መመሪያው ከወጣ በኋላ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት መስተናገድ የነበረባቸው ስለሆነ የተሰጠው ምላሽ በእኛ በኩል ተቀባይነት የለውም፡፡

ረ) **የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር 15,339,299.93 ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ**

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 እና ይኸን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው የዋጋ መመሪያ መሰረት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ እቃዎች ዋጋ እየተሰጠ ቀረጥና

ታክሱ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ካየናቸው ውስጥ በተወሰነ ሰነዶች ላይ ከምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የገበያ ጥናት በማድረግ በሚል የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋውን ለመወሰን ማለትም፣

Fob value= MV *0.7--------------

(1+ እቃው ጠቅላላ የሚከፈልበት ቀረጥና ታክስ መጠን(Rate) +0.2+0.09)*0.85

የምንዛሬ መጠን

በመጠቀም ዋጋ እየተወሰነ መስተንግዶ የተሰጠ ሲሆን ዋጋውን ለመወሰን የተጠቀሙበት የስሌት ዘዴ በአዋጁም ሆነ አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ላይ ያልተገለፀ በመሆኑ በእቃዎቹ ላይ የተሰበሰበውን አጠቃላይ ቀረጥና ታክስ ብር 15,339,299.93 ትክክለኛት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት

ቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ የዋጋ ትመና በሚሠራበት ጊዜ የዋጋ አተማመን ዘዴው አዋጁ እና መመሪያው በሚያዘው መሰረት የሚሰራ ካልሆነ የሚሰበሰበው ቀረጥና ታክስ በመንግስት ገቢ ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር አልያም አስመጪውን ሊጎዳ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በአዋጁ ወይንም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ላይ ያልተገለጸ ፎርሙላ መጠቀሙ መንግስትን ወይንም ነጋዴውን ሊጎዳ የሚችል ውሳኔ ሊተላለፍ ስለሚችል የፎርሙላውን ትክክለኛነት የሚመለከታቸውን የባለስልጣን መ/ቤቱን ሀላፊዎች በማማከር ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ በማድረግ ስራ ላይ እንዲውል ካልተፈቀደ በስተቀር ፎርሙላውን መጠቀሙ አግባብ አይደለም፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሲሰራበት የነበረው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ስሌት አሰራር እንዲቋረጥ የተደረገ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሰ) <u>***ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ያለባቸው አስመጪዎች ላቀረቡት ቅሬታ ውሳኔ ያልተሰጠው ሂሳብ ብር 4,213,266.42 መኖሩ-***</u>

<u>*ግኝት*</u>

የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀፅ 5(1 እና 3) መሰረት በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ግኝት መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ ያለባቸው አስመጪ ድርጅቶች በተወሰነው ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን በወቅቱ ለጽ/ቤቱ በሚያቀርቡበት ጊዜ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ያቋቋመው የጉምሩክ ጉዳዮች አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታቸውን ተቀብሎ በ 10 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአስመጪዎች ማሳወቅ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስራው የሚሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል በድምሩ ለብር 4,213,266.42 ለተጠየቀ ተጨማሪ የግብር ዉሳኔ ላይ ለቀረበ አቤቱታ ውሳኔ ሳይሰጥ ከአንድ ወር እስከ 19 ወር (አመት ከሰባት ወር) የዘገየ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>*ስጋት*</u>

የጉምሩክ ጉዳዮች አጣሪ ኮሚቴ በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ተወስኖ ቅሬታ ለቀረበበት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በመመሪያው መሰረት ውሳኔውን ቶሎ የማይሰጥ ከሆነ የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላላ፡፡

<u>*የማሻሻያ ሃሣብ*</u>

በቅ/ጽ/ቤቱ የተቋቋመው የጉምሩክ ጉዳዮች አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታውን ተቀብሎ በመመሪያወ መሰረት በ 10 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአስመጪው በማሳወቅ ተጨማሪ የግብር ውሳኔው ቶሎ እንዲሰበሰብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

<u>*የሥራ አመራሩ ምላሽ.*</u>

ለብር 4,035,208.64 ለቀረበ አቤቱታ ታይቶ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሸ) **<u>በስህተት ተሰብስቦ የነበረ ቀረጥና ታክስ ሂሳብ ተመላሽ ቢደረግም ከገቢ ሂሳቡ ላይ ግን ተቀናሽ ያልተደረገ ብር 5,352,952.57 ሂሳብ መኖሩ</u>**

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፣ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 35 መሠረት ለመንግሥት መ/ቤት በስህተት ገቢ የተደረገ ሂሣብ መኖሩ ሲረጋገጥ ገንዘቡ ለባለመብቱ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በ2006 በጀት ዓመት ፡-

- በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ብር 2,630,021.95
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 1,504,337.85
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 582,757.62
- በመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ብር 635,835.15 የሆነ ሂሳብ አስቀድሞ በገቢ የተመዘገበና ለከፋዩ ተመላሽ የተደረገው ማስተካከያ ሳይደረግበት በዘመኑ የተሰበሰበው ትክክለኛ ገቢ ጋር ተዳምሮ እየተመዘገበ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

ቀደም ሲል በብልጫ የተሰበሰበ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ በሚደረግበት ጊዜ የሂሳብ ማስተካከያ የማይደረግለት ከሆነ ሪፖርት የሚደረገውን የገቢ መጠን ተመላሽ በተደረገው መጠን ከፍ ሊያደርገው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ በተለያያ ምክንያት በስህተት ተሰብስቦ የነበረው ገቢ ለባለመብቱ ተመላሽ ሲደረግ የገቢ ሂሳቡም በተመሳሳይ መልኩ ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- የኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፤የመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፤የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራሮች የቀረጥ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ አግባብነቱን በማረጋገጥ በቅ/ጽ/ቤቱ በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል ወደ ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ተጠይቆ በእነሱ በኩል እንደ በጀት ተመድቦ የሚመጣ እና ተመላሽ የሚደረግ መሆኑን በመግለፅ በቀጣይ በምን አይነት ሁኔታ ሂሳቡ መያዝ እንዳለበት ከዋናው መ/ቤት ጋር በመነጋገር ምላሽ ለመስጠት ጥረት የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
- የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር የቀረጥ ተመላሽ ክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቁጥር 7/መ/ታ/4/14 መስከረም 06/2007 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ የሚቀርበው የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ በበጀት ዓመቱ እና የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ከሆነ በምን መልኩ መፈፀም እንዳለበት የተገለፀ በመሆኑ በዚሁ መሰረት ለወደፊቱ ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ቀ) **<u>ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ቢጠናቀቅም ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 96,679,240.58 መኖሩ</u>**

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 54 እና 55 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መዉጣት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃው አገር ዉስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ዉስጥ እቃዉ ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና ያስያዘዉ ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከአዋጁ አንጻር በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግ መሆኑንና በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር በማይወጡት እቃዎች ላይ በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በጊዜያዊነት ለገቡት እቃዎች በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ የተጠናቀቀ በመሆኑ ምክንያት፡-

- በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 6,858,177.47
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 89,821,063.11 ባጠቃላይ በሁለቱም ቅ/ፅ/ቤቶች በኩል በድምሩ 96,679,240.58 በጊዜያዊነት ለገቡት እቃዎች በህግ የተወሰነዉ የመቆያ ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልሆነ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በጊዜዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ተመልሰው እስከሚወጡ ድረስ መረጃው በአግባቡ ተይዞ የቆይታ ጊዜያቸው ላይ ተገቢው ክትትል የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ እቃዎች መረጃው በአሲኩዳ ከሚመዘገበው ውጪ ኤክሴል ላይም ሆነ በሌላ ለክትትል ምንም አይነት ምዝገባ የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

ወደ አገር በገቡ እቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በአዋጁ መሰረት በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ መሆን አለበት፡፡ ለወደፊቱም በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ በአዋጁ መሰረት ተገቢዉ ቁጥጥርና እርምጃ ካልተወሰደ በጉምሩክ የቀረጥና ታክስ ገቢ አሰባሰብ ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት ከፍተኛ ይሆናል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የሚመለከታቸው አስመጪዎችና ዋስትና የሰጠው ድርጅት በወቅቱ ተጠይቀው ግዴታቸውን ባለመወጣቸው ጉዳዩ ለአቃቤ ህግ ተላልፎ በክትትል ላይ የሚገኝ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር በቦንድ አስተዳደር ማንዋል በሚያዘው መሰረት የቦንድ ሂሳብ ያለባቸውንና በቫውቸር ቦንድ መስተንግዶ ለተስተናገዱት የኢንሹራንስ ድርጅቶች የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተዘጋጅቶ የተላከላቸው መሆኑን እንዲሁም ያልተወራረዱ የኮንቴይነር መስተንግዶ የተሰጣቸው ደንበኞች ሂሳብን

የመከታተል ስራ እየተሰራና ለአቃቤ ህግ እየተላለፈ እንደሆነና የኢንሹራንስ ድርጅቶቹም እንዲከፍሉ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የተፃፈላቸው መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

- በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በተሰጠው አስተያየት መሰረት በኮምፒውተር እና በማኑዋል መዝገብ ተዘጋጅቶ እየተመዘገበ በመሰራት ላይ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

በ) <u>በዱቤ ሽያጭ ከተላለፉት የውርስ ዕቃዎች ውስጥ ሳይሰበሰብ ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ ሂሳብ ብር 354,731,428.16 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋገድ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 56/2003 አንቀጽ 16(1) መሰረት በተለያዩ አካላት በድርድር የሚሸጡ ዕቃዎችን የሽያጭ ገንዘብ ገዢዎች ዕቃውን በተረከቡ እስከ 45 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ ባለስልጣኑ በሚያሳውቀው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ወይም በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው በተጨማሪም በድርድር ለተሸጡ ዕቃዎች በተገለጸው ጊዜ ገንዘቡን ገቢ ያላደረገ ገዢ በዚሁ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የተገለጸው የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ ባለው ከፍተኛ ምጣኔ ወለድ እንደሚታሰብበት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ለጅንአድና ለአዲስ ፋና በዱቤ ሽያጭ ከተላለፉ እቃዎች በመመሪያው መሰረት ገንዘቡ በወቅቱ የሚሰበሰብ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- እስከ 30/10/2006 ድረስ ሳይሰበሰብ ከ 2 ወራት እስከ 6 ዓመት የቆየ የዱቤ ሽያጭ በድምሩ ብር 354,731,428.16 ሂሳብ መኖሩ፤
- መመሪያ ቁጥር 56/2003 ተግባራዊ እንዲሆን ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ በህግ የተገለጸው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ለተሰበሰበውም ገንዘብ ወለድ እየታሰበ ገቢ የሚደረግ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት

በዱቤ ለተሸጡ ዕቃዎች ክትትል እየተደረገ በወቅቱ ገቢው እንዲሰበሰብ የማይደረግ ከሆነ መንግስት ማግኘት የሚገባውን ገቢ በወቅቱ እንዳያገኝ ሊያደርው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሣብ

ያልተሰበሰበው ገንዘብ ወለዱን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ ችግር ሲሆን ይህን ችግር ለማቃለል ባለስልጣን መ/ቤቱ በ 2006 ዓ.ም ባደረገው ክትትል ከጅንአድና ከአዲስ ፋና ላይ ከነበረው ውዝፍ ገንዘብ ከብር 253,196,449.58 ውስጥ በ2007 ዓ.ም ግማሽ በጀት ዓመት ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ የተደረገ ሲሆን በውሉ መሰረት ወለድ ለመጠየቅና ውዝፉን በህግ ለማስከፈል የሚረዱ መረጃዎችን ማሰባሰብ የተጀመረ መሆኑን በመግለፅ በቀጣይም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ሥራ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ተ) ፈታሽና አሰሰር በሲስተም(አሲኩዳ) የማይመደብ መሆኑ

ግኝት፡-

የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ለማጥበቅ ሲባል ፈታሽና አሰሰር እንዲሁም የዲክላራሲዮኖች የስጋት ደረጃቸውም በሲስተሙ (አሲኩዳ) የሚመደብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ፈታሽ፣ አሰሰርና የስጋት ደረጃም በሲስተም አለመመደቡን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ፈታሽና አሰሰር እንዲሁም የስጋት ደረጃ በሲስተም ካልተመደበ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የዲክላራሲዎን የስጋት ደረጃ፤ አሰሰሮችና ፈታሾች በሲስተም ቢመደብ የቁጥጥር ስርዓቱን በጣም የተጠናከረ ስለሚያደርገው በሲስተም መስራቱ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ምንም እንኳን የሰው ሀይል በመደቡ ያለ ቢሆንም የተጀመረ ስራ ግን የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ይህም ሊሆን የቻለው የዋናው መስሪያ ቤት የስጋት ስራ አመራር በቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ እንዲጀመር በወቅቱ ኔትዎርክ አለመትከል፤ ሲስተም አለመዘርጋት እና ለሰራተኞች አጥጋቢ ስልጠና አለመሰጠቱ መሆኑን ገልፀው ከዋናው መስሪያ ቤት ጋር በመነጋገር ችግሩን የሚፈቱ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

2. የውጪ ንግድን በተመለከተ

ሀ) ጥሬ እቃ በቫውቸር ስርአት ከቀረጥ ነፃ ገብቶ ያልተወራረደ ብር 700,946.29 ሂሳብ

ግኝት

በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እና በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት የጉምሩክ ስነስርአት አፈፃፀምና ፈቃድ አሰጣጥ የተጠቃለለ መመሪያ ቁጥር 86/2005 ንዑስ ክፍል አራት(19) መሰረት የጉምሩክ ስነስርአት ተፈፅሞባቸው ከቀረጥ ነፃ በገቡ የምርት ግብአቶች በአዋጁ በተወሰነው ጊዜና ሁኔታ ለወጪ ምርት መዋላቸውን ለማረጋገጥ የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ ቫውቸር ከተሰጠበት ወይም ቫውቸሩ ከታደሰበት ቀን ጀምሮ በ11ኛው ወር የማወራረድ ጥያቄ በማቅረብ ማወራረድ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ከቀረጥ ነፃ ባስገቡት ጥሬ እቃ ላይ ተገቢውን ምርት ለውጪ ገበያ እያቀረቡ ለመሆኑና በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ባላዋሉት ጥሬ እቃ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች የቀረጥ

ማስከፈያ ዋጋው ብር 700,946.29 የሆነ ጥሬ እቃ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ ቢሆንም ያልተወራረደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ከቀረጥ ነፃ በገባው ጥሬ እቃ ልክ ምርት ለውጪ ገበያ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት

ድርጅቶቹ በቫውቸር ስርአት ከቀረጥ ነፃ ባስገቡት ጥሬ እቃ ምርት አምርተው ወደ ውጪ ለመላካቸው ቀርበው በአዋጁ በተቀመጠው ጊዜ የማያወራርዱ ከሆነ ከቀረጥ ነፃ የገባው ጥሬ እቃ አገር ውስጥ ለገበያ ሊውል የሚችል ከመሆኑም በላይ የገበያ ስርአቱን ሊያበላሽ ይችላል፡፡በተጨማሪም መንግስት በጥሬ እቃው ምርት ተመርቶ ወደ ውጪ በመላክ ሊገኝ የሚገባውን የውጪ ምንዛሬም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች ላይ አዋጁና ደንቡ በሚያዘው መሰረት ቅ/ጽ/ቤቱ ክትትል በማድረግ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ድርጅቱ ቀርቦ እንዲያወራርድ በደብዳቤና በስልክ እንዲያዉቁት የተደረገ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ለ) ጥቅም ላይ ባልዋለ ጥሬ እቃ ላይ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት መሆኑ

በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀፅ 10(3 እና 5) መሰረት በቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ወደ አገር የገባ ጥሬ እቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጪ ገበያ መላክ እንዳለበት ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጥሬ እቃውን ባህሪ መሰረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ አመት እንዲራዘም ሊፈቅድ እንደሚችል ነገር ግን የመጠቀሚያ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ወይም ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ 50 % እንዲከፍል እንደሚደረግ ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንፃር የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ባስገቧቸው ጥሬ እቃዎች ልክ

በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነ ምርት ለውጪ ገበያ የሚያቀርቡ መሆኑን ይህ ካልሆነ ግን ከቀረጥና ታክስ ነፃ አስገብተው ጥቅም ላይ ባላዋሉት ጥሬ እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-

- የቀረጥ መጠኑ ብር 28,252,497.56 የሆነ ጥሬ እቃ በቫውቸር ስርአት ከቀረፅ ነፃ ገብቶ በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ቢሆንም በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው የቀረጥ መጠን ያልተሰበሰበ መሆኑን፣
- የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋው ብር 2,905,137.04 የሆነ ጥሬ እቃ በቫውቸር ስርአት ከቀረፅ ነፃ ገብቶ በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ቢሆንም በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው የቀረጥ መጠን ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ አራትን ይመልከቱ)

ስጋት

ድርጅቶቹ በቫውቸር ስርአት ከቀረጥ ነፃ ባስገቡት ጥሬ እቃ ምርት አምርተው ወደ ውጪ ባላኳቸው ጥሬ እቃዎች ላይ ተገቢው ቀረጥና ታክስ የማይሰበሰብ ከሆነ መንግስት ከገቢ እቃዎች የሚያገኘውን ቀረጥና ታክስ የሚያጣ ከመሆኑም በላይ የገበያ ስርአቱንም ሊያበላሽ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በአዋጁና በደንቡ መሰረት በድርጅቶቹ ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ በእቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ከነቅጣቱ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ድርጅቶቹ ቀርበው ክፍያ ለመፈፀም ፍቃደኛ ባለመሆናቸው በህግ ተገደው ቀረጥና ታክሱን እንዲከፍሉና በህግ እንዲጠየቁ ለዓቃቢ ህግ ስራ ሂደት የተላለፈ እንደሆነና የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥም ለዋና መስሪያ ቤት የተላከ መሆኑንና ከኢንዱስትሪ ሚ/ር ጋርም በተደረገ ውይይት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ እንደሚሰጡ ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

3. የአገር ውስጥ ገቢ ሂሳብን በተመለከተ

ሀ) ያልተሰበሰበ ብር 6114157.93 ግብር መኖሩ

ግኝት

በየቅ/ጽ/ቤቱ ግብር ከሚከፍሉ ድርጅቶች ለናሙና ከመረጥናቸው ውስጥ የንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የአመቱ (የ2005 የግብር ዘመን) ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ የተጨማሪ እሴት ታክሰ ማስታወቂያ ላይ ከተገለጸው የአመቱ(የ2005 የግብር ዘመን) የ12 ወራት ጠቅላላ የሽያጭ ድምር ጋር ሲነጻጸር የተለያየ በመሆኑ ምክንያት ፡-

- በከምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ብር 230,616.11 ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር
- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 3,273,809.06 ተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተሰበሰበ
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 725,993.53 ያልተከፈለ የንግድ ትርፍ ግብር እና ብር 4,408.79 የተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ ብር 730,402.32 ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ ፡፡
- በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በንግድ ትርፍ ማሳወቂያና ሽያጭ ማጠቃለያ z-report/የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ በተገኘ የሽያጭ ልዩነት ምክንያት ብር 130,896.61 ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር መኖሩ እንዲሁም በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሺያጭ ዋጋ በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ ከተገለጸው ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ጋር ሲነጻጸር የአራት ድርጅቶች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ የተመለከተው የሺያጭ ዋጋ በብር 977,359.50 ያነሰ በመሆኑ ብር 146,603.93 የተጨማሪ አሴት ታክስ በድምሩ ብር 277,500.54 ያልተሰበሰበ መሆኑ፡፡
- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በንግድ ትርፍ ማሳወቂያና በተጨማሪ እሴት ታክሰ ማስታወቂያ ላይ ባለው የሽያጭ ልዩነት ምክንያት

ብር 1,527,665.88 የትርፍ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ እንዲሁም ሁለት ግብር ከፋዮች የሽያጭ ገቢያቸውን አሳንሶ በማሳወቃቸው ምክንያት ብር 74,164.02 የንግድ ትርፍ ግብር በድምሩ ብር 1,601,829.90 ያልተሰበሰበ ሂሳብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ይህ ሁኔታ የመንግስትን ገቢን የሚቀንስ ከመሆኑም በተጨማሪ ክትትል የማይደረግ ከሆነ ግብር ከፋይ ድርጅቶች ሆን ብለው ገቢያቸውን በመቀነስ መክፈል የሚገባቸውን ግብር በየአመቱ ሊሰውሩ ይችላሉ፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ያልተከፈለውን ግብር በአዋጁ መሰረት የግብር ዕዳቸውን ከነመቀጫ እና ወለድ ሊሰበስብ ይገባል፡፡ለወደፊቱም ግብር ከፋዮች በሚያቀርቡት ንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የሽያጭ መጠን በ12 ወራት ከሚያሳውቁት የቫት ዲክላራሲዎን ላይ ከተገለፀው የሽያጭ መጠን ጋር ልዩነት ሲኖረው የልዩነቱ መንስኤ ሊጣራ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- ቅ/ጽቤቶቹ በልዩነቱ ላይ በየደረጀው ክትትልና እርምጃ እየወሰዱ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል።

ለ) የጥገናና የማሻሻያ ወጪ በአዋጁ መሰረት ባለመያዙ ምክንያት ብር 133,612.16 የገቢ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

ድርጅቶች ወጪያቸውን በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 እና በገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 608/2001 አንቀጽ 3 መሰረት የሚይዙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ገቢያቸውን እያሳወቁ ግብራቸውን የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች በየምድቡ ለሚኖሩ የድርጅቱ የቋሚ እቃዎች የጥገናና የማሻሻያ ወጪያቸው ለእርጅና ቅናሽ መሰረት ከሆነው ዋጋ ከ 20 በመቶ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ወጪው ሙሉ በሙሉ በዕቃው የእርጅና ቅናሽ መሰረት በሆነው ዋጋ ላይ ተደምሮ ወጪው በእርጅና ቅናሽ ደንብ መሰረት መታሰብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ለናሙና ወስደን ኦዲት

ካደረገናቸው የግብር ከፋይ ፋይሎች ውስጥ ግብር ከፋዮች ከላይ በተገለጸው አዋጅ መሰረት የቋሚ እቃዎች የጥገናና ማሻሻያ ወጪ ባለመያዙ ምክንያት፡-

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 82,428.04 የገቢ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 32,927.63 የገቢ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ሽላናት ኮንስትራክሽን(0023942812) ግብር ከፋይ ገቢ ያልሆነ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 18,256.49 መኖሩ፤ በድምሩ ብር 133,612.16 ያልተሰበሰበ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ኪዎ ሀ/የ/የገ/ማህበር (የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0016958839 የሆነ) በግብር ዘመኑ ለጥገናና ማሻሻያ ወጪ በጥቅል ለቋሚ እቃዎች የወጣ ብር 501,700.00 መኖሩን ባሳወቀው ሂሳብ መግለጫ ላይ የገለፀ ቢሆንም የጥገና ወጪዎቹ ግን ለየትኛው ቋሚ እቃ እንደወጣ ስላልተገለፀ የወጣው የጥገናና የማሻሻያ ወጪ የዘመኑ ወጪ ወይም በእቃው ዋጋ ላይ መደመር ያለበት ወጪ መሆኑን ማረጋገጥ ባለመቻሉ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም ፡፡

<u>ስጋት</u>

ተገቢው ክትትል የማይደረግ ከሆነ ግብር ከፋይ ድርጅቶች አዋጁ ላይ ከተቀመጠው በተቃራኒው ሆን ብለው የጥገናና ማሻሻያ ወጪን የዘመኑ ወጪ እንደሆነ በመውሰድ ለመንግስት መክፈል ያለባቸውን የገቢ ግብር አላግባብ እንዲቀንስ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- በአዋጁ መሰረት በድጋሚ የግብር ማሳወቂያ በመስጠት ያልተሰበሰበው የንግድ ትርፍ ግብር መቀጫ እና ወለድን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ሊሰበስብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባል፡፡
- ኪዎ ሀ/የ/የገ/ማህበርን በተመለከተ ተገቢው መረጃ እንዲቀርብ በማድረግና አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ የጥገናና ማሻሻያ ወጪው በአዋጁ መሰረት የተያዘ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከሚፈለገው ሂሳብ ውስጥ ብር 55,972.24 ተሰብስቦ ገቢ የተደረገ መሆኑን ፡፡
- የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ቀሪ ሂሳቡ እንዲሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት የገለፁ መሆኑ
- የመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ሽላናት ኮንስትራክሽንን በተመለከተ ግኝቱ ትክክል በመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለው የውሳኔ ማስታወቂያ የሚያወጡ መሆኑን፡፡ በተጨማሪ ኪዎን በተመለከተ የኦዲት ግኝቱን መሰረት በማድረግ ከግብር ከፋዩ በሚቀርብ ተጨማሪ ሰነድ መሰረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በተሰጠው ማሻሻያ ሀሳብ መሰረት መሰብሰብ ያለበት ግብር ካለ እንዲሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሐ)ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ መቀናነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀናነሳቸው ምክንያት ብር 253,117.02 የገቢ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 20 መሰረት ለንግድ ስራው ገቢ ለማግኘት፣ ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ብቻ መቀናነስ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ መቀናነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀናነሳቸው ምክንያት ፡-

- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከአንድ ድርጅት (ድራር ትሬዲንግ ኃ/የ/የግል ማህበር) ብር 5,540.79 ያልተሰበሰበ የገቢ ግብር መኖሩ፡፡
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል አንድ ድርጅት ላይ የእርዳታ ወጪ ብር 2,500.00 ከንግድ ስራው ገቢ ላይ በማቀናነሱ ምክንያት ብር 750.00 ያልተሰበሰበ የገቢ ግብር መኖሩ፡፡
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ለ2005 የግብር ዘመን የቋሚ እቃዎች ትክክለኛው የእርጅና ቅናሽ መጠን ከንግድ ገቢው ላይ ባለመቀናነሱ

እንዲሁም ሎሎች ወጪዎችን ያለአግባብ ከፍ እንዲል በማድረጋቸው ምክንያት ከትራንስ ኢ.ትዮ ኃ/የተ/የግል ማህበር(0000060188)

ብር 106,218.53 ያልተሰበሰበ ፍሬ ግብር መኖሩ፡፡

በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 140,607.70 ያልተሰበሰበ መሆኑን

ስጋት

ግብር ከፋዮች የሚያቀርቡት የንግድ ትርፍ ማስታወቂያ በትክክል እየተሞላ የሚቀርብ መሆኑን በአግባቡ የማይጣራ ከሆነ በማስታወቂያው ላይ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ በመሙላት ግብር ከፋይ ድርጅቶች ግብራቸውን ሊሰውሩ ይችላሉ መንግስትም ማግኘት የሚገባውን ገቢ ሊያጣ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በአዋጁ መሰረት በድጋሚ የግብር ማሳወቂያ በመስጠት ያልተሰበሰበው የንግድ ትርፍ ግብር መቀጫ እና ወለድን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ሊሰበስብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- ቅ/ጽ/ቤቶቹ ቀሪውን ሂሳብ እንደሚሰበስቡ ምልሽ ሰጥተዋል።

መ) ያልተሰበሰበ ብር 6,563,817.54 የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ

ግኝት

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/2002 ክፍል 7/26 መሰረት እያንዳንዱ ግብር ከፋይ በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ለታክስ ባለስልጣኑ ማስታወቅና ለእያንዳንዱ የተሰጠውን የመጨረሻ ታክስ መክፈያ ጊዜ ጠብቆ ታክሱን መክፈል እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ፡-

- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በግብር መክፈያ መለያ ቁጥር 000793747 የተጠቀሰው ግብር ከፋይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ በየወሩ የሚያቀርብ ቢሆንም የነሀሴ/2005 ብር 732,813.00, የመስከረም/2006

ብር 1,727,846.90 እና የጥቅምት /2006 ብር 972,548.42 በድምሩ ብር 3,433,208.37 ባሳወቀው የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ መሰረት መክፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ያልፈፀመ መሆኑ ፡፡

- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዜድ ሪፖርት እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ መካከል ባለው ልዩነት ምክንያት ብር 997,400.38 የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፡
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት በኩል በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ እና በዜድ ሪፖርት መካከል የሽያጭ ልዩነት በመኖሩ ብር 1,534,819.54 ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ
- በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ሁለት ግብር ከፋዮች ካከናወኑት ግብይት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሰበሰቡ ቢሆንም ገቢ ያላደረጉት የተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ ብር 38,103.32 መኖሩ።
- በባህዳር ቅ/ፅ/ቤት በኩል አንድ ግብር ከፋይ (ህዳሴ የገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ህ/ሽ/ማህ (tin 0026872962) የህዳር /2006 ተ.እ.ታ ሲያሳውቅ ጠቅላላ ተከፋይ ብር 299,701.20፤ እና የሚያዚያ ወር 2006 ተ.እ.ታ ሲያሳውቅ ጠቅላላ ተከፋይ ብር 260,584.73 በጠቅላላው ብር 560,285.93 ቢያሳውቅም ገንዘቡ ለቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ ያልሆነ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

መሰብሰብ የሚገባው ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ያልተሰበሰበው የግብር መጠን ከሚመለከተው ግብር ከፋይ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ግብር ከፋዩ ባሰወቀበት ወቅት የሚፈለግበትን ግብር ሊከፍል ይገባል፡፡ ለዚህም የሚመለከተው አካል ወቅታዊ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- ድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት፣ የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤትና የምስራቅ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ልዩነቱ የካሽ ሬጂስተር ማሽን ስህተት ጋር እንደሚያያዝና በማስረጃ ላይ ተመስረተው በመጣራት ውሳኔ እንዲደርሳቸው እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
- የባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ግብር ከፋዩ እስከ መስከረም 2006 ዓ.ም ድረስ ብር 1,100,798.18 ውሳኔ ወጥቶለት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ወስዶ ሲከፍል ከቆየ በኋላ ውሳኔው ላይ ከተካተቱት ወራት የሚያዝያ 2005 ብር 523,890.87 ቀድሞ ስለከፈልኩት ሊታይልኝ ይገባል የሚል ጥያቄ በማቅረቡ ቅሬታው ታይቶ እልባት ሲያገኝ የሚታይ እንደሚሆን በመውጫ ውይይቱ ላይ እና በላኩት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

- የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር የተወሰዱትን እርምጃዎች እና የተደረሰበትን ውጤት የሚያስረዳ ማስረጃ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ሊቀርብ አልቻለም ፡፡

ሠ) ከተመዘገቡ ጊዜ ጀምረው ሪፖርት የማያደርጉና ባዶ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች መኖራቸው

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 አንቀጽ 86 እንዲሁም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/2002 አንቀጽ 26 በአንድ የሂሳብ ግዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ግዜ ሂሳቡን ለታክስ ባለስልጣኑ ማስታወቅ እንዳለበት ደደነግጋል፡፡በዚህ መሰረት ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን እየተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ማጣራት በናሙና ከታዩት ውስጥ፡-

- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል በታክስ ከፋዮይነት ተመዝግበው ነገር ግን ከተመዘገቡበት ጊዜ አንስቶ ወደ ታክስ ማዕከሉ መጥተው የማያሳውቁ 329 ግብር ከፋዮች እንዲሁም በተደጋጋሚ ባዶ / Nil / የሚያሳውቁ 88 ግብር ከፋዮች መኖራቸው ፡፡
- በከምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ለገቢ ግብር፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስና ለተርን ኦቨር ታክስ ተመዝግበዉ ገቢያቸውን በወቅቱ የማያሳውቁና

ግብርም የማይከፍሉ እንዲሁም ገቢያቸውን ማሳወቅ ያቆሙ 6 ግብር ከፋዮች መኖራቸው ፡፡

- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ለገቢ ግብር፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስና ለተርን ኦቨር ታክስ ተመዝግበው ገቢያቸውን በወቅቱ የማያሳውቁና ግብርም የማይከፍሉ እንዲሁም ገቢያቸውን ማሳወቅ ያቆሙ 27 ግብር ከፋዮች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶቹ በግብር ከፋይነት ተመዝግበው ነገር ግን በአዋጁ መሰረት ግብራቸውን የማያሳውቁ ከሆነ የመንግስት ግብር በአግባቡ እንዳይሰበሰብ ከማድረጉም በላይ ህግ አክብሮ በአግባቡ የግብር ግዴታውን የሚወጣውን ግብር ከፋይ የሚጎዳ ይሆናል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በአዋጁ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የስራ እንቅስቃሴያቸውን በማያሳውቁት ላይ ቅ/ጽ/ቤቶቹ ሁኔታውን በማጣራት እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤትና መቀሌ ቅ/ፅ/ቤት ክትትል በማድረግና የማጣራት ስራ እየተሰራ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
- በከምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ሁለት ድርጅቶች ግብራቸውን ያሳወቁ እንደሆነ ነገር ግን አንድ ድርጅት ወደ ክልል የዞረ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ረ) <u>የግብር ዕዳ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው ያልተከፈለ ወይም የግብር ይግባኝ አቤቱታ ያልቀረበበት ሂሳብ ብር 324,799,447.86 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 77/1 መሰረት በታክስ ኦዲትም ሆነ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አማካኝነት ውዝፍ የግብር ዕዳ ያለባቸው ግብር ከፋዮች የግብር ዕዳቸውን በ 30 ቀናት ውስጥ እንዲከፍሉ ውሳኔ ደርሷቸው ያለባቸውን የግብር እና የታክስ ዕዳ እስካሁን ደረስ ባልከፈሉ ግብር ከፋዮች ላይ ንብረት በመያዝ ያለባቸውን የግብር ዕዳ ለመሸፈን እንዲሆን በአዋጁ መሰረት የንብረት መያዝ እርምጃ እየወሰዱ ስለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፡-

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 2,348,844.23 (ሳይሰበሰብ ከ5 ወር እስከ 1 አመት ከ 7ወር የዘገየ ሂሳብ) የሚገኝ መሆኑ
- በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት በኩል ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቅሬታ ሰሚ ውሳኔ ሰጥቶባቸው ከ1 ዓመት እስከ 7 ዓመት ድረስ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ግብር ብር 185,602,808.91 ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፡፡
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤቱ የግብር ውሳኔው ከወጣ አንድ አመት ከስድስት ወር እስከ ሰባት አመት ከስምንት ወር ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ በድምሩ ብር 132,881,518.48 የሚገኝ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የገቢ ግብር ብር 2,342,626.40 ፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,240,419.59፤ የተርን ኦቨር ታክስ ብር 278,989.88፤ የቅድመ ገቢ ግብር ብር 72,129.23፤ የወለድ ገቢ ብር 32,111.23፤ በጠቅላላው ብር 3,966,276.24 ያልተሰበሰበ የግብር ሂሳብ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል ፡፡
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል 16 ግብር ከፋዮች በውሳኔው መሰረት የግብር ዕዳቸውን ያልከፈሉ በመሆናቸው ሳይሰበሰብ ከ 4 ወር እስከ 2 ዓመት ከ 8 ወር ድረስ የቆየ በድምሩ ብር 24,609,972.93 ያልተሰበሰበ ግብር መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ባጠቃላይ ከሁሉም ቅ/ፅ/ቤቶች የግብር ዕዳ ውሳኔው ደርሷቸው ነገር ግን በገቢ ግብር አዋጁ መሰረት በ 30 ቀናት ውስጥ መጥተው ዕዳቸውን ያልከፈሉ ወይም አቤቱታ ያልቀረበበት ሂሳብ በድምሩ 324,799,447.86 ያለ ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቱም በግብር ከፋዮቹ ላይ ምንም አይነት የንብረት መያዝ እንቅስቃሴ ያላደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

<u>ስጋት</u>

የተወሰነውን ውዝፍ የግብር ዕዳ በአዋጁ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ በማይከፍሉ ግብር ከፋዮች ላይ በአዋጁ መሰረት እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ በወቅቱና በአግባቡ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

__የማሻሻያ ሃሣብ__

ያልተሰበሰበው የግብር እዳ ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑት ግብር ከፋዮች ላይ በአዋጁ መሰረት ንብረታቸውን በመያዝ ወይም እንዲታገድ በማድረግ ያልተከፈለ ዕዳቸውን እንዲሸፍን መደረግ ይኖርበታል፡፡

__የሥራ አመራሩ ምላሽ__

- ከሚፈለገው ሂሳብ ውስጥ በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት ብር 112,597.37፣ በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት 10,356,610.84 ተሰብስቦ ገቢ የተደረገ መሆኑን ፡፡

- የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት አዲስ ኮሚቴ አቀቁሞ በክትትል ላይ መሆኑን ፣ የጅማ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ የሚቀበሉት መሆኑንና

- የመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በአጠቃላይ ውዝፍ ለመሰብሰብ የተወሰኑ ጥረቶች ቢኖሩም ክትትሉ በአጀማመር የዘገየ መሆኑንና በተቻለ መጠን በተቀመጠለት ጊዜ እስታንዳርድ እንዲከፍሉ ወይም ንብረት እንዲያዝ የማድረግ ስራ በቀጣይ ለመስራት ጥረት እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሰ) __ግብር ከፋዮች የግብር ግዴታቸውን ሳይወጡ ከግብር እዳ ነፃ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑ__

__ግኝት__

የግብርና ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎች አነሳስ፣የክፍያ ጊዜ ስምምነት እና የግብር ግዴታውን ስለመወጣት በማረጋገጫነት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት(ክሊራንስ) አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 55/2003 አንቀጽ 14/2 መሰረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ተሰጥቷቸው ግዴታቸውን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መወጣት ያልቻሉ ማስረጃ ሲያቀርቡ አግባብነት ያለው ሰራተኛ ጉዳዩን በመመርመር ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለስራ ሂደት ባለቤቱ በማቅረብ የስራ ሂደት ባለቤቱም ማስረጃውን በመመዘን በድጋሚ የክፍያ ጊዜ እንዲራዘም ሊፈቅድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡በተጨማሪም በዚሁ መመሪያ አንቀፅ 19 መሰረት ማናቸውንም የምስክር ወረቀት ለመስጠት ግብር ከፋዩ የግብር ግዴታውን እየተወጣ ለመሆኑ መረጋገጥ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ቅ/ፅ/ቤቶች በድጋሚ የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ውል ስምምነት ለመግባት ለሚያመለክቱና

ከግብር ዕዳ ነጻ ደብዳቤ /የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ለሚጠይቁ ግብር ከፋዮች በመመሪያው መሰረት እየተስተናገዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፦

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የወል ኃ/የተ/የግል ማህበር (የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0004060161)የሆነ ድርጅት ከዚህ በፊት ለገባው የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ውል ያቋረጠበት በቂ ማስረጃ ሳያቀርብ በድጋሚ የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲሰጣቸው መደረጉን ለማረጋገጥ ችለናል፡፡
- በተጨማሪ ግብር ከፋዩ ከላይ በዝርዝር በተገለጸው መሰረት የግብር ግዴታውን በአግባቡ ያልተወጣ መሆኑ እየታወቀ በመመሪያው አንቀጽ 19 መሰረት ሳይጣራ ለድርጅቱ በቀን 10/06/06 የንግድ ፈቃድ/የተሽከርካሪ ዓመታዊ ምርመራ ለማድረግ ከግብር ዕዳ ነጻ/ክሊራንስ ደብዳቤ የተሰጣቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

<u>ስጋት</u>

የክፍያ ጊዜ ስምምነትንም ሆነ የምስክር ወረቀት አስጣጥን አስመልክቶ ከላይ በተገለጸው መመሪያ መሰረት የማይፈጽም ከሆነ በግብር ከፋዮች እጅ ያለውን የግብር ዕዳ በአግባቡ ለመሰብሰብ የሚያስቸግር ይሆናል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- የስራ ሂደቱ ግብር ከፋዮች ከዚህ በፊት የገቡትን የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ውል ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ያቋረጡ መሆኑንና በድጋሚ የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ውል እንዲሰጣቸው ካመለከቱ ግብር ከፋዩ በውሉ መሰረት የግብር ዕዳውን መክፈል ያልቻለበትን ማስረጃ እንዲያቀርብ ማድረግና የሚመለከተው ባለሙያም ማስረጃው ትክክለኛና አሳማኝ መሆኑን በማጣራትና የውሳኔ ሃሳቡን በመስጠት ለስራ ሂደቱ ማቅረብ ይኖርበታል፤ የስራ ሂደቱም በውሳኔ ሀሳቡ ከተስማማ ስምምነቱን በድጋሚ ስለመፈቀዱ የሚያስረዳ የውሳኔ ሃሳቡን ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
- የምስክር ወረቀት/ክሊራንስ አሰጣጥን በተመለከተ የስራ ሂደቱ ከላይ በተገለጸው መመሪያ 55/2003 አንቀጽ 19 መሰረት ካጣራ በኋላ የምስክር ወረቀቱን/ክሊራንሱን መስጠት ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በወቅቱ የግብር ከፋዩን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር በማየት የተፈፀመ መሆኑን በመግለፅ ለወደፊቱ ተገቢው ጥንቃቄ የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሸ) የወጪ መጋራት የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች በወቅቱ እየከፈሉ ለመሆኑ የሚረጋገጥበት ስርአት አለመዘርጋቱ

ግኝት

ስለከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት በወጣው ደንብ ቁጥር 91/2003 አንቀፅ 7(ለ እና ሐ) እንዲሁም አንቀፅ 11 መሰረት አሰሪዎች የተቀጣሪዎችን ዝርዝር በሶስት ወር ጊዜ ዉስጥ ለፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢዎች ባለስልጣን ማሳወቅ እንዳለባቸውና ከተቀጣሪው ደመወዝ በየወሩ እየቀነሱ ማስተላለፍ እንዳለባቸውና ባለስልጣን መስሪያ ቤቱም አጠቃላይ ክፍያውን የመሰብሰብ መከታተልና መቆጣጠር እንዳለበትና ይኸውም ተፈፃሚ እንዲሆን አስፈላጊውን ስርአት የመፍጠርና ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው በመንግስት ተቋም ከተቀጠሩ ሰራተኞች የሚፈለግባቸውን የወጪ መጋራት አሰሪው መስሪያ ቤት በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እየሰበሰበ ገቢ እያደረጉ ለመሆኑ የሚከታተልበት ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ቅ/ጽ/ቤቱ አዋጁ በሚያዘው መሰረት ከመንግስት ዩኒቨርስቲ ተመርቀው መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩትን ሠራተኞች መረጃ በመሰብሰብ የሚከታተልበት ስርአት ካልዘረጋ መንግስት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው ስራ ላይ ከሚሰማሩ ተማሪዎች መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ በአግባቡ እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሣብ

በደንቡ መሰረት አሰሪ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች አዲስ ስለቀጠሩዋቸው ሰራተኞች ዝርዝር በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግና

በዚያው መሰረት የሚፈለገውን ገንዘብ ከሰራተኛው በወቅቱ እየቀነሱ ፈሰስ የሚያደርጉ መሆኑን የሚረጋገጥበት ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

የፌደራል መስሪያ ቤቶች አዲስ የሚቀጥራቸውን ሰራተኞች ዝርዝር በየሶስት ወሩ እንዲያቀርቡና ትክክለኛውን የገንዘብ መጠን እየቀነሱ ገቢ ስለማድረጋቸው ተገቢ ክትትል የሚደረግበት ስርአት እንዲኖር ጥረት ይደረጋል ፡፡

ቀ) **ለአንድ ግብር ከፋይ ሁለት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው መሆኑ**

ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 43(ሀ) መሰረት ማንኛውም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በማናቸውም ሁኔታ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ የበለጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲይዝ አይፈቀድለትም፡፡ ነገር ግን በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከቢረ ኢንተርፕራይዝ ሀላ/የተ/የግል/ማህ አዋጁ በማይፈቅደው አኳኋን አንድ ግብር ከፋይ ሁለት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 43/ሀ ላይ ከተደነገገው ወጪ ማንኛውም ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሚሰጠው ከሆነ ግብር ከፋይ አላስፈላጊ የግብር ማጭበርብር ስራ ሊያከናውን ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በአዋጁ መሰረት ተገቢው የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በተለይ ሁለት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ግብር ከፋዩ ለመንግስት መክፈል ያለበትን ግብር በትክክል የከፈለ ለመሆኑ ሊጣራ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- ግኝቱ ትክክል መሆኑን በመግለፅ ለድርጅቱ ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ ምስክር ወረቀት የሰጠው ድርጅቱ ቀደም ሲል በጋርመንት ጨርቃጨርቅ ምርትና ሂልቶፕ ሆቴል ዘርፎች ላይ የተሰማራው ድርጅት በተሰጠው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000344132 ሲታወቅ የነበረው ከቢረ

ኢንተርፕራትዝ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በማዕከል ለውጥ ወቅት በተፈጠረ በስህተት የተሰጠው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲዘጋ ማህደሩ ወደ ታክስ ኦዲት ተመርቶ በተለያዩ ምክንያቶች ኦዲት ማድረግ እንደማይችሉ ስለተገለፀልን በቀን 16/08/2006 በቁጥር ቀ65/p-75/9749 በተፃፈ ሸኚ ደብዳቤ የድርጅቱ ማህደር ወደ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች የተላከ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

በ) <u>በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔው ያልተሰጠው ግብር ብር 8,922,637.37 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 105(2) መሰረት የአቤቱታ አጣሪው ከግብር ከፋዮቹ የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ግብር ከፋዩ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ከቻለ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታው ሊታይለት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንፃር ለሚቀርቡ አቤቱታዎች በወቅቱ ውሳኔ በመስጠት የመንግስት ግብር እንዲሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ሶስት ግብር ከፋዮች ለኮሚቴው አቤቱታ አቅርበው ነገር ግን ውሳኔ ሳይሰጥበት ከ 8 ወር እስከ 2 ዓመት የቆየ የግብር ዕዳ ብር 8,922,637.37 መኖሩን
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት የትርፍ ግብር ብር 2,719,737.10 ያለባቸው 11 ግብር ከፋዩች፣ ለብር 716,554.08 የኪሳራ ሪፖርት ያቀረቡ 2 ግብር ከፋዮች፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 902,398.81 ያለባቸው 6 ግብር ከፋዮች፣ ዲቪደንድ ብር 206,782.70 ያለባቸው 2 ግብር ከፋዮች እና የተርን ኦቨር ታክስ ብር 166,128.27 ያለበት አንድ ግብር ከፋይ እንዲሁም ብር 66,813.64 ያለባቸው 3 የቅድመ ግብር ከፋዮች በ2006 በጀት ዓመትና ከዚያ በፊት የአጠቃላይ ኦዲት ውሳኔ ተሰጥቷቸው ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም አሁንም ውሳኔ ያልተሰጣቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በአጠቃላይ ኦዲት ውሳኔ መሰረት የተወሰነው ያልተከፈለ የግብር ዕዳ በግብር ከፋዩ ቅሬታ የቀረበበት ከሆነና በአስቸኳይ በቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ተሰጥቶበት የግብር ዕዳው በአግባቡና በወቅቱ የማይሰበሰብ ከሆነ መንግስት ገቢውን ማግኘት ባለበት ወቅት እንዳያገኝ ሊያደርገው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ኮሚቴው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 105 (2) መሰረት ግብር ከፋዩ ቅሬታውን ያቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ በተቻለው መጠን በፍጥነት ውሳኔ በመስጠት የመንግስት ግብር ቶሎ እንዲሰበሰብ ማደረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- መቀሌ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ሁለት ግብር ከፋዮቹን በተመለከተ በኦዲት የተወሰነባቸው ግብር ላይ ምንም አይነት ወጪ ያልተያዘላቸው በመሆኑ ይህ ደግሞ ፍትሀዊ ግብር እንዲወሰን ዘንድ ኮሚቴው ለግብር ከፋዩ የወጪዎቹን ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተጠይቆ እስከአሁን ድረስ መረጃ ሊገኝ ባለመቻሉ ሳይወሰን መቆየቱን፤ አንዱን ግብር ከፋይ በተመለከተ ግን የግብር ውሳኔው በኢንቨስትጌሽን ኦዲት ቡድን የተወሰነ ሲሆን በግብር ከፋዩ ላይ የተጣለው ቅጣት ለማሻሻል ወይም ለማንሳት ግብር ከፋዩ የፈፀመው ድርጊት የወንጀል እንደምታ ያለው መሆኑና አለመሆኑን ማጣራት የሚያስፈልግ በመሆኑ እና ይህም እስከ አሁን በሂደት ላይ ያለ በመሆኑ የግብር ከፋዩ ቅሬታ እንዲዘገይ ምክንያት የሆነ ቢሆንም በኮሚቴው እጅ ያሉ ጉዳዮች በወቅቱ እልባት እንዲያገኙ የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
- የጅማ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ የሚቀበሉት መሆኑንና ስራው በኮሚቴ የሚሰራና ኮሚቴውም በተለያየ ሥራ የተጠመደ በመሆኑ በተፈለገ መጠን በቀረቡት አቤቱታዎች ላይ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት እና ገቢውን መሰብሰብ ያልተቻለ መሆኑን በመግለፅ በቀጣይ የተለያዩ ክፍሎችን ቅሬታ ሊፈታ የሚቻልበት አግባብ ላይ አቅጣጫ ተይዞ ወደ ስራው የሚገቡ መሆኑን በመውጫ ውይይቱ ላይ እና በላኩት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ተ) <u>በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) ያልተመዘገበ ብር 346,538.17 ገቢ ስለመኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

ከግብር ከፋዩ የሚሰበሰብ ግብር ወይም ገቢ በሙሉ በሲግታክስ (በሲስተም ላይ) የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ከታዩት ውስጥ :-

- በባህርዳር ቅ/ፅ/ቤት በኩል በማኑዋል ደረሰኝ የተሰበሰበ ገቢ ብር 264,710.30 በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) ያልተመዘገበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከ5 ግብር ከፋዮች በማኑዋል ደረሰኝ የተሰበሰበ ገቢ ብር 81,827.87 በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) ያልተመዘገበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

በገቢ ሂሳብ መግለጫ እና በመረጃ ቴክኖሎጂ (MIS) መካከል ልዩነት ከማሳየቱም በላይ በገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የተሰበሰበ ገቢ በሪፖርት እንዳይጠቃለል ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡ በተጨማሪም የግብር ከፋዮችን ትክክለኛ ሂሳብ ለማወቅ አያስችልም፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ወደ ሲስተም ያልገቡት ገቢዎች በሙሉ በSIGTAS መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- የባህርዳር ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ችግሩ ትክክል መሆኑን በመግለፅ በመረጃዎቹ መሰረት ወደ ሲስተም ያልገቡት በሪአሰስመንት በማኑዋል የተቆረጠ በመሆኑ ተከታትሎ ወደ ሲስተም ማስገባት ባለመቻሉ ችግሩ ሊከሰት መቻሉንና ለወደፊትም ቅ/መ/ቤቱ ክትትል በማድረግ ወደ ሲስተም እንዲገባ ጥረት የሚያደርግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ሂሳቡ በሙሉ በሲግታስ(ሲስተም ላይ) የተመዘገበ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል ፡፡

ቸ) <u>የግብር ከፋዮን የሽያጭ መጠን ብር 12,702,189.30 ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፤</u>

<u>ግኝት</u>

በባህር ዳር የቅ/ፅ/ቤት በኩል የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች ያሳወቁት ወርሃዊ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሽያጭ መጠን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ የባህር ዳር ጨርቃ-ጨርቅ ፋብሪካ አ.ማ የሀምሌ እና የነሐሴ ብር 12,098,238.87 እንዲሁም የመስከረም፤ የጥቅምት፤ የህዳር እና የታህሳስ በባለስልጣኑ የታተመ ደረሰኝ የተሰበሰበ ሽያጭ ብር 603,950.43 በጠቅላላው የብር 12,702,189.30- summery report ባለመቅረቡ የሽያጩን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>ስጋት</u>፡-

ቅ/ፅ/ቤቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ማግኘት የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ቅ/ጽ/ቤቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች ሽያጫቸውን ሲያሳውቁ በፎርሙ ላይ የሽያጭ መጠን ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የሽያጭ መመዝገቢያ ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች በትክክለኛው አሰራር summery report በየወሩ ከሂሳብ ሪፖርታቸው ጋር ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም የማያቀርቡበት ሁኔታ ያለ እና የግብር ከፋዮችም ለማቅረብ ፈቃደኛ አለመሆናቸውንና ሳያቀርቡ ሲቀሩ ደግሞ የሚጠየቁበት ግልፅ የአፈፃፀም መመሪያ ባለመኖሩ ማብራሪያ ተጠይቆ ምላሽ በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን በመግለፅ አሰፈላጊነቱን የሚያምኑበት በመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት በመቀበል የመሳሪያው ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ላይ ክትትል በማድረግ እንዲያቀርቡ እንደሚደረግ በላኩት ምላሽና በመውጫ ውይይቱ ወቅት ገልፀዋል፡፡

ነ) <u>በግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ የሌለ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ ሀ-ለ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 ክፍል 7 ንዑስ አንቀጽ 26 ተራ ቁ. 1 ሀ እያንዳንዱ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ግብር ባለስልጣኑ ዘንድ በመቅረብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ ወይም ባለስልጣኑ ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም ማስታወቅ እና ለእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ የተሰጠውን የመጨረሻ ታክስ መክፈያ ጊዜ ገደብ ጠብቆ ለባለስልጣኑ ለወከለው ሰው ከገቢ ማስታወቂያው ጋር በአንድነት ታክሱን መክፈል አለበት በሚለው መሰረት የቅርጫፍ ጽ/ቤቱ የግብር ከፋዮች የ2006 በጀት ዓመት የተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል ማሳወቀቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ቁጥራቸው 21 የሆኑ ድርጅቶች የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ በግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ ባለመገኘቱ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት አልተቻለም ፡፡
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የሊሙ ሊበን የመጋቢት ወር የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቀና በፋይሉ ውስጥ ያልተገኘ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ቁጥራቸው 9 የሆኑ ድርጅቶች የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ በግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ ባለመገኘቱ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት አልተቻለም፡፡

<u>ስጋት</u>

ሊሰበሰብ የሚገባውን የገቢ መጠን በትክክል ለማስላት ሁኔታው ስለማያስችል መሰብሰብ ያለበት ገቢ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሣብ</u>

ለኦዲት ስራ ያልቀረቡትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ቅፅና ንግድ ትርፍ በተመለከተ ተፈልገው ከተገቢው ፋይል ጋር እንዲያያዙ እንዲደረግና የሂሳቡ

ትክክለኛነት እንዲጣራ ሆኖ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት እንዳይደርስ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል ፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ከመውጫ ውይይት በኋላ በተደረገ ማጣራት ግብር ከፋዮቹ ያላሳወቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ባለማሳወቁ ተቀጥቶ ያሳወቀ መሆኑን ፡፡
- የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ነሀሴ 26/2006 ዓ.ም በተደረገው የመውጫ ስብሰባ ውይይት ላይ ሌዊ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር እና አለምፀሀይና ሐጎስ ያሳወቁ ቢሆንም መረጃው መዝገብ ቤት ያልደረሰ መሆኑ እና ሆንድዋሽቆ ኃ/የተ/ግ/ማ በገንዘብ ያገኘች እጅ ያለና መዝገብ ቤት ያልደረሰ መሆኑን ገልጸው ሌሎቹ ድርጅቶች ግን ያላሳወቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራ ሌዊ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አለምፀሀይና ሐጎስ ያሳወቁ ቢሆንም መረጃው መዝገብ ቤት ያልደረሰ መሆኑ እና ሆንድዋሽቆ ኃ/የተ/ግ/ማ በገንዘብ ያገኘች እጅ ያለና መዝገብ ቤት ያልደረሰ መሆኑ ተብሎ ቢገለጽም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ድረስ ማስረጃው ለኦዲት አልቀረበም፡፡

ኘ) **የታክስ ማዕከል ያልተቀየረላቸው ግብር ከፋዮች ስለመኖራቸው**

ግኝት

ግብር ከፋዮች የሚከፍሉት ግብር በሲግታስ የግብር መመዝገቢያ ሶፍትዌር ስለመመዝገቡ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል 23 ግብር ከፋዮች ፋይላቸው ወደ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ሲዛወር በሲስተም ግን የታክስ ማዕከል ያልተቀየረላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

አሰራሩ ሁሉም የግብር ገቢ በሲግታስ እንዳይመዘገብ ከማድረጉም በላይ በገቢ ሂሳብ ሪፖርትና በመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት መካከል በሚፈጠረው ልዩነት ምክንያት በደረሰኝ የሚሰበሰበው በሙሉ ሪፖርት መደረጉን ለማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የታክስ ማዕከላቸው ሊቀየርና የሚከፍሉትም ግብር በሲግታስ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ከተጠቀሱት ግብር ከፋዮች ውስጥ 9 ግብር ከፋዮች የታክስ ማእከላቸው ወደ ጅማ የተቀየረ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ከ) **<u>ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነስ (Withholding Tax) ስሌት መሰረትና በንግድ ትርፍ እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ሪፖርት መካከል በተገኘ የሽያጭ ልዩነት ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 7,555,096.62 ስለመኖሩ፣</u>**

<u>ግኝት</u>

ግብር ከፋዮች የ2005 በጀት ዓመት ንግድ ትርፍ መግለጫ ላይ ባሳወቁት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነስ (Withholding Tax) 2% መሰረት የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ ሲሰላ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት በኩል በ2 ድርጅቶች የቀረበው በንግድ ትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ ላይ ካሳወቁት ጠቅላላ ሽያጭ ጋር ልዩነት በመኖሩ ያልተከፈለ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 7,555,096.62 መኖሩን ያሳያል፡፡

<u>ስጋት</u>

ያልተሰበሰበ ግብር ቢኖርም ግብሩ እንዳይታወቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

በእያንዳንዱ ግብር ከፋይ የታየው ልዩነት ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ገንዘቡ ይፈለግባቸዋል የተባሉ 2 ድርጅቶች ሂሳብ በሚመለከተው የባለስልጣኑ የስራ ክፍል ተጣርቶ በቅድሚያ ክፍያ ላይ ተቀነሰ የተከፋይ ተቀናሽ በመኖሩና በበፊተኛው ዓመት ሪፖርት ለተደረገ ሽያጭ ገንዘቡ የተሰበሰበው በ2005 ዓመት በመሆኑ የተፈጠረ ልዩነት መሆኑን ከኦዲት መውጫ ውይይት ቡኃላ በቀረበ አስተያየት ተገልጻል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

ለተሰጠው ምላሽ መሰረት ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

4. **የወጪ ሂሳብ**

ሀ) **ያለ አግባብ የተከፈለ ከተከፋይ ላይ ተቀናሽ ብር 5,670.80 መኖሩ**

ግኝት:-

በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24 (1 እና 2) መሰረት በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸዉ ድርጅቶች, የመንግስት መሰሪያ ቤቶች,ለትርፍ ያልተቋቃሙ የግል ድርጅቶች እና መግንስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም በአንድ የእቃ አቅርቦት ዉል ከብር 10,000.00 በላይ ለሆነ የእቃ አቅርቦት ከሚፈፀም ክፍያ ላይ እንዲሁም በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም በአንድ የአግልግሎት ውል ከብር 500.00 በላይ በሚፈፀም ክፍያ ላይ ሁለት በመቶ(2 ፐርሰንት) የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰዉ ማስቀረት እንዳለባቸው ይደነግጋል.፡፡ ከዚህ አንፃር ስራው የሚሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በድምሩ ብር 5,670.80 ከተከፋይ ላይ መቀነስ የነበረበት ሂሳብ ያልተቀነሰ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

መሰብሰብ ያለበት ግብር ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለወደፊቱ የሚመለከታቸው ሰራተኞች በደንቡ መሰረት መሰብሰብ ያለበት ቅድመ ግብር እንዲሰበሰብ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ያልተሰበሰበ የቅድመ ግብር ታክስ መኖሩ ታምኖበት ለወደፊቱ ከሚመለከተው የስራ ክፍል ጋር በመነጋገርና ክትትል በማድረግ የሚስተካከል መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ለ) <u>ማስረጃ ሳይኖር የተከፈለ ውሎ አበል</u>

<u>ግኝት</u>

የቅ/ጽ/ቤቱ ባልደረባ ላልሆኑ ሠራተኞች የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጸም የውሎ አበሉ ሂሳብ በቅ/ጽ/ቤቱ የሚሸፈን ስለመሆኑ ደብዳቤ (ማስረጃ) ሳይኖር ብር 1,930.20 የውሎ አበል ከአዲስ አበባ ለመጡ አንድ ሠራተኛ በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል ፡፡

<u>ስጋት</u>

የመንግስት ገንዘብ ከሁለት ቦታ ወጪ ሊደረግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለወደፊቱ የቅ/ጽ/ቤቱ ባልደረባ ላልሆኑ ባለጥቅሞች ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ወጪው በማን እንደሚሸፈን ስምምነት የተደረሰበት ደብዳቤ ወይም ሌላ ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ ሊፈጸም የማይገባ ሲሆን ከላይ የተመለከተውን የውሎ አበል ክፍያ በተመለከተ ጉዳዩ ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሰረት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለው ለወደፊቱ ተመሳሳይ ክፍያዎች ላይ ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

ሐ) <u>ገንዘቡ ለባለጥቅሙ ለመከፈሉ ማስረጃ ያልቀረበለት የትራንስፖርት ሂሳብ</u>

<u>ግኝት</u>

ለትራንስፖርት ወጪ ሆኖ የተከፈለው ሂሳብ በትክክል ቅ/ጽቤ/ቱ ላገኘው የትራንስፖርት አገልግሎት ለትራንስፖርት ሰጪዎች የተከፈለ መሆኑ ኦዲት ሲደረግ በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ቅ/ፅ/ቤቱ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘቱና ገንዘቡ ለትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ለመከፈሉ ማረስጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ ምንም የተጓዥ ስም፣ የተጓዘበት ቀን፣ የተከፈለው የገንዘብ ልክ

እና መነሻና መድረሻ ቦታ ባልተጻፈበት የትራንስፖርት ደረሰኝ (ፋክቱር) ብቻ ሂሳብ የሚወራረድ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

<u>ስጋት</u>

ቅ/ጽ/ቤቱ ላላገኘው የትራንስፖርት አገልግሎት ክፍያ ሊፈጸም ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለወደፊቱ ማንኛውም የትራንስፖርት ወጪ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ጽ/ቤቱ ላገኘው የትራንስፖርት አገልግሎት ለአገልግሎት ሰጪው ገንዘብ የተከፈለ መሆኑ ሳይረጋገጥ ሂሳብ እንዳይወራረድ ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ የሚገባ ሲሆን ለትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪው ለመከፈሉ ማስረጃ ሳይቀርብለት የተወራረደውን ሂሳብ በተመለከተ ማስረጃው እንዲቀርብ ካልሆነ ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለው ለወደፊቱ ተመሳሳይ ክፍያዎች ላይ ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

መ) <u>አላግባብ የተከፈለ የደሞዝና የውሎ አበል እንዲሁም የስልክ ወጪ ብር 27,402.03 መኖሩ.</u>

<u>ግኝት</u>

በኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 648/2001 መሰረት የመስሪያ ቤቱ ገንዘብና ንብረት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉንና ሀምሌ 1 ቀን 2004 ተግባራዊ እንዲሆን በተደነገገው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ መሰረት የውሎ አበል ክፍያ የሚፈፀም መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከስራ ቦታቸው ሳይንቀሳቀሱ የውሎ አበል በድምሩ ብር 1,526.32 እንዲሁም ለቦታው(ለደሴ ከተማ) ከተፈቀደው የቀን ውሎ አበል በላይ በእላፊ የተከፈለ የውሎ አበል በድምሩ ብር 9,534.12 መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ሰራተኞች ከስራ ቦታቸው ሳይንቀሳቀሱ በድምሩ ብር 8,166.00 ያለ አግባብ ውሎ አበል የተከፈላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በዋናው መስሪያ ቤት በኩል ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች ያለአግባብ በድምሩ ብር 3,465.77 ክፍያ የተከፈላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ለመስሪያ ቤቱ አገልግሎት የዋለ ስመሆኑ መረጃ ሊቀርብ ያልቻለ ለውጪ አገር ጥሪ የተከፈለ በድምሩ ብር 1,222.50 የስልክ ክፍያ መኖሩ እንዲሁም መስሪያ ቤቱን ለለቀቁ ሁለት ሰራተኞች የስልክ ወጪ በድምሩ ብር 3,487.32 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

ቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ከስራ ቦታቸው ሳይንቀሳቀሱ ከስራ ቦታ እንደተንቀሳቀሱ በመቁጠር አበል የሚከፍል ከሆነና ስራ ላይ ለሌሉ ሰራተኞች ደመወዝ የሚከፍል ከሆነ የመንግስት ሀብት አላግባብ የሚባክን ከመሆኑም በላይ አሰራሩም ለብልሹ አሰራር ክፍተት ያለው ይሆናል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- አላግባብ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም በመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ አንቀጽ 5/1 መሰረት ብቻ ከስራ ገበታቸው ላይ ተነስተው ወደ ሌላ ቦታ ለተንቀሳቀሱና ለቦታው በተፈቀደው የውሎ አበል መጠን መሰረት ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል፡፡
- የደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የሰው ሀብት ስራ አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች የተላኩ በስራ ገበታቸው ላይ ያልተገኙ ሰራተኞችን ዝርዝር በአግባቡ በመመልከት በስራ ገበታ ላይ ያልተገኙ መሆናቸውን መመሪያ በሚያዘው የቀን ገደብ ውስጥ ለግዢና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ ይኖርበታል በተጨማሪም ለለአግባብ የተከፈለው የደ መወዝ ክፍያ ከሚመለከታቸው አካላት ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥ ብር 9,116.72 ተመላሽ የተደረገ መሆኑን፣ የሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራ አላግባብ የተከፈለው የውሎ አበል ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ ስምምነት ላይ የደረሱ መሆኑንና የሰራተኞች የስራ ገበታቸው ላይ አለመገኘት ክፍያ ከተፈፀመ በኂላ በመሆኑ በተሰብሳቢነት ይዘው በሰው ሀብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት ተከታትሎ ሳይሰሩ የተከፈላቸውን ሂሳብ ገቢ እንዲያደርጉ በደብዳቤ የተገለፀ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
- የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር የውጭ ሀገር ጥሪን በተመለከተ በቀጣይ ማን፤ ለምን አገልግሎት እንደተደወለ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ የሚወሰዱ መሆኑን እንዲሁም መስሪያ ቤቱን ለለቀቁ ሰራተኞች የተከፈለ የስልክ ወጪን በተመለከተ በቀጣይ የሚገኙበትን አድራሻ በመፈለግ ገንዘቡ የሚተካበት መንገድ እንዲመቻች የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሠ) **<u>በቼክ መከፈል ሲኖርበት ከሳጥን ወጪ ሆኖ የተከፈለ ብር 49,158.05 ሂሳብ መኖሩ፡</u>**

<u>ግኝት</u>

በፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 24/5 መሰረት የወጪ መጠናቸው አነስተኛ የሆኑ ወይም ወጪያቸው ከብር 2,000.00 በታች ለሆኑ የተለያዩ ጥቃቅን ዕቃ እና አገልግሎት ግዢ እንዲሁም ሌሎች ክፍያዎችን ለመፈጸም ብቻ ከሳጥን ወይም ከካዝና እየከፈሉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በናሙና ከታዩት ውስጥ የወጪ መጠናቸው ከብር 2,000.00 በላይ መሆኑ እየታወቀ በድምሩ ብር **10,822.22** በቼክ መክፈል ሲገባቸው ከሳጥን ወጪ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ፡፡
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በ 3 የክፍያ ቫውቸሮች ብር 38,335.83 በቼክ መከፈል ሲገባው ከሳጥን ወጪ ተደርጎ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

ለወደፊቱም ከመመሪያው ውጪ ክፍያቸውን በዚሁ መልኩ የሚቀጥሉ ከሆኑ የመንግስት ገንዘብ አለአግባብ ሊባክን ይችላል ::

የማሻሻያ ሃሣብ

የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር የቁጥጥር ስርዓትን ከማጠናከር አንጻር ቅ/ጽ/ቤቶቹ በመመሪያው መሠረት አሰራራቸውን ሊያስተካክል ይገባል ::

የስራ አመራሩ ምላሽ

- የመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር አንደኛው ክፍያ የስልክ ክፍያ ሆኖ የተከፈለበት ቀን 09/11/05 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ቀን ባንካቸው ወደ ትሬዠሪ ፈሰስ ተደርጎ ገንዘብ ስለሌላቸውና ካልተከፈለ ደግሞ አገልግሎቱ ስለሚቋረጥ ከካዝና እንዲከፈል የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው ሌላኛው ክፍያ ደግሞ ለሁመራ የመኪና ምርመራ የተፈጸሙ ክፍያ መሆኑን በመግለፅ ዋና ምክንያትም ፈራሚ ለስራ ጉዳይ ወጥተው በከተማ ውጪ ስለነበሩ የሚቆዩበት ጊዜም ረዥም ስለነበር የሁመራ የኮትሮባንድ ስራ ደግሞ ያለ ተሽከርካሪ አስቸጋሪ በመሆኑ መኪናዋን ቶሎ ለመስራት የተከፈለ ክፍያ መሆኑን በመግለፅ በቀጣይ ግን ይህን መሰል ክፍተት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል አሰራሩ አሁን የተስተካከለ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል ::

ረ) **የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጁ ከሚያዘው ውጪ በብር 270,190.25 የተፈጸመ ግዥ መገኘቱ**

ግኝት

በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 33 (2) እና 56/1 መሰረት የእቃም ሆነ የአገልግሎት ግዢ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም እንዳለት እና በፕሮፎርማ የሚገዛ ከሆነ ግዢ ከመፈጸሙ በፊት ቢያንስ 3 አቅራቢዎች በውድድሩ ላይ እንዲሳተፉ እየተጋበዙ መሆን እንዳለበት

ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንጻር ግዢዎች ሲፈፀም በአዋጁ በተደነገገው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡-

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በብር 151,574.25 ክፍያ የተፈፀመለት ግዥ በጨረታ መገዛት ሲኖርበት ከተፈቀደው የግዥ ዘዴ ውጪ በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ የተገዛ መሆኑ እንዲሁም በድምሩ በብር 118,616.00 የሆነ የአገልግሎት እና የዕቃ ግዢ ያለውድድር ከአንድ አቅራቢ ብቻ የተገዛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

የዕቃም ሆነ የአገልግሎት ግዢ ሲፈጽም በአዋጁ በተደነገገው መሰረት የማይፈጽም ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ሊባክን ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የፌደራል መንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ በሚፈቅደው የግዥ ዘዴና የጨረታ ማሰታወቅያ መሰረት ግዥዎች መፈፀም አለባቸው::

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከ2007 በጀት አመት ጀምሮ በጋዜጣ ጨረታ እየወጣ ግዥ በመፈፀም ላይ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሰ) **ለመ/ቤቱ ገቢ ያልሆነ ንብረትን በተመለከተ**

ግኝት

በፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት በመስሪያ ቤቱ ስም የተገዛ ንብረት ተገቢው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥለት እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ በእርዳታም ሆነ በስሙ ለገዛቸው ንብረቶች በንብረት ገቢ ደረሰኝ (በሞዴል/ 19) ገቢ የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በሂሳብ ማዘዥያ ቁጥር 371413 ወጪው ለተመዘገበው ኬብል በብር 1,269.00 ግዥ ተፈጽሞ ንብረቱ ግን በእቃ ወይም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ለመ/ቤቱ ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት

የተገዙት ንብረቶች የገቢ ደረሰኝ የማይቆረጥላቸው ከሆነ ለብክነት ወይም ለስርቆት ሊጋለጡ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ቅ/ጽ/ቤቱ በመመሪያው መሰረት የገዛውን ንብረት የእቃ ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት ንብረቱ ገቢ ሊሆን ይገባል ፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ለእቃው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት ገቢ የተደረገ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል ፡፡

5. የሂሳብ ሪፖርትን በተመለከተ

ሀ) የተለያዩ ሂሳብ መደቦች በብር 131,224,465.64 ያልተለመደ (አብኖርማል) ባላንስ የሚያሳዩ መሆኑ

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 (2ለ) መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን/ዴቢት ወይም ክሬዲት/ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡በዚህ መሰረት ሰኔ 30/2006 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ ለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የስራ ሂደት በኩል(ለGOV-1133) የተጣራ ሀብት (Equity Account) በብር 299,806.45 ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ ፡፡
- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በመደበኛ ሂሳብ ላይ የባንክ ሂሳብ በብር 37,465.83 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፡፡

- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በጉምሩክ ስነስርአት የስራ ሂደት (በገቢ ዋስትና ሂሳብ ቡድን) በኩል በብር 4,945,805.67 እንዲሁም በግብር ማስታወቂያና የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ቡድን በኩል በብር 25,304,286.35 የተጣራ ሀብት ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ ፡፡

- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የገቢ ሂሳብ የተጣራ ሀብት በብር 98,292,906.94 እንዲሁም የመደበኛ ሂሳብ የተጣራ ሀብት በብር 534,373.52 ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ

- በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በኩል የተጣራ ሀብት ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000026238521 በብር 218,319.27 እንዲሁም በዲፖዚት ባንክ ሂሳብ ቁጥር1000026238537 በብር 18,072.15 በድምሩ በብር 236,391.42 የተጣራ ሀብት ያልተለመደ (ዴቢት) ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን፣

- በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የዋስትና ሂሳብ የተጣራ ሀብት በብር 428,768.51 ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት በኩል የሚከፈለው ሰው/ግለሰብ እና የቆየበት ጊዜ የማይታወቅ በዴቢት(ያልተለመደ ሚዛን) ብር 25,836 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በኩል ሂሳብ መደብ 4103(ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 1962) በብር 890,854.76 እና ሂሳብ መደብ 4103-5 (ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 512c21002084) በብር 227,970.19 በድምሩ በብር 1,118,824.95 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ ባልተለመደ ሂሳብ የተመለከቱት ሂሳቦች ወደተጠቃለለ ሂሳብ ባሉበት ሁኔታ ሪፖርት መደረግ ሲገባቸው እንዲካካሱ/ከሌሎች ትክክለኛ ሚዛን ካላቸው እንዲቀነሱ መደረጋቸው ታውቋል፡፡

ስጋት

በዓመቱ መጨረሻ በሚቀርበው የሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታዩ የሂሳብ መደቦች ትክክለኛ ሚዛናቸውን ጠብቀው በተጠቃለለው ሂሳብ ላይ ሪፖርት የማይደረግ ከሆነ የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ ላይገልጽ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከላይ የተገለጸ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ያልጠበቀበት ሁኔታ ሊጣራና ለሂሳቡም አስፈላጊው የምዝገባ ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል ፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የሂሳብ ማስተካከያ ተሰርቶለት ትክክለኛውን ሚዛን እንዲያሳይ የተደረገ መሆኑን፣ ሲገልጽ ሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶችም ለረጅም ጊዜ የቆዩ ከተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የዊዝሆልዲንግ ተከፋይ ሂሳብ ፈሰስ ጋር የተያያዘ በመሆናቸው በማጥራት ለማስተካጀል ጥረት እንደሚያደርጉ ምላሽ ሰጠተዋል፡፡

ለ) ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ ብር 11,230,845.16 ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር በሂሳብ መግለጫ ላይ ለሰፈረው ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ የሆነ ደጋፊ ሰነድ ያለው ለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-

- በጉምሩክ ስነስርአት የስራ ሂደት (ገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን) በኩል በድምሩ ብር 673,639.81 እንዲሁም በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት በኩል(ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 6226) በሂሳብ መደብ ቁጥር 4201 ብር 44,337.98 ቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ከማን እንደሚሰበስበው

መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ ሰኔ 30/2006 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ በተሰብሳቢነት ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፡፡

- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል (ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 2643) በተቀፅላ ሌጀር ላይ በኮድ ብቻ ተመዝግቦ ነገር ግን ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ በድምሩ ብር 16,169.49 የረጅም ጊዜ የደመወዝ ብድር ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም በተሰብሳቢ ተቀፅላ ሌጀር ላይ ሂሳቡ በክሬዲት ሚዛን የሚታይ በድምሩ ብር 26,953.43 ሂሳብ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል ፡፡
- በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት የአገር ውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ በሂሳብ መደብ 4201 ለተመለከተው ብር 7,798.52 የሂሰቡ መነሻ ሰነድ(ከማን እና መቼ እንደሚሰበሰብ) ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ መኖሩ
- በዋናው መስሪያ ቤት በግዢና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬቱ በኩል (በባንክ አካውንት ቁጥር1000005069401) በድምሩ ብር 10,372,719.65 በተሰብሳቢነት ሪፖርት ለተደረገው ሂሳብ ደጋፊ ሰነድ ሊቀርብለት አለመቻሉ፣
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በመደበኛ ሂሳብ ላይ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ከማን እንደሚሰበሰብ መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለና በተፅላ ሌጀር ላይ በኮድ ብቻ ተመዝግቦ ያለ ሂሳብ በድምሩ ብር 61,786.20 መኖሩ እንዲሁም ሒሳቡ በተቀፅላ ሌጀር ላይ በኮድ ብቻ ተመዝግቦና ክሬዲት ሚዛን ላይ የሚታይ ሂሳብ በድምሩ ብር 27,440.08 መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሚቀርበው የሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ትክክለኛ የመ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሆናቸው በሰነድ የተረጋገጠ ካልሆነ በቅርንጫፍ ፅ/ቤቱም ሆነ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ደረጃ የሚዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በመመሪያው መሰረት በተሰብሳቢ ሂሳብነት ሊያዝ የሚገባዉ ሂሳብ አግባብነት ያለው ደጋፊ ሰነድ ሊኖረው ስለሚገባ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ሂሳቡ ሊስተካከል ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- የድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት፣ የመቀሌ ቅ/ፅ/ቤትና የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ሂሳቦቹ ከ2001 በፊት ጀምሮ ያሉ በመሆኑ በተሰጠው የማሻሻያ እርምጃ መሰረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ሂሳቡን ለማስተካከል እንደሚሰሩ፣ ገልጸዋል፡፡

<u>የዋናው መስሪያ ቤት ስራ አመራር፡-</u>

- 4201 በተመለከተ የሚጣሩ ሰነዶች ተደራጅተው የሚወራረድ፣ አንዳንዶቹ ተጣርቶ ማስተካከያ እንደሚደረግ፣ በተመለከተ ከ2000 በጀት ዓመት ከውህደት ጊዜ ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ የገንዘብ እጥረቱ የሚታይባቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ሰነዶችን ባለማግኘታቸው ለመክፈል (write off) ማስደረግ ያልቻሉ ሲሆን ሰነድ ማደራጃ እና ሰነድ አደራጅ ሰራተኛ የተመደበ በመሆኑ እስከ መጋቢት 30/2007 ዓ.ም ማስተካከያ የሚደረግበት እንደሆነ፡፡
- 4253 በተመለከተ ብር 382,256.70 ሶስቱ መ/ቤቶች ሲቀላቀሉ የተመዘገበ እና በጥር ወር 2006 ዓ.ም በድምር የዞረ፣ ብር 23,181.00 የአመዘጋገብ ስህተት ማስተካከያ የሚደረግበት መሆኑ፣
- የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ጉዳዩን በተመለከተ ከ 2002 ጀምሮ ገንዘብ ሚ/ር ብድር በሚሰጥበት ወቅት እና በኦዲት ግኝት ይመለሱ ተብለው በስህተት የተከፈሉ የትርፍ ሰአት ክፍያ እና ሌሎች የሚመለሱ ሂሳቦች ሲመዘገቡ የተፈጠረና ምዝገባው ሁለት ግዜ(ደብል) እየተደረገ የተመዘገበ ሊሆን እንደሚችል በመግለፅ አስፈላጊውን ማጣራት አድርገው ምላሻቸውን የሚያሳውቁ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሐ) **<u>ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ ብር 117,574,106.58 መኖሩ</u>**

<u>ግኝት</u>

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጽምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸዉን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለዉ አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በቂ የሆነ ማስረጃ ያላቸውና ወደፊትም ክፍያ የሚፈፀምባቸዉን ሂሳቦች ብቻ በተከፋይነት መዝግቦ ሪፖርት የሚዘጋጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በኩል ለባንክ አካውንት ቁጥር 3756 በሂሳብ መደብ 5051 ብር 72,561.97 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 5054 ብር 344,885.45 የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ እዳና ወደፊትም ክፍያ የሚፈፅምበት ለመሆኑ መረጋገጥ ያልቻለ ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 417,447.42 መኖሩ፣

- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ እዳ ለመሆኑ ማረጋገጥ ያልተቻለበት ሂሳብ ብር 165,329.82 በተከፋይነት ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣

- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በአገር ውስጥ ገቢ ሂሳብ በኩል ብር 25,409,984.75፤ በጉምሩክ ስነ-ስርዓት የስራ ሂደት በኩል ብር 5,024,865.91 እንዲሁም በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል ብር 47,035.33 የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ እዳና ወደፊትም ክፍያ የሚፈፅምበት ለመሆኑ ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ መኖሩ፣

- በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በአገር ውስጥ ገቢ የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5026 የተመለከተው ብር 1,826,510.21 የሂሰቡ መነሻ ሰነድ (ሂሳቡ ለማን እና መቼ እንደሚከፈል) ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ መኖሩ፣

- የዋና መ/ቤቱ እዳና ወደፊትም ክፍያ የሚፈፅምበት ለመሆኑ ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 2,350,867.88 መኖሩ፣

- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በገቢ አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት በኩል በአደራ የባንክ ሂሳብ ቁጥር (214-3332) በሂሳብ መደብ 5026(ለክልሎች ተከፋይ ሂሳቦች) የተጠቀሰው ብር 82,327,443.74 ምንነት ለማጣራት ተሞክሮ ማስረጃዎቹ ባለመገኘታቸው ሂሳቡን ለማጣራት ያለመቻሉ፤ እንዲሁም በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት የተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5005(ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች) ከተጠቀሰው ብር 8,221.52 ውስጥ ለብር 4,621.52 ማስረጃዎች ባለመገኘታቸው ሂሳቡን ለማጣራት ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

ሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሣይ ሊያደርገው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በሂሳቡ ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲያሳይ አስፈላጊው ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት ችግሩን በተመለከተ ከሀብት አስተዳደር ጋር በመነጋገር የሚፈታ መሆኑን፡፡

- የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ሁለቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ሲቀላቀሉ የአዲስ አበባና ሌሎች ወጪዎች ማስተናገጃ ቅ/ፅ/ቤት የ2005 ከሀምሌ-መስከረም ድረስ ያለ የደመወዝ መዋጮ ምዝገባ አለማለፉ እንደሆነና IBEX ተከፍቶ ችግሩን በማየት የምዝገባ ማስተካከያ በማድረግ የደረሱበትን የሚያሳውቁ መሆኑን ፣

- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በጉምሩክ ስነስርአት በኩል የታየውን ተከፋይ ሂሳብ በተመለከተ ችግሩ ከ 1996 ዓ.ም ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣና ገንዘቡ ወደቀጥታ ገቢ ሂሳብ ፈሰስ ስለመሆኑ የባንክ ስቴትመንት የሚያመላክት ቢሆንም ፣ የተሟላ የገቢ ማስረጃ ያልተያያዘለትና የሂሳብ አመዘጋገብ

ስህተት ስላለበት እንዲስተካከል ለዋና መ/ቤት በተደጋጋሚ ተጠይቆ እስካሁን ምላሽ/ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ፤ በኦዲተሮቹ የተሰጠውን የማሻሻያ እርምጃ መሰረት ከባለስልጣን መ/ቤቱና የሚመለከታቸው ጋር በመመካከር የማስተካከያ ስራ ለመስራት ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን ፣

- የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር በተከፋይ ሂሳብነት የተያዘው ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ በወቅቱ በገቢ ድርሻ ክፍፍል መሠረት ለክልሎች እና ለከተማ መስተዳደሮች መላክ ሲገባ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የተደረገ ሲሆን የማን ክልል ወይም የከተማ መስተዳድር ተከፋይ መሆኑን መለየት ያልተቻለ ገንዘብ ስለሆነ ዋናው መ/ቤትን አቅጣጫ እንዲያስቀምጥ መጠየቃቸውን ፣

- የዋናው መስሪያ ቤት ስራ አመራር በሂሳብ ኮድ 5021 የተያዘው ብር 1,101,421.77 በተመለከተ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከቀድሞ ጉምሩክ ባለስልጣን በ/ቤት ከሚያዙ የኮትሮባንድ እቃዎች ሽያጭ ለሰራተኞች የሚከፋፈል በሚል የተያዘና በአሁኑ ጊዜ ለሰራተኞች በጋራ ለሚያገለግሉ ተግባራት ላይ የሚገኝ መሆኑን ፤ በሂሳብ ኮድ 5004 ሪፖርት ለተደረገው ግን ወደ ፊት አጣርተው የሚያወራርዱ መሆኑን፣ እንዲሁም በሂሳብ ኮድ 5006 ሪፖርት የተደረገው ከ2001 ዓ.ም ሲንከባለል የመጣ ብር 669,105.38 እና የ2006 ዓ.ም በማኑዋል ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች የተከፈለ ነገር ግን በሲስተም ያልተመዘገበ ብር 501,926.55 ያለ መሆኑን ፣

- የጅማ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር በገቢ አሰባሰብ በኩል ያለው የአመዘጋገብ ስህተት ሊሆን እንደሚችል እና ስለሂሳቡ ማጣራት እንደሚያደርጉ፤ በሃብት አስተዳደር በኩል ያለውም ብር 4000.00 ለአባይ መዋጮ በብልጫ ተከፍሎ የነበረና በተከፋይነት ተይዞ ፈሰስ የሆነ ሂሳብ መሆኑን፤ ለብር 621.52 ግን ሰነዱን ለማግኘት አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

በዋናው መስሪያ ቤት በኩል በሂሳብ ኮድ 5021 የተያዘው ሂሳብ ብር 1,101,421.77 ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በባንክ ተቀምጦ የሚገኝ በመሆኑ የሚመለከተው አካል አስፈላጊውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

መ) **በባንክ መግለጫ(bank statement)ና በሪፖርት የተጠቀሰው ገንዘብ በብር 29,603,876.70 የተለያየ መሆኑ**

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8(8) መሰረት በባንክ ሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ላይ የሚታየው የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት መረጋገጥ እንደለበት ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንፃር ለእያንዳንዱ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት በባንክ ያለውን ገንዘብ ትክክለኛነት የሚረጋገጥ ለመሆኑና የባንክ ሂሳቡም ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በተስተካከለው የባንክ አካውንት ሌጀር ባላንስ, ሰኔ 30/2006 በተዘጋጀው የቅ/ጽ/ቤቱ የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት መሰረትና በባንክ ማስታረቂያ መካከል የባንክ ሂሳብ ለባንክ አካውንት ቁጥር 100000184418(በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፊንፊኔ ቅርንጫፍ) በብር 10,813,412.07 እንዲሁም ለባንክ አካውንት ቁጥር 1000019737342 (በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሞጆ ቅርንጫፍ) በብር 18,790,464.63 በድምሩ በብር 29,603,876.70 ልዩነት ያለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

ስጋት

ትክክለኛው የቅ/ጽ/ቤቱ እንቅስቃሴ ማወቅ አይቻልም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

መስሪያ ቤቱ መመሪያው በሚያዘው መሰረት የባንክ ሂሳብ በማስታረቅ የሂሳብ ሪፖርቱን ሊያስተካክል ይገባል ፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ሂሳቡን የማጥራት ስራ እየተሰራ እንደሆነና በአሁኑ ጊዜ በባንክ መግለጫ (bank statement)እና በሪፖርት የተጠቀሰው ገንዘብ ልዩነት ወደ ብር 17,112,372.73 ዝቅ ያለ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

6. የበጀት ሂሳብ

ከበጀት በላይ ብር 14,250,809.51 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ

ግኝት

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 30 መሠረት በአንድ የበጀት አመት ውስጥ በበጀት አዋጁ ለተመለከቱት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እንዲከፈል በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ መፈፀም እንደማይቻል፣ እንድሁም በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 መሠረት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ መሆኑን ይደነግጋል ፡፡ ነገር ግን በሂሳብ መደብ 6111(ለደመወዝ) ብር 9,576,315.58፤ በሂሳብ መደብ 6217(ለነዳጅና ቅባት) ብር 1,544,844.66 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 6231(ለውሎ አበል) ብር 3,129,649.27 በድምሩ ብር 14,250,809.51 ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከተፈቀደው በጀት በላይ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ያለአቅድ ወጪ እንዲወጣና የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊደረግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የበጀት እጥረት ቢያጋጥመው እንኳን በህጉ መሰረት ተጨማሪ በጀት እንዲፈቀድ ወይም የበጀት ዝውውር ማድረግ ይኖርበታል እንጂ ከተፈቀደለት በጀት በላይ ወጪ ማውጣት የለበትም፤፤

የስራ አመራሩ ምላሽ

ከበጀት በላይ የወጣውን በተመለከተ አዲስ ሰራተኞች የተቀጠሩ በመሆኑና ከኢፍሚስ ጋር በተያያዘ የ2006 በጀት ዓመት የሂሳብ አመዘጋገብ ወደ ኋላ

ቀርተው በመሆኑ በጊዜው አስፈላጊውን የበጀት ማስተካከያ ማድረግ አለመቻላቸውን ሆኖም መረጃውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚ/ር ያቀረቡ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

7. <u>ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ</u>

ሀ) <u>ሳይወራረድ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ብር 251,674.12 ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶለት ክትትል በማድረግ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠርና ሂሳቡም በወቅቱ እንዲወራረድ ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የፈደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 16/4 መሰረት የውሎ አበልና የመጓጓዣ ቅድመ ክፍያ ሠራተኛው ስራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኂላ በሰባት(7) ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተገቢው የቁጥጥር ስርአት የተዘረጋላቸውና በወቅቱም የሚወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል (የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1131) ብር 6,050.09 የሆነ የውሎ አበልና ትራንስፖርት ቅድሚያ ክፍያ(suspense),፣የረዥም ጊዜ የደመወዝ ብድር፣ እንዲሁም ሌሎች ቅድመ ክፍያዎች ሳይወራረድ ከ2 ወር እስከ 3 አመት ያስቆጠሩ መሆኑ
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል (ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 2643) የሰራተኞች ደመወዝ ቅድሚያ የተከፈለ ሳይሰበሰብ ከ 5 አመት እስከ 12 አመት ያስቆጠረ ብር 35,761.34 ሂሳብ መኖሩ ፡፡
- በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት በኩል በሂሳብ መደብ በ4203 በተሰብሳቢነት ከተያዘው ብር 201,002.04 ውስጥ ብር 176,679.81 ሳይወራረድ ከ1 ዓመት እስከ 4 ዓመት ድረስ የሆነው ሂሳብ መኖሩ፡፡

- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በሂሳብ መደብ 4210 ብር 24,156.53 በተለያየ ጊዜ ለክልሎቹ የተላከና ማስረጃው ቀርቦ ያልተወራረደ መሆኑ
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 5,183.99 ከ7 ወር እስከ 2 ዓመት ከ4 ወር የቆየ እንዲሁም ብር 59.81 የቆየበት ጊዜ የማይታወቅ በድምር ብር 5,243.80 ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል (ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 2643) ብር **3,782.55** የሆነ ቅድሚያ ክፍያ(suspense) ሳይወራረድ ከ 9 ወር እስከ 7 አመት ያስቆጠረ ሂሳብ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

በመመሪያው መሰረት ማንኛውም ቅድመ ክፍያዎች በህግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማይሰበሰብ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ለብክነት ይጋለጣል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ሳይሰበሰብ የቆየው የመንግስት ገንዘብ ከሚመለከታቸው አካለት ሊሰበሰብ ይገባል ፡፡ ለወደፊቱም ሳይሰበሰቡ ረጅም ግዜ የሚያስቆጥሩ ሂሳቦች እንዳይፈጠሩ ወቅታዊ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥ በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 698.96 ተመላሽ የተደረገ መሆኑን፣ በባህርዳር ቅ/ፅ/ቤት ብር 107258.68 ከኦዲት በኂላ የተወራረደ መሆኑንና በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የተጠቀሰው ሂሳብ በ2007 በጀት አመት በሙሉ የተወራረደ መሆኑን ፣
- የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ክሊራንስ ሳይወስዱ ከመ/ቤቱ ለለቀቁ ሰራተኞች ለሰው ሀብት ስራ አመራር ቡድን ደብዳቤ የተጻፈ መሆኑን እና በ2007 በጀት ዓመት በህግ ተጠይቆ እንዲወራረድ ጥረት እንደሚደረግ ከኮንትራት ሰራተኞች ለአባይ ግድብ መዋጮ ተመላሽ የተደረገው በቀጣይ

በማኔጅመንት ውሳኔ የሚሰጠው መሆኑ በስራ አመራር ምላሽ ወቅት በጽሁፍ ምላሽ ከመሰጠቱም በተጨማሪ በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

- የመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ከ 1995 እስከ 2001 ዓ.ም ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ መረጃ ያልተገኘለት እና ሰራተኞቹም የት እዳሉ መረጃ ያልተገኘላቸው መሆኑን በመግለፅ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ሂሳቡን ለማጥራት ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ለ) <u>ለተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ የሂሳብ ቋት ያልተቋቋመ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 4(ረ)፣ 5(መ)እና 8(ሀ) መሰረት የሂሣብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የተሰብሣቢና የተከፋይ አጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብ ሚዛንን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር በኩል ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ አጠቃላይም ሆነ ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ::

<u>ስጋት</u>

ለእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ አጠቃላይና ተቀጽላ ሌጀር ካልተቋቋመ የሂሳቡን ትክክለኘነት ለማረጋገጥ እያስችልም፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለእያንዳንዱ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣብ አጠቃላይና ተቀጽላ ሌጀር ሊቋቋምለት ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

በኦዲቱ የተሰጠው አስተያየት እንደግብአት በመውሰድ ለወደፊቱ እንደሚያስተካክሉ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ሐ) <u>የተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ</u>

<u>ግኝት</u>

በየመስሪያ ቤቱ የተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ የሰፈሩት የተከፋይ ሂሳቦች ትክክለኛ እዳ መሆናቸውንና በማስረጃ የተደገፉ ለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በባህርዳር ቅፅ/ቤት፡-

- በጉምሩክ ስነስርዓት የስራ ሂደት በኩል በተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ላይ ሂሳቡ ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ሲከፈል የሚቀናነሰው ከማጠቃለያ ሌጀር ላይ በመሆኑ እንዲሁም ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ሲከፈል ከተቀፅላ ሌጀር ላይ የማይቀናነስ በመሆኑ በተቀፅላ ሌጀሮች ላይ ሊኖር የሚችለውን ባላንስ ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 5054 የሚታየው ተከፋይ ሂሳብ በህገ-ወጥ ሲዘዋወር ከተያዘ ቡና ሽያጭ በተገኘ ገቢ ላይ ለጠቋሚ የሚከፈል ተብሎ የተያዘ ሲሆን ውሳኔ እስኪያገኝ ተብሎ በመያዙ ምክንያት ወደ ገቢነት ሳይቀየር ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት የቆየ መሆኑ፤
- በሃብት አስተዳደር በተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ላይ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ላይ የሚታየው የተከፋይ ሂሳብ ብር 70,708.57 ማስረጃው ለኦዲቱ ስለአልቀረበ የሂሳቡን ሁኔታ ማጣራት ያለመቻሉ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

በሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚገለፁ አሃዞች በማስረጃ ያለመደገፍ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማኒነት ከማሳጣቱም በላይ የህግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

ሂሳቡ ተጣርቶ ትክክለኛው መታወቅና ማስረጃውም መያያዝ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥ ብር 59,972.53 ወጪ ሆኖ ለባለመብቶቹ የተከፈለ መሆኑንና ቀሪው ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ በመሆኑ ለባለመብቱ የሚከፈል መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

8. ንብረት

ሀ) ለንብረት ተገቢው የቁጥጥር ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑ

ግኝት

በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 6/1 ረ እና አንቀጽ 10/ሀ መሰረት ለመንግስት ንብረት የተሟላ የቁጥጥር ስርአት የተዘረጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በውርስ መጋዘን ውስጥ በሚገኙና በመደበኛ በጀት በተገዙ ንብረቶች ላይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡-

በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በውርስ መጋዘን ውስጥ ለሚገኙ ንብረቶች፡-

- አመታዊ የንብረት ቆጠራ የማይካሄድ መሆኑ
- የንብረት ምዝገባና የንብረት ጥበቃ ስራ በተለያዩ ሰራተኞች የማይሰራ (በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወን) መሆኑ
- የተወረሱ ንብረቶች በአግባቡ በመዝገብ የማይመዘገቡ መሆናቸው ታውቋል፡፡

በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-

- በመደበኛ በጀት ለተገዙ የቋሚም ሆነ የአላቂ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ
- በመደበኛ በጀት ለተገዙ እቃዎች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የንብረት ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም የንብረት ከወጪ ቀሪ ያልተመሳከረና ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ መሆኑ፤
- በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ንብረቶች ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ ሁኔታ ተደባልቀው የተገኙ መሆናቸው በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በላጋር ጉምሩክ ለሚገኘው ዉርስ መጋዘን የስቶክ ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑ
- ለተወረሱ ንብረቶች አመታዊ ቆጠራም የማይካሄድ መሆኑ

- በሐረር የሚገኘው የውርስ መጋዘን እና በላጋር ጉምሩክ የሚገኙ የተወሰኑ ውርስ መጋዘኖች መደርደሪያ የሌላቸው በመሆኑ ንብረቶቹን በእቃዎቹ ባህሪና አይነት ለያይቶ ለማስቀመጥ የማያመች በመሆኑና ንብረቶቹ መሬት ላይ ስለተቀመጡ ለብልሽት የሚዳረጉበት ሁኔታ ያለ መሆኑ
- በሐረር ለሚገኘው የውርስ መጋዘን ንብረት ጠባቂና የንብረት መዝጋቢ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>**በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በመደበኛ በጀት ለተገዙ ንብረቶች፡-**</u>

- የቋሚም ሆነ የአላቂ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ያልተቋቋመ በመሆኑ ንብረት ከወጪ ቀሪ ለማወቅ የማይቻል መሆኑና ከቆጠራ ውጤቱ ጋር ለማመሳከር የማይቻል መሆኑ፤
- የንብረት መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ የሌለ መሆኑ
- በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ንብረቶች የሚገኙ ሲሆን የሚሸጡ፤የሚተላለፉ ወይም ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ተለይተው እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፤፤
- በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ንብረቶች ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ ሁኔታ ተደባልቀው የተገኙ መሆናቸው ፤፤
- በቅ/ጽ/ቤቱ የንብረት ጠባቂና መዝጋብ በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የተለያዩ ንብረቶች የመኪና ጎማዎች, ኮምፒተሮች፣ ፕሪንተሮች፤ ስፔርፓርቶች፤ የተለያዩ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች ያለ አገልግሎት በቅ/ጽቤቱ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

<u>**በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-**</u>

- በ2006 በጀት አመት አመታዊ የአላቂም ሆነ የቋሚ ንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራ ዉጤቱ ግን ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ በመሆኑ

በቆጠራዉና በንብረት መዝገብ መካከል ልዩነት ይኑር አይኑር ማወቅ አለመቻሉ፡፡

- ዋጋቸው ከብር 1000/አንድ ሺህ/ በታች የሆነ የአግልግሎት ዘመናቸው ከአንድ አመት በላይ የሆኑ ንብረቶች በመዝገብም ሆነ በእስቶክ ካርድ ላይ የማይመዘገቡ መሆኑን ፡፡
- ኒሳን ደብል ጋቢና (ሰሌዳ ቁጥር 4-16323 ኢት) እንዲሁም ቶዮታ ደብል ጋቢና (ሰሌዳ ቁጥር 4-17130 ኢት) በመስሪያ ቤቱ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

<u>**በውርስ መጋዘን የሚገኙ ንብረቶችን በተመለከተ**</u>

- ውርስ መጋዘኑ መደርደሪያ የሌለው በመሆኑ ንብረቶቹን በእቃዎቹ ባህሪና አይነት ለያይቶ ለማስቀመጥ የማያመች በመሆኑና ንብረቶቹ መሬት ላይ ስለተቀመጡ ለብልሽት የሚዳረጉበት ሁኔታ ያለ መሆኑ
- በናሙና ከታዩት ንብረቶች ውስጥ ሳይወገዱ ረዘም ላለ ጊዜ በመጋዘን የቆዩ ንብረቶችና ኬሚካሎች የሚገኙ መሆኑ.
- ጉዳዩ ያላለቀ (በክርክር ላይ) ላለ አንድ ተሽከርካሪ ጊዜያዊ እቃ መረከቢያ ደረሰኝ ሞዴል 270 ያልተቆረጠለት መሆኑ.
- የተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ላሉ 21 ተሽከርካሪዎች ለብቻው የተከለለ ቦታ የሌለ በመሆኑና ለሰው እንቅስቃሴ ክፍት በመሆኑ ንብረቶቹ ለተለያየ ነገር የተጋለጡ መሆኑ
- የተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉት 21 ተሽከርካሪዎች በመዝገብ እና እስቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>**በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-**</u>

- በመደበኛ በጀት ለተገዙ ንብረቶች በ2006 በጀት አመት አመታዊ የአላቂም ሆነ የቋሚ ንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራ ውጤቱ ግን ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ በመሆኑ በቆጠራውና በንብረት መዝገብ መካከል ልዩነት ይኑር አይኑር ማወቅ አለመቻሉ ፡፡

- አንድ ባጃጅ (ሳሌዳ ቁጥር 4-0747 ኢ.ት) በመስሪያ ቤቱ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌለው መሆኑ፡፡

<u>በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-</u>

- የሚወገዱ ንብረቶች (በውርስ መጋዘን ካሉት በስተቀር) ተለይተው የተቀመጡ ቢሆንም በቅ/ፅ/ቤቱ በኩል የተወሰደ እርምጃ ያለመኖሩ፡
- የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር 4-16322 የባለቤትነት ደብተር በመስሪያ ቤቱ ሊገኝ ያልቻለ መሆኑ፡
- ለጣቢያዎች የሚላኩ ደረሰኞች ማለትም(የጉምሩክ ቀረጥ መሰብሰቢያ፤ የኮንትሮባንድ ዕቃ ገቢ ማድረጊያ ሞ/265፤ የኮንትሮባንድ ዕቃ ወጪ ደረሰኝ ሞ/266 እና ሞ/270 የጥቆማ መቀበያ ቅፅ፤ በኮንትሮባንድ ተይዘው መወገዳቸውን ወደ ሌላ መተላለፋቸውንና መቀመጣቸውን ማረጋገጫ ቅፅ፤)ተሰርቶባቸው ሲያልቁ ወደ ጣቢያዎች ንብረት ክፍል መመለሳቸውንና በጥንቃቄ መቀመጣቸውን ቅ/ፅ/ቤቱ የማይከታተል መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በውርስነት የተያዙ ንብረቶችን በተመለከተ ፡-</u>

- በጅማ የውርስ መጋዘን ውስጥ ረጅም ጊዜ የሆናቸው የተወረሱ 1239 የተለያየ ሞዴል ያላቸው የሞባይል ቀፎዎች ከሦስት ዓመታት በላይ የቆዩ እንዲሁም ሁለት የወርቅ መፈለጊያ ማሽኖች ያለአገልግሎት የተቀመጡና ውሳኔ ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- በአሶሳ የውርስ መጋዘን ውስጥ እቃዎች በአይነታቸው እና በመጠናቸው ተለይተው ያልተቀመጡ በመሆኑ ለቁጥጥር አመቺ አለመሆኑ ፤ በመጋዘኑ ውስጥ 44 ማዳበሪያ ቡና እና 10 ማዳበሪያ ስኳር በሚዛን ተመዝኖ ትክክለኛው መጠን በሞዴል ያልተመዘገበ መሆኑ፤ በአቀማመጥ ችግር ምክንያት በእርጥበት ለብልሽት የተጋለጠ መሆኑ፤እንዲሁም በዚሁ መጋዘን ውስጥ ብዛት ያላቸው የወርቅ መፈለጊያ ማሽን፤ የነብር ቆዳ፤ የዘንዶ ቆዳ፤ የዝሆን ጥርስና መድሃኒቶች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፤ እንዲሁም ሌሎች የተለያዩ እቃዎች የተበላሹና የሚወገዱ ተብለው ተለይተው የተቀመጡ ቢሆንም መፍትሔ ያልተሰጣቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በከፍተኛ ግብር ከፋይ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል፡-

- በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል በ2006 በጀት ዓመት የቋሚ ንብረት ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ
- ሁለት (2) ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ጋራዥ ከ7 ወር እስከ 1 ዓመት ከ6 ወር የቆየ መሆኑን እና በመ/ቤቱ ጋራዥ ከ1ዓመት ከ11 ወር እስከ 2ዓመት ከ11ወር የቆሙና መወገድ የነበረባችው አራት (4) ተሽከርካሪዎች መኖራቸው ታውቋል፡፡

ስጋት

- ለንብረቶች ተገቢው የቁጥጥር ስርአት የማይዘረጋላቸው ከሆነ ለብክነትና ለብልሽት ይዳረጋሉ፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

- የስቶክ መዛግብት መያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሰራተኛ መሰጠት የለባቸውም
- በየአመቱ በውርስ መጋዘን ውስጥ ያሉ ንብረቶች በመ/ቤቱ በተቋቋመው የቋሚ ንብረት ቆጠራ ኮሚቴ ሊቆጠር ይገባል፡፡
- የውርስ መጋዘን ንብረትን የሚያስተዳድር ክፍል የተጠናከረ መረጃ የያዘ የተወረሱ ንብረቶችን መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ መያዙን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ቅፅ/ቤቶቹ የተሰጠው አስተያየት ትክክል መሆኑንና ለችግሮቹ የተለያዩ ምክንያቶች መኖራቸውን በመግለጽ ለወደፊት በተሰጠው አስተያየት መሰረት የሚያስተካክሉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ለ) በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ

ግኝት

በፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት የወረሷቸውን እንዲሁም ጉዳያቸው

በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ያሉ 12 ተሽከርካሪዎችን በአግባቡ እየተጠበቁ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ለንብረቶቹ ለብቻው የተከለለ ቦታ የሌለ በመሆኑና ለሰው እንቅስቃሴ ክፍት በመሆኑ ንብረቶቹ ለስርቆት የተጋለጡ ሲሆን ተሽከርካሪዎቹም ያሉበት ቦታ ለአቧራና ለፀሀይ የተጋለጠ በመሆኑ ተሽከርካሪዎቹ እየተበላሹና ከጥቅም ውጪ እየሆኑ መሆኑ
- ንብረቶቹም በመዝገብ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በቅ/ጽ/ቤቱ የተወረሱ እና በአደራ የተመዘገቡ መኪናዎች በአግባቡ መጠለያ ተብጅቶላቸው የማይቀመጡ ከሆነ በቀላሉ ለአደጋ የተጋለጡ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም ንብረቶቹ ከስቶክ ካርዱ እና ከሞዴሎቹ በተጨማሪ በመዝገብ የማይመዘገብ ከሆነ ለቁጥጥር የሚያስቸግር ይሆናል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

- ንብረቶቹ በመዝገብ ላይ ተመዝግበው ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡
- ለንብረቶቹ የተለየ የተከለለ ቦታ በማቋቋም ንብረቶቹን ከሰው እንቅስቃሴ በመከለል ለተለያዩ አላስፈላጊ ድርጊቶች እንዳይፈፀምባቸው ሊደረግ ይገባል፡፡
- ተሽከርካሪዎች በቆዩ ቁጥር ዋጋቸው እየቀነሰና መወገድም ከማይችሉበት ደረጃ ሊደርሱ ስለሚችል መመሪያው በሚያዘው መሰረት በተለይ ጉዳያቸው አልቆ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በቶሎ ሊወገዱ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- የኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር ለንብረቶቹ ለብቻ የተከለለ ቦታ የሌለ በመሆኑ እና ለሰው እንቅስቃሴ ክፍት ለመሆኑ ንብረቶቹ ለተለያየ ነገር ማለትም ለውስጥ ዕቃ ስርቆት፣ ለጸሀይና ለአቧራ የተጋለጡ እንዲሁም እየተበላሹና ከጥቅም ውጭ እየሆኑ መሆኑ በትክክልም በየጊዜው የሚገመገሙት መሆኑን በመግለፅ ያሉበት ግቢ የተቋሙ ሳይሆን ተከራይተው በመሆኑ የሚቆዩበት በጊዜያዊነት ስለሆነና የተሰጣቸውን አዲሱ ግቢ

ለመውሰድ በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልፀው የተሰጠውን አስተያየት ግን የሚቀበሉት መሆኑን እንዲሁም ንብረቶች በመዝገብ አለመያዛቸውን በትክክል የሚቀበሉት ሲሆን ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ የተሰጠውን አስተያየት ተግባራዊ እናደርጋለን በማለት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

9) <u>ልዩ ልዩ</u>

ሀ) <u>የባለፈው የኦዲት ሪፖርትን በተመለከተ ግኝት</u>

በፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 17(3)መሰረት ተመርማሪ መስሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገኙ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት ከዚህ በፊት ለተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች የእርምት ወይም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በትክክለኛው የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ(CPC) ባለመስተናገዳቸው ያልተሰበሰበ ብር 2,462,599.46 ሂሳብ መኖሩ እንዲሁም በውርስ መጋዘን ውስጥ የምግብ ዓይነቶች፤ ኬሚካሎች፤ መድሀኒቶች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ ፡፡

<u>በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-</u>

- በሀብት አስተዳደር በኩል (ለባንክ ኮድ 1961) በተዘጋጀዉ የ2005 በጀት አመት ሂሳብ መግለጫ ላይ ሪፖርት ለተደረገው በድምሩ ብር 62,119.31 ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች ምንም አይነት ደጋፊ ሰነድ የሌላቸው በመሆኑ ሂሳቡ እንዲስተካከል አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሁንም መረጃ የሌለው ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ በሪፖርቱ ውስጥ ተካቶ የሚገኝ መሆኑ፡፡
- ውርስ መጋዘኑ መደርደሪያ የሌለው በመሆኑ ንብረቶቹን በእቃዎቹ ባህሪና አይነት ለያይቶ ለማስቀመጥ የማያመች በመሆኑና እቃዎቹም መሬት ላይ ተቀምጠው ለብልሽት የሚዳረጉበት ሁኔታ ስላለ በውርስ መጋዘን ለሚገኙ

ንብረቶች የእቃ መደርደሪያ እንዲዘጋጅላቸው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሁንም ያልተስተካከለ መሆኑ

- ሳይወገዱ ረዘም ላለ ጊዜ በመጋዘን የቆዩ ንበረቶች(ፌስታልና ሞተር ብስክሌቶች) የሚገኙ በመሆኑ እንዲወገዱ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሁንም ንብረቶቹ በመጋዘን የሚገኙ መሆኑ
- ጉዳያቸው ያላለቀ (በክርክር ላይ) ላሉ ተሽከርካሪዎች ጊዜያዊ እቃ መረከቢያ ደረሰኝ (ሞዴል270) እንዲሁም ለተወረሱት ደግሞ የውርስ ወይም የኮትሮባንድ መቀበያ ደረሰኝ (ሞዴል 265) ሊቆረጥላቸው ሲገባ ምንም የገቢ ሞዴል 270ም ሆነ ሞዴል 265 የማይቆረጥላቸው በመሆኑ እንዲስተካከል አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ያልተስተካከለ መሆኑ

<u>**በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-**</u>

- ያልተሰበሰበ ውዝፍ የታክስ ሂሳብ ብር 13,749,613.86
- ያልተሰበሰበ ውዝፍ የኤክሳይዝ ታክስ ሂሳብ ብር 3,028.72፤
- የታክስ ተቀናሽ ቅጽ ሳይቀርብ ተቀናሽ የተደረገ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,888,191.28 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤
- የግብር ማሳወቂያው በወቅቱ ያልቀረበ ብር 3,033,014.15 በ2002 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት ላይ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እስከአሁን ድረስ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>**በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-**</u>

ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት በ2005 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠባቸው ጉዳዮች ቢሆኑም እርምጃ ግን ያልተወሰደባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ቦረና አግሮ ኢንዱስትሪ ብር 502,248.06፤ ኑድ ቢዝነስ ኃ.የተ. የግ.ማ ብር 1,209,391.94 እንዲሁም ሊሙ ሊበን ኃ.የተ. የግ.ማ ብር 267,893.77 በድርጅቶቹ ቅሬታ ቀርቦባቸው ቅሬታቸው ያልታየና ውሳኔ ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

- ከቤስት ኢስት አፍሪካ ኃ.የተ. የግ.ማ የሚፈለግ ግብር ብር 22,261.17 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

- ጌቶ ኃ.የተ. የግ.ማ ለተወሰነበት ብር 505,906.30 ቅሬታ ያቀረበና በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ የገቢ ግብር ብር 139,708.96 በኪሳራ የተሸጋገረ ሲሆን የትርፍ ክፍፍል ግብር ብር 53,463.72 እንዲከፍል የተወሰነ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ያልተሰበሰበ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

በኦዲት አስታየት ላይ እርምጃ ካል ተወሰደ የኦዲቱን ዓላማ ካለማሳካቱም በላይ ችግሮች ከአመት አመት እንዲቀጥሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

አሁንም ከላይ ለተገለፁት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ቅ/ጽ/ቤቶች ግኝቶቹ ላይ እርምጃ ለመውሰድ በተለያየ ደረጃ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሆኑ ገልጸዋል ፡፡

<u>በባህርዳር ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-</u>

- ያልተሰበሰበውን ውዝፍ የታክስ ሂሳብ ብር 13,749,613.86 እና ብር 3,028.72 የኤክሳይዝ ታክስ ሂሳብን በተመለከተ ገንዘቡ በሙሉ ከ2002 ኦዲት በኂላ ከጥቁር አባይ ድርጅት እና ከባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ተሰብስቦ ገቢ የተደረገ መሆኑን ፡፡

- የታክስ ተቀናሽ ቅጽ ሳይቀርብ ተቀናሽ የተደረገ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,888,191.28 በተመለከተ ግኝቱ የተገኘባቸው ባህርዳር ጨርቃጨርቅ እና ዳሽን ቢራ ፋብሪካ ከግኝቱ በኂላ የታክስ ተቀናሽ ቅፅ እያዘጋጁ በማሳወቅ ላይ መሆናቸውን መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ለ) <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በየወሩ የማይታረቅ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርአት ነሐሴ 1990 ተሻሽሎ የወጣና ከዚህ አስቀድሞ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ማንዋል መሠረት የሂሳብ ኃላፊው በካዝና ውስጥ የሚገኘውን ገንዘብ መጠበቅና መቆጣጠር እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በሂሳብ ክፍሉ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ተደርጎ ከመዝገብ /ሌጀር/ ከሚያሣየው ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

ቢያንስ በወሩ መጨረሻ የሳጥን ከወጪ ቀሪ ቁጥጥር የማይደረግ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት እንዲጋለጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ከማጠናከር አንጻር ሂሳብ ክፍሉ ቢያንስ በወር አንዴ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከመዝገብ ጋር እንዲመዛዘን በማድረግ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የጥሬ ገንዘብ ቆጠራው የሚደረግ መሆኑንና የቆጠራው ሰርተፊኬት ግን ያልተያያዘ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ቆጠራ የሚደረግ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም ማስረጃው ካለመቅረቡ በተጨማሪ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር የማይረጋገጥ መሆኑ፡፡

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2006/2007 ዓመት የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት

1. ጥሬ ገንዘብ

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል የቁጥጥር ስርአት መዘርጋቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በኢትጵያ ብሔራዊ ቴአትር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መደብ 4101 የሂሣብ ቋት (General Ledger) ከወጪ ቀሪና በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ መካከል የታየው ብር 51,968.64 ልዩነት መንስኤ የማይታወቅ መሆኑ (ቆጠራ በማነስ)፣
- በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ሰኔ 30/2006 በተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ብር 44,445.23 በጥሬ ገንዘብ እና በሰነድ የተገኘ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ደግሞ ብር 52,501.24 በመሆኑ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራው በብር 8,056.01 በማነስ የሚታይ መሆኑ፤
- በኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ ሰኔ 30/2006 በውስጥ ኦዲተሮች በተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ብር 36,174.34 በጥሬ ገንዘብ እና በሰነድ የተገኘ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ደግሞ ብር 37,013.75 በመሆኑ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራው በብር 839.41 በማነስ የሚታይ መሆኑ፤
- በፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ መሰብሰቡ የተቋረጠ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ሂሳብ ብር 12,697.87 የሚገኝ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም ከላይ ለተመለከቱት ግኝቶች ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) የተሰብሳቢ ሂሳብ

በፋይናንስ አስተዳር ደንብ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መወራረዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ16 መ/ቤቶችና በ5 የገ/ን/ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 687,904,623.73 ከሶስት ወር እስከ 42 ዓመታት የቆዩ ሰነድ ሂሳብ የሚገኝበት ሳይወራረድ ተገኝቷል:: / ዝርዝሩ በአባሪ-9 ተመልክቷል/

በመሆኑም ውዝፍ ሰነዱን በወቅቱ አለማወራረድ ለመንግስት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት ፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል::

2.2 ውዝፍ /የዱቤሽያጭ የተሰብሳቢ ሂሳብ

- የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከ2002-2006 ዓ.ም በዱቤ ካስተላለፈው ማስታወቂያ መሰብሰብ የነበረበት ውዝፍ ሂሳብ ብር 42,522,317.52 እስከአሁን አለመሰብሰቡ፣
- የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ከ2000 ዓ.ም እስከ 2003 ዓ.ም ብር 9,492.66 ከደንበኞች ሊሰበስብ ይገባው የነበረውን ውዝፍ ሂሳብ አለመሰብሰቡ፣፡
- የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ 320 ለሚሆኑ ደንበኞች ከ1971-2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት በዱቤ የተሰጠ አገልግሎት ክፍያ ሳይሰበሰብ፣ ከ33 ዓመት በላይ የቆየ ብር 2,120,858.84፤በ2005 በጀት ዓመት በዱቤ ተሰጥቶ የነበረ እና ሳይሰበሰብ ለ 2 ዓመት የቆየ ብር 2,292,584.54 እንዲሁም በ2006 በጀት ዓመት ተሰጥቶ ሳይሰበሰብ የቆየ ብር 4,072,921.96 ሲሆን በጠቅላላው ብር 8,486,365.34 ያልተሰበሰ በሂሳብ መኖሩ፤

ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት የዱቤ ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.3 ማስረጃ ያልቀረበለት የተሰብሳቢ ሂሳብ

- በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተሰብሳቢ ሪፖርት ላይ ብር 597,124.07 ከማን እንደሚሰበሰብ መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ መኖሩ፣
- በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተሰብሳቢ ሪፖርት ላይ ብር 14,853.55 ማስረጃው ባለመቅረቡ ምክንያት የሂሳቡን ምንነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ፤ የተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ እና ይህን ሂሳብ በተመለከተ ባለፈው የኦዲት ሪፖርት ላይ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣

2.4 ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሣቦች

- በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን ዴቢት ሆኖ ሳለ በ7 የግዢ ሰራተኞች ላይ ብር 314,751.25 ክሬዲት ባላንስ ያልተለመደ ሚዛን (Abnormal balance) የሚታይ መሆኑ፣ እንዲሁም በ4 የግዢ ሠራተኞች ላይ ደግሞ ሂሳቡ ካለፉት አመታት ጀምሮ የመነሻ ሂሳባቸው በብር 1,110,062.67 ያልተለመደ ሚዛን /Abnormal balance/ እየታየ እያለ ሌላ ገንዘብ በመጨመር የነበረው ባላንስ እየተቀናነሰ የሄደበት ሁኔታ በመኖሩ በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ መታየት የነበረበትን ባላንስ በብር 1,110,062.67 ያዛባው መሆኑ፤ በእያንዳንዱ በኮንትራክተሮች ስም የተያዘ ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ በዩኒቨርሲቲው ለተሰጠ ብድር ተመላሽ የተቀነሰ ብር 200,000 ብድሩ ሲሰጥ የተመዘገበበት 4201 የሂሳብ መደብ ማስተካከያ ሳይሰራለትና የተቀነሰው ብድር በ4251 የሂሳብ መደብ የተወራረደ

መሆኑ እና ክፍያ ላይ የተቀነሰ ብር 400,000.00 ዩኒቨርሲቲው ከሰጠው ብድር ቀሪ የተመለሰ ሆኖ ሳለ ትምህርት ሚኒስቴር የሰጠው የሲሚንቶ ብድር ተብሎ የተያዘ መሆኑ፤

3. የገቢ ሂሳብ

የገቢ ሂሳብ በትክክል መሰብሰቡን እና መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

- በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ በሰኔ 30 በተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 1443 የተመለከተው የገቢ ሂሳብ ብር 8,155,452.40 ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ በ2006 በጀት ዓመት ከውስጥ ገቢ የሰበሰበውን ብር 28,178,903.75 ትክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ እና በ2006 በጀት ዓመት ከውስጥ ገቢ የሰበሰበውን ብር 28,178,903.75 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተላከው የሂሳብ ሪፖርት ላይ አለመካተቱ እና ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት ከ1999 ጀምሮ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣
- የቤተመንግስት አስተዳደር በየእለቱ ተሰብስቦ በመ/ቤቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ የሚደረገው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ከመመዝገቡ በፊት ባንክ ገቢ የተደረገው ሂሳብ በተሰበሰበበት ደረሰኝ ልክ ስለመሆኑ ተሰልቶ የደረሰኙ ቁጥር ከ እስከ በተገቢ ማስረጃዎች ላይ የማይወራረስ መሆኑ፣
- በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በሰኔ ወር የተሰበሰበው ገቢ ብር 10,454.92 ለሚመለከተው አካል ገቢ ፈሰስ አለመደረጉ፣
- በደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ በተቋሙ ለማታው የትምህርት ክፍል ለተለያዩ የትምህርት ዓይነት ለወሰነ ትምህረቱ /semester/ መመዝገባቸውንና አስቀድመው ክፍያ የፈጸሙ መሆኑን እንዲሁም የትምህርቱን ዓይነት ለመተዋቸው ተገቢ ማስረጃ /drop course slip/ ሳይቀርብ ብር 4,615.00 ያለ ማስረጃ ተመላሽ ተደርጎ መገኘቱ፣
- በብሔራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት በበጀት ዓመቱ ለተሰበሰበው ገቢ የገቢ ተመኑ በሚመለከተው የበላይ አካል ያልፀደቀ መሆኑ፤

ታውቋል።

ከላይ ለተመለከተው የገቢ ሂሳብ ድክመት መ/ቤቱ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1. የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

ግዥዎች በመንግስት የግዥ ደንብና መመሪያ መሰረት መፈፀማቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

- በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከአንድ አቅራቢ ለመስተንግዶ የብር 297,652.35 ግዥ መፈጸሙ እና በውስን ጨረታ የሠራተኞች የደንብ ልብስ በብር 117,000.43 መገዛቱ፣
- በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ለመስተንግዶ አገልግሎት ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ ሆቴል ግዥ በመፈጸሙ ብር 15,531.36 ሊከፈል ከሚገባው ገንዘብ በላይ መከፈሉ መታወቁ፣
- በቤተ መንግስት አስተዳደር የዋጋ ማቅረቢያ ሳይሰበሰብ በቁጥር 31 የተለያዩ የመስተንግዶ ግዥዎች በብር 1,119,791.35 የተፈጸሙ መሆኑ፣
- በመንግስት ፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ የግልጽ ጨረታ ማስታቂያ ሳይወጣ ለኤጀንሲዉ ለቢሮ አገልግሎት ኪራይ በተለያዩ 11 ክፍያዎች በድምሩ ብር 1,139,377.92 ክፍያ መፈጸሙ፣ለፖሊሲ ጥናትና ምርምር ከፍተኛ ኃላፊዎች ጽ/ቤት/ቢሮ ኪራይ ብር 3,693,006.96 ክፍያ መፈጸሙ፣ ለፖሊሲ ጥናትና ምርምር ከፍተኛ ኃላፊዎች ጽ/ቤት/ቢሮ መከፋፈያ (Partition) ብር 187,638.00 ክፍያ መፈጸሙ እና ለፖሊሲ ጥናትና ምርምር ከፍተኛ ኃላፊዎች ጽ/ቤት/ቢሮ ለፅዳት አገልግሎት በተለያዩ 5 ክፍያዎች በድምሩ ብር 121,807.35 ክፍያ መፈጸሙ፣
- በፌዴሬሽን ምክር ቤት በጨረታ ወይም በፕሮፎርማ ግዢ መከናወን ሲኖርበት ለመስተንግዶ ግዢ ብር 2,683,105.03
- በኢትጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን በግዥ መመሪያው ከተቀመጠው በላይ የብር 34,802.65 ቀጥታ ግዥ መፈጸሙ፣

- በሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የብር 23 874.19 ቀጥታ ግዥ መፈጸሙ፣

- በመድን ፈንድ ኤጀንሲ ብር 7,500.00 የሚያወጣ የወረቀት መጠረዣ /ትልቁ/ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴው ግዥውን ውድቅ ካደረገው በኋላ ከዚያው (የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውድቅ ካደረገው) ድርጅት ግዥው ተፈጽሞ መገኘቱ እና ብር 30,000.00 የሚያወጣ የማማከር ሥራ አገልግሎት ያለዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ ተፈፅሞ መገኘቱ፡

- በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብር 498,205.93 በቀጥታ ግዥ፣ እና ብር 201,695.00 የሚያወጣ የወለል ምንጣፍ ደግሞ በዋጋ ማወዳደሪያ የግዢ ዘዴ ብቻ ግዥው ተፈፅሞ መገኘቱ፤

- በድሬዋ ዩኒቨርስቲ በብር 72,275.00 የተባይ ማጥፊያ መድሀኒት የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ግዥ የተፈፀመ ቢሆንም ከ3ቱ ተወዳዳሪዎቹ ሁለቱ የግዢ መስፈርቱን ለሚሟላታቸው ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤

- በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የፕሮቶኮል እና የቋንቋ ስልጠና ግዥ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ሲያከናውን በርከት ያሉ ዩኒቨርስቲዎችን መጋበዝ ሲቻል 4 ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ የተጋበዙና ስለአመራረጡም ማብራሪያ ሳይሰጥበት አንድ/ ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ምላሽ በመስጠቱ ብቻ በቂ ውድድር ሳይደረግ ወይም ሌላ አማራጭ በመጠቀም ሌሎችን በድጋሚ ምርጫ እንዲወዳደሩ ባልተደረገበት የብር 121,000.00 ግዥ መፈጸሙ፣

- በፕሬዚዲንት ጽ/ቤት በተለያዩ 162 የወጪ ቫውቸሮች ብር 96,528.46 የቀጥታ ግዥ በመፈጸሙ በመመሪያው ከተቀመጠው በላይ የብር 66,528.46 (ብር 96,528.46-30,000.00) የቀጥታ ግዥዎች ተፈጽሞ መገኘቱ፣

- በኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ ብር 325,471.06 የሚያወጣ የቀለም ቶነር ግዢ ሲፈፀም ለማይታይም ጠቅላላ አስመጪ የተከፈለ ሲሆን የጨረታ ሰነዱ ያልቀረበ መሆኑ፤

በመሆኑም ከመመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቱን ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል ለወደፊቱ መመሪያው ተፈፃሚ መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.2. ***ያለ ሂሳብ መደባቸው የተመዘገቡ ወጭዎች***

ወጪዎች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት /chart of account/ መሰረት በትክክለኛው የሂሳብ መደባቸው መመዝገባቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ለለገሀር ፖሊስ ጣቢያ ድጋፍ የተለገሰው ብር 2,500.00 በሂሳብ መደብ 6419 መመዝገብና ሪፖርት መደረግ ሲገባው ሂሳቡ በሂሳብ መደብ 6254 (ኢንሹራንስ) ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጎ መገኘቱ፣
- በኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ለትራንስፖርት ወጭ ሆኖ የተከፈለው ብር 42,631.96 በሂሳብ መደብ 6232 መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 6417 ተመዝግቦ ሪፖርት መደረጉ እና ለመስተንግዶ ወጪ ሆኖ የተከፈለው ብር 114,000.00 በወጪ ሂሳብ መደብ 6233 በመስተንግዶ መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 6417 ተመዝግቦ ሪፖርት መደረጉ፣
- በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ለሁለት የተለያዩ የስልጠና ክፍያዎች ብር 368,188.38 የተከፈው የመስተንግዶ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 6271(በስልጠና ሂሳብ ርዕስ) መመዝገብ ሲገባው በትራንስፖርት ሂሳብ መደብ 6232 የተመዘገበ እና ለነዳጅ ግዥ ወጪ ሆኖ የተከፈለው ብር 1,630.38 በነዳጅ ሂሳብ መደብ 6217 መመዝገብ ሲገባው በትራንስፖርት ሂሳብ መደብ 6232 የተመዘገበ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማእከል የግዕዝ ጉባኤ ለማካሄድ የተደረገ የገንዘብ ድጋፍ ብር 200,000.00 በሂሳብ መደብ 6417 (ለግለሰቦችና ድርጅቶች ድጋፍ) መመዝገብ ሲገባው በውሎ አበል ሂሳብ መደብ 6231 ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጎ መገኘቱ፣
- በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ ለነዳጅ መግዣ ወጪ ሆኖ የተከፈለው ብር 14,452.75 በሂሳብ መደብ 6217 ተመዝግቦ ሪፖርት

መደረግ ሲገባው በውሎ አበል ሂሳብ መደብ 6231 ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጎ መገኘቱ፣

መመዝገቡ ታውቋል።

የሂሳብ መደብን ጠብቆ ያለመመዘገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅእኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም ከበጀት በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱንም ያዛባል። በመሆኑም የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ትክክለኛ የሂሣብ መደቡን ጠብቆ መመዝገብ ያለበት ሲሆን ሂሣቡም በትክክል ስለመመዝገቡ የሚረጋገጥበት ሥርዓትም መዘርጋት አለበት። ለወደፊቱም የታየው የምዝገባ ስህተት የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የተስተካከለ የሂሳብ ሪፖርት እንዲዘጋጅ ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አሳስበናል::

4.3 <u>ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች</u>

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የትርፍ ሰአት ክፍያ ሊከፈል ለሚገባው በተከታታይ ከሥራ ሰዓት ውጪ በምሽትና በእረፍት ቀናት ለሰሩ ያለአግባብ የውሎ አበል ክፍያ በሂሳብ መደብ (6231) ብር 6,632.00 መፈጸሙ እና በደብረ ዘይት ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ወጪያቸው (የምግብ እና የመኝታ) ለተሸፈነላው ሠራተኞች (ለሥራ ደረጃ ምዘና አጥኚዎቹ) የማበረታቻ አበል በቀን ብር 206. ሂሳብ በድምሩ ብር 63,654.00 ክፍያ ተፈጸሞ መገኘቱ፣

- በቤተመንግስት አስተዳደር ለቀንድ ከብት ግዥ ወደ ተለያየ ቦታዎች ለሄዱ ሠራተኞች ከውሎ አበል በተጨማሪ የመስተንግዶ ሂሳብ ብር 21,184.44 ተከፍሎ መገኘቱ፣

- በቅርስና ጥናት ጥበቃ ባለስልጣን የምግብና የመኝታ ወጪያቸው በደብረ ዘይት ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ለተሸፈነላቸው የሥራ ምዘና አጥኚዎች የማበረታቻ ክፍያዎች (በተለያዩ 4 ክፍያዎች) በድምሩ ብር 110,097.00 ክፍያ ተፈጸሞ መገኘቱ፣

- በኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን በውሎ አበል ታሪፍ መሰረት ሊከፈል ይገባው የነበረ (የህዳሴ ግድብ ጎብኚዎች ክፍያ) ለመስተንግዶ በጥሬ ገንንብ

ለመክፈል የሚያስችል መመሪያ ሳይኖር ብር 114,000.00 ለሠራተኞች መከፈሉ፣

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል በደብረ ዘይት ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ለሥራ ደረጃ ምዘና ጥናት ለቆዩ አጥኚዎች የምግብና የመኝታ ወጪያቸው ለተሸፈነላቸው የውሎ አበል የማበረታቻ ክፍያ ብር 49,440.00 ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- በመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የደመወዝ መጠናቸው ሳይገለጽ ለምሳ እና ለትራንስፖርት ብር 1,815,950.00 የተከፈለው ሂሳብ ለባለጥቅሞቹ ሊከፈላቸው በሚገባው ልክ ስለመከፈሉ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣ ጽ/ቤቱ ባዘጋጀው ውይይት ላይ ለተሳተፉ የመስተንግዶ አገልግሎት ተሰጥቶ ሳለ ያለአግባብ የምሳ አበል ብር 15,300.00 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ እና ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በምሽት፣ በእረፍት ቀናት፣ ቅዳሜና እሁድ እና ለህዳሴ ግድብ ጉብኝት መሳካት በትርፍ ሰዓታቸው ለሰሩ በሚል ከደንብና መመሪያ ውጭ ለጽ/ቤቱ ሠራተኞች ብር 356,723.05 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ በደብረ ዘይት ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት በሥራ ምዘና ጥናት ላይ ለተሳተፉ አጥኚዎች ወጪያቸው (የምግብና የመኝታ) በኢንስቲትዩቱ ተሸፍኖ ሳለ በተለያዩ 15 ክፍያዎች በድምሩ ብር 34,024.00 የማበረታቻ አበል ክፍያ መፈጸሙ፣ በምሽት፣ ቅዳሜ እና እሁድ ለሠሩ ሠራተኞች በተለያዩ 8 ክፍያዎች ብር 13,036.10 የውሎ አበል ክፍያ መፈጸሙ እና ለቤተመጻህፍት አምሺ ሠራተኞች በሂሳብ መደብ 6121 ብር 122,243.33 የትራንስፖርት አበል እንዲከፈል በሚመለከተው መ/ቤት ሳይፈቀድ ክፍያ መፈጸሙ፣
- በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለሂሳብ ክፍል ሰራተኞች ቅዳሜና እሁድ ለሰሩበት በሚል ብር 7,390.75 የምሳ አበል ያለአግባብ መከፈሉ፣፤
- በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ለጥበቃ ሠራተኞች የትርፍ ሰአት ክፍያ ሳይፈቀድ የትርፍ የሥራ ሰዓት ክፍያ ብር 33,256.80 ተከፍሎ መገኘቱ፣

- በብሔራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት ሁለት ሠራተኞች ለምርጫ በሄዱበት ወቅት በአዋጁ መሠረት ልዩ ፈቃድ ከደመወዛቸው ጋር ብቻ መስጠት ሲገባው ምርጫ ላይ በቆዩበት 28 ቀናት በድምሩ ብር 3,480.48 አላግባብ ክፍያ መፈፀሙ እና የኢንስቲትዩቱ አንድ ሠራተኛ ሥራ ላይ ለመሆናቸው በሠራተኞች የስራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ቅፅ ላይ በፈረሙበት የሥራ ቀኖች መስክ ሥራ ላይ እንደሆኑ ተደርጎ አላግባብ ብር 2,254.60 የውሎ አበል ተከፍሏቸው መገኘቱ፤

አሰራሩ ስራዎች በመደበኛ የስራ ሰዓት እንዳይሰሩ የሚገፋፋና ያልተፈቀዱ ክፍያዎችን በመፈፀም መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል በመመሪያው መሰረት መስራት ወይም የሚመለከተውን ክፍል ማስፈቀድ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.4 <u>መመሪያን ሳይከተል የተፈፀመ የክፍያ ሂሳብ</u>

ለባለመቶች (ለዕቃና ለአገልግሎት አቅራቢዎች) ወጪ እየተደረጉ የሚከፈሉ ክፍያዎች በደንብና በመመሪያ መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በወለጋ ዩኒቨርስቲ ወደ ባለመብቶች የባንክ ሂሳብ ቁጥር መተላለፍ የነበረበት ብር 903,898.20(በተለያዩ 5 ክፍያዎች) በቼክ መከፈላቸው፣
- በመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ በባንክ በኩል ለባለመብቶች መተላለፍ የነበረባቸው 15 ክፍያዎች ብር 6,509,280.52 በቼክ መከፈላቸውና እና በቼክ መከፈል የነበረባቸው 2 ክፍያዎች ብር 4,505.40 በጥሬ ገንዘብ መከፈላቸው፣
- በፌዴሬሽን ምክር ቤት በቼክ ሊፈጸም ይገባው የነበረ ክፍያ ብር 110,674.78 ከካዝና ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ፡፡
- በሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 451,559.55 በቼክ ሊፈጸሙ ይገባቸው የነበሩ ክፍያዎች ከካዝና መከፈላቸው፣
- በደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ ብር 82,999.99 በባንክ በኩል ለባለመብቶች መተላለፍ የነበረባቸው 2 ክፍያዎች በቼክ መከፈላቸው እና በቼል ሊከፈሉ የሚገባቸው ብር 6,699,854.04 ክፍያዎች ደግሞ በጥሬ ገንዘብ መከፈላቸው፣

- በፕሬዚደንት ጽ/ቤት በተለያዩ 33 የክፍያ ቫውቸሮች በቼክ ሊከፈሉ ይገባቸው የነበሩ የዕቃዎችና የአገልግሎት ክፍያዎች ብር 108,519.23 በጥሬ ገንዘብ ክፍያው መፈጸሙ፣

ታውቋል።

ከላይ ለተመለከቱት ሁኔታዎች ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

4.5 <u>የደመወዝ ሂሳብ</u>

የደመወዝ ሂሳብ ሠራተኞች ለሰጡት አገልግሎት ብቻ የተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ ዩኒቨርሲቲውን ለለቀቁ 7 መምህራኖች ብር 85,672.17 ከ1ወር እስከ 6 ወር እንዲሁም ለአንድ የወጪ አገር ዜጋ የአንድ ወር ከ 8 ቀን 1900 USD ወይም ብር 28,891.64 በጠቅላላው ብር 114,563.81 ዩኒቨርሲቲውን ለለቀቁ መምህራኖች አላግባብ ተከፍሎ መገኘቱ፤
- በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ 8 ሰራተኞች ከስራ ሲሰናበቱ የዓመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሲሰጣቸው ብር 7,351.94 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፣ ለ20 የመ/ቤቱ ቋሚ ሠራተኞች የዓመት ፈቃዳቸው በገንዘብ ተለውጦ ሲሰጣቸው ብር 8,487.09 በብልጫ የተከፈለ በመሆኑ እና ለቦርዱ የጥበቃ ሠራተኞች የትርፍ ስዓት ለሰሩበት ለተከፈለው ክፍያ ብር 55,916.24 ትርፍ ስዓት የሰሩበት ማስረጃ ተሟልቶ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያለመቻሉ፤

መከፈሉ ታውቋል።

ለየመ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

4.6 የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ቅድመ ታክስ ያልተቀነሰለት ወጪ

የተጨማሪ እሴት ታክስ በመመሪው መሰረት መቀነስ ካለባቸው ክፍያዎች ላይ መቀነሱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በመድን ፈንድ ኤጀንሲ ለመስተንግዶ ከተከፈለው ብር 14,716.24 ክፍያ ላይ ብር 2,206.99 የተጨማሪ እሴት ታክስ ቆርጦ ማስቀረት ሲገባው ሳይቆረጥ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- በፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ከቤት ኪራይ ክፍያ ላይ ተቀንሶ መቅረት የነበረበት ቅድመ ታክስ (Withholding tax) ብር 72,000.00 (3,600,000* 2%) ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸሙ፣

4.7 የሂሳብ ማስተካከያን በተመለከተ

የሂሳብ ማስተካከያ ሲሰራ የምዝገባ ሰነድ ቁጥር የሚጠቃቀስ መሆኑን (መጀመሪያ የተሳሳተውን ምዝገባ የሚያሳይና በትክክል ሊስተካከል እንደሚገባው ገላጭ መሆኑን) ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ በተለያዩ የሂሳብ አርዕስቶች ላይ ብር 633,458.92 የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ(መሂ9) ላይ የሂሳብ ማስተካከያ በሚል የተያዘ ቢሆንም የትኛውን የወጪ ሰነድ ለማስተካከል እንደተመዘገበ እና የስህተቱ ምክንያት ያልተገለፀ ከመሆኑም በላይ ያዘጋጀው እና ያረጋገጠው ሰራተኛ ስምና ፊርማ የሌለ መሆኑ፤

4.8 በብልጫና በማነስ የተመዘገበ

በተመዘገቡ ሂሳቦች ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን ለምዝገባ መነሻ ከሆኑት ሰነዶች ጋር እኩል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ያልተጠናቀቁ ህንፃዎችን የማጠናቀቂያ ክፍያ ለህንፃ ስራ ተቋራጮች የተከፈለው ክፍያ ላይ ብር 471,105.62 በማስበለጥ እና ብር 1,936,945.08 በማሳነስ የተመዘገበ መሆኑ፤

4.9 አላግባብ የተከፈለ በግንባታ ስራ ቦታ ላይ ስለሚገኝ የግንባታ ግብዓት ክፍያ

- በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ብር 591,163.89 በግንባታ ስራው ቦታ ላይ የሚገኙ የግንባታ ግብዓቶች (material on site) ክፍያ መፈፀሙና ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፤

4.10 ሪፖርት ያልተደረገ የወጪ ሂሳብ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ከውስጥ ገቢው ወጪ ያደረገውን ብር 17,455,616.94 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖረት ያላደረገ መሆኑ፣

4.11 ከተቋራጮች ያልተሰበሰበ የመቀጫ ሂሳብ

ተቋራጮች በገቡት ውል መሰረት የግንባታ አገልግሎታቸውን በገቡት የውል ጊዜ መሰረት የግንባታውን አገልግሎት ጨርሰው ማስረከባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ የግንባታ አገልግሎታቸውን በገቡት የውል ጊዜ መሰረት ካልፈጸሙ ሁለት ተቋራጮች መሰብሰብ የነበረበት ቅጣት ብር 272,501.04 አለመሰብሰቡ መታወቁ፣

4.12 አላግባብ በመንግስት የተሸፈነ የተሽከርካሪ ግጭት ጥገና

በብሔራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት የመ/ቤቱ ንብረት የሆነው ኮድ 4-00845 መኪና ከሠሌዳ ቁጥር 2-A88317 ቶዮታ ኮሮላ መኪና ጋር ተጋጭቶ የተጎዳውን የመ/ቤቱን ተሽከርካሪ ክፍል ለማስጠገን ወጪ የተደረገው ብር 88,724.76 የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በደብዳቤ ቁጥር ምአዲ/ኮር/06080/05 ግጭቱ የተከሰተው መኪናውን ለማሽከርከር ከሚጠይቀው ደረጃ በታች በሆነ የመንጃ ፈቃድ በያዙ የመ/ቤቱ ሹፌር ምክንያት የተከሰተ አደጋ መሆኑን በመግለፅ የካሳ ጥያቄውን እንደማያስተናግድ ገልፆ ሳለ በጥንቃቄ ጉድለት ለደረሰው አደጋ ወጪው በመ/ቤቱ (በመንግስት) እንዲሸፈን መደረጉ፤

5. ተከፋይ ሂሳብ

5.1 በወቅቱ ያልተከፈሉ ተከፋዮች

በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ የመ/ቤቱ ትክክለኛ እዳ መሆኑንና ሂሳቡም ትክክለኛ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ;

- በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሳብ መግለጫ ላይ በሂሳብ መደብ 5005 (የደመወዝ ተቀናናሾች) ብር 64,935.81፣ በሂሳብ መደብ 5006 ቅድመ ታክስ(የዊዝሆልድ ታክስ) ብር 10,333.47.14 እና በሂሳብ መደብ 5059 ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,722.87 በድምሩ ብር 76,992.15 ሁለት ዓመት ከ 3 ወር የቆየ እና ሂሳቡ መነሻ ሰነድ(ለማን፣ ለምን እና መቼ እንደሚከፈል) የሌለው መሆኑ፣

- በኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሳብ መግለጫ ላይ በተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ መደቦች ብር 211,247.47 ሳይከፈል የቆየ ተከፋይ ሂሳብ መገኘቱ፣

- የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሳብ መግለጫ ላይ ብር 2,120,880.67 በወቅቱ ያልተወራረደ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፣

- በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሳብ መግለጫ ላይ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች የሚከፍል የተከፋይ ሂሳብ ብር 47,58.48 መኖሩ፤

- በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5054 ብር 460,160,937.67 ከግንቦት 2004-እስከ መስከረም 21/2007 ድረስ የቆየና ለሚመለከተው አካል ያልተከፈለ መሆኑ፡

- በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5002 ብር 11,748.25 የሂሳቡ ሁኔታ ያልታወቀ እና ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ማስተካከያ ሳይደረግ የቆየ ሂሳብ መኖሩ፣

- በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 6,936,916.26 ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ የተከፋይ ሂሳብ መገኘቱ፣

- በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 111,163.36 በተከፋይነት የሚገኝ እና ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተወራረደ መሆኑ፤
- በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 2,117,025.23 ከአንድ ዓመት በላይ ሳይከፈል የሚገኝ መሆኑ፣
- በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ከተመለከተው ሂሳብ ውስጥ ብር 1,060.86 ለሚመለከተው ክፍል ሳይከፈል እስከ 6 ወር የቆየ የተከፋይ ሂሳብ መኖሩ እና ብር 535.53 የተከፋይ ሂሳብ ሳይሆን በተከፋይ ተይዞ መገኘቱ፣
- በኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ በሂሳብ መደብ 5005 የተያዘ ለቁጠባ ከሠራተኞች የተቀነሰ እና ለ3 ወር ያህል ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል የቆየ ብር 953.95 የተከፋይነት ሂሳብ መኖሩ፤

ለየመ/ቤቶቹ በተከፋይ ሂሳብ ላይ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግና በመክፈያ ጊዜያቸው ክፍያ በመፈፀም ተገቢው ምዝገባ እና ማስተካከያ ሊሠራ እንደሚገባ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ ያልተመዘገበ የተከፋይ ሂሳብ</u>

- የደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ በግቢው ውስጥ ላስገነባው የኮብል ስቶን ንጣፍ መንገድ ከፍቅርና ሠላም የኮብል ስቶን አንጣፊዎች ማህበር የቀነሰውን ብር 223,914.76 እንዲሁም በግቢው ውስጥ ለተገነባው አጥርና የዘበኛ ቤት ከአበበ መብርሃቱ ህንጻ ስራ ተቋራጭ የቀነሰውን ብር 168,641.48 የመያዣ ሂሳብ በተከፋይ ሂሳብ (5061) መያዝ ሲገባው በተከፋይነት ያልተመዘገበ መሆኑ እና ከከሰተ ብርሃን ህንፃ ስራ ተቋራጭ (LOT 4B/BB) ከ6ኛ ክፍያላይ የተቀነሰው የሲሚንቶ ዕዳ ብር 462,794.83 በባለበጀት መ/ቤቶች መካከል ያሉ ተከፋይ ሂሳቦች (5028) የሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው በ4251 (ለተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ) የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ እና የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከሚገነቡ ግንባታዎች ክፍያ ላይ ከተለያዩ

ኮንትራክተሮች የተቀነሰው የመያዣ ሂሳብ ብር 477,272.54 በሂሳብ መደብ 5061 በተከፋይ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ መሆኑ፤

ዩኒቨርስቲው ሂሳቡን በትክክል ሊመዘግብና ሪፖርት ሊያደርግ እንደሚገባው በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. የገቢ እቅድና ክንውን በተመለከተ

- የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ ገቢ ማስገኛ የስራ ዘርፎች ለመሰብሰብ ካቀደው ብር 348,000,000.00 ውስጥ መሰብሰብ የቻለው 216,628,656.50 (62%) ብቻ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ በበጀት ዓመቱ ይሰበሰባል ተብሎ የታቀደው ብር 95,999,000 ሲሆን የተሰበሰበው ግን ብር 78,343,941.33 በመሆኑ የብር 17,655,058.70 (18.39%) ልዩነት ያለው መሆኑ፤

በመታወቁ ለየመ/ቤቶቹ የገቢ ሂሳብ በጀታቸው በጥናት ላይ የተመሰረተ ሊሆን እንደሚገባና እቅዳቸውን ለማሳካት ለወደፊቱ ጥረት ሊያደርጉ እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7 የበጀት ሂሳብ

7.1 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ

- መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለመረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ5 መ/ቤቶች ብር 28,749,427.27ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ዩኒቨርሲቲው እንዲጠቀም የተፈቀደለት ብር 3,667,500.00 ሆኖ ሳለ ብር 15,865,584.66 በመጠቀሙ ብር 12,198,084.66 (332%) በብልጫ የተጠቀመ መሆኑና ከውስጥ ገቢ ባልተፈቀዱ የሂሳብ አርእስቶች ብር 6,342,700.37 አድርጓል፡፡ /ዝረዝራቸው አባሪ-33 ተመልክቷል/

ለየመ/ቤቶቹ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የበጀት አጠቃቀም ግድፈት እንዳይደርስ ጥንቃቄ እንዲያድርጉ አሳስበናል፡፡

7.2 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤በ14 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 296,101,638.17 እና በ4 መ/ቤቶች ከካፒታል በጀት ብር 157,718,677.80 በስራ ላይ ልዋለ መሆኑ ተረጋግጧል።/ዝረዝራቸው አባሪ-33 ተመልክቷል/

በመሆኑም መንግስት ለሌሎች መሠረታዊ ለሆኑ ሥራዎች ሊያውል የሚችለውን ገንዘብ በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ እንዳይውል ሊያደርግ ስለሚችል የበጀት ዝግጅት ጥያቄ መ/ቤቶች ሲያቀርቡ በተጨባጭ ሊሰራ ከታቀደው ተግባር ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ያለፉትን ዓመታት የዕቅድ አፈፃፀም በመገምገም ሊከናወን የሚገባ ሲሆን ለወደፊቱም የበጀት ጥያቄ ሲቀርብ ከእቅድ ጋር እየተገናዘበ የሚቀርብበት ሁኔታ እንዲመቻች ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አሳስበናል።

8. ንብረት

8.1 የዕቃና ንብረት አስተዳደርና አጠባበቅ ሁኔታ

- በወለጋ ዩኒቨርስቲ የ2006 በጀት ዓመት የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ያልተጠናቀቀ መሆኑና የአላቂ ንብረት ቆጠራ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ መሆኑ፣
- በቤተ መንግስት አስተዳር ውስጥ ለሚገኙት ውድ ለሆኑ ጌጣጌጦችእና ቅርሳቅርሶች ምዝገባ የተደረገ ለመሆኑ እና በየዓመቱ ቆጠራ እየተደረገ በሚገኘው ውጤት መሰረት እርምጃ የሚወሰድ ለመሆኑ ማስረጃ ባለመቅረቡ ውድ ለሆኑት ጌጣጌጦች እና ቅርሳቅርሶች ምዝገባ ያላቸው ስለመሆኑም ሆነ በአካል ስለመኖራቸውም ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በቅስና ጥናት ጥበቃ ባለስልጣን በ2006 በጀት ዓመት የቋሚ ንብረትና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተመዛዘነ መሆኑ፣
- በመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ የቋሚና አላቂ ንብረቶች የሚመዘግብበት መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፣

- በመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት በ2006 በጀት ዓመት የቋሚ ንብረትና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ እና ለአንዳንድ ቋሚ ዕቃዎች (ንብረቶች) የመለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ ፣

- በፌዴሬሽን ምክር የ2006 በጀት ዓመት የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ፣

- በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የ2006 በጀት ዓመት የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር ያልተሳከረ መሆኑ፡ የንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ እና የሚሰጡ ንብረቶች በአንድ ላይ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ላይ የዕቃው መለያ ቁጥር፤ ሴርያል ቁጥር እና ሞዴል ቁጥር ሙሉ ለሙሉ ያልተሞላ መሆኑና፤ እንዲሁም የእቃዎቹ ዋጋ ያልተመዘገ መሆኑ እና በሰነድ ርክክብ ሳይፈጸም በሌሎች ተገልጋዮች ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ፤አንዳንድ በግለሰቦች እጅ ያሉ ነገር ግን በተጠቃሚው ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ እቃዎች የሚገኙ መሆኑ፣) ለምሳሌ ያህል 4 የፋይል ካቢኔት በመዝገብ ቤት ሃላፊ ስር ፤ ዴል ኮምፒውተር በህጻናት መዝገብ ቤት ፤ ተገጣሚ የብረት ደረጃ በካርድና ማህደር አከናዋኝ ስር ሚገኙ መሆኑ፣

- በድሬደዋ ዩኒቨርስቲ በ2006 በጀት ዓመት የዩኒቨርሲቲው ንብረት በንብረት ቆጣሪ ኮሚቴ ያልተቆጠረ መሆኑ፡ ለአንዳንድ ቋሚ ንብረቶች ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤ የቋሚም ሆነ የአላቂ እቃ ቢን ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም ምዝገባው የቆመ መሆኑ፤

- በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከመዝገብ ጋር ያልተመዛዘነ መሆኑ፤ በተለያየ ወቅት ከአማራ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት የገዛቸው (176 ቤቶችና 29 ሱቆች) ያሉት 11 የመኖሪያ ህንፃዎች ኮንደምኒየም ቤቶች በንብረት ክፍል በኩል የገቢ ሰነድ የሌላቸውና እና በማን ስም ወጪ እንደተደረጉ እንዲሁም ያሉበትን ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ የሌለ

መሆኑ፤ ህንፃዎችና ግንባታዎች በንብረት ቆጠራው ውስጥ ያልተካተቱ መሆኑ፤ ከአማራ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት የተገዙት የመኖሪያ ቤቶችና ግንባታቸው ተጠናቅቆ ርክክብ የተፈፀመባቸው ህንፃዎች በንብረት መዝገብ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፤ሰባት(7) መምህራን የተለያዩ የቢሮ እቃዎችን ሳያስረክቡ የለቀቁ መሆኑ፤ አንድ የሜካኒካል ኢነጂነሪንግ መምህር አንድ Toshiba laptop serial no 580474350 ሳያስረክብ የለቀቀ መሆኑ እና ባለፈው የኦዲት ሪፖርት ላይ አስተያየት ተሰጥቶባቸው ያሉ ግኝቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች መኖራቸው፤

- በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የመለዋወጫ እቃዎች ቢን ካርድ የሌላቸው እና ስቶክ ካርድ ላይ ያሉት የመለዋወጫ እቃዎች የንብረት ቆጠራ ሪፖርት ላይ ያልተካተቱ መሆኑ፣ ቶፕላሬ ብረቶች እና ቁጥራቸው በዛ ያሉ ቆርቆሮዎች በሞዴል ገቢ ያልሆኑ እና አመታዊ ቆጠራ ላይም ያልተጠቃለሉ ከመሆኑ በተጨማሪ ለብልሽት ሊጋለጡ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፤
- በፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የ2006 በጀት ዓመት የአላቂና የቋሚ ዕቃ (ንብረት) ቆጠራ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ መሆኑ እና ለአንዳንድ ቋሚ ዕቃዎች (ንብረቶች) የመለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

ከላይ ለተመለከቱት የንብረት ሂሳብ አስተዳደር ድክመቶች ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8.2 <u>የንብረት አወጋገድን በተመለከተ</u>

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል በብልሽት ምክንት ያለ አገልግሎት የተቀመጡ የተለያዩ ወንበርሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ፕሪንተሮች፣ ዩፒኤስ እና ከመሰብሰብያ አዳራሽ የተነሳ አሮጌ የወለል ምንጣፍ የሚገኙ መሆኑ፣
- በቅርስና ጥናት ጥበቃ ባለስልጣን የተለያዩ ካሜራዎች፣ ላፕቶፖች፣ ፕሪንተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን እና ኮምፒዩተሮች በመጋዘን ዉስጥ ተከማችተው መገኘታቸው መታወቁ፣
- በኢትዮጵ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በጎጃ ዴራ ሬዲዮ ግቢ ውስጥ 1 ጄኔሬተር ከ2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት መቆሙ፣ 4 ትራንስሚተሮች፣ 4

የትራንስሚተሮች ራክ፣ 6 ትራንስፎርመሮች፣ 1 ዊንች፣ 6 የናፍታ በርሜሎች፣ የውሃ ፓምፕ ሞተር፣ በጌጃ ጃዊ ሬዲዮ ግቢ ውስጥ ኮንክስትየ አጭር ሞገድ ማሰራጫ ለ3 ዓመት ያህል በብልሽት ምክንያት መቀመጡ፣ 5 የትራንስሚተር ፋይናል ቲዩቦች፣ በርካታ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ኬብሎችና ካቦዎች በመጠለያ የተቀመጡ፣ በርካታ አገልግሎት የማይሰጡ ኬብሎች፣ ካቦዎች፣ ቁርጥ ራጭ ብረታ ብረቶች፣ መወጣጫ መሰላሎችና1 ሚክሰር (የሲሚንቶ ማቡክያ) እና በፋሪ ማሰራጫ ጣቢያ 1ዲሀይድሬተር፣ ሪሞት ኮንተሮል ፣ ትራንስሚተር ፣በርካታ UPS ባትሪዎች እና 1 ጄኔሬተር በሽራ ተሸፍኖ ውጪ የሚገኙ መሆኑ፣

- በፌዴሬሽን ምክር ቤት አገልግሎት የማይሰጡ ብዛት ያላቸው 160 የተለያዩ ጎማዎች፤ 22 ኮምፒውተሮች እና ብዘት ያላቸው ተያያዥ የኤሌትሮኒክስ ዕቃዎች እንዲሁም ብዛት ያላቸው ልዩ ልዩ ዕቃዎች መገኘታቸው፣
- በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ኤል-ሲዲ ፕሮጀክተር እና ወረቀት መጠረዣ በቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ ላይ ተመዝግበው በአካል ግን በሴቶች ወጣቶች ማስፋፋት ተሳትፎ ክፍል ያልተገኙ መሆኑ፣
- በድሬደዋ ዩኒቨርስቲ ፕላስቲክ በርሚሎች፡ ቁጥራቸው ከ600 በላይ የሚሆን የካፍቴሪያ ሳህኖች፡ የዳቦ ማስቀመጫዎች፡ ትላልቅ ጎላዎች(ብረት ድስት)፡ ማንቆርቆሪያዎች፡ ጠረጴዛ፡ የውሃ ቱቦ ቆርቆሮዎች እና የመሳሰሉትን ከቢሮ ውጪ ሜዳ ላይ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤ ከተገዛ ጀምሮ (ከ1 ዓመት በላይ) አገልግሎት የማይሰጥ ጄኔሬተር መኖሩና የመመረቂያ ጋዋኖች አግባብ ባለው ቦታ አለመቀመጣቸው፣
- በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወገዱ ንብረቶች አቀማመጥ አስተማማኝ ባለመሆኑ በቀላሉ ለብክነት እና ለጉዳት ሊዳረጉ እንደሚችሉ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት መቻሉ፣
- በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ አገልግሎት የማይሰጡ በቁጥር 26 የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪዎች በድርጅቱ ማዕከላዊ ገራዥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

- በኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ ንብረት ክፍል አገልግሎት የማይሰጡ ፎቶ ኮፒ ማሽን፤ ኮምፒውተር ስታንድ፤ ቴለቭዥን፤ ኮሚፒውተር ከነተንዳኙ፤ የፊልም ማድረቂያ፤ ፕሪንተር፤ካዝና፤ የኬሚካል ማስቀመጫ ታንከር፤ ፊልም ማጥቆሪያ እና ሌሎችም ብዛት ያላቸው እቃዎች አገልግሎት የማይሰጡ እቃዎች ለረጅም አመታት ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

በመታወቁ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት ንበረቶች ተጠግነው ለአገልግሎት እንዲበቁ ሊጠገኑ በማይችሉት ላይ ደግሞ ተገቢው የማሶገድ ሂደት እንዲፈጸም በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

8.3 የተሽከርካሪዎች ሁኔታ

8.3.1 ያለአገልግሎት የቆሙ ተሽከርካሪዎች

- በቤተመንግስት አስተዳደር በተለያዩ ምክንያቶች ለብዙ አመታት አገልግሎት ሳይሰጡ ቆመው የሚገኙ 96 የተለያዩ ተሽከርካሪ መኪናዎች መኖራቸው፣
- በፌዴሬሽን ምክር ቤት 4 ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣
- በፕሬዚዲንት ጽ/ቤት 1 ፔጆ 4-00045 ለ3 ዓመት እና ሚስትቡሽ 4-00135 ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የቆሙ መሆኑ መታወቁ፣

በመታወቁ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት ተሽከርካሪዎች ተጠግነው ለአገልግሎት እንዲበቁ ሊጠገኑ በማይችሉት ላይ ደግሞ ተገቢው የማስወገድ ሂደት እንዲፈጸም በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

8.3.2 የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ/ በተመለከተ

- በወለጋ ዩኒቨርስቲ አምስት ተሽከራካሪዎች (ታርጋ ቁጥር 4-18507 እና 4-18489 ቶዮታ ሎንግ ቤዝ፣ ታርጋ ቁጥር 4-18513 እና 4-18514 ማዝዳ እና ታርጋ ቁጥር 4-18490 ቶዮታ ሚኒባስ) መኪኖች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ፣

- በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኮድ 4-01664 ቶዮታ ላንድ ክሩዘር ተሽከርካሪ መኪና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌለው መሆኑ፣
- በቤተመንግስት አስተዳደር 121 የተለያዩ ተሽከርካሪ መኪናዎች የበለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ
- በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል በብልሽት የቆመ ተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌለው መሆኑ፣

ከላይ በተመለከቱት ተሽከርካሪዎች ላይ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

9. <u>ልዩ ልዩ</u>

9.1 በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራቦርድ የተሸጡ የመንግስት ድርጅቶች የተጠቃለለ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ የማይዘጋጅ በመሆኑ የድርጅቶችን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ በመሆኑ መ/ቤቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በባለፉት በጀት ዓመታት በተከታታይ ኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በ2006 በጀት ዓመትም እርምጃ ያልተወሰደ በመሆኑ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በተደጋጋሚ የሚነሱትን የሰው ሃይልና ሌሎች ችግሮች ለሚመለከተው አካል በመጠየቅና በማስፈቀድ ሥራው በማከናወን ዓመታዊ ሪፖርት ሊያዘጋጅ እንደሚገባ በላክነው የኦዲት ሪፖርት በድጋሚ አሳስበላል፡፡

9.2 በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ስር በተለያዩ መጋዘኖች ከ18 ድርጅቶች ከተወረሱ ንብረቶች ውስጥ በናሙና ከታዩት መጋዘኖች ውስጥ 617 ዓይነት እቃዎች የሚገኙ መሆኑና በአብዛኛው ጣቃዎች፤ የተሰፉ ቱታዎች፤ ጥቅል ክሮች ፤ ሹራቦች፤ ጥቅል እና ብትን ጥጦች፤ የተለያየ ስፔር ፓርቶች እንዲሁም በጣም የተከማቹ ኬሚካሎች፤ መስሪያ ማሽኖች እና የመሳሰሉት የሚገኙ እና ሳይሸጡ ወይም ሳይወገዱ ለብዙ ዓመታት የቆዩ በመሆናቸው ጨርቆቹ በአይጥ ከመበላታቸው በተጨማሪ ኬሚካሎች በጸሀይ ደርቀው እና ተበላሽተው የሚገኙ መሆኑ፤ በሰነድ አስተዳደር

እና ሰራተኛ ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ከሚፈርሱ ድርጅቶች የተረከባቸው የሰራተኞችን የግል ማህደሮች፤ የሂሳብ ሰነዶች፤ የመዝገብ ቤት ፋይሎች፤ ደንቦች እና መመሪያዎች፤ ማንዋሎች እና የመሳሰሉት በ6 መጋዘኖች በመረከብ ለይቶ በመያዝ እና በማደራጀት ለተገልጋዮች ግልጋሎት እየሰጠ የሚገኝ ቢሆንም በኦዲት በታዩት 4 መጋዘኖች በተለይም በስላሴ መጋዘን የሚገኙት ሰነዶች መደርደሪያ ቢኖርም በቂ ባለመሆኑ እና ፋይሎች በመበታተናቸው በጎርፍ ሳቢያ፤እንዲሁም በንጽህና ጉድለት ምክንያት ተመልካች በማጣታቸው ብዙዎችም መደርደሪያቸው ተዛሞ ሊወድቅ በመድረሱ ከጥቅም ውጭ እየሆኑ መሆኑ እና በሌሎችም መጋዘኖች ተመሳሳይ ችግር ያላቸው ከመሆኑም በላይ በመጋዘን እጦት በየጆንያ ውስጥ ታስረው የሚገኙ በመሆኑ ለችግሮቹ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>አቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት</u>
<u>የ2006/2007 ኦዲት ዕቅድ የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት</u>

I. <u>ዕቅድና ክንውን፣</u>

በዳይሬክቶሬቱ የታቀዱ 34 መ/ቤቶች ኦዲት በሙሉ የተከናወነ ሲሆን በኦዲቱ የተሸፈነ መደበኛ በጀት ብር 6,476,704,141.36 እና ካፒታል በጀት ብር 11,420,126,174.00 በድምሩ ብር 17,817,157,421.90 ነው::

<u>**የተሰጠው የኦዲት አስተያየት፣**</u>

በኦዲቱ በተሰጠው አስተያየት ሲተነተን ነቀፌታ የሌለበት (Clean Opinion 4 መ/ቤቶች፣ ከጥቂት ስህተቶች በስተቀር አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት(Except for opinion) 13 መ/ቤቶች፣ የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ(Adverse opinion) 9 መ/ቤቶች እና አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው (Disclaimer opinion) 8 መ/ቤቶች ናቸው:: /ዝርዝራቸው ከአባሪ- 2 እስከ 5 ተመልክቷል/

II. <u>ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣</u>

1. <u>የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ፣</u>

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣</u>

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣-

• መቱ ዩኒቨርስቲ	20,988.65
• ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ	3,538.06
• የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ከጤና ሳይንስ ኮሌጁ	24,821.50
• ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	29,893.34
ድምር	**79,241.55**

በጉድለት የሚታይ መሆኑ ተረጋግጧል::

1.2 <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፣</u>

- ወሎ ዩኒቨርስቲ፣ ብር 327,433.34 በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 41,790.70 በአዳማ ዩኒቨርሲቲ፡- ብር 31,381.78 በበጀት ዓመቱ

መጨረሻ በገንዘብ ያዦች እጅ የተገኘው የጥሬ ገንዘብ ና በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገው ሲነጻጸር በገንዘብ ያዦች እጅ የተገኘው የጥሬ ገንዘብና ሰነድ በማነስ የሚያሳይ መሆኑ፤

- ወሎ ዩኒቨርስቲ፤ በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ 4101-0003 ተቀጽላ ሌጀር ብር 300,886.74 ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ወይም ክሬዲት የሚታይ መሆኑ፤
- ወሎ ዩኒቨርስቲ፣ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፤ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ፣ በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲ የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ መግለጫ የማይዘጋጅ መሆኑ፤

2. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

2.1 <u>ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ፣</u>

ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ የሚወራረድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ24 መ/ቤቶች ብር 866,529,560.55 ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰበብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል። /ዝረዝሩ በአባሪ-9 ተመልክቷል/

ከዚህ ከተገለጸው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ፣

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 51,148,784.84 የተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ ከ4 ዓመት በላይ የቆየ ፣ ወላይታ ዩኒቨርስቲ ብር 4,203,867.18፣ ሰመራ ዩኒቨርስቲ በሂሳብ ኮድ 4273 ብር 3,141,616.56፤ በሂሳብ ኮድ 4251 ብር 5,105,796.77፤ ለተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ በወቅቱ ያልተወራረደ መሆኑ፣ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ ብር 1,683,317.28 በቤቶች ልማት በኩል የተሰጠ የግንባታ ቅድሚያ ክፍያ ከሁለት ተቋራጮች የሚፈለግና ያልተሰበሰበ መሆኑ፣የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ብር 72,905,956.91 የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 89,214,013.76 ለGIZ-IS International Service ጂ.አይ.ዜድ.-አይ.ኤስ ለተባለ ድርጅት ቀደም ብሎ የተሰጠውን ቅድሚያ ሂሳብ የተሟላ ማስረጃ የሌለው በመሆኑ ምክንያት ያልተወራረደ መሆኑ፣
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 4,179,855.38 አለአግባብ ከመደበኛ በጀት ለውስጥ ገቢ የተላለፈ እና በወቅቱ ያልተወራረደ፣ ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ ብር 1,789,736.30 ጉዳዩ በፍ/ቤት የተያዘ መሆኑ፣ የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር

14,917,826.02 በመንግስት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የጋምቤላ ግብርና ኮሌጅ ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ እና ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች፣ የሚዛን-ቴፒ ብር 97,256.26 በአጠቃላይ በሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች ተይዘው በወቅቱ ሳይወራረድ መገኘቱ፣

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 4,093,918.20፣ ወላይታ ዩኒቨርስቲ ብር 405,078.90 ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ ብር 11,778,500.89 የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር 14,838,505.22 የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 7,928,812.47 ሰመራ ዩኒቨርስቲ፡ ብር 1,015,865.75 የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 371,066.67 ለተለያዩ ዕቃ አቅራቢዎች በቅድሚያ ክፍያ ተፈጽሞ በወቅቱ ዕቃዎች ገቢ ባለመደረጋቸው ሳይወራረድ መገኘቱ፣የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 4,914,384.73 የግዥ ቅድሚያ ክፍያ የተሰጣቸው ሠራተኞች ዝርዝር የማይታወቅና ሂሳቡም በወቅቱ ሳይወራረድ መገኘቱ፣
- ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ ብር 3,533,252.73 ለተለያዩ ክፍያዎች ቅድሚያ የተከፈለው ከ6 ወራት እስከ ሦስት ዓመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፣
- የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 764,054.37 በተለያዩ ሠራተኞች እጅ የሚገኝ እየተንከባለለ የመጣ ሂሳብ ሳይወራረድ መገኘቱ፣
- የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር 3,843,178.82 ለጥቃቅን ወጪዎች በብድር ተሰጥቶ ሳይወራረድ መገኘቱ፣

<u>የትምህርት ሚኒስቴር</u>

- በሂሳብ መደብ 5217109/4210/ ብር 262,572,434.86 ከ1996 ጀምሮ ለተለያዩ ዩኒቨርስቲ ተከፍሎ ያልተወራራደ፤
- በሂሳብ መደብ 5217301 /4201/ ቅድሚያ ክፍያ ብር 3,283,747.11 ፣ በሂሳብ መደብ 5217302 /4202/ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 2,051,111.31 እና በሂሳብ መደብ 4274 (ልዩ ልዩ) ብር 37,883,977.02 በድምሩ ብር 43,218,835.44 ከ1996 ዓ/ም ጀምሮ ያልተወረረደ መሆኑ፣
- 5217101 ፣ 5217110፣ 5217201፣5217205 እና በሌሎች የሂሳብ መደብ ብር 127,674,948.80 ያልተወራረደ ሂሳብ

በድምሩ ብር 433,466,219.10 መኖሩ በኦዲቱ ተረጋግጧል።

2.2 በደንቡና በመመሪያው መሰረት ያልተመዘገበና ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ

- ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ፡- ብር 10,221,832.80፣ ወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 34,490,622.58 ማስረጃ ቀርቦለት የተወራረደ ሂሳብ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው አላግባብ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

- ወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 914,211.82 ጎንደር ዩኒቨርስቲ፡- ብር 1,907,215.25 በአዳማ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 2,113,456.06 የተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የሚያሳዩ በመሆኑና ማስተካከያ ባለመሰራቱ የበጀት ዓመቱ የተሰብሳቢ ሂሳብ ጠቅላላ ሚዛን ዝቅ ብሎ ሊታይ ችሏል፡፡

- ቡሌሆራ ዩኒቨርስቲ_፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሂሳብ ኮድ 4251 ለተቋራጮች ቅድሚያ ብር 78,891,586.69 ተሰብሳቢ ሂሳብ የነበረ ሲሆን ቅድሚያ ክፍያውን በወሰደው ድርጅት ወይም አቅራቢ ስም ተቀጽላ ሌጀር የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

- **ወሎ ዩኒቨርስቲ፡-** ብር 212,250.00 **ዲላ ዩኒቨርሲቲ፤**ብር 9,541,896.06 በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 1,123,672.56 ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ ሲሆን ዩኒቨርስቲው አገልግሎቱን ያላገኘ በመሆኑ ቅድሚያ ክፍያው በተሰብሳቢ መመዝገብ ሲገባው ተገቢውን ጥቅምና አገልግሎት ሳያገኝ በወጪ የተያዘ መሆኑ፤

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 14,023,145.30 በግንባታ ለሚነሱ ነዋሪዎች ያልተከፈለ የጉዳት ካሣ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

- በአዳማ ዩኒቨርሲቲ ፣ ለሠራተኞች ሌሎች ቅድሚያ ክፍያ ፣ እና የሥራ ተቋራጮች የቅድመ ክፍያ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች (የሂሳብ መደብ 4251-0006 እና 4251-0007) ብር 330,579.57፣ በድምሩ ብር 1,248,891.62 በበጀት ዓመቱ ተሰብሳቢ የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ መያዝ ሲገባው ያልተያዘ መሆኑ፣

- ➢ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ፣ በዕቃ አቅራቢዎች የቅድሚያ ክፍያ (የሂሳብ መደብ 4253) ተቀጽላ ሌጀር (4253-0002) ላይ በአንድ ሥራ ተቋራጭ ስም ያለው ሂሳብ ትክክለኛ ሚዛን ብር 4,362,936.55 ሆኖ እያለ በሪፖርት የተያዘው ብር 5,724,656.44 በመሆኑ ብር 1,361,719.89 በሂሳብ መደቡ በሪፖርት በብልጫ የተያዘ መሆኑ፣
- ➢ በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ከ2005 በጀት ዓመት ወደ 2006 በጀት ዓመት የዞረ የተለያዩ የሥራ ተቋራጮች የቅድመ ክፍያ ተሰብሳቢ ሂሳብ (የሂሳብ መደብ 4251) ብር 32,610,629.97 በእያንዳንዱ የሥራ ተቋራጭ በተከፈተ የተቀጽላ ሌጀር ላይ ተለይቶ መዞር ሲገባ በአጠቃላይ በአንድ የሥራ ተቋራጭ ስም በተከፈተ የተቀጽላ ሌጀር ላይ የዞረ ተብሎ መመዝገቡ፣
- ➢ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 301,033.61 የግንባታ ቅድሚያ ክፍያ በሥራ ተቋራጮች የቅድሚያ ክፍያ (የሂሳብ መደብ 4251) መመዝገብ ሲገባው በዕቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ (የሂሳብ መደብ 4253) መመዝገቡ፣

3. <u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

3.1 <u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ፣</u>

• ጎንደር ዩኒቨርስቲ	8,321,951.86
• ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	3,092,542.30
• መቐለ ዩኒቨርሲቲ	9,536,938.52
• ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	20,792,238.44
• አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	2,149,555.50
በድምሩ	**43,893,226.62**

- ➢ ከላይ በሰንጠረዥ የተገለጸው የጎንደር ዩኒቨርስቲ፡- ግብርና ምርት ውጤትና ቢዝነስ ሴንተር የውስጥ ገቢ ሂሳብ በውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ መቀመጥ ሲገባው የአደራ ሂሳብ እንደሆነ ተደርጎ አላግባብ በ"D"' የባንክ ሂሳብ የሚቀመጥ መሆኑ፣ የባንክ ማስታረቂያ የማይዘጋጅ ሲሆን የተሰበሰበው ብር 1,506,135.86 እና ከልዩ ፋርማሲ ክፍል በቀረበው የእቅድ ክንውን ሪፖርት

መሰረት የተሰበሰበ ብር 6,815,816.00 በድምሩ ብር 8,321,951.86 የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ከሰበስበው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 3,092,542.30 በመቐለ ዩኒቨርሲቲ በበጀት ዓመቱ ከተሰበሰበ የውስጥ ገቢ ብር 9,536,938.52 በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ 20,792,238.44 በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,149,555.50፣ በድምሩ ብር 43,893,226.62 ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ያልቀረበ በመሆኑ፣

- የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ብር 1,128,665.32 በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 18,612,054.99 በአዳማ ዩኒቨርሲቲ 3,953,291.55 ፣በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ 2,149,555.50 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሳይፈቀድ ከውስጥ ገቢ ተጠቅሞ የተገኘ መሆኑ፣

ከተቋራጮች የተቀነሰ ቅጣት እና በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢ ከወጪ ቀሪ ብር 600,126.90 ሂሳብ በገቢ ያልተያዘ እና በሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ እንዲሁም ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣

- ወሎ ዩኒቨርስቲ፡-ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጥያቄ ሳይቀርብና ሳይፈቀድ መመሪያውን በመተላለፍ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደብረታቦር ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000074370668 በተቋሙ ስም ተከፍቶ መገኘቱ፤

- ወሎ ዩኒቨርስቲ፡- የውስጥ ገቢ ሂሳብ ኦዲት ሳይደረግና ከወጪ ቀሪው ሳይረጋገጥ ብር 1,019,424.00 ለ2006 በጀት ዓመት የሂሳብ መክፈቻና የመነሻ ሂሳብ ተደርጎ የተመዘገበ በመሆኑ፤

- ዲላ ዩኒቨርስቲ፡- ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ሪፈራል ሆስፒታል ከላብራቶሪና የራጅ ምርምራ አገልግሎት፤ ከተመላላሽ ህክምና እና ከመሳሰሉት ብር 1,145,253.22 የተሰበሰበ ሂሳብ ሲሆን ከእያንዳንዱ የህክምና አገልግሎት የሚሰበሰበው ገቢ ተቀፅላ የሂሳብ ሌጀር ባለመከፈቱና ገቢው በጥቅል በመያዙ፤

ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች የውስጥ ገቢ ሂሳብ በዝርዝር ኦዲት ማድረግ አልተቻለም፡፡

- ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤- ብር 124,238,523.61 ወልድያ ዩኒቨርስቲ ብር 1,118,160.54 የውስጥ ገቢ የሰበሰበ ቢሆንም የገቢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤ የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት መሠረት የገቢ መቀበያ ደረሰኝ ተፈላጊውን መረጃ አሟልቶ መያዝ እንዳለበት የተደነገገ ቢሆንም በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ ተፈላጊ መረጃዎች በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ በመሆኑ፤ብዛት ያላቸው ከፋዮች ባንክ ገቢ ያደረጉት ገንዘብ በጥቅል አንድ ቅጠል የገቢ ደረሰኝ መሆኑ፣

የተሰበሰበው ገንዘብ መሰብበሰብ በሚገባው መጠን መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም።

- ወልድያ ዩኒቨርስቲ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ የዩኒቨርሲቲው የመምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች መዝናኛ ክበብ፤ የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ እና በቁጥር 21 ከሚሆኑ የተለያዩ አገልግሎት መስጫዎች (የፎቶ ኮፒ ፤የቁንጅና ሳሎኖች፤ የወንዶች ፀጉር ማስተካከያ ቤቶች፤ ሱቆች፤ ቁርስ ቤቶች፤ ሻይ ቤቶች) የመሳሰሉት የገቢ ማመንጫዎች በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኙ ቢሆንም ምንም አይነት የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍሉ አለመደረጉ፤

3.2 <u>ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ የገቢ ሂሳብ</u>

- ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ለትምህርት ልኳቸው በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸው ካልተወጡ መምህራን ተመላሽ የተደረገ ብር 3,139,977.85 ፣ የመድሃኒት ሽያጭ ገቢ ብር 2,388,393.45፣ ከጠፋ ከተማሪዎች መመገቢያ ካርድ፣ከጠፋ የተማሪዎች መታወቂያ ካርድ፣ የጨረታ ሰነድ ሽያጭ ከተለያዩ የህክምና አገልግሎት ላብራቶሪ፣የራጅ አገልግሎት፣ ተመላላሽ ህክምና አገልግሎት እና ከመሳሰሉት የተሰበሰበ ገቢ ብር 4,891,857.52 ጠቅላላ ድምር ብር 10,420,228.82
- ዲላ ዩኒቨርስቲ፡- ከመድኃኒት ሽያጭ የተሰበሰበ ገቢ ብር 2,057,269.98 እንዲሁም ከጠፋ የተማሪዎች የመመገቢያ ካርድና የተማሪዎች የመታወቂያ ካርድ፣ የጨረታ ሰነድ ሽያጭ እና ከመሳሰሉት የተሰበሰበ ልዩ ልዩ ገቢ ብር

889,140.02 ለኮንትራክተሮች የተሰጠ የቅድመ ክፍያና የሲሚንቶ ተመላሽ ብር 6,948,555.32 በድምሩ ብር 9,894,965.32

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ተመላሽ የተደረገ ብር 1,157,349.11 እና ተመላሽ ያልተደረገ ብር 633,291.86 የቤት አበል በድምሩ ብር 1,790,640.97 ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ሳይደረግ መገኘቱ፣

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል።

3.3. ያልተሰበሰበ ገቢ

• ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ	5,238,841.79
• ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	1,779,589.08
• ዲላ ዩኒቨርስቲ	375,526.66
• በመቐለ ዩኒቨርሲቲ	43,092,521.89
• በአዴግራት ዩኒቨርሲቲ	112,586.76
• በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	332,457.32
• በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	327,420.86
• በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ	224,393.20
ድምር	**51,483,337.56**

በድምሩ ብር 51,483,337.56 አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው፣ ህንፃዎች በውላቸው ላይ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቃቸው ላደረሱት የጉዳት ካሳ፣ውዝፍ የቤት ኪራይ ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉን፡ለማረጋገጥ ተችሏል።

3.4 ማስረጃ ባለመሟላቱ የገቢውን ትክክኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፣

- የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ወንዶ ገነት የደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ከወርክሾፕ የሰበሰበው ገቢ ብር 3,284,006.68 እና የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከህክምና አገልግሎት የተሰበሰበ ገቢ ብር 1,672,887.37 በድምሩ ብር 4,956,894.05 የጎንደር ዩኒቨርስቲ፡- የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከተለያዩ የህክምና አገልግሎቶች ብር 5,796,331.68 የተሰበሰበው ገቢ ከእያንዳንዱ አገልግሎቶች የተሰበሰበ ገቢ ትክከለኛነት ለማረጋገጥ እንዲያስችል ለገቢ ሂሳቡ ተቀፅላ የሂሳብ ሌጀር ያልተከፈተ መሆኑ፤

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ በመ/ቤቶች የተላኩ ተማሪዎች በገቡት ውለታ መሠረት ክፍያው እንዳልተሰበሰበና ሂሳቡም በገቡት ውል ላይ ከመመልከቱ በቀር ያልተሰበሰበው ሂሳብ መጠን በትክክል የማይታወቅ መሆኑ እና 12 ሩዋንዳዊያን በዩኒቨርስቲው ከ2006 መጀመሪያ ክፍለ ጊዜ (ሴሚስተር) ጀምሮ በተለያየ የትምህርት ዘርፍ የድኅረ-ምረቃ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች ስምምነት የተደረገበት የክፍያ መጠን የሚያመለክት ውል (ሌላ የጽህፍ) ማስረጃ ለኦዲቱ ያልቀረበ መሆኑ፤

- የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የዩኒቨርስቲው የውስጥ ገቢ ከተከታታይ ትምህርት መሆኑን ቢገለጽም ተቋሙ የውስጥ ገቢ ሊያዳብር የሚችል አደረጃጀትና መረጃ ባለመኖሩ የውስጥ ገቢ ምንጮቹ በዝርዝር የማይታወቁ መሆኑ፤

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ የውስጥ ገቢ ማስገኛ ምንጮች በዝርዝር የሚያሳይ ማስረጃ የሌለው መሆኑ፤

- የጅማ ዩኒቨርስቲ የሚሰበስበውን ገቢ የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ምዝገባና የተሟላ ተቀፅላ ቋት የሌላቸው መሆኑ፣ ሂሳቦች እንደየባህሪያቸው በተሟላ መልኩ ምዘግባ አለመካሄዱ፣ ህጋዊ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች የሌላቸው እና ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ገቢና ወጪ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ መሆኑ፣

- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ የሚሰበስበውን ገቢ እንደገቢው ሁኔታ ቋት ተከፍቶ መመዝገብና ክትትል የማያደርግ እና ባልተሟላ መልኩ በእጅ የሚመዘገብ በመሆኑ በውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ምን ያህል ገንዘብ ከእያንዳንዱ የገቢ ዓይነት እንደተሰበሰበ ማወቅ ባለመቻሉ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3.5 በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች የአሠራር ድክመቶች፣

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ለማህበረሰቡ እንዲሸጥ ከተወሰነው ውጭ በድምሩ 650 ኩንታል ብር 140 (650-510) ተቀንሶ በመሸጡ ብር 91,000.00 መሰብሰብ የሚገባው የመንግሥት ገቢ በማነስ የተሰበሰበ መሆኑ እና የተለያዩ መዝናኛ ክበቦች አገልግሎት አሰጣጥ እና አቀራረብ ደንብና መመሪያ በሚያዘው መሠረት የማይከናወን መሆኑ፣
- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሠራተኞች ክበብ አገልግሎት ያለምንም ውድድር ለተለያዩ ሰዎች በወር ብር 650.00 ኪራይ ተይዞ የቆየ ቢሆንም የየወሩ ኪራይ በውለታው መሠረት የማይሰበሰብ መሆኑ፤
- የመቱ ዩኒቨርስቲ የውስጥ ገቢ ሂሳብ በየወሩ መጨረሻ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማይዘጋጅ በመሆኑ በባንክ የታየውን ብር 4,325,399.55 ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ለገቢ ሂሳብ በየሂሳብ መደቦቹ ተቀፅላ ሌጀር (subsidiary ledger) አለመዘጋጀቱን፤
- መቐለ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢ እና የፕሮጀክት ሂሳብ በአንድ የባንክ ሂሳብ እንዲያዙ በመደረጉ እና የአጭር ጊዜ የፕሮጀክት ሂሳቦች በተከፋይ ሂሳብ መያዝ ሲገባቸው በገቢ የሚያዝ በመሆኑ የውስጥ ገቢ ሂሳብ አለአግባብ ከፍ እንዲል መደረጉን፡
- መቐለ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ ኮሌጆች በገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የተሰበሰበ በድምሩ ብር 959,993.25 የውስጥ ገቢ በድጋሚ ተመዝግቦ መገኘቱን፤

ተረጋግጧል፡፡

3.6 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሳያስፈቅድ ደረሰኝ በማሳተም መጠቀም

መቐለ ዩኒቨርሲቲ ለገንዘብና ኢኪኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሳያሳውቅ በስሙ ደረሰኝ በማሳተም ከአጫጭር ፕሮጀክቶች እና ከውስጥ ገቢ ብር 12,879,067.34 ሰብስቦ መገኘቱን፤

4. የወጪ ሂሳብ፣

4.1 ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ፣

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ለመመዝገቡ ኦዲት ሲደረግ፣

• የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	8,596,830.92
• አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ	1,100,000.00
• የመቱ ዩኒቨርስቲ	601,066.37
• የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ	421,272.18
ድምር	**10,719,169.47**

በድምሩ ብር 10,719,169.47 ማስረጃ ሳይቀርብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

4.2 የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ

- ዲላ የኒቨርሲቲ፤ በገባዉ ውል መሰረት ክፍያ የተፈጸመባቸው በቁጥር 38 የወጪ ቫውቸሮችና ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች ለኦዲት ያልቀረቡ መሆኑ፣
- በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ በወጪ ሂሳብ ሥር በዴቢት (መደበኛ ሚዛን) የተመዘገበ ብር 110,930,205.38 እና በክሬዲት (ያልተለመደ ወይም መደበኛ ያልሆነ ሚዛን) የተመዘገበ ብር 5,338,813.62 በሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓመታዊ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ የተካተተ ቢሆንም ማስረጃዎቹ ለኦዲት ሥራ ባለመቅረባቸው የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣

4.3 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ የተሟላ የወጪ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ14 መ/ቤቶች ብር 95,445,380.45 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

4.4 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች፤

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ በመንግስት የወጡ በስራ ላይ ያሉ ደንብና መመሪያን ተከትለው የተከፈሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ22 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 49,673,916.01/ዝርዝሩ በአባሪ-22 ተመልክቷል/ ለትርፍ ስዓት

ሥራ፣ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች አበል፣ ደመወዝና ማበረታቻ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ክፍያዎች ተገኝተዋል፡፡

ስለሆነም ከደንብና መመሪያ ውጭ እየተከፈሉ ያሉ ጥቅማጥቅሞች እንዲቋረጡ አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ሆኖ ገንዘቡ ፈሰስ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ቤት ያላገኙ መምህራን እያሉ ለ23 የአስተዳደር ሠራተኞች በዋናው ግቢ የመኖሪያ ቤት መሰጠቱ ታውቋል፡፡

4.5 <u>በብልጫ የተከፈለ</u>

• ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	374,860.00
• ጎንደር ዩኒቨርስቲ	310,320.00
• ሰመራ ዩኒቨርስቲ	85,305.00
• ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	196,935.75
• ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ	144,000.00
• በማይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር(የቆላ ዝንብ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ	22,049.70
• ዲላ ዩኒቨርስቲ፡	32,466.89
ድምር	**1,165,937.34**

በድምሩ ብር 1,165,937.34 ለትርፍ ሰአት፣ለውሎአበል እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተተመነው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 190,264.00 ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት ግዥ በመፈጸሙ በብልጫ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ብር 1,149,195.19 ከውለታ በላይ ለመምህራን የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ መከፈሉ፣
- የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ብር 52,371.01 ውለታ ከተገባበት ዋጋ በላይ የህንጻዎች የመስኮት የግሪል ሥራ አገልግሎት ለሰጠው ድርጅት ተከፍሎ መገኘቱ፣
- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 963,233.57 ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት ግዥ ባለመፈጸሙ ማግኘት ያለበት ገንዘብ እንዲያጣ መደረጉ፣

4.6 <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች፣</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳብ ግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ24 መ/ቤቶች ብር 184,600,282.00 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች፣መሆኑን ተረጋግጧል። /ዝርዝሩ በአባሪ- 24 ተመልክቷል/

ይህም ግዥውን በመከፋፈል፣ በቀጥታ ግዥ፣ ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ግገር፣ ያለበቂ ተወዳዳሪና በውስን ጨረታ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

4.7 <u>ኃላፊዎች ከተፈቀደላቸው የክፍያ መፍቀድ ስልጣን ገደብ በላይ መፍቀድ</u>

• በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር	303,705.40
• በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር	480,050.64
• በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ	15,307,065.56
ድምር	16,090,821.60

4.8 <u>ያለ ሂሳብ መደቡ የተመዘገበና ሪፖርት የተደረገ ወጪ ሂሳብ፣</u>

• የመቱ ዩኒቨርስቲ	ብር	986,212.87
• በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ		11,978,865.61
• በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር		135,173.58
በድምሩ	ብር	12,114,039.19

ያለ ሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረጉ፣

4.9 <u>በተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ያልተደረገ የወጪ ሂሳብ</u>

በመቐለ ዩኒቨርሲቲ ከተሰበሰበው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ውስጥ ወጪ የተደረገው ሂሳብ ብር 2,452,885.19 በማነስ በወጪ ሪፖርት መደረጉ፣

4.10 የተለያዩ የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪዎችን በተመለከተ፣

4.10.1 ለተለያዩ ለግንባታ የቀረቡ ዕቃዎች /በሥራ ላይ ላልዋሉ Materials on site ተብሎ የተከፈለ፣

- ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣- ብር 3,375,443.62
- ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ፡- 21,947,043.49

በድምሩ ብር ብር 25,322,487.11

ሥራ ላይ ለመዋሉ ላልተረጋገጠ የግንባታ ግብአት ዕቃ ወይም "Material on site" ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 991,509.73 በውል ባልተካተተ በግንባታ ቦታ ለሚገኝ ዕቃ፣ ውሃና ጄኒሬተር አቅርቤአለሁ በሚል የተከፈለ መሆኑ፣

4.10.2 ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የግንባታ ሰነዶች

- ወሎ ዩኒቨርስቲ፣ GIZ-IS ከሚባለው ድርጅት የተረከባቸውና በደሴ ካምፓስ እና በቴክኖሎጂ ፋካልቲ ኮምቦልቻ ካምፓስ የሚገኙ ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች
- ዲላ ዩኒቨርስቲ፡- በትምህርት ሚኒስቴር እና በGIZ-IS ሲከናወኑ የነበሩና ያልተጠናቀቁ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲዉ ዋና ግቢ ነዳጅ ማደያ አጠገብ የሚገኝ የተጀመረ ህንፃ እና በተከታታይ እና የርቀት ትምህርት አካባቢ የሚገኝ ህንፃ ግንባታ በዩኒቨርሲቲው የሰው ሃይል ከሚከናወኑ ግንባታዎች ውስጥ በአዲሱ የቴክኖሎጂ ግቢ የላብራቶሪና ወርክ ሾፕ ሁለት ህንፃ፣ በመኖሪያ ግቢ መዋኛ ገንዳ፣ ገስት ሃዉስ፣ ጂም፣ ሱፐር ማርኬት ግንባታ የሚገኙበት ሁኔታ የሚገልጽ ወቅታዊ መረጃ ለኦዲት እንዲቀርብ የተጠየቀ ቢሆንም መረጃው ሊቀርብ አለመቻሉ፣

- ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ፡-በትምህርት ሚኒስቴር እና በGIZ-IS ሲከናወኑ የነበሩና ያልተጠናቀቁ የግንባታ ፕሮጀክቶች፤

ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጹ የግንባታ ሰነዶችና ወቅታዊ መረጃ ለኦዲት እንዲቀርብ የተጠየቀ ቢሆንም መረጃዎቹ አልቀረቡም፡፡

- መቐለ ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲው የአዲስ አበባ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ለማሰራት በተገባው የግንባታ ውል 30 በመቶ ብር 5,152,276.82 የቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ በጥቅምት/2006 እንዲጠናቀቅ የውል ስምምነት ቢፈረምም ግንባታው ሳይጀመር ከሁለት አመታት በላይ መቆየቱን ፤
- መቐለ ዩኒቨርሲቲ ዩኒቨርሲቲው ካስገነባቸው እና ከተጠናቀቁት ግንባታዎች መካከል ከሥራ ተቋራጮች ጋር ሙሉ በሙሉ ርክክብ ሳይፈጸም ለዩኒቨርሲቲው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ህንፃዎች የሚገኙ መሆኑን፡

4.10.3 ያልተሰበሰበ በብድር የተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ፤

- የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር 12,549,872.04 ኮንትራክተሮች የገንዘብ እጥረት ስላጋጠማቸው በሚል ብድር ተሰጥቶ መገኘቱ እና ከድርጅቶቹ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ እና ብር 3,568,559,99 መቀነስ ከሚገባው የስሚንቶ ዋጋ በታች በመቀነሱ ከኮንትራክተሮች በዕዳ የሚፈለግ ሲሆን፣ ብር 962,557.36 ደግሞ ከኮንትራክተሮች ላይ መቀነስ የሚገባው የስሚንቶ ዕዳ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ
- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 3,214,769.10 በገባው ውል መሠረት መቀነስ ያለበት ገንዘብ ሳይቀነስ መገኘቱ፣

ተረጋግጧል፡፡

4.10.4 ሌሎች ከግንባታዎች ጋር የተያየዙ ችግሮች፣

- የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የሕንፃና መሠረተ ልማት ግንባታዎች፡
  - ✓ የሕንፃ ሥራ ተቋራጮች ግንባታዎችን ማስረከብ ከነበረባቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማያጠናቅቁ መሆኑ፣
  - ✓ የቅድሚያ ክፍያ አቀናነስ ሲደረግ አልፎ አልፎ የስሌት ስህተት የሚከሰት መሆኑንና አንዳንድ ጊዜ ሳይቀነስ የሚዘገይ መሆኑ፣
  - ✓ ተቋራጮች አስቀድሞ ከወሰዱት የግንባታ ዕቃ የቀራቸው ሳይታወቅ ቀጣዩን እንዲወስዱ የሚደረግ መሆኑ፤ እና
  - ✓ በግንባታ ዕቃ ግምጃ ቤት ከክፍያቸው የተቀነሰውን የሚያዝበት /የሚከታተልበት/ አሠራር የሌለ መሆኑ፤
  - ✓ ለመምህራን መኖሪያነት የሚያገለግሉ 180 የጋራ መኖሪያ ቤቶች (12 ህንጻዎች) ግዢ በተገባው ውለታ መሠረት ሳይጠናቀቅ ዩኒቨርስቲው እንዲረከብ መደረጉ፣
- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በGIZ የተጀመሩ ያልተጠናቀቁ የግንባታና የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች በተመለከተ ለኦዲቱ ሥራ አሰፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መረጃ ባለመቅረቡ ሂሳቡን ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፣
- የመቱ ዩኒቨርስቲ የሕንፃና መሠረተ ልማት ግንባታዎች፡
  - ✓ ብር 21,152,378.97 ዩኒቨርሲቲው ከተቋራጮቹ መስብሰብ ያለበት ቅጣት ሳይሰበሰብ መገኘቱ፣
  - ✓ ብር 12,225,995.14 በነጭ ወረቀት የተዘጋጀና የደረሰኝ መለያ ቁጥር በሌለው ተራ ወረቀት ለኮንትራክተሮች ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
  - ✓ ብር 151,137.00 የግንባታ ሥራ የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች አፈር በመድፋታቸው እና አፈሩን ለማስነሳት በሚል ተከፍሎ መገኘቱ፣

- ✓ ብር 15,842,757.83 ንብረቱ ወጪ የሆነበት ሞዴል 22 ማስረጃው ከሰነድ ጋር ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

➢ የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ የሕንፃና መሠረተ ልማት ግንባታዎች፡

- ✓ ብር 67,000,000. ለGIZ-IS በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቻይና አፍሪካ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 017182746100 ትራንስፈር ተደርጎ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- ✓ የብር 8,503,372.69 የግንባታና የኮብል ስቶን ሥራዎች ለኮንትራክተሮችና ለግንባታ ማህበራት ሕጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- ✓ ብር 5,987,630.10 ማስረጃ ሳይቀርብ የዋጋ ማስተካከያ /price Adjustment/ በሚል ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- ✓ ብር 2,735,378.09 ማስረጃ ሳይኖር የለውጥ ሥራ/variations order/ና ተጨማሪ ሥራ /supplementary Agreement/ በሚል የተከፈለ መሆኑ፣
- ✓ ብር 2,455,440.41 ለኮንተርክተሮች የግብአት ዕቃ እዳ የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል 22 ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ✓ ብር 821,449.21 ውል ከተገባው በላይ እና ላልተሠራ የግንባታ የክትትል ሥራ ያለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- ✓ በቴፒ ካምፓስ ለኢንጂነሪንግ ተማሪዎች አገልግሎት የሚውል የቤተ መጻህፍት ግንባታ እንደ ተጀመረ ቢታወቅም ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ በመቋረጡ ለብልሽት እየተዳረገ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

➢ ዲላ ዩኒቨርስቲ፦

- ✓ የቲችንግና ሪፈራል ሆስፒታል የተማሪዎች ማደሪያ ግንባታ ሥራ ዩኒቨርሲቲው ባወጣው ጨረታ ዩኒቲ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ የተባለው ተቋራጭ ብቸኛ ተወዳዳሪ በመሆን የቀረቡ በመሆኑ በግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ ውድድር የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆንና ይህን ተጫራች በብቸኝነት እንዲቀርብ ያስቻለውን በጨረታ ሰነዱ ላይ ለውጥ በማድረግ በርካታ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ማግኘት እንዲቻል ድጋሚ ጨረታ መውጣት ሲገባው በድጋሚ ጨረታ ሳይወጣና ውድድር ሳይደረግ መጀመሪያ በወጣው ጨረታ ብቸኛ ተወዳዳሪ የሆኑት ተቋራጭ ብር 57,602,233.62 የሚያወጣ ግንባታ ሥራ እንዲያሸንፉ መደረጉ፤
- ✓ ለሳይለም ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ ለተማሪዎች መማሪያና ማደሪያ፣የሰራተኞችና የመምህራን ካፌ፣ ጋራዥ እና የስፖርት ሜዳ ግንባታለማከናወን በገባው ውል መሰረት የውሉ ዋጋ 30% ብር 6,474,297.53 ቅድመ ክፍያ የተሰጠው ሲሆን በቅድሚያ ለወሰደው ገንዘብ ያቀረበው ዋስትና ከjuly05,2014 በሁዋላ የማያገለግል ቢሆንም ዋስትናው አለመታደሱ፤
- ✓ ለረድኤት ዳግም ኢንጅነሪንግ ከተፈጸመው የግንባታ የቅድመ ክፍያው ብር 1,824,860.23 ተመላሽ ሳይደረግ ከሚፈለግባቸው ዕዳ ላይ አላግባብ የተሰረዘ መሆኑ፤
- ✓ ከፍተኛ ዋጋ በሚጠይቁና ውስብስብ ወይም ቴክኒካል የሆኑ ስራዎች በሙያው በቂ ዕውቀት ያላቸው የውጭ አማካሪዎች በመቅጠር ማሰራት እንደሚገባ በመንግስት በወጣው የግዥ መመሪያ ላይ የዩኒቨርስቲው የግንባታ ፕሮጀክት ፅ/ቤት ከሚመለከተው ክፍል የተሰጠ አማካሪ መሃንዲስ ለመሆን

የሚያስችል የስራ ፍቃድም ሆነ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ሳይኖረው ብር 51,721,919.78 ዋጋ ያላቸው ፕሮጀክቶች እንደአማካሪ መሃንዲስ በመሆን የክፍያ ሰርቲፊኬት የሚያጸድቁ መሆኑን፡

- ➢ በሰመራ ዩኒቨርስቲ በ2006 በጀት ዓመት የተገነባው የውስጥ ለውስጥ የኮብል ስቶን መንገድ ግንባታ ብር 5,367,150.81 የወጣ ቢሆንም በውሉ መሰረት የጥራት ደረጃው ተጠብቆ ባለመሰራቱ መንገዱ የተበላሸና የፈራረሰ መሆኑ የኦዲት ቅኝትና ዳሰሳ በተደረገበት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡
- ➢ ወልድያ ዩኒቨርስቲ፡-አልታቤ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከሚገነባቸው መሰረተ-ልማት ውስጥ አንዱ ስፖርት ፋሲሊቲ ግንባታ ሲሆን ዋናው ውል ብር 6,568,585.15 ቢሆንም ተጨማሪ ስራ (ትዕዛዝ) ከመመሪው ውጪ ብር 23,127,639.00 በግዢ አፈጻጸም መመሪያ ከተፈቀደው 25% በላይ በተጨማሪ ውል የተሰጠ መሆኑ፤

4.10 <u>የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ፣</u>

- ➢ የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ በዩኒቨርሲቲው ስር የሚገኙት ተሽከርካሪዎች በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጠቀሙት የነዳጅ መጠንና ከሸፈኑት ኪ/ሜትር ርቀት በየወሩ ምዝገባ እየተከናወነ ተገቢው ሪፖርት ከፋሲሊቲ አስተዳደር እንዲቀርብ ተጠይቆ በቀረበው ሪፖርት መሰረት፤ የተሰራው ኖርማላይዜሽን፤ የተጠቀሙት ነዳጅ፤ መነሻና መድረሻ ኪ/ሜትር ማስረጃው እንዲቀርብ ተጠይቆ ባለመቅረቡ ምክንያት፤ በሰኔ 30/2006 በሂሳብ መደብ 6217 የሚታየው የነዳጅና ተዛማጅ ወጪዎች ብር **1,843,881.63** ሂሳብ ለማጣራት ያልተቻለ መሆኑ፣
- ➢ የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 4,511,722.33 የኤ.ቢ.ኤች. ከተባለ ድርጅት በጋራ የሚከናወን የድህረ ምረቃ ትምህርት ድርጅቱ ባቀረበው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ብቻ የተወራረደ በመሆኑና ተገቢው ዝርዝር የወጪ ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም።

4.11 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ወጪ ሂሳብ፣

- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 2,474,812.23 ወሎ ዩኒቨርስቲ፡- ብር 43,232.84 የሚያወጡ የመድኀኒት እና የላቦራቶሪ ኬሚካል ዕቃዎች፣ የመቐለ ዩኒቨርሲቲ በብር 605,745.67 የተገዙ ፓምፕ እና ጀኔሬተር በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 53,692.00 እና 12606.92 በሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል በብር 32,315.00 የተገዛ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ያልተቀረጠለት መሆኑን፡ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ

5.1 ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፣

- ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ መከፈለቸውን ለመማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ14 መ/ቤቶች ብር 107,526,920.03 በወቅቱ ያልተከፈለ ወዝፍ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 32 ተመልክቷል/
- በተጨማሪም በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ በውዝፍ የሚታየው ብር 1,437,086.76 ተከፋይ ሂሳብ የ2004 መሆኑ፣
- በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ለዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር በተዘጋጀዉ የዉስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የቫት ተከፋይ ሂሰብ (የሂሳብ መደብ 5059) ብር 44,262.25 መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ መሆኑ፣
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ፣
- ብር 47,536,866.11 የአደራ ሂሳብ ውስጥ ብር 839,048.91 ከማን እንደተሰበሰበ የሚገልጽ ሲሆን፣ ቀሪው ተከፋይ ሂሳብ ግን ለማን እንደሚከፈል የሚያመለክት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ብር 20,774,466.40 (በ4104 ሂሳብ መደብ) በሌተር ኦፍ ክሬዲት መያዝ ሲገባው፣ (በ5511 ሂሳብ መደብ) ለትምህርትና ሥልጠና በሚል የተያዘና የሂሳብ ማስተካከያ ሳይሰራለት ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣

- ብር 2,417,452.36 የቢድ ቦንድ ዲፖዚት ውስጥ ብር 2,085,522.73 ከ2002 ዓ.ም. ጀምሮ በተከፋይነት የሚታይ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 331,929.63 ጊዜው የማይታወቅና ያለምንም እርምጃ በዕዳነት የሚታይ መሆኑ፣
- ብር 705,413.88 የተጨማሪ እሴት ታክስ ለሚመለከተው አካል ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ፣ ብር 1,227,506.66 ግብርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣

የመቱ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ፣

- ብር 1,385,440.11 የተጨማሪ እሴት ታክስ ለግብር ሰብሳቢዉ መ/ቤት ገቢ ሳይደረግ መገኘቱ፣
- ብር 86,002.52 ከተከፋይ ተቀናሽ የተደረገውን ታክስ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ ሳይደረግ መገኘቱ፣
- ብር 5,465.87 ልዩ ልዩ የደመወዝ ተቀናሽ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ያልተከፈሉ መሆኑ፣
- ብር 4,844.52 ከሠራተኞች የተሰበሰበው የወጪ መጋራት ለሚመለከተው አካል ገቢ ሳይደረግ መቆየቱ፣

የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ፣

- ብር 10,096,508.00 የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ከተከፋይ ተቀናሽ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ ሳይደረግ መገኘቱ፣
- ብር 231,662.05 የጡረታ መዋጮ ተከፍያ ሂሳብ ለባለመብቱ መ/ቤት ያልተከፈለ መሆኑ፣
- ብር 131,198.17 የደመወዝ ተከፍያ ሂሳብ ሳይወራረድ መገኘቱ፣
- ብር 55,209.06 ከሠራተኞች ለአባይ ቦንድ ግዥ የተሰበሰበ ባለቤት የሌለው ገንዘብ እንደሆነ የሚያሳይ ቢሆንም በዕዳ ተመዘገቦ መገኘቱ፣
- ብር 20,546.10 የፍርድ ቤት መያዣ ሂሳብ ከ2004 ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ ለባለመብቱ ከፍያው ሳይፈጸም መገኘቱ፣

የጅማ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ፣

- ብር 782,121.02 የደመወዝ ተከፍያ ሂሳብ ሳይወራረድ መገኘቱ፣
- ብር 570,234.75 የሆስፒታል መያዣ ሂሳብ ለባለመብቱ ክፍያ ሳይፈጸም መገኘቱ፣
- ብር 25,559.31 የተጨማሪ እሴት ታክስ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ ሳይደረግ መገኘቱ፣

ተረጋግጧል።

5.2 ከተከፋይ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ ግብርና ታክስ፣

የመ/ቤቱ ስም	የገንዘቡ ልክ
የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ	2,823,420.72
የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	2,223,167.80
የመቱ ዩኒቨርስቲ	554,484.19
የጅማ ዩኒቨርስቲ	136,198.07
የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ	1,160.94
ዲላ ዩኒቨርስቲ	97,547.13
ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	589,619.15
ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	638,823.53

ከተከፋይ ላይ ተቀናሽ ግብር እና የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ብር በአዋጁ መሰረት በቀጣዩ ወር ለሚመለከተው አካል ያልተላለፈ መሆኑ ታውቋል።

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ፡-

- ብር 2,489879.55.96 የተከፋይ ሂሳብ በዴቢት የሚታይ በመሆኑ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን አላግባብ ዝቅ እንዲል ተደርጓል።
- ብር 5,323,667.58 የሂሳብ ማስተካከያ በመሥራትና ገቢውን በመሰረዝ በተከፋይ ሂሳብ አላግባብ በዕዳ ተመዝግቦ ተገኝቷል።
- ከተለያዩ ለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በእርዳታ የተገኘው የፕሮጀክት ፈንድ በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት /Charts of accounts/

መሰረት ገቢው በገቢ አርዕስት ወጪውም በወጪ አርዕስት ተመዝግቦ መያዝ ሲገባው በተከፋይ ሂሳብ በዴቢትና በክሬዲት እየተመዘገበ ስለሚቀናነስ ከፕሮጀክት ፈንድ የተገኘውን ገቢ እና ለፕሮጀክቱ አገልግሎት የወጣውን ወጪ የማያሳይ ምዝገባ እየተከናወነ መሆኑ ፤

ዲላ ዩኒቨርስቲ፡-

- ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ ተደረገ ብር 9,553,199.31 እና በድጋሚ ተመዘገበ ብር 22,541.57 በድምሩ ብር 9,575,740.88 አላግባብ በተከፋይ ዕዳ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ፡-

- ብር 4,784,197 በብድር ለተቋራጮቹ የተሰጠው ገንዘብ ተቋራጮቹ ገንዘቡን ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ለቤቶች ልማት ድርጅት የሚከፈል ተብሎ በተቋሙ ላይ አላግባብ በዕዳ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

ሰመራ ዩኒቨርስቲ፡-

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ኮድ 5061 ብር 8,420,895.45 የመያዣ ሂሳብ የሚገኝ ቢሆንም ገንዘቡን ባስያዘው ድርጅት ስም ተቀጽላ ሌጀር የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ፡-

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ኮድ 5061 ብር 10,647,904.70 የመያዣ ሂሳብ የሚገኝ ቢሆንም ገንዘቡን ባስያዘው ድርጅት ስም ተቀጽላ ሌጀር የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመቐለ ዩኒቨርስቲ፡-

- በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በተከፋይ የተያዘ በድምሩ ብር 5,136,874.37 በወቅቱ ያልተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 19,151,730.44 ከተቋራጮች ተቀንሶ በሂሳብ ስርዓቱ መሠረት በዕዳነት (በ5061 ሂሳብ መደብ) ያልተያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ ከሂሳቡም የመንግሥት ታክስ ተቀንሶ ገቢ መደረግ ሲገባው ያልተቀነሰ መሆኑና ሪፖርትም ያልተደረገ መሆኑ፤

ተረጋግጧል፡፡

6. በበጀት ላልተሸፈነ ሂሳብ ወጪ የተደረገ፣

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 431,887.72 ለተከታታይ እና ርቀት ትምህርት ክፍል መምህራን ላስተማሩበት ከመደበኛ በጀት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- የወላይታ ዩኒቨርስቲ ብር 3,808,800.34 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ መገኘቱ፣
- የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 2,532,985.50 በ2005 በጀት ዓመት ለዋለው የምግብ ፍጆታ በ2006 በጀት ዓመት ተመዝግቦ መገኘቱ እና ብር 505,550.18 መነሻ ካፒታል ተመድቦለት ለሚንቀሳቀስና የራሱ የገቢ ምንጭ ላላቸው መዝናኛ ክበቦች የዕቃና አገልግሎት ግዥ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- በመቐለ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ ቀናት ማስረጃ ቀርቦለት ብር 4,117,231.93 በወጪ ከተመዘገበ በኋላ ገንዘቡ ተመላሽ ሳይደረግ በተሰብሳቢ እንዲያዝ ከተደረገ በኋላ በ1/11/2005 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ከተሰብሳቢ እንዲቀነስ ተደርጎ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

7. ሌሎች ከወጪ ሂሳብ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች፣

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 9,000.00 ዋጋ ያለው ብዛት 7 ኩ/ል ሽንኩርት ሳይገዛ ሞ/19 ተዘጋጅቶለት በወጪ የተያዘ መሆኑ፤
- የመቱ ዩኒቨርስቲ በብር 1,514,821.52 የስፖርት ትጥቅ ግዢ ሲፈጸም በስፔስፍኬሽኑ እና በናሙናው መሰረት ግዢው የተፈጸመ ለመሆኑ ከባለሙያ ማስረጃ አለመቅረቡን፣
- የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር 401,274.20 በውሉ መሠረት የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ መገኘቱ፣
- የጅማ ዩኒቨርስቲ የብር 1,347,873.48 ግዥ ሲፈጸም የዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ እንደ ሽያጭ ደረሰኝ ቀርቦ መገኘቱ እና ብር 6,431.04 አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ማቅረብ ከሚገባቸው ቀን ያሳለፉበት ቅጣት ሳይቆረጥ መገኘቱ፣

ተረጋግጧል፡፡

8. የበጀት አጠቃቀም፣

8.1 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለመረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ15 መ/ቤቶች ብር 112,712,696.25 በመደበኛ በጀት እና በሁለት መ/ቤቶች ብር 1,916,486.66 የካፒታል በጀት በድምሩ 114,629,182.91 ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል። /ዝረዝራቸው በአባሪ-33 ተመልክቷል/

ለየመ/ቤቶቹ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የበጀት አጠቃቀም ግድፈት እንዳይደርስ ጥንቃቄ እንዲያድርጉ አሳስበናል።

8.2 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤በ24 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 433,906,495.32 እና በ15 መ/ቤቶች ከካፒታል በጀት ብር 776,312,883.15 በድምሩ 1,210,219,378.94 በስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ተረጋግጧል።/ዝረዝራቸው በአባሪ-33 ተመልክቷል/

9. የዕቃና ንብረት አስተዳደር

9.1 ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር፣

9.1.1 ለቋሚ ንብረት መዝገብ ያልተቋቋመባቸው /ያልተመዘገቡ/ መቤቶች፣

- መቱ ዩኒቨርስቲ በጋምቤላ ካምፓስ ለአላቂ ንብረት መዝገብ(ስቶክ ካርድ) ያልተዘጋጀና ምዝገባም የማይከናወን ሲሆን፣ በዋናው ካምፓስ ደግሞ መዝገብ ቢቋቋምም ምዝገባ ያልተደረገ፣ ከወጪ ቀሪያቸው የማይመዛዘን መሆኑ፣
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ፣ የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ፣ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ፣
  - የመጻህፍት አያያዝና አጠባበቅ ደንብና መመሪያ በሚያዘው መሠረት የማይከናወን መሆኑ፣

- በመድኃኒት አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ላይ ደንቡ በሚያዘው መሠረት ተፈጻሚ አለመደረጉ፣
- የተማሪዎች ምግብ አያያዝና አጠባበቅ ደንብና መመሪያ በሚያዘው መሠረት የማይከናወን መሆኑ፣

9.1.2 ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያላደረጉ መቤቶች፣

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ለአገልግሎት ወጪ የተደረጉ ቋሚ ንብቶች ቆጠራ ካለመደረጉም በተጨማሪ የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

9.1.3 ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች የታዩባቸው መቤቶች፣

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ፣
  - ✓ የዋናው ግቢ በተቋሙ በንብረትነት ያልተያዙ (ገቢ ያልተደረጉ) ከ2005 በፊት ጀምሮ በንብረት ክፍል 46 LCD ያለምንም እርምጃ የተቀመጡ መሆኑ፤
  - ✓ የዋናው ግቢ የተለያዩ አሮጌ ዕቃዎች ዕቃዎች LCD የፎቶ ኮፒ ማሽን ፍሪጅ ፤ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር በተለያዩ ክፍሎች ያለምንም እርምጃ የሚገኙ መሆኑ፤
  - ✓ ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት ሲቀያየሩ ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፤
  - ✓ ብዛት ያላቸው ኮንቴይነሮች በሙሉ በቁልፍ የተቆለፉ ባለቤቶቻቸው (የሚጠቀምባቸው ማን እንደሆነ) በትክክል የማይታወቅ መሆኑ፤
- የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የዩኒቨርስቲው የንብረት አስተዳደር ሲታይ፣-
  - ✓ የዕቃ ወጪ መጠየቂያ (ሞ/20) ሳይቀርብና በኃላፊዎች ሳይፈቀድ ብር 7,482,518.45 ዋጋ ያላቸው ንብረቶች ወጪ የተደረጉ መሆኑ፣

- ✓ ብር 418,091.04 ዋጋ ያላቸው ንብረቶች በኃላፊዎች ከተፈቀደው በላይ ተጨምረው ወጪ የተደረጉ መሆኑ፤
- ✓ በተደለዙና በተፈቀደው ላይ ቁጥር በመጨመር በድምሩ ብር 695,100.80 ዋጋ ያላቸው ንብረቶች ወጪ የተደረጉ መሆኑ፤
- ✓ የቋሚ ንብረት ምዝገባ የተጀመረው አስቀድሞ የነበረው ከወጪ ቀሪ መነሻ ሳይዝ በቀጥታ ከጥቅምት/2006 ጀምሮ ገቢና ወጪ ምዝገባ እየተከናወነ መሆኑ፤

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ የንብረት አስተዳደር ሲታይ፣-
  - ✓ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የዕቃ ምዝገባና የግምጃ ቤት ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት ሲቀያየሩ ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ሳይረጋገጥ ርክክብ የሚያደርጉ መሆኑ፣
  - ✓ የተለያዩ ያገለገሉ ዕቃዎችን በማሰባሰብ በደንቡ መሠረት እርምጃ አለመወሰዱ፡
  - ✓ ከትምህርት ሚ/ር የተላኩ የተለያዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት በሳጥን ታሽገው መገኘታቸው፣
- የመቱ ዩኒቨርስቲ የንብረት አስተዳደር ሲታይ፣-
  - ✓ ለቋሚ ንብረቶች የመለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- ወሎ ዩኒቨርስቲ፤በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ የንብረት ግምጃ ቤት የሚገኙ አላቂና ቋሚ ዕቃዎች ፤ከዋናው የዕቃ ክምችት መጋዘን ወጪ ሆነው ወደ ሚኒ ዕቃ ግ/ቤት ገቢ የተደረጉ የምግብ ጥሬ እቃዎች፤
- ወሎ ዩኒቨርስቲ፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ከዋናው የመድኃኒት ስቶር ወጪ ሆኖ ወደ መድሃኒት ስርጭት ክፍል የገባ መድሃኒት አገልግሎት ላይ ለመዋላቸው የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤
- **ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ**
  - ✓ የተማሪዎች ክሊኒክ የመድሃኒት መጠበቂያ ሚኒ ስቶር ገቢ የሚደረጉ እንዲሁም ከሚኒስቶር ወጪ የሚደረጉ መድሃኒቶች ገቢና ወጪ ስለማይመዘገብ ከወጪ ቀሪው የማይገናዘብ

መሆኑ፤የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች በዋናው ግቢ፤ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ፤ በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፤ በሕግና መሬት አስተዳደር የሚገኙ ሲሆን በደንቡ መደረት እንዲወገዱ አለመደረጉ፡

- **ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ** ፣ የሠመራ ዩኒቨርስቲ የሚገለገልባቸው የመኖሪያና መኖሪያ ያልሆኑ ሕንጻዎች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች በቋሚ የንብረት መዝገብ ያልተመዘገቡ መሆኑ፤
- **ጎንደር ዩኒቨርስቲ፡-**
  - ✓ በድምሩ ብር 74,490.00 የሚያወጡ ላፕቶፖች መምህራኑ ከዩኒቨርሲቲው ንብረቱን የወሰዱ ቢሆንም ንብረቱን ተመላሽ ሳያደርጉ በግል ፈቃዳቸው ከስራ የለቀቁ መሆኑን፤
  - ✓ በነዳጅ ማከማቻ ዴፖ ገቢ ሆኖ ለተሽከርካሪዎች የሚታደለው ነዳጅ እና ለጀኔረተር የሚውለው ነዳጅ ላይ አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋቱ፤
- **ሰመራ ዩኒቨርስቲ፡**
  - ✓ አቶ ኢሳያስ ገ/ማሪያም ኮምፒተሮች ብዛት 103 ኤል ሲ ዲ ፕሮጀክተሮች 2 እና ሌሎች ለኮምፒተር ሳይንስ ትምህርት ለማስተማር የሚያገለግሉ ንብረቶች ሳያስረክብ ከስራ ቦታ የጠፉ መሆኑ፣
  - ✓ በ2006 የበጀት ዓመት ከአካዳሚክ ሰራተኞች ብዛት 38 ከድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች 43 በድምሩ 81 ሰራተኞች ከስራ ገበታቸው መልቀቂያ ሳይወስዱ የጠፉ ሲሆን ያላስረከቡትን ንብረት ለመኖሩ ተጣርቶ እንዲያስረክቡ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፣
  - ✓ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በቀን 29/08/06 በብር 3,338,000.00 የተገዙ በቁጥር 4 (አራት) የዳቦ መጋገሪያ ማሽኖች አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን የኦዲት ቅኝትና የመስክ ስራ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት እንዲሁም ማሽኖቹን ከሚገለገሉበት ሠራተኞች

በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ መቻሉን በተጨማሪም የዳቦ መጋገሪያ ማሽኖቹ ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ አገልግሎት አለመስጠታቸው፤

- ✓ 2 የእቃ ማጠቢያ ማሽኖች እና በተቋሙ የተገዙ 2 የጤፍ መፍጫ ወፍጮዎች ሁለት ጀነሬተሮች አገልግሎት ባለመስጠታቸው ምክንያት ተቋሙ ለአላስፈለጊ ወጪ መዳረጉ፤

- **ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ፡-**

በቋሚ እቃ ስቶር ክፍል የተለያዩ ለኢንጅነሪንግ አገልግሎት የሚውሉ አዳዲስ እቃዎች ከሁለት ዓመት በላይ የተቀመጡ እና ለተጠቃሚው አካል ያልተሰጡ ዕቃዎች መኖራቸው፣

- ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ፡-
  - ✓ በተማሪዎች የመመገቢያ ክፍል ውስጥ አንድ ትልቅ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን እና ትልቅ ሁለት ፍሪጅ ያለምንም አገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
  - ✓ በምግብ ጥሬ ዕቃዎች ግ/ቤት ውስጥ ከጥቅም ውጭ የሆኑ 24 ኬሻ መኮረኒ፣ 30 ኪ.ግ ፓስታ እና 279 ኪ.ግ አተር ክክ እንዲወገዱ አለመደረጉ፣ በተጨማሪም 19.5 ኩንታል አገልግሎት መስጠት የሚችል ጎመንዘር ከአንድ ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጠ መሆኑ፣
  - ✓ ከዋናው የመድኃኒት ማከማቻ ክፍል ወጪ ሆኖ ወደ መድሃኒት ስርጭት ክፍል የገባው መድሃኒት በመድኃኒት ማዘዣ/ፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ለታካሚው የሚሰጥ ቢሆንም ወደ መድሃኒት ስርጭት ክፍል የገባው መድሃኒት ብዛትና ዓይነት በመድኃኒት ማዘዣ ፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ላይ ከተጻፈው መድኃኒት ጋር እየተመሳከረ ከወጪ ቀሪ የሚረጋገጥበት ስርዓት አለመኖሩ፣

- **ወልድያ ዩኒቨርስቲ፡-**
  - ✓ ዩኒቨርስቲው የሚገለገልባቸው ሕንጻዎች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች በቋሚ የንብረት መዝገብ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
  - ✓ የተለያየ ዓይነትና መጠን ያላቸው ንብረቶች በዩኒቨርሲቲው መጋዘንና ግቢ ያለአገልግሎት ተከማችተው መገኘታቸው፤
  - ✓ ልዩ ጠቀሜታ ያላቸው ለሳይንስ ላቦራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች ካላቸው የተፈጥሮ ባሕርይ የተለየ ቦታ መቀመጥ ሲገባቸው በባህርይ ከማይገናኙ ከቋሚ ንብረቶች ጋር በአንድ ላይ በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ መሆኑ፤
  - ✓ ከማዕከላዊ ዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ ሆነው በሚገኙት የተማሪዎች ክሊኒክ ሚኒ ስቶር ገቢና ወጪ የሚደረጉ መድሃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤
  - ✓ ከፍተኛ ዋጋና ብዛት ያላቸው መጽሐፍት ለብልሽት በሚያጋልጥ /በሚዳርግ/ ሁኔታ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- **ዲላ ዩኒቨርስቲ**
  - ✓ በአላቂ ግምጃ ቤት የተለያዩና ብዛት ያለቸው የጽህፈት መሳሪያዎች በግምጃ ቤት ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
  - ✓ ለሰራተኞች ደንብ ልብስ የሚሆን ሸሚዝ ከ2005 በጀት ዓመት ጀምሮ ብዛት 397 የአንዱ ዋጋ ብር 230.00 ጠቅላላ ሂሰብ ብር 91,310.00 የሆነ ያለአገልግሎት የተቀመጠ መሆኑ፣
  - ✓ የመጠቀሚያ ግዜአቸው ያለፈ በርካታ መድሃኒቶች እና የተለያዩ የላብራቶሪ ኬሚካሎች እንዲወገዱ አለመደረጉ፡ በተጨማሪም የመጠቀሚያ ጊዜአቸው የተላለፈ መድሃኒቶች ሳይለዩ አገልግሎት ከሚሰጡ መድሃኒቶች ጋር አንድ ላይ የሚቀመጡ መሆኑ፤
  - ✓ የንብረት ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

- ✓ ሁለት የሆስፒታሉ የልብስ ማጠቢያ ማሽን ማጠቢያዉም መጭመቂያዉም የተበላሸ በመሆኑ ሰራተኞች የህሙማን ቢጃማ፣ አንሶላ፣ ብርድልብስ እና የመሳሰሉት በእጅ የሚያጥቡ መሆኑ፣
- ✓ ተመላሽ የተደረጉ ያገለገሉ ንብረቶች እንዲወገዱ አለመደረጉ፤

- **ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ፡-**
  - ✓ በአቶ ዳግም ተስፋዬ ስም ወጪ ሆኖ ብር 49,750.00 ዋጋ ያለው Vedio Camera በቆጠራ አለመገኘቱ፤
  - ✓ አቶ ግዛው ከበደ የተባሉት ሰራተኛ ለስራ የወሰዱት አንድ ላፕ ቶፕ እና external hard disk ተመላሽ ሳያደርጉ ዩኒቨርስቲውን የለቀቁ መሆኑ፣
  - ✓ የንብረት መከታተያ ስቶክ ካርድ አያያዝ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
  - ✓ በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች ዓመታዊ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የንብረት ምዝገባ ስለማይከናወን በቆጠራ የተገኘውን ዕቃ ከምዝገባ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱ የሚረጋገጥበት አሰራር ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
  - ✓ ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ የተለያየ መጠን ያላቸው በርካታ የአርማታ ብረቶች ለጥበቃ አመች ባልሆነ ሁኔታ የተቀመጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ የኦዲት ቅኝት በተደረገበት ወቅት ለጥበቃ የተመደቡ ሰራተኞችን ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ እና ዩኒቨርሲቲው የግቢ አጥር እንደሌለው ለመገንዘብ የተቻለ መሆኑ፣
  - ✓ በትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ዋጋ ተገዝተው የቀረቡና ለምግብ ቤት የሚያገለግሉ የተለያዩ የማብሰያ ቋሚ ዕቃዎች የኤሌክትሪክ ምድጃዎች፣ ፍሪጆች እና የሻይ ማፍያ ማሽኖች የተተከሉ ቢሆንም አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፣በምግብ

ማብሰያ ቤት ውስጥ ብዛት ሁለት ትልቅ WestPoint ፍሪጅ በ2004 ዓ.ም የተገዛ ተበላሽቶ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣

- ✓ የምግብ ማብሰያ ህንፃ ፍሳሽ ማስወገጃ በአግባቡ የማይሰራ በመሆኑ ፍሳሹ በመከማቸቱ በምግብ ቤቱ አካባቢ በጤንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መጥፎ ጠረንና ሽታ የተፈጠረ መሆኑ፣
- ✓ በአላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ለሽንት ቤት ንጽህና መጠበቂያ ፍላግ ብዛት 2712 እና በረኪና ብዛት 2020 ተከማችቶ የሚገኝ ቢሆንም አገልግሎት ላይ እየዋለ አለመሆኑ፤
- ✓ መፅሀፍት ግምጃ ቤት በቂ የሆነ የመፅሀፍት መደርደሪያ የሌለው ከመሆኑ በተጨማሪ የክፍሉ መስኮቶች ዝናብ የሚያስገባ በመሆኑ መፅሀፍት ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ በክፍሉ ወለል ላይ የተቀመጡ መሆናቸው፣
- ✓ በቤተ-መፅሀፍት ግምጃ ቤት ውስጥ በሶፍት ኮፒ በርካታ መፅሀፍት ያሉ ሲሆን ነገር ግን በቂ የሆነ ማባዣ ማሽን/duplication machine/ የሌለ በመሆኑ መፅሀፍቶችን በበቂ ሁኔታ አባዝቶ ለተጠቃሚ ማድረስ ያልተቻለ መሆኑ፣
- ✓ የመፅሀፍት ግምጃ ቤት የሆነ ክፍል መስኮቶች ዝናብ የሚያስገባ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲው መፅሀፍት ወደ ግምጃ ቤቱ በሚገባ ፍሳሽ ለብልሽት የተጋለጡ መሆኑ፣

- **ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ፡-**
  - ✓ በዋናው ግቢ፤ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ግብርና ኮሌጅ በተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የተከማቹ በርካታ ያገለገሉ ንብረቶ እንዲወገዱ አለመደረጉ፡
  - ✓ ዩኒቨርስቲው የሚገለገልባቸው ሕንጻዎች በቋሚ የንብረት መዝገብ ያልተመዘገቡ መሆኑ፡

- ✓ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም በመዝገብ ከተመለከተው ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱ የማይረጋገጥ መሆኑ፤

<u>አክሱም ዩኒቨርሲቲ</u>

- ✓ መድሃኒቶች በተገቢው ማስቀመጫ እንዲቀመጡ ባለመደረጋቸው ለብልሽት መዳረጋቸውን፤
- ✓ በመድሃኒት ግምጃ ቤት የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱ እና መወገድ የሚገባቸው መድሃኒቶች እንዲወገዱ ባለመደረጋቸው ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ተከማችተው መገኘታቸውን፤
- ✓ ከፍተኛ ዋጋ እና የተለያየ መጠን ያላቸው የአርማታ ብረቶች እና የፕላሰቲክ ቱቦዎች በመስክ ላይ ተጥለው የሚገኙ መሆኑን፤
- ✓ ዩኒቨርሲቲው የተደራጀ የንብረት መጋዘን የሌለው እና አያያዛቸውም የተቀናጀ ባለመሆኑ ንብረቶቹ በየኮሌጁ እና በየማዕከላቱ ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ በሽሬ ካምፓስ ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸውና ምዝገባም ያልተከናወነ መሆኑ፤ ከወተት ሽያጭ የሚገኘው ገቢ በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ የማይካተት እና የምርቱን መጠን የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ አለመኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

- <u>መቐለ ዩኒቨርስቲ</u>
  - ✓ በዋናው ግቢ የተማሪዎች ምግብ ቤት ንብረት ክፍል መወገድ ያለባቸው ማቀዝቀዣዎች፤ የወጥ ገለባጭ ማሽኖች፤ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች እና የውሃ ማሞቂያዎች እንዲቀመጡ መደረጉን፤
  - ✓ በሃይደር ሪፈራል ሆስፒታል የማያገለግሉ ብዛት ያላቸው አሮጌ የሆስፒታል አልጋዎች፤ወንበሮች የአካል ጉዳተኞች ወንበሮች፤ የውሃ ማሞቂያ ማሽኖች ፤የወጥ መገልበጫ ማሽኖች እና

የኤሌክትሪክ ምድጃዎች ባለመወገዳቸውና በመስክ ላይ በመጣላቸው ለበለጠ ብልሽት በመዳረግ ላይ መሆናቸውን፤

- ✓ መወገድ የሚገባቸው አሮጌ የመኪና ጎማዎች፤እና ኮምፒዩተሮች፤ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ ብዛት ያላቸው የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች እና ቁርጥራጭ ብረቶች ለብዙ ጊዜ ተከማችተው ከመገኘታቸው በተጨማሪ የአካባቢ ብክለትን እያስከተሉ መሆኑን፣ በተጨማሪም በሃይደር ሪፈራል ሆስፒታል በመድሃኒት ንብረት ክፍል እና በተማሪዎች ክሊኒክ ብዛት ያላቸው የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ መድሃኒቶች መገኘታቸውን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡፡

አዴግራት ዩኒቨርሲቲ

የመኪና ጎማዎች እና የሴቶች አልባሳት በንብረት ክፍል አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲቀመጡ መደረጉን እና የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ የተለያየ መጠን ያላቸው የተሽከርካሪ ጎማዎች እና የመኪና ባትሪዎች እንዲሁም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ መድሃኒቶች እንዲወገዱ ባለመደረጉ በንብረት ክፍል ተከማችተው መገኘታቸውን፣

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ

- ✓ በ2004 በጀት ዓመት ተገዝተው በግምጃ ቤት የተቀመጡ የዳቦ መጋገሪያ ማሽኖች ፍሪጆች የሊጥ ማቡኪያ ማሽኖች እና የማፍያ ማሽኖች አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲቀመጡ መደረጉን፡
- ✓ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ በበጀት አመቱ መጨረሻ አለመደረጉን፤ እና የመለያ ቁጥር አለመሰጠቱን፣ በተጨማሪም ፋይል ካቢኔቶች፤ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች እና የቡና ጠረጴዛዎች አገልግሎት ሳይሰጡ በግምጃ ቤት ተከማችተው መገኘታቸውን፤

በመገናኛና ኢንፎርሚሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

- ✓ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ዕቃዎች በወቅቱ ለመ/ቤቱ አገልግሎት እንዲውሉ ባለመደረጋቸው ከ2003 ዓ.ም በፊት ጀምሮ

አቃቂ በሚገኘው መጋዘን ውስጥ አዳዲስ ፣ አገልግሎት የሚሰጡ እና ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የተለያዩ አይነት ቋሚ ዕቃዎች ተቀላቅለው በአንድ መጋዘን መገኘታቸውን፤

- ✓ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ከፍተኛ ዋጋ እና ብዛት ያላቸው አዳዲስ ወንበሮች፤ ጎማዎች፤ጠረጴዛዎች፤ የኮምፒዩተር እና የቢሮ ጠረጴዛዎች አገልግሎት ከማይሰጡ ንብረቶች ጋር ተቀላቅለው ለብልሽት በመጋለጥ ላይ የሚገኙ መሆኑን፤

<u>በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ</u>

- ✓ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ፤ጠረጴዛዎች፣ የመጽሃፍ ማስቀመጫ ቁምሳጥኖች ፣ ሳህኖች፣ የቡና ማቅረቢያ ጠረጴዛዎች፣ የአልጋ ብረቶች፣ 1 የብረት ቁምሳጥን፣ አልጋዎች፣ ኤጋ ቆርቆሮዎች፣ ሶፋ ወንበሮች እንዲሁም 378 ኮሜዲኖዎች ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ መደረጉን ለማየት ተችሏል፡፡

<u>ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር</u>

<u>የንብረት አያያዝ ድክመቶች</u>

በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፡-

<u>ዋና ግቢ (Main campus)፤</u>

- ✓ በተጠቃሚዎች እጅ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ የሌለ መሆኑ፣
- ✓ ከሰራተኞች የተረፉ የቆዳ ጫማዎችና ቦቲዎች ያለ አገልግሎት መጋዘን ውስጥ መቀመጣቸው፣

<u>አሰላ ግብርና ት/ቤት፣</u>

- ✓ በተጠቃሚዎች እጅ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ የሌለ መሆኑን፣
- ✓ ከሰራተኞች የተረፉ የሴት ቆዳ ጫማዎች፣ ቦቲዎች፣ አሮጌ ብርድ ልብሶች፣ ብዛት ያላቸው ሸሚዞች፣ የሴት ቀሚስ እና የውስጥ ልብስ

ጨርቆች እና ቁርጥራጭ ነጭ የጋዎን ጨርቆች ያለ አገልግሎት ለብዙ አመት መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣

- ✓ በዋና መጋዘን አካባቢ የወዳደቁ የተሰባበሩ ወንበሮች እና የምግብ ጠረጴዛዎች፣ የከብቶች ሚዛኖች እና የማይሰሩ ጎማዎች በሜዳ ላይ ተጥለው ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣
- ✓ አላቂ ንብረት ገቢና ወጪ የሚያርግ ሰራተኛ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችና የመኪና መለዋወጫ እቃዎችን ገቢና ወጪ ሥራ ደርበው እንዲሰሩ በመደረጋቸው ንብረቶችን ለመከታተልና ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ሁኔታ መፈጠሩ፣
- ✓ በተመላሽ የዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸው የተለያዩ መፅሔቶች እና ጋዜጦች፣ የማይሰሩ የመኪና መለዋወጫ እቃዎችና ባትሪዎች፣ የናይትሮጅን መያዣ ኮንቴይነር፣ አሮጌ የተማሪዎች ትራስ እና ብርድ ልብሶች፣ የተሰባበሩ ወንበሮች ፣ ጠረጴዛዎች እና አልጋዎች፣ የተበላሹ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ታይፕሪይተሮች፣ የወረቀት ማባዣ /ጀስትነር/ መሽን፣ የማይሰሩ ፍሪጆች፣ ፎቶኮፒ ማሽኖች ጊዜ ያለፈባቸው የፊልም ፕሮጀክተሮች፣ የተበላሸ ጀነሬተር ሳይወገዱ ለረዥም ጊዜ መቆየታቸው፣
- ✓ በቁጥር 26 የከብት ሚዛኖች፣ 8 ሴንተር ፓንች፣ 14 ማጭዶች፣ 8 ስክሩ ድራይቨር፣ 8 መዶሻ፣ 27 መሮዎች ፣ ከፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር የመጡ 3 የእህል መውቂያ መሳሪያዎች፣ 1 በቆሎ መፈልፈያ ማሽን፣ ብዛት ያላቸው አካፋዎች፣ መኮትኮቻዎች፣ በእርዳታ የመጡ 32 አዳዲስ የአረም መርጫ መሳሪያዎች ካለአገልግሎት መጋዘን ውስጥ ለብዙ ጊዜ መቆየታቸው፣
- ✓ በቁጥር 23 የመኝታ አልጋዎች፣ 3 ኮምፒተሮች እና 2 የፎቶኮፒ መሽኖች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እየቻሉ በትንሽ ብልሽት ለረጅም ጊዜ ሳይጠገኑ ተመላሽ የዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ መቀመጣቸው፣

<u>አሰላ ጤና ሳይንስ ት/ቤት፣</u>

- ✓ በተጠቃሚዎች እጅ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች የመቆጣጠሪ ካርድ የሌለ መሆኑ፣
- ✓ በመጋዘን አካባቢ የወዳደቁና የተሰባበሩ የህሙማን ተሽከርካሪ አልጋዎች፣ የኤክስሬይ መሽኖች፣ ስቶቭ፣ ፊሪጅ፣ ወንበሮች እና የማይሰሩ ጎማዎች በሜዳ ላይ ተጥለው ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣
- ✓ ከጀርመን ሀገር በእርዳታ የተገኙ በርካታ የታሸጉ የህክምና እቃዎች በቋሚ ንብረት መጋዘን ውስጥ ያለ ሥራ መቀመጣቸው፣
- ✓ በቋሚ ዕቃዎች መጋዘን ውሰጥ የሚሰሩና የማይሰሩ ቋሚ ንብረቶች በአንድ ላይ ተቀላቅለው መገኘታቸው፣ እንዲሁም የጀርም ማፅጂያ /አውቶክላቭ/ መሳሪያና የማዋለጃ አልጋዎች ካለአገልግሎት መቀመጣቸው፣
- ✓ 2 የልብስ ማጠቢያ መሽን እና 1 የልብስ መጭመቂያ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እየቻሉ ለረጅም ጊዜ ሳይጠገኑ በልብስ ማጠቢያና ማድረቂያ ክፍል ተቀምጠው መገኘታቸው፣ በዚህም ምክንያት አብዛኛው ስራ የሚሰራው በእጅ መሆኑ፣

በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ፣

- ✓ ብዛታቸዉ 4 የሆኑ አክራ ቴሌቪዥኖች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እየቻሉ ሳይጠገኑ ለረጅም ጊዜ በንብረት ክፍል መጋዘን ውስጥ መቀመጣቸው፣
- ✓ ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም በመዝገብ ከታየው ምዝገባ ጋር እየተመሳከረ ስለትክክለኝነቱ የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- ✓ በተማሪዎች እህል መጋዘን አካባቢ የወዳደቁና የተሰባበሩ ወንበሮች እና የእቃ ጋሪዎች፣ እንዲሁም በመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች መጋዘን አካባቢ በርካታ አሮጌ የመኪና ጎማዎች፣ አሮጌ ወንበሮች፣ የብረት ካብኔቶች፣ የውሀ ፕላስቲክ ጎማዎች፣ የብረት መቁረጫ መሳሪያ፣

የጣሪያ ቆርቆሮዎችና የመኪና ባትሪዎች በሜዳ ላይ ተከማችተው ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣

- ✓ በቋሚ ዕቃዎች መጋዘን ውስጥ የሚሰሩና የማይሰሩ ቋሚ ንብረቶች በአንድ ላይ ተቀላቅለው መገኘታቸው፣ ከነዚህም ውስጥ የማያገለግሉ ብዛታቸው 49 የሆነ የኮምፒውተር CPU፣ 26 አሴር ኮምፒውተሮች፣ ብዛታቸዉ 13 የሆነ ፕሪንተሮች፣ 2 ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ብዛታቸው 2 የሆነ ፋክስ ማሽን፣ 1 ኪቦርድ በአንድ ላይ መቀመጣቸው፣
- ✓ አብዛኞቹ አላቂ ዕቃዎች ቢን ካርድ የሌላቸውና ከወጪ ቀሪያቸው በጊዜ የማይሰራ መሆኑ ፣
- ✓ በመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች መጋዘን ውስጥ የማያገለግሉና የሚያገልግሉ ዕቃዎች አንድ ላይ መቀመጣቸው እና ቢን ካርድም የሌላቸው መሆኑ፣
- ✓ ረጅም ጊዜ የቆዩ አሮጌ ፍራሾች ሳይወገዱ መጋዘን ውስጥ መቀመጣቸው፣
- ✓ የተማሪዎች ምግብ መስሪያ ክፍል ውስጥ አራት የሚሆኑ የምግብ ማብሰያ ስቶቮች ከ1999 ጀምሮ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው እንዲሁም መጠገን የሚችሉ የኤሌትሪክ ምጣዶች ሳይጠገኑ ተከማችተው የተቀመጡ ሲሆን የምግብ ቤት ሰራተኞች ምግብ ሚያበስሉት ግን በባህላዊ ዘዴ መሆኑ፣
- ✓ የአላቂና የቋሚ ንብረት መጋዘኖች ቀደም ሲል ማዕድ ቤት የነበሩና ጠባብ ከመሆናቸው የተነሳ ንብረቶች ተደራርብውና የተወሰኑ ንብረቶች በማዳበሪያ ውስጥ ታጭቀው መሬት ላይ መቀመጣቸው፣

<u>በተማሪዎች ክሊኒክ፣</u>

- ✓ በመድሀኒት ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ ለሚገኙት መድሀኒቶች እስቶክ ካርድ ለኦዲት ተጠይቆ ባለመቅረቡ የመድሃኒት ባላንስ ትክክለኛነትን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- ✓ በግዥ ወይም በእርዳታ ተገኝተው ወደ መድሃኒት መጠበቂያ ክፍል /ስቶር/ ገቢ የሚደረጉ እና ከክፍሉ ወደ ህክምና መስጫ /Dispensary Room/ ክፍል የሚተላለፉ መድሃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ቢኖራቸውም ምዝገባው የተሟላ ባለመሆኑ ባላንሱን የማያሳይ መሆኑ፣ በመድሀኒት መጠበቂያ ግምጃ ቤት እና በህክምና መስጫ ክፍል /Dispensary Room/ የሚገኙት መድሀኒቶች በአይነታቸው ተለይተው የማይቀመጡ እና የመድሃኒት መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ የማይጠቀሙ መሆኑ፣
- ✓ በመድሃኒት መጠበቂያ ግምጃ ቤት እና በህክምና መስጫ ክፍል የሚገኙ መድሀኒቶች በአመት አንድ ጊዜ እንኳ ቆጠራ ተደርጎ ያልተመዛዘኑ መሆኑ፣
- ✓ የመድሀኒት መጠበቂያ (እስቶር) እና የመድሀኒት ማሰራጫ መግቢያው በር አንድ በመሆኑ ንብረት በቀላሉ እንዲጠፉ የሚጋብዝ መሆኑ፣
- ✓ የመድሀኒት መጠበቂያው እስቶር ጠባብ በመሆኑ መድሀኒቶች በካርቶን እንደታሸጉ በወለሉ ላይ በመቀመጣቸው በእጥበት በቀላሉ ለብልሽት እየጋለጡ መሆኑ፣

በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ፡-

- ✓ ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም በመዝገብ ከሚመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከርና ትክክለኝነቱ የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- ✓ በሚወገዱ ንብረት መጋዘን አካባቢ የወዳደቁ ሊጠገኑ የሚችሉ የተሰባበሩ ወንበሮች፣ አልጋዎች፣ የብረት መደርደሪያዎች እና የማይሰሩ የመኪና ጎማዎች በተጨማሪም በዋና የእህል መጋዘን አካባቢ የተማሪ ሎከሮች /መደርደሪያዎች/ በሜዳ ላይ ተጥለው ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣

- ✓ በቋሚ ዕቃዎች መጋዘን ውስጥ የሚሰሩና የማይሰሩ ቋሚ ንብረቶች በአንድ ላይ ተቀላቅለው መቀመጣቸው፣ ከነዚህም ውስጥ የማያገለግሉ በእርዳታ የተገኙ የመለዋወጫ እቃዎች የጎደላቸው 2 ሳይክሎች እና10 ጥገና የሚያስፈልጋቸው አሰር ኮሚፒተሮች በአንድ ላይ መገኘታቸው፣
- ✓ ለአላቂ ዕቃዎች ቢን ካርድ የማይጠቀሙ መሆኑ ፣
- ✓ በአላቂ ዕቃዎች መጋዘን ውስጥ የመኪናዎች መለዋወጫ እቃዎች፣ አንድ የማይሰራ ፕሪንተር፣ የመኪና ጎማዎች አንድ ላይ ተቀላቅለው መገኘታቸው፡፡
- ✓ በአላቂ እቃዎች መጋዘን ውስጥ ንብረት የሚጠብቀው እና ሞዴል 19 እንዲሁም ሞዴል 22 በአንድ ሰራተኛ የሚሰራ መሆኑ፣
- ✓ በቋሚ እቃዎች መጋዘን ውስጥ ንብረት የሚጠብቀው እና ሞዴል 19 እንዲሁም ሞዴል 22 በአንድ ሰራተኛ የሚሰራ መሆኑ፣
- ✓ በቋሚ እቃዎች መጋዘን ውስጥ በቁጥር 3 የሚሆኑ ቴፒሪከርደሮች ፣ 1 ፕሮጀክተር እና 14 ወንበሮች በ2005 ዓ.ም ገቢ የተደረጉ ቢሆንም ያለጥቅም የተቀመጡ መሆኑ፣
- ✓ በቋሚ እቃዎች መጋዘን ውስጥ አብዛኛው ንብረት በተስተካከለ መልኩ ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- ✓ ያገለገሉ ዕቃዎች የሚቀመጥበት መጋዘን ውስጥ ጥቅም መስጠት የሚችሉ ብዛታቸው 28 የሆኑ ስቴፕለሮች፣ 4 የመኪና ባትሪዎች፣ 4 የወረቀት መብሻ እና በርካታ የበር እጀታዎች ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- ✓ በዋና ምግብ መጋዘን ውስጥ የፅዳት ዕቃዎች እና ኬሚካሎች /ሳሙና፣ በረኪናዎች/ መገኘታቸው፣
- ✓ በዋና ምግብ መጋዘን ውስጥ በ2006 ዓ.ም የተገዛ 69 ኩንታል ጨው በመቅለጥ እና በብልሽት ላይ መሆኑ፣

- ✓ በርካታ ቁጥር ያላቸው የምግብ ዘይት ጀሪካኖች ያለጥቅም መለስተኛ መጋዘኑን እያጣበቡ መሆኑ፣
- ✓ በተማሪዎች የመመገቢያ አደራሽ አካባቢ በርካታ መጠገን የሚችሉ የተሰባበሩ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች መሬት ላይ ተጥለው መገኘታቸው፣
- ✓ በምግብ ማብሰያ ክፍል እና መለስተኛ መጋዘን (ሚኒስቶር ክፍል) ውስጥ ስምንት ኩንታል የአተር ክክ ከጥቅም ውጭ ሆኖ መገኘቱ፣
- ✓ ብዛታቸዉ 10 የሆኑ ትልቁ ስቴፐለር፣ 4 የውሃ ቧንባ መክፈቻዎች፣ 70 የኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያ /ስታብላይዘር/፣ 7 የብረት በሮች እና 8 የእቃ ጋሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እየቻሉ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ሳይጠገኑ ያገለገሉ በዕቃዎች መቀመጫ መጋዘን ውስጥ ተቀምጠው መገኘታቸው፣
- ✓ ብዛት ያላቸው የብረት መደርደሪያዎች፣ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያዎች፣ 2 የውሃ በርሜሎች፣ 1 የውሀ ማጠራቀሚያ /ሮቶ/፣ 10 የኤሌክትሪክ ምጣዶች፣ 2 ጠረጴዛዎች፣ 4 ወንበሮች፣ 3 ኮምፒውተሮች፣ 200 የሆኑ ጎማዎች ሳይወገዱ ያገለገሉ ዕቃዎች በሚቀመጥበት መጋዘን ውስጥ መገኘታቸው፣

<u>የተማሪዎች ክሊኒክ፣</u>

- ✓ በመድሀኒት መጠበቂያ (እስቶር) ውስጥ እስቶክ ካርድ፣ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 በንብረት ተረካቢው /ጠባቂው/ የሚሞሉና የሚያዙ መሆኑ፣
- ✓ በመድሀኒት መጠበቂያ ግምጃ ቤት እና በህክምና መስጫ ክፍል /Dispensary Room/ የሚገኙት መድሀኒቶች በመደርደሪያቸው ላይ የመድሀኒቱ ዓይነት በሼልፍ ላይ ሌብል አለመለጠፉ፣
- ✓ በመድሃኒት መጠበቂያ ግምጃ ቤት እና በህክምና መስጫ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ መድሀኒቶች ቆጠራ ቢደረግም የማይመዛዘን መሆኑ፡

- ✓ በህክምና መስጫ ክፍል /Dispensary Room/ ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸው መዳኒቶች መገኘታቸው፣

በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ፣

- ✓ የቋሚ ንብረት መዝገብ የሌለ፤ ቆጠራ የማይደረግ፣ ለተጠቃሚ ሲሰጥ የትውስት ፎርም የማይሞላ እና የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- ✓ የአላቂ እቃ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ የማይሰራባቸው መሆኑ፣ የንብረት የገቢና ወጪ ማመዛዘኛ የማይሰራ መሆኑ፣
- ✓ አዲስ ተገዝተው አገልግሎት ላይ ያልዋሉ፣ አሮጌ ሆነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ እንዲሁም የሚወገዱ ቋሚ ንብረቶች ንብረት ክፍል አንድ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ✓ መወገድ ያለባቸው በርካታ የተለያዩ ንብረቶች ያልተወገዱ መሆኑ፣
- ✓ በቁጥር 175 አዲስ የተማሪ መኝታ (አልጋ) ሜዳ ላይ ተበታትኖ ዝናብና ፀሐይ እየተፈራረቀበት መሆኑ፣
- ✓ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ በርካታ የተለያዩ ንብረቶች ጥገና ያልተደረገላቸውና አገልግሎት እንዲሰጡ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ ለግንባታዎች የሚውል የአርማታ ብረት የተቀመጠበት ቦታ ለጥበቃ ምቹ ያልሆነ አጥር የሌለው መሆኑ፣
- ✓ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- ✓ በኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ከአገልግሎት ዉጭ የሆኑና መወገድ ያለባቸው ንብረቶች በንብረት ክፍል ዉስጥ መቀመጣቸው፣
- ✓ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል በአገልግሎት ላይ ለሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር አለመሰጠቱ፣

በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር፡-

- ✓ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የቋሚና የአላቂ ዕቃ ቆጠራ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተከናወነ ቢሆንም የንብረት ማመዛዘኛ ያልተሠራ መሆኑ፣

- ✓ አገልግሎት መስጠት እየቻሉ ያለ አገልግሎት የተቀመጡ እና መወገድ ሲገባቸው ያልተወገዱ በርካታ ንብረቶች መኖራቸው፣

9.14. <u>የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም፣</u>

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ 8 ተሽከርካሪዎች በጥገና ምክንያት የቆሙና የማይሰሩ መሆኑ፣
- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅት በእርዳታ የተሰጡ ሁለት አምቡላንሶች እና 8 ተሽከርካሪዎች ሰሌዳ ቁጥራቸው ደህ(ደቡብ ህዝቦች) በሚል የሚንቀሳቀሱ መሆኑን፣ የአንዱ አምቡላንስ ቁልፍ ለኮሌጁ ያልተሰጠ እና ሁለት የሞተር ብስክሌቶች የሰሌዳ ቁጥራቸው አርባ ምንጭ በሚል የሚንቀሳቀሱ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

- በአክሱም ዩኒቨርሲቲ የትራንስፖርትና ስምሪት ክፍል የተሽከርካሪዎችን ሁኔታ እንዲከታተል ባለመደረጉ በዩኒቨርሲቲዉ ስድስት ተሽከርካሪዎች ለጥገና እንደወጡ ቢገለፅም ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ አለመቻሉን፤ እንዲሁም በመቐለ ዩኒቨርስቲ ከአገልግሎት ወጪ የሆኑ 8 ተሽከርካሪዎች እንዲወገዱ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ሊብሬ ያልቀረበላቸው፣</u>

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ 6 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው፣</u>

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ የህይወት ታሪክ ምዝገባ የሚከናወንበት የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ መረጃዎች ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም</u>

- **ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ**፤- በቁጥር 7 ተሽከርካሪዎችና 3 ትራክተሮች በብልሽት የቆሙ መሆኑ፤
- **ጎንደር ዩኒቨርሲቲ**፤- በቁጥር 15 ተሽከርካሪዎች በብልሽት የቆሙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 9 ተሽከርካሪዎች የውስጥ አካላቸው የሌሉ መሆኑ፤
- **ወሎ ዩኒቨርስቲ፡-** የተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ለተወስኑ መኪናዎች የተዘጋጀ ቢሆንም ለአብዛኛዎቹ ተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ያልተቋቋመ መሆኑን እንዲሁም ለተወስኑ መኪናዎች የተዘጋጀው ማህደርም ቢሆን ተፈላጊ መረጃዎችን በሙሉ አካቶ ያልያዘ መሆኑ፤እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ ብዛት ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ ለሚመለከተው አካል የማይቀርብ መሆኑ፣

ስለሆነም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመነጋገር ከጥቅም ውጭ የሆኑ እንዲወገዱ በቀላል ብልሽት የቆሙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ መፍትሄ እንዲፈለግ አሳስበናል፡፡

- በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፡-
  - ✓ የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ መኪና የህይወት ታሪክ ምዝገባ የማይደረግ መሆኑ፣
  - ✓ 9 ተሽከርካሪ መኪናዎች ጌጅ የሌላቸው በመሆኑ ነዳጅ በግምት የሚቀዳላቸው መሆኑ፣
  - ✓ 7 ተሽከርካሪ መኪናዎች ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፣
  - ✓ 3 ተሽከርካሪ መኪናዎች ሳይጠገኑ አንድ ዓመትና ከዚያ በለይ መቆየታቸው፣

በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ፡-

- ✓ ለመኪናዎች የነዳጅ መቅጃ ኩፖን የማይጠቀሙ እና ነዳጅ ቀጥታ ከማደያ ከተቀዱ በኋላ የተጠራቀመ ሂሳብ ለባለማደያው የሚከፈል መሆኑ፣
- ✓ 3 ተሽከርካሪ መኪናዎች ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፣
- ✓ የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ መኪና የህይወት ታሪክ ምዝገባ የማይደረግ መሆኑ፣
- ✓ በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ 3 ተሽከርካሪ መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ፣
- ✓ በአምቦ ዩኒቨርሲቲ አንድ ተሽከርካሪ መኪና በብልሽት ምክንያት ከአገልግሎት ውጭ መሆኑ፣
- ✓ በኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት አንድ ተሽከርካሪ መኪና በብልሽት ምክንያት ከሁለት ዓመት በላይ የቆመና እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣
- ✓ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል 4 ተሽከርካሪ መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላቸው መሆኑ፣
- ✓ የመንግሥት መ/ቤቶች በኃላፊነታቸው ሥር ያሉትን ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ ዓይነት፣ የሚገኙበትን ሁኔታ የመሳሰሉትን መረጃዎች በማጠናከር የበጀት ዓመቱ እንደተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሪፖርት ማቅረብ እንደሚገባቸው በመመሪያ የታዘዘ ቢሆንም የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የሚጠቀምባቸውን ተሽከርካሪዎች ዝርዝር ሁኔታ ለኤጀንሲው አለማቅረቡ፣

10. <u>የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት፣</u>

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በዋናው ግቢ ከተማሪዎች ምግብ ቤት የሚሰበሰበው ተረፈ ምግብ አያያዝና አወጋገድ በአካባቢ ጥበቃ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- በመደወላቡ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምግብ ማዘጋጃ ወጥ ቤት እጥብጣቢ እና የተማሪዎች ሽንት ቤት የሚወጣው ፍሳሽ ማስወገጃ በአግባቡ ስለማይሰራ በአባቢው መጥፎ ሽታ እያመጣ መሆኑ፣
- በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ እንደ የሽንኩርትና የድንች ልጣጭ ያለና ከተማሪዎች ካፍቴሪያ የሚወጣ ትርፍራፊ ምግብ በመመገቢያ አዳራሽ አቅራቢያ በአግባቡ ባልተሰራ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦይ ውስጥ እየተደፋ በመሆኑ በአካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን እየፈጠረ መሆኑ፣ እንዲሁም የተማሪዎች ካፍቴሪያ የምግብ ማብሰያ አዳራሽ በአግባቡ የማይጸዳ መሆኑና ይህም በተማሪዎችና በሰራተኞች ላይ የጤና ችግር ሊያስከትል እንደሚችል፣

11. <u>ልዩ ልዩ፣</u>

<u>ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፣</u>

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ፣ የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ፣ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ፣ የመቱ ዩኒቨርስቲ፣ የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ እና የጅማ ዩኒቨርስቲ ባለፈው በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ላይ እርምጃ አለመወሰዱ ተረጋግጧል፡፡
- <u>በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ</u> በተሰብሳቢ የተያዘ ብር 2,766,293.08 በስህተት በድጋሚ የተመዘገበ ተብሎ በሀምሌ/2005 ማስተካከያ የተሰራለት መሆኑ በተሰጠው ምላሽ ቢገለጽም ማስረጃው ሊቀርብ አለመቻሉን፣

በልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የ2006 የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የልማትና ማኅበራዊ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ፡በዳይሬክቶሬቱ የታቀዱ 36 መ/ቤቶች ኦዲት የ35መ/ቤቶች (የዕቅዱን 97%) የተከናወነ ሲሆን፣ የግብርና ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት እና በስሩ የሚተዳደሩ፣ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ፣ የአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ የምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት የብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል የቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል እንዲሁም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና በስሩ የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል እና በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት በኦዲቱ ተካተዋል፡፡

በዕቅድ የተያዙት መሥሪያ ቤቶች በሙሉ የኦዲት ሥራቸው ተጠናቆ ለመሥሪያ ቤቶች ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት የተላከ ሲሆን፣ መሥሪያ ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ ሃሣብ መሠረት የወሰዱትን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣ የአማኑኤል ሆስፒታል የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲሁም የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን ምላሽ አልሰጡም፡፡ በዕቅድ ከተያዙት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ሒሳቡን ዘግቶ ለኦዲት ሥራው ባለማቅረቡ ምክንያት እንዲሁም የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ በጊዜ እጥረት ምክንያት የኦዲት ሥራቸው ተቋርጧል፡፡ ሂሳባቸው በግብርና በጤና ጥበቃና በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥር ለሚጠቃለሉ ሰባት ተጠሪ መሥሪያ ቤቶች የመጨረሻው የሥራ አመራር

ሪፖርት ብቻ የተላከላቸው ሲሆን፣ ለቀሪዎቹ ሰላሳ አራት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶች ደግሞ የኦዲት አስተያየቱን የያዘ የኦዲት ሪፖርት እና የመጨረሻው የሥራ አመራር ሪፖርት እንዲላክላቸው ተደርጓል፡፡

2. የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ አስተያየት ለስድስት መሥሪያ ቤቶች ፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት ለአሥራ ሁለት መሥሪያ ቤቶች፣ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት ደግሞ ለአስራ ስድስት መሥሪያ ቤቶች ተሰጥቷቸዋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -2 እስከ 5 ተመልክቷል/

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በዳይሬክቶሬቱ በ2006 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሒሳብ

1.1 በጥሬ ገንዘብና የባንክ ሒሳብ ላይ የታዩ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የተፈጸመ መሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

1.1.1 ግኝት

1. የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ

- ✓ ብር 41,092.10 ዋጋ የያዙ የተለያዩ ቼኮች በሒሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ እና በሌጀር ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፤
- ✓ ከዜድ አካውንት ብር **256,515.06** ዋጋ የያዙ የተለያዩ ቼኮች ተዘጋጅተው በመዝገብና በሌጀር ላይ ተመዝግበው ወደ ሪፖርት

ከተላለፉ በኋላ ቼኮች በልዩ ልዩ ምክንያት ቮይድ (እንዲሰረዙ) የተደረጉ ቢሆንም ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ስለመሰራቱ ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤

- ✓ በቼክና በደብዳቤ ትዕዛዝ በተለያየ ጊዜያት ከባንክ ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች ብር 17,874.74 በባንክ ስቴትመንት ላይ የሚታዩ ቢሆንም በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብና በሌጀር ላይ ስለመመዝገባቸው የሰነድ ማረጋገጫ ሊቀርብላቸው መሆኑ፤

2. በገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በመመሪያው መሰረት በሂሣብ ክፍሉ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተደረገና ከመዝገብ (ከሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
3. በኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ለጥቃቅን ወጪዎች ብር 30,000.00 ብቻ በካዝና መያዝ ሲገባው በአንድ ጊዜ ብር 30,000.00 በዋና ገንዘብ ያዥ እጅ፣ ብር 10,000.00 ደግሞ በረዳት ገንዘብ ያዥ እጅ፣ በድምሩ ብር 40,000.00 ለጥቃቅን ወጪዎች እንዲያዝ የተደረገ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

1.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ✓ ወደ ባንክ ገቢና ወጪ ለተደረጉት ሂሳቦች ተገቢው የገቢና የወጪ ሂሳብ ሰነዶች ሊቀርብላቸው እንደሚገባ እንዲሁም በልዩ ልዩ ምክንያት ተመላሽ ተደርገው ቮይድ (እንዲሰረዙ) ለተደረጉ ቼኮች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራላቸው መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡
- ✓ መሥሪያ ቤቶቹ በጥሬ ገንዘብ አስተዳደሩ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢ የሆነ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

2 የገቢ ሂሳብ

2.1 በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የታዩ የአሰራር ክፍተቶች፤

2.1.1 ግኝት

1. **በብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ**

- ኤጀንሲው በበጀት ዓመቱ ለሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ትንቢያ መረጃ አገልግሎት ለሰጠበት ብር 507,000.00 ገቢ የሰበሰበ ቢሆንም ለገቢው በሚመለከተው አካል የጸደቀ ታሪፍ ባለመኖሩ ምክንያት ገቢው በታሪፉ መሰረት ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶቹ ከሜትዎሮሎጂ መረጃ ሽያጭ የተሰበሰበው ገቢ ብር 9,729.27 የደንበኞች የአገልግሎት መጠየቂያና መፍቀጃ መረጃ ሳይኖር ገቢው የተሰበሰበ መሆኑ፤

2. **በገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል**

ማዕከሉ ተቀናሽ ያደረገውን ብር 65,762.12 የቅድሚያ ግብር ክፍያ በሂሳብ መደብ 5006 መመዝገብ ሲገባው በ1485 የመዘገበ መሆኑ፤

3. **በፌደራል ስፖርት ኮሚሽን**

- ✓ ስታዲየም ዙሪያ ቤቶች የሚሰበሰበሰበው የቤት ኪራይ በወቅቱ ላልተከፈለው ገቢ የተከፈለው ቅጣት ብር 10,624.45 በ1489 የሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው በ1102 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣
- ✓ ሳር የተሸጠበት ሂሳብ ብር 6,500.00 በገቢ ደረሰኝ ላይ በ1489 የሂሳብ ኮድ መመዝገብ ሲገባው በ1185 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣

4. <u>በኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን</u>

- ብር **357,127.73** የገቢ ሂሳብ በ1459 መመዝገብ ሲገባው በ1489 እንዲሁም ብር 100.00 ደግሞ በ1489 መመዝገብ ሲገባው በ1459 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣
- ባንክ ገቢ የተደረጉ ነገር ግን የገቢ ምንጫቸው የማይታወቅ እና በትክክለኛው ታሪፍ መሰረት ገቢው ስለመሰብሰቡ ሳይረጋገጥ ብር 456,225.55 በገቢ የተመዘገበ መሆኑ፤
- አዋሽና ባቢሌ ብሄራዊ ፓርኮች ገቢ የሰበሰቡበት ደረሰኞችን ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ያልላኩ በመሆናቸው ለብር 513,240.00 በባንክ በኩል የተላኩት ገቢዎች በታሪፉ መሰረት የተሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

5. <u>በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>

- የገቢ ደረሰኞች፣ የወጪ ማስመስከሪያና የጆርናል ቫውቸሮች ከነማስረጃቸው በየተዘጋጁበት ወር በቅደም ተከተል ፋይል ተደርገው የማይቀመጡ መሆኑ፤

6. በኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር በባለሥልጣን ከውጪ ከሚገቡ መድሐኒቶችንና የመድኃኒት እቃዎች ምዝገባና ፈቃድ የአገልግሎት ገቢ የሚሰበሰብ ቢሆንም ለአገልግሎት ክፍያው በሚመለከተው አካል የፀደቀ ታሪፍ ባለመኖሩ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

2.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ✓ ያለታሪፍ ለሚሰበሰበው ገቢ ታሪፍ እንዲወጣለትና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ መደረግ እንዳለበት እንዲሁም ለተሰበሰበው ገቢም የደንበኞች የአገልግሎት መጠየቂያና መፍቀጃ መረጃ ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

- ✓ ገቢዎች ከመመዝገባቸው በፊት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ለመመዝገባቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2.2 ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ

2.2.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 190/2002 መሰረት ገቢን ያገኘው መሥሪያ ቤት በገቢው መጠቀም ካልተፈቀደለት በስተቀር በመንግሥት ንብረት በመገልገል ወይም የመንግሥት ንብረት በማስወገድ የተገኝ ማናቸውም ገቢ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ገቢ መደረጉን እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 መሰረት በመንግሥት ሥም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜው ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ በፈሰስ ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡

1. በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፡
   - ✓ ከግል ጤና አገልግሎት ከሐምሌ 2005 እስከ ሰኔ 2006 ድረስ ከኮሌጁ ገቢ ለመንግሥት ገቢ መደረግ ያለበት 15% የሆስፒታሉ የትርፍ ድርሻ ብር 1,611,851.48 የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለትና ፈሰስ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፣
   - ✓ ከልዩ ፋርማሲ የመድሃኒት ሽያጭ ገቢ 50 በመቶ ለኮሌጁ ገቢ እንዲደረግ በመጋቢት 19/2004 በቁጥር 1.3/82 በተላለፈው መመሪያ መሰረት ከግንቦት 2004-ታህሳስ 2006 ከተሰበሰበው ገቢ ውስጥ ብር 49,521.32 ለሆስፒታሉ ገቢ ያልሆነና ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣

- ✓ በገቢ ደረሰኝ (ገ/ሂ/21/1) የተሰበሰበው የሆስፒታሉ የህክምና ገቢ በገቢ ሂሳብ ማጠቃለያ ደረሰኝ (ሞ/64) ሲጠቃለል በብር 1,341.70 ያነሰ መሆኑ፣
- ✓ የህክምና ገቢ የሚሰበሰብበት የገቢ ደረሰኝ (ገ/ሂ/21/1) ሁለተኛው ኮፒ ተጕርዶ ከሞ/64 ጋር የማይያዝ በመሆኑ ብር 1,132,679.35 ገቢ የተሰበሰበባቸው የገቢ ደረሰኞች ለኦዲቱ ሥራ ሊቀርቡ ያልቻሉ መሆኑ፣

2. የአለርት ማዕከል በ2005 በጀት ዓመት ከግል የህክምና አግልግሎት ከሰበሰበው ገቢ ውስጥ የማዕከሉን ድርሻ 15% ለሆስፒታሉ ገቢም፣ ፈሰስም ያላደረገ ሲሆን፣ በዚህ በጀት ዓመት በተመሳሳይ ሁኔታ የማዕከሉን ድርሻ ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

2.2.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ገቢ ያልተደረገው የሆስፒታሉና የማዕከሉ ድርሻ በተላለፈው መመሪያ መሰረት ገቢ ተደርጎ ፈስስ መሆን እንዳለበት፤ ለወደፊቱም የሆስፒታሉና የማዕከሉ ድርሻ ገቢ ሆኖ ፈሰስ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3 <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

3.1 <u>በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ</u>፤

3.1.1 <u>ግኝት</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያው ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በሃያ አራት ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶች እና በሶስት ለግብርና

ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 267,354,369.34 ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡/ ለዝርሩ አባሪ-9 ተያይዟል/

3.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡት ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4. <u>ተከፋይ ሒሳብ</u>

4.1 <u>ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ተይዞ የሚገኝ ሂሳብ</u>

4.1.1. <u>ግኝት</u>

በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑን በተገቢው ጊዜ ለሚመለከተው አካል የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤ሂሳብ አቅራቢ ከሆኑ አስራ አንድ መሥሪያ ቤቶች እና ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ከሆኑ ሶስት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 54,535,967.92 በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡/ ለዝርሩ አባሪ- 32 ተያይዟል፡፡/

4.1.2. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ስለሚችሉ መሥሪያ ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳቦቹን ሁኔታ በማጣራት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

4.2 በተከፋይ ያልተመዘገበ ሂሳብ፤

4.2.1 ግኝት

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የባንክ ሂሳብ ገቢ ለተደረገው የመያዣ ሂሳብ ብር 452,602.23 ምዝገባ ሳይከናወን ቆይቶ ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ተዘጋጅቶ ገንዘቡ ከባንክ ወጪ ሆኖ ለባለመብቱ እንዲከፈል ሲደረግ የመያዣ ሂሳቡ በዴቢት እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ቀደም ሲል ገንዘቡ ገቢ ሲደረግ ምዝገባ ያለመከናወኑ በባንክና በመያዣ ሂሳብ ምዝገባ ላይ ልዩነት የሚያስከትል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

4.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ እንዲመዘገብ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት እና ለሒሳቡ ተገቢ የሆነ ማስተካከያ እንዲሰራለት አሳስበናል፡፡

4.3 በማዕድን ሚኒስቴር የሮያሊቲ ክፍያው ለተላከላቸው ለመድረሱ ማስረጃ ያልቀረበለት ስለመሆኑ፤

4.3.1 ግኝት

የማዕድን ፍቃድ አውጥተው ማዕድን በማምረት ላይ ከሚገኙ ግብር ከፋዮች ውስጥ የሮያሊቲ ክፍያ 40 ከመቶ የክልሎች ድርሻ ለአፋርና ለኦሮሚያ ክልሎች እንዲሁም ለድሬዳዋ መስተዳደር የሮያሊቲ ድርሻ ክፍያ ሲፈጸም ገንዘቡ ለመድረሱ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 44,614,430.61 ለክልሎቹ የተከፈለው ሂሳብ ለመድረሱ የሚያሳይ ማረጋገጫ (ደረሰኝ) ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ገንዘቡ ለመድረሱ የደብዳቤ ማረጋገጫ (ደረሰኝ) መቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5. የወጪ ሂሳብ

5.1 ጨረታ ሳይወጣ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ

5.1.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት ከብር 100,000.00 በላይ የሚፈጸሙ የዕቃ ግዥዎች እንዲሁም ከብር 75,000.00 በላይ የሚፈጸሙ የአገልግሎት ግዥዎች በግልፅ ጨረታ መከናወን እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ሂሳብ አቅራቢ በሆኑ ስምንት መሥሪያ ቤቶች እና ለግብርናና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ ሁለት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው በብር 751,915,320.72 ለተፈጸሙ የእቃና የአገልግሎት ግዥዎች ጨረታ ያልወጣ፣ አስራ አንድ መሥሪያ ቤቶችና ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ ሁለት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው በብር 2,5491,915.75 ለተፈጸሙ የእቃና የአገልግሎት ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡/ ዝርዝሩ በዚሁ ጽሁፍ አባሪ - 3 እና በጥቅል በአባሪ- 24 ተያይዟል፡፡/

5.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ግዥዎች የግዥ መመሪያውን ተከትለው እንዲፈጸሙ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.2 ያለውል ሥምምነት የተፈጸመ ግዥና ክፍያ፤

5.2.1 ግኝት

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

- ✓ የኢንዱስትሪ ዞን የማስፋፋት ጥናት ለማካሄድ ግብአት የሚሆን የቶፖግራፊ ማፕ ተሰርቶ እንዲቀርብ የካርታ ሥራ ኤጀንሲን በደብዳቤ የጠየቀና ለኤጀንሲው ብር 742,816.22 ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም ከኤጀንሲው ጋር የውል ስምምነት ያልተፈረመ መሆኑ፤
- ✓ መሥሪያ ቤቱ በቋሚነት ዓለሙ ወ/ፃድቅ ወንድማማቾች የተባለውን የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት ጋራዥ በመምረጥ በብር 171,246.27

የጥገና አገልግሎት ግዥ የፈጸመ ሲሆን ከጋራዡ ጋር የተደረገ የውል ሥምምነት ያለመኖሩ፤

ታውቋል፡፡

5.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በውል ያልታገዘ ስምምነት በገንዘብ፣ በጥራትም ሆነ ከጊዜ አንፃር ህጋዊ በሆነ መንገድ ስራዎችን ለመቆጣጠርና ለመከታተል አስቸጋሪ እንዲሆን ሊያደርገው እና በሂደት ችግር ቢከስት ለመፍታት ሊያስቸግር ስለሚችል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ውል ለሚያሥፈልጋቸው ግዥዎች በግዥ መመሪያው መሰረት ተገቢውን ውል መፈጸም ይኖርበታል፡

5.3 ደንብና መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመ ክፍያ፤

5.3.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች የፈጸሟቸው ክፍያዎች ደንብና መመሪያን የተከተሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል ለማዕከሉ ለተለያዩ ሰራተኞች ብር 57,475.14 የህይወት አረቦን ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ ሲሆን፣ በበጀት ለሚተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ክፍያው እንዲፈጸም የሚደግፍ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ በሚመለከተው አካልም ክፍያው ለመፈቀዱ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ክፍያውን የሚደግፍ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይኖር ክፍያው መፈጸሙ አግባብ ስላለሆነ አሰራሩ መስተካከል እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.4 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ

5.4.1 ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በተገቢው የሒሳብ መደብ የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአስራ ዘጠኝ ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶችና ለጤና ጥበቃና ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ ሁለት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 18,261,471.08 መመዝገብ

ባለባቸው የሂሳብ መደቦች ሳይመዘገቡ ተገኝቷል፡፡ /ለዝርዝሩ አባሪ - 29 ተያይዟል፡፡/

5.4.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያ ከመፈጸሙና ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ለወጪዎቹ በጀት መያዙንና በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ለመመዝገባቸው መረጋገጥ እንዳለበትና ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.5 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

5.5.1 ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት በ2006 በጀት ዓመት በተፈቀደው የበጀት ድልድል መሰረት መሆኑን እና የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአሥር ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 1,745,791.37 የ2005 በጀት ዓመት የወጪ ሂሳቦች በ2006 በጀት ዓመት በወጪ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ ለዝርዝሩ አባራ- 28 ተያይዟል፡፡

5.5.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.6 በድጋሚ በወጪ የተመዘገበ ሒሳብ

5.6.1 ግኝት

የወጪ ሒሳቦች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትለው የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡

- ✓ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በብር 182,900.73 የተፈጸሙት የዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች በድጋሚ የወጪ ቫወቸር ተዘጋጅቶላቸው በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) እና በሌጀር ላይ ተመዝግበው የተገኙ መሆኑ፤

- ✓ በአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ከ2006 በጀት ዓመት በፊት የነበሩ የወጪ ሂሳቦች ብር 99,883.05 በ2005 በጀት አመት ወደ ማስተባባሪያው ተልኮ በወጪ የተመዘገበ ቢሆንም በድጋሚ በ2006 በጀት ዓመት በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

5.6.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በድጋሚ የተመዘገቡት ወጪዎች ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

5.8 አለአግባብ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ፤

5.8.1 ግኝት

- ✓ የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል በፌኔት ሆቴል ሥልጠና አዘጋጅቶ ለምግብ፣ ለመኝታና ለመሳሰሉት ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም በተጨማሪ ለውሎ አበል ብር 222,670.00 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- ✓ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባዘጋጀው ስልጠና ላይ ለተሳተፉ 123 ሰራተኞች በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደው የምሳ አበል ብር 15,083.00 መክፈል ሲገባው በደብዳቤ ከተፈቀደው በተጨማሪ ለቁርስና ለእራት ብር 21,116.20 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- ✓ የአለርት ማዕከል ለ93 የማዕከሉ ሰራተኞች ለአሥራ አምስት ቀናት ባዘጋጀው ስልጠና ላይ የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያው ከተቀመጠው የቀን የወሎ አበል አከፋፈል ተመን በላይ የቁርስና የምሳ አበል ክፍያ በመፈጸሙ ብር 9,207.00 በብልጫ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- ✓ በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን በቢሾፍቱ ሥልጠና በካሄደበት ወቅት፤ እንደ ሰልጣኞቹ የደመወዝ መጠን ብር 123፤ ብር 147 እና ብር 171 መክፈል ሲገባው ለሁሉም የሥልጠና ተሳታፊዎች ብር 170 እንዲከፈል በመደረጉ ምክንያት እና በሆቴሉ የሁለት ቀናት

የምሳ አበል ተሸፍኖ እያለ በተጨማሪ የምሳ አበል ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ ምክንያት ብር 25,569.05 ያለአግባብ ወጪ መሆኑ፣

- ✓ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ሠራተኞች ለሥራ ጉዳይ ሞጆ ሲሄዱ መንግሥት ባወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት ክፍያ መፈጸም ሲገባው ኮሌጁ ለዳኤማ ሆቴል ብር 22,374.17 ሆቴሉ ባቀረበው ቢል መሰረት የአልጋ ሂሳብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤
- ✓ የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሉ በቢሾፍቱ ከተማ ለባለሙያዎች የስነ-አእምሮ ጤና እና የሜዲካል ሪከርድ ሥራ አመራር ሥልጠና በሰጠበት ወቅት የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ በቢሾፍቱ የውሎ አበል ክፍያ መሰረት መከፈል ሲገባው ለ93 ሰልጣኞች በአዲስ አበባ ከተማ የውሎ አበል ታሪፍ መሰረት ክፍያ በመፈጸሙ ምክንያት ብር 4,927.00 አለአግባብ ወጪ የተደረገ መሆኑ፤
- ✓ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት በመስክ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች ከውሎ አበል ክፍያ በተጨማሪ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይፈቀድ ለውሃ መግዣ ተብሎ ብር 6,632.96 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 312,496.38 አለአግባብ የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

5.8.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ከደንብና መመሪያ ውጪ ክፍያ መፈጸም አግባብ ስላልሆነ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

5.9 <u>አግባብ ያልሆነ ግዥ በመፈጸሙ ምክንያት ወጪ የተደረገ ተጨማሪ ክፍያ፤</u>

5.9.1 <u>ግኝት</u>

ግዥዎች የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው የሚፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡

- ✓ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የፅህፈት መሳሪያና አላቂ እቃዎች እንዲሁም የፅዳት እቃዎች ግዥ በግልጽ ጨረታ ሲፈጽም የጨረታ ኮሚቴው የጥራት መስፈርት ሳያወጣ ነገር ግን ጥራትን ብቻ መሰረት በማድረጉ እና ግዥው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡ ተጫራች እንዲፈጸም በመደረጉ ምክንያት ብር 37,067.86 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

- ✓ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፡
  - ♦ ለኮሌጁ ጤና ባለሙያዎች የሚያገለግል ነጭ ቲትረን 6ሺ ጨርቅ 1450 ሜትር እንዲገዛ ከተጠየቀውና በግዥ ኮሜቴ ከተወሰነ በላይ 2000 ሜትር በመገዛቱ ምክንያት 550 ሜትር በብር 74,002.50 እንዲገዛ ከተጠየቀው በላይ በብልጫ ተገዝቷል፡፡
  - ♦ ለሆስፒታሉ ሕሙማን እና ተማሪዎች የክርስቲያንና የሙስሊም የበሬ ሥጋ ዝቅተኛ ዋጋ ለማቅረብ ያሸነፈው ድርጅት ሞሲሶ ትሬዲንግ የተባለው ድርጅት ሆኖ እያለ የበሬና የበግ ስጋ ያንዱን ዋጋ በብር 69.00 እና በብር 80.00 ካቀረበው አሰፋ ሸዋነ ሥጋ ቤት ግዥው በመፈጸሙ ምክንያት በድምሩ ብር 12,309.00 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
  - ♦ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ በፀደቀው ቃለጉባኤ መሰረት ኦሞ ዘሀራን ያንዱን ዋጋ በብር 7.38 ካቀረበው ከእርግቤ ጠቅላላ አስመጪ መገዛት ሲገባው ነስሮ አህመዲን ሲራጅ ከተባለው ድርጅት ያንዱን ዋጋ በብር 8.75 ብዛቱ 5422 ኦሞ ዘሀራን እንዲገዛ በመደረጉ በድምሩ ብር 7,428.14 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

- ✓ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የፈፅማቸው የዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች በዕቃ ግገር መጠየቂያ በተጠየቀው መሠረት እና በተቋቋመው ጊዜያዊ የግዥ ኮሚቴ በተመረጠው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በብር 72,683.51 የተፈፀሙት ግገሮች በእቃ ግገር መጠየቂያ

ከተጠየቀው ብዛት በላይ እና በግዥ ኮሚቴ እንዲገዛ ካልተመረጠው አቅራቢዎች ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

5.9.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ግዥዎች የግዥ መመሪያውን ተከትለው እንዲፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

5.10 <u>ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው መሆኑ</u>፤

5.10.1 <u>ግኝት</u>

መሥሪያ ቤቶች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባልሥልጣን በተጻፈላቸው ደብዳቤ መሠረት የቀረጥ ሂሣብ ምዝገባ የሚያከናውኑ ሲሆን፣ ቀረጡ የተከፈለባቸው እቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ገቢ ለመደረጋቸው ሲጣራ ፡

- ✓ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በ2006 በጀት ዓመት ብር 32,128,296.51
- ✓ በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በ2006 በጀት ዓመት 41,189,738.68
- ✓ በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ለብር 2,734,486.29፤

በጠቅላላው ለብር 76,052,521.48 የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) እንዲያያዝ ባለመደረጉ ዕቃዎቹ ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

5.10.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶች የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጥ የተከፈለባቸው ንብረቶች ከቀረጥ ሂሳብ ምዝገባው ጋር እንዲያያዙ መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.11 ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉ እና ገቢ ለመደረጋቸው ኮፒ ደረሰኝ የቀረበላቸው ንብረቶች ፤

5.11.1 ግኝት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የሚፈጽማቸዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥዎች በፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን የተከተሉ መሆናቸውን፣ የተገዙትም እቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ የሚደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ✓ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በብር 2,416,905.52 የተገዙት የተለያዩ ዕቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ለመደረጋቸው ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤
- ✓ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለአራቱ ከተሞች ከገዛቸው ካቢኔቶች ውስጥ (SPACE SAVIND FILE CABINAT AND ALLBODY PARTS OF CABINATES) በብር 192,461.86 የተገዙትን ካቢኔቶች ለትግራይ ክልል ሲያስረክብ ንብረቶቹ ገቢ ለመደረጋቸው የቀረበው ኮፒ የንብረት ገቢ ደረሰኝ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

5.11.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ለተገዙት ዕቃዎች እንዲሁም ለተላኩት ዕቃዎች ኦሪጅናል የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልቀረበ ንብረቶቹ በትክክል መግባታቸውን ለማረጋገጥ የማያስችል በመሆኑ ለዕቃዎቹ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲቀርብላቸው አሳስበናል፡፡

5.12 ለኦዲት ሥራ ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ሂሳብ ማስረጃዎች ስለመኖራቸው፤

5.12.1 ግኝት

1. በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፡-
    - ♦ ብዛታቸው አራት የሆነ ብር 300,792.64 የያዙ የወጪ ቫውቸሮች ለኦዲት ሥራ እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሊቀርቡ ያልቻሉ መሆኑ፤

- ለመድሃኒት መግዣ ብር 879,135.93፣ ለመጽሐፍት መግዣ ብር 259,167.47 እንዲሁም ለሌሎች ዕቃዎች መግዣ ብር 1,726,650.52 በድምሩ ብር 2,864,953.92 ወጪ ሆኖ የተመዘገበ ቢሆንም ለወጪ ሂሳቦቹ ማስረጃ (ፋክቱር) ያልቀረበላቸው መሆኑ፤
- ለኦዲት ሥራ በናሙና ከተመረጡት ሂሳቦች ውስጥ ለብር 316,229.63 ገቢ፣ ለብር 3,587.00 ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ለብር 315,738.16 ተከፋይ ሂሳብ ፣ ለብር 5,881,634.01 የወጪ ሂሳብ ሁኔታዎች ለማጣራት የገቢ ደረሰኞች፣ የወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች እና የወጪ ቫውቸሮች ለኦዲት ሥራ እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሊቀርቡ ያልቻለ መሆኑ፤

2. የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የአውሮፓ ህብረት ለኢኒስትቲዩቱ ከሰጠው ዕርዳታ ውስጥ ብር 3,211,746.00 ተቀባይነት የሌለው ወጪ በመሆኑ ለኤውሮፓውያን ዲቨሎፕመንት ፈንድ ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ በተጠየቀው መሠረት ከበጀት ሂሳብ ላይ የተከፈለ ሲሆን፣ የወጪ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤
3. በኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ለብር 51,332.63 የወጪ ማስረጃ ሊቀርብላቸው ያልቻለ መሆኑ፤
4. የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ለነዳጅ መግዣ የተፈጸመው ክፍያ ብር 40,000.00 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

5.12.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በወጪ ለተመዘገቡት ሂሳቦች ማስረጃዎቹ መቅረብ እንዳለባቸው፤ ማስረጃዎቹ ሊቀርቡ ካልቻሉ ግን ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.13 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፤

5.13.1 ግኝት

በወጪ ለተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ መመሪያው መሰረት የተሟላ የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

1. በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅፅ ላይ መነሻ ሰዓት፣ መድረሻ ሰዓት እና ሠራተኛው በጉዞ ላይ የቆይባቸው ቦታዎች (ለቁርስ ፣ ለምሳ ፣ ለእራት) የማይገለፅ ከመሆኑም በተጨማሪ በሠራተኛው የተሞላው ቅፅ በትክክል መሞላቱን ውሎ አበል እንዲከፈለው በጠየቀው ሰራተኛ ሥራ ኃላፊ ሳይረጋገጥ ብር 8,331.99 የተከፈለ መሆኑ፤
2. በኤሌክትሪክ ኤጀንሲ በብር 5,750.00 ለተፈጸመው የመኪና ኪራይ ግዥ መጠየቂያ ያልቀረበለት መሆኑ፤
3. በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ ብር 1,995.30 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
4. የውሃ ልማት ጽህፈት ቤት፡
   - የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ግንባታ ስትራክቸሮችንና ቁሳቁሶችን ለጠበቁ ጊዜያዊ የጥበቃ ሰራተኞች ብር 34,500.00 ክፍያ ሲፈፀም ጥበቃዎቹ አገልግሎት በሰጡባቸው ቀናቶች ስለመከፈሉና ተገቢ የሆኑ ከደመወዝ ክፍያው ላይ ለተቀናነሱ ሂሳቦች ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያው በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤
   - የስልክ አገልግሎት ሂሳብ ክፍያ ብር 4,343.46 ሲፈጸም እያንዳንዱ ስልክ የተጠቀመበትን ዝርዝር የሚያሳይ ቢል ያልቀረበ በመሆኑ የክፍያዎቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

5. የማዕድን ሚኒስቴር በፋይናንስ መመሪያው መሰረት የደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሂሳብ ክፍሉ ተቀናናሽ ሂሳቦችን (የሥራ ግብር፣ የጡረታ፣ የተሰብሳቢና ሌሎች ተቀናናሽ ሂሳቦች) የሚያሳይ የ2006 በጀት ዓመት የየወሩ የደመወዝ መክፈያ ፔይሮል (Payroll Sheet) ሊያቀርብ ባለመቻሉ ምክንያት የተቀናናሽ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

6. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን በጎንደር ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ለነዳጅ መግዣ እና ለእጥበትና ግሪስ በድምሩ ለብር 10,824.26 የቀረቡት ደረሰኞች የገዥውን ማንነት እንዲሁም ቀኑንና ነዳጁ የተሞላላቸውን እጥበትና ግሪስ የተደረገለትን መኪና ሰሌዳ ቁጥሩን የማይገልጽ መሆኑ፣

7. <u>**በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ**</u>

- ለሆስፒታሉ ሕሙማን እና ተማሪዎች የምግብ እና የተለያዩ ዕቃዎችና የአገልግሎቶች ግዥዎችን በብር 29,134,733.40 የፈጸመ ቢሆንም ጨረታ ሰነድ የወጣበት፣ የማወዳደሪያ ሠንጠረዥ፣ የግዥ ኮሚቴ እና የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ቃለጉባኤ፣ የውል ስምምነት ሰነድ እና የዋጋ ማወዳደሪያ ለኦዲት ሥራ ተጠይቀው ሊቀርቡ ያልቻሉ መሆኑ፣
- የጽህፈት መሣሪያ እና የፕሪንተር ቀለም በድምሩ በብር 131,224.00 ግዥውን የፈጸመ ይሁን እንጂ ግዥው ከድርጅቶቹ እንዲፈጸም የግዥ ኤጀንሲ የጻፈው ደብዳቤ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

5.13.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ለመሥሪያ ቤቶቹ ለተከፈለው ገንዘብ ማስረጃው እስኪቀርብ ድረስ በተሰብሳቢ መዝግቦ በመያዝ ገንዘቡ ለመድረሱ የገቢ ደረሰኝ ወይም ደብዳቤ ሲቀርብ በወጪ መመዝገብ እንዳለባቸው እንዲሁም ገንዘቡ

ለመድረሱ ከድርጅቶቹ የገቢ ደረሰኝ ወይም ደብዳቤ ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

- በመስክ ሥራ ላይ የቆዩ ሰራተኞች የወጪ ሂሳብ ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ሰራተኞቹ በሥራው ላይ ቆይተው ሥራቸውን አጠናቀው የተመለሱ ለመሆኑ ስራውን ባዘዘው የስራ ክፍል ሊረጋገጥና የቆዩባቸው ቀናትም በዝርዝር በውሎ አበል ቅጾቹ ተሞልቶ በሚመለከታቸው ኃላፊዎች መረጋገጥ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.14 ከልዩ ልዩ የጥቅማጥቅም ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰ ሥራ ግብር፤

5.14.1 ግኝት

በገቢ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም (ለምሳሌ የቤት አበል፣ ቦነስ፣ የኣመት ፍቃድ ክፍያ፣ የአገልግሎት ካሳ.... ወዘተ ከወር ደሞዝ ጋር እተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ነሐሴ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር 1አውግ-54 በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባሳወቀው መሠረት መሰራቱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡

1. የአባይ ተፋሰስ ባለስልጣን ከሐምሌ 2005 እስከ ሰኔ 2006 ከፈጸመው የቤት አበል ክፍያ ላይ ብር 6,300.00 የሥራ ግብር ተቀናሽ ያላደረገ መሆኑ፤
2. የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን ከሐምሌ 2005 እስከ ሰኔ 2006 ዓ.ም ከፈጸመው የቤት አበል ላይ ክፍያ ላይ ብር 6,300.00 የሥራ ግብር ተቀናሽ ያላደረገ መሆኑ፤
3. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ከሐምሌ 1/2005 እስከ ህዳር 30/2006 ከፈጸመው የቤት አበል ክፍያ ላይ ብር 2,625.00 የሥራ ግብር ተቀናሽ ያላደረገ መሆኑ፤

4. የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሉ በበጀት ዓመቱ ከፈጸመው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 1,601,290.49 ላይ የሥራ ግብር ያልቀነስ መሆኑ፤

5. ለቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሉ የጤና ባለሙያዎች ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የተፈቀደው የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ከክፍያው ላይ የገቢ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

5.14.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በገቢ ግብር አዋጁ፣ ደንብና በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡

5.15 <u>የበጀት ዝውውር ሳይፈጸም ከደመወዝ በጀት ለሥልጠና የተከፈለ</u>፤

5.15.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 መሰረት ለደመወዝ የተፈቀደን በጀት ለሥራ ማስኬጃ ለመጠቀም በቅድሚያ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መፈቀድ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለግል ኢኮኖሚ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ለኮንትራት ቅጥር ሰራተኞች ከተፈቀደው የደመወዝ በጀት ላይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር የበጀት ዝውውር ሳይጠይቅ ለካፒታል ሥራ ማስኬጃ ብር 25,897,129.51 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.15.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለደመወዝ የተፈቀደን በጀት በቅድሚያ የበጀት ዝውውር ሳይጠየቅ ለስራ ማስኬጃ ለማዋል የማይፈቀድ መሆኑ እየታወቀ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለስራ ማስኬጃ መጠቀሙ አግባብ አለመሆኑ ተገልጾ ለወደፊቱ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በቅድሚያ ተገቢ የሆነ ዝውውር መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.16 ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ ተዛውሮ በወጪ እንዲመዘገብ የተደረገ ሂሳብ

5.16.1 ግኝት

በውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት:

1. ጽህፈት ቤቱ በ6412 በሂሳብ መደብ ለብድር መስጠትና ማስመለስ እንዲውል ከተፈቀደለት በጀት ብር 50 ሚሊዮን ውስጥ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተረፈውን ብር 37,915,592.09 በወጪ ሒሳብ መደብ 6412 መዝግቦ ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ እንዲዞር ያደረገ መሆኑ፤

ታውቋል።

5.16.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ገንዘቡ ከበጀት ሂሳብ ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ ተዛውሮ ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደበት ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል ። ማስረጃ የማይቀርብ ከሆነ ግን ገንዘቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተመላሽ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም ቢሆን በሚመለከተው አካል እስካልተፈቀደ ድረስ ተራፊው ገንዘብ ወደ ፕሮጀክቱ ሂሳብ እንዲዛወር መደረግ እንደሌለበት አሳስበናል።

5.17 በስሌት ስህተት በብልጫ የተቀነሰ ተጨማሪ ዕሴት ታክስ፤

5.17.1 ግኝት

በተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የሚቀነስ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በዱር እንስሳ ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰላው የተጨማሪ ዕሴት ታክስን አጠቃሎ ከያዘው ሂሳብ ላይ በመሆኑ ብር 20,244.91 አለአግባብ ተቀናሽ የተደረገ መሆኑ ታውቋል።

5.17.2 የማሻሻያ ሃሳብ

አለአግባብ የተቀነሰው ክፍያ ለባለመብቱ ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱም በተጨማሪ ዕሴት ታክስ አቀናነስ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል።

5.18 ሳይፈቀድ ከመመሪያ ውጪ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፤

5.18.1 ግኝት

በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 34/2 መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ የትርፍ ሰዓት ሥራ አከፋፈል መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደገና ጳጉሜ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/13/37/820 በተጻፈ ደብዳቤ የትርፍ ሰዓት ክፍያው ተግባራዊ ሳይደረግ እንዲቆይ ማሳወቁ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ፡

- በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ብር 911.40፤
- በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 32,191.39፤
- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በሕክምና አስተማሪነት በትርፍ ሰዓት ለሰሩ ዶክተሮች በሰዓት ብር 120.00 እየተከፈላቸው በድምሩ ብር **799,849.85** የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል። ሆኖም በኮሌጁ በትርፍ ሰዓት ለሚሰሩ በሰዓት ብር 120.00 ክፍያ እንዲፈጸም በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 832,952.64 ደንብና መመሪያን ሳይከተል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል።

5.18.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ክፍያውን የሚደግፍ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይኖር እንዲሁም በሲክፍያው መፈጸሙ አግባብ ስላልሆነ አሰራሩ መስተካከል እንዳለበት አሳስበናል፡

5.19 በመመሪያው መሰረት ያልተቀነሰ የህክምና ክፍያ፤

5.19.1 ግኝት

ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር መ30-899/4 የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የሚመሩ ዋና እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅሞች አሰጣጥ በተመለከተ በተላለፈው መመሪያ መሰረት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተርና ቤተሰቦቻቸው በጦር ሀይሎች ሆስፒታል የነጻ ህክምና አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ ለዚሁም ከወር ደሞዛቸው ላይ 1% የህክምና መቀነስ እንዳለበት መመሪያ ተላልፏል፡፡ ሆኖም ከሐምሌ 2005 እስከ ሰኔ 2006 ዓ.ም ድረስ በመመሪያው መሰረት መቀነሱ ሲጣራ፡

- በኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዲስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 1,149.70 ፤
- በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን ብር 993.24፤
- በስፖርት ኮሚሽን ብር 1,328.40 ፤
- በአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን ብር 648.00፤

በድምሩ ብር 4,119.34 ያልተቀነሰ የህክምና ክፍያ መኖሩ ታውቋል፡፡

5.19.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የህክምና ክፍያ እንዲቀነስ፤ ለወደፊቱም በተላለፈው መመሪያ መሰረት እንዲፈጸም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.20 በመመሪያው መሰረት ተይዞ ያልተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

5.20.1 ግኝት

የካቲት 8/2002 ዓ.ም በቁጥር ታክ/ቀ/5/102 በግዥ ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው መመሪያ መሰረት ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ከመጋቢት 1 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ከብር 5,000.00

በላይ ከሚፈጸሙት ግዥ ላይ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ክፍያውን በመቀነስ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለባቸዉ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም፡

1. በገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል ልዩ ልዩ ግዢዎችን ሲያከናውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያውን ብር 189,605.38 ቀንሶ ለታክስ ሰብሳቢዉ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባዉ ክፍያውን ለድርጅቶቹ የፈጸመ መሆኑ፤

2. የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት የ15 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የመንግሥትንና የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ በገቡት ውል መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ (ዮቫት) ክፍያ የፌደራል መንግሥት ድርሻ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ብር 6,147,366.49 የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ተቀንሶ ተገቢው ምዝገባ የተከናወነ ለመሆኑ እና ታክሱም ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

5.20.2 የማሻሻያ እርምጃ

በተጨማሪ ዕሴት ታክስ መመሪያው መሰረት ተገቢው ታክስ እንዲቀነስ፤ ለወደፊቱም ታክሱ ለመቀነሱ ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

5.21 ተቀናሽ ያልተደረገ የቅድሚያ ግብር

5.21.1 ግኝት

በገቢ ግብርና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት መሥሪያ ቤቶች ከፈጸሟቸው ክፍያዎች ላይ ተገቢውን ተቀናናሾች የሚቀነሱ እና ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚያደርጉ መሆኑ በናሙና ሲጣራ፣

የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጀንሲ

- ከመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ ላይ ብር 435.83 ሳይቀነስ የተገኘ መሆኑ፣

- የጎንደር ቅ/ጽ/ቤት የቢሮ ኪራይ ከመጋቢት 1/2006 እስከ ሰኔ 30/2006 ድረስ ብር 90,360.00 ሲከፍል የቅድሚያ ግብር 1,807.20 ያልተቀነሰ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 2,243.03 የቅድሚያ ገቢ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.21.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በታክስ አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያው መሰረት ሊቀነሱ የሚገባቸው ታክሶች መቀነስ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.22 የሥራ መደብ ላልተሰጣቸው ሠራተኞች የደመወዝ ክፍያ የተፈጸመ ስለመሆኑ፤

5.22.1 ግኝት

የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን ለአምስት ግለሰቦች በየወሩ ለእያንዳዳቸው ብር 1,602.10፤ ለሶስት ግለሰቦች ደግሞ በየወሩ ለእያንዳንዳቸው ብር 1,307.80 የሚከፈላቸው ሲሆን ግለሰቦቹ በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሥራ መደብ ያልተሰጣቸውና ተንሳፋፊ ሆነው እያለ በየወሩ ደመወዝ እየተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

5.22.2 ሥጋት

የሥራ መደብ ላልተሰጣቸው ተንሳፋፊ ሰራተኞች ክፍያ መፈጸም አግባብ ስላልሆነ መሥሪያ ቤቱ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም ለወደፊቱ በደመወዝ አከፋፈል ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.23 በመንግሥት ሳይፈቀድና የትምህርትና ምርምር ዕዉቅና ሳይኖር ለምርምርና ለሥልጠና የተፈጸመ ክፍያ፤

5.23.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ክፍል ሁለት አንቀጽ 11/2 መሰረት የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ (ሚኒስቴር) የልዩ ልዩ አበል ዓይነቶችን እና ክፍያዎችን እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውሳኔ

አቅርቦ ሲፈቀድ ሥራ እንደሚውል ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የትምህርትና ምርምር ዕዉቅና ሳይኖረው ለምርምርና ለሥልጠና ብር 987,182.00 ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም ክፍያው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.23.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መመሪያው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.24 <u>ማስተካከያ ያልተሰራለት ያልተከፈለ የደመወዝ ሂሳብ</u>፤

5.24.1 <u>ግኝት</u>

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በተለያዩ ምክንያቶች ለሰራተኞች ላልተከፈሉ የደመወዝ የማስተካከያ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን ሰኔ 30/2006 ላይ በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫው ላይ ያልተከፈለ የተጣራ ደመወዝ ብር 3,054.46 በተከፋይ የሂሳብ መደብ (5004) ተይዞ የሚገኝ ቢሆንም ላልተከፈሉት የደመወዝ ሂሳቦች ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

5.24.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ላልተከፈሉት የደመወዝ ሂሳቦች በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራላቸው መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.25 <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆኑ ድርጅቶች የተፈጸሙ የአገልግሎት ግዥ</u>፤

5.25.1 <u>ግኝት</u>

በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 27/2004 ለማሻሻል የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሰኔ 19 ቀን 2004 በቁጥር ታ/ክ/ቀ15/688 ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ከብር ከ50,000.00 በላይ

ዋጋ ያላቸው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥዎች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ላይ የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ✓ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን በብር 57,115.30 ለፈጸመው ለፓርቲሽን ሥራ አገልግሎት ግዥ ፣
- ✓ የአካባቢና ደን ሚኒስቴር በብር 50,400.00 ለፈጸመው የአገልግሎት ግዢ ፣
- ✓ የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን በብር 105,600.00 ለፈጸመው የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት ግዥ

በድምሩ በብር 213,115.30 የተፈጸመው ግዥ የተጨማሪ እት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆነ ድርጅት የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.25.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በተሻሻለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መሥሪያ ቤቶቹ ከብር 50,000.00 በላይ ዋጋ ያላቸው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ ሲፈጸሙ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ላይ መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.26 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልቀረበለት የአገልግሎት ግዥ፤

5.26.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምረው ለፈጸሙት የእቃና የአገልግሎት ግዥ ክፍያ ሲፈጽሙ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ የተቀበሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ ዘርፍን የ15 ዓመታት የእድገት አቅጣጫ ለማመልከት በተዘጋጀው ፍኖተ ካርታ (Road Map) ላይ ዝርዝር ጥናቶችን (ስትራቴጂክ ጥናት 2015-2025) ከሚያካሂዱ ከአራት የከፍተኛ ተቋማት እና ከአንድ ድርጅት ጋር የውል ስምምነት ውስጥ ገብቶ ብር 8,907,336.46 የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም ዩኒቨርሰቲዎቹና ድርጅቱ

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመዝጋቢ ለመሆናቸው የምዝገባ ሰርተፊኬት እንዲሁም ለክፍያው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.26.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዩኒቨርሰቲዎቹና ድርጅቱ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመዝጋቢ ለመሆናቸው የምዝገባ ሰርተፊኬት እንዲሁም ለክፍያው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.27 <u>ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበለት የደመወዝ ገቢ ግብር፤</u>

5.27.1 <u>ግኝት</u>

የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤቱ የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ግንባታ ስትራክቸሮችንና ቁሳቁሶች ጥበቃ አገልግሎት ለሰጡት ጊዚያዊ የጥበቃ ሰራተኞች ክፍያ ሲፈጸም ተቀናሽ ያደረገው ብር 9,803.33 የደመወዝ ገቢ ግብር ለገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል፡፡

5.27.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለጊዚያዊ የጥበቃ ሰራተኞች ደመወዝ ሲከፈል ተቀናሽ የሆነው የደመወዝ ገቢ ግብር ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ በማስረጃ መደገፍ እንዳለበት፤ ለወደፊቱም ደመወዝ እንደተከፈለ ወዲያውኑ ተቀናሽ የሆነው የደመወዝ ገቢ ግብር ለሚመለከተው አካል ገቢ ተደርጎ ማስረጃው መቅረብ እንዳለበት አሳስበናል።

5.28 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Trancation Register) ላይ በወጪ ያልተመዘገቡ ሂሳቦች ስለመኖራቸው፤

5.28.1 ግኝት

የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል የመጀመሪያ ተመራቂ ተማሪዎቹን በሸራተን አዲስ ለማስመረቅ ለመስተንግዶ የፈጸመው ክፍያ ብር 247,452.29 እንዲሁም ለጽዳት ዕቃ (የሽንት ቤት መርዝ) ግዥ የፈጸመው ክፍያ ብር 296,201.27 በድምሩ ብር 543,653.56 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) ላይ በወጪ ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል ፡፡

5.28.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በሂሳቡ የታዩት ክፍተቶች ተጣርተው ተገቢው የማስተካከያ ምዝገባ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.29 በዕቃ ግዢ መጠየቂያ ሳይጠየቅ የተፈፀመ ግዢ፤

5.29.1 ግኝት

የዕቃ ግዥዎች በዕቃ ግዢ መጠየቂያ ተጠይቀው የሚፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በብር 230,740.37 ለፈጸማቸው ግዥዎች የእቃ የግዥ መጠየቂያ ያልቀረበላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

5.29.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ግዥ ከመፈጸሙ በፊት በቅድሚያ ለግዥዎቹ የእቃ ግዥ መጠየቂያ መቅረቡን ማረጋገጥ እንዳለበት አሳስባናል፡፡

5.30 በተከፋይ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ፤

5.30.1 ግኝት

የገ/ኢ/ል/ሚ ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለህንፃ ተቋራጭ ክፍያ ለመፈጸም የክፍያ የምስክር ወረቀት ሲቀርብ ለሚቀነሰው የመያዣ ሂሳብ ምዝገባ የሚከናወን

መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለህንፃ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈጽም፡

- ✓ ከክፍያው ላይ የቀነሰው የመያዣ ሂሳብ ብር 7,108,899.28 በወጪ ሒሳብ መደብ 6323 በዴቢት እንዲሁም በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5061 በክሬዲት ያልተመዘገበ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

5.30.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የግንባታ ሂሳብ ምዝገባ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ እንዲመዘገብ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ፤ ለሒሳቡም ተገቢ የሆነ ማስተካከያ እንዲሰራለት እናሳስበናል፡፡

5.31 <u>ከውል በላይ የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ፤</u>

5.31.1 <u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግሥት የግዥ መመሪያ መሰረት በውሉ ላይ የዋጋ ለውጥ ወይንም ማንኛውም ማሻሻያ ማድረግ ከተፈለገ በውሉ ውስጥ የተካተቱትን እና ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን የውሉን ክፍሎች በመለየት ከአማካሪው ጋር በመስማማት እና ማሻሻያው ያስፈለገበትን ምክንያት ከሚገልጽ ሪፖርት ጋር በመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ የፀደቀ ረቂቅ ውል መኖሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በመጀመሪያው ዙር ለቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ዞን ግንባታ ለማካሄድ ከኤምኤች ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ብር 4,093,080.00 የውል ስምምነት ያደረገ ሲሆን፣ ለአማካሪው ግን እስከ 18ኛው ክፍያ ሰርተፍኬት ድረስ ብር 5,507,029.96 ክፍያ የፈጸመ በመሆኑ ከውል ስምምነቱ በላይ ብር 1,413,949.96 (34.5%) ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ እና ለተጨማሪው ክፍያ ተገቢው ውል ያልተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.31.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ከውል በላይ ክፍያ የተፈጸመበት ምክንያት ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ፣ ለወደፊቱ በአከፋፈሉ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.32 <u>ከውል ውጭ ለግንባታ አማካሪ ድርጅት ባለሙያዎች የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ክፍያ</u>፤

5.32.1 <u>ግኝት</u>

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከኤምኤች ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር በገባው ውል ላይ ስለትርፍ ሰዓት ክፍያ (Over Time Payment) የተገለጸ ነገር ሳይኖር ለአማካሪው ድርጅት ባለሙያዎች ከጥቅምት 05 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ ጥር 05 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ በትርፍ ሰዓት ለሰሩበት ተብሎ ብር 114,619.06 ለኤምኤች ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለሙያዎች ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

5.32.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ክፍያው አግባብነት የሌለው በመሆኑ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት ለወደፊቱም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚፈጽማቸው ክፍያዎችም በውል የተደገፉ ስለመሆናቸው መረጋገጥ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.33 <u>በተሰብሳቢ መመዝገብ ሲገባው በክፍያ ሰርተፊኬቱ ላይ አየር በአየር እንዲቀናነስ የተደረገ የግንባታ እቃዎች ግዥ</u>፤

5.33.1 <u>ግኝት</u>

1. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፡

   1.1 ለኮንትራክተሮቹ የሚያቀርባቸው አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የግንባታ እቃዎች ዋጋ አስቀድሞ በወጪ የተመዘገቡ በመሆኑ እና የክፍያ ሰርተፊኬት ሲቀርብ ደግሞ አስቀድሞ በወጪ ለተመዘገቡት ሂሳቦች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራላቸው ባለመደረጉ ምክንያት የክፍያ የምስክር ወረቀት ሲቀርብ ተመላሽ

ለተደረገው ብር 15,612,307.09 አገልግሎት ላይ የዋሉ እቃዎች ዋጋ በክፍያ ሰርተፊኬቱ ላይ አየር በአየር ብቻ እንዲቀናነስ የተደረገ ሲሆን ይህም፤

- ✓ የየፕሮጀክቱን ትክክለኛ ወጪ ሊያሳይ የማይችል መሆኑ፤
- ✓ ኮንትራክተሮቹ የወሰዱትን የግንባታ እቃዎች ዋጋ በትክክል ተመላሽ ማድረጋቸው ለመከታተል አስቸጋሪ መሆኑ፤
- ✓ በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት ለኮንትራክተሮቹ በውሉ መሰረት እስከ 30% ድረስ የቅድሚያ ክፍያ የሚፈጸም ሲሆን፣ በተጨማሪም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የግንባታ እቃዎች እየተገዙ የሚቀርቡበት አግባብ በግዥ አዋጁና መመሪያው ላይ ያልተፈቀደ (ያልተደገፈ) መሆኑ፤

1.2 ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከተገጣጣሚ ሕንጻ አቅራቢ ድርጅት ፕሪካስት ቢም እና የስላብ ብሎኬቶች አቅራቢ ድርጅት በብር 3,109,890.85 የግንባታ ዕቃዎቹ ግዥ እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም በብር 10,900,707.40 የግንባታ እቃዎች ግዥ ፈጽሞ ግንባታው ሳይፈፀም ዕቃዎቹ በወጪ እንደሚመዘገቡ የተደረገ መሆኑ፤

1.3 ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለኤ.ኤም.ቢ. ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የቅድሚያ ግንባታ ክፍያ ብር 743,053.87 ሲፈጸም በተሰብሳቢ ሒሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው የግንባታው ክፍያ ሰርተፊኬት ቀርቦ ሥራው ለመከናወኑ ሳይረጋገጥ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ

2. የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ለፋና ብሮድካስቲንግ እና ለታደለ ገብሬ ህንፃ ስራ ተቋራጭ በቅድሚያ ብር 403,936.40 ክፍያ ሲፈጸም ለክፍያው ማስረጃ

እስኪቀርብ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

5.32.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ለምዝገባው አስፈላጊዉ ማስተካከያ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ምዝገባ ሲከናወን ከላይ በተገለጸው መሰረት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.34 በወጪ መመዝገብ ሲገባው በተሰብሳቢ የተመዘገበ ሂሳብ፤

5.34.1 ግኝት

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት የወጪ ሂሳቦች በተገቢው የሒሳብ መደብ የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት በት በአውሮፓ ኢንቬስትመንት ባንክና በአውሮፓ ሕብረት ብድርና እርዳታ ለሚከናወነው ለ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ግንባታ ለፈጸመው ክፍያ ብር 10,675,268.31 የክፍያ የምስክር ወረቀትን ጨምሮ ሁሉም አሰፈላጊ ማስረጃዎች ቢቀርቡለትም ሂሳቡ በወጪ መመዝገብ ሲገባዉ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.34.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ለአመዘጋገብ ስህተቱ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም በወጪ ሂሳቦች አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.35 ሊቀርቡ የሚገባቸው ማስረጃዎች ሳይቀርቡ ለመንገድ ግንባታ የተፈጸሙ ክፍያዎች ስለመኖራቸው፤

5.35.1 ግኝት

የአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ጳውሎስ ዘለቀ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ የኮሌጁን የውስጥ ለውስጥ የመንገድ ሥራ ላከናወነበት ብር 4,099,865.18 ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም፡

- ተቋራጩ ሥራውን ስለመስራቱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ (Take-off Sheet) እንዲቀርብ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በግዥ መመሪያው ክፍል 7 አንቀጽ 28.5(ሀ) መሰረት ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ክፍያ የሚፈጸመው የሥራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲሱ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ መሆን እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም የክፍያ የምስክር ወረቀት (Payment Certificate) እንዲቀርብ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የመንገዱ ሥራ በአግባቡና በውሉ መሰረት መፈጸሙን የሚያረጋጋጥ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ያልተመደበ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

5.35.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የመንገድ ሥራው ጥራቱ ተጠብቆ እንዲሰራ በግዥ መመሪያው መሰረት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች እንዲሟሉ ተደርጎ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ፤ ለወደፊቱ ኮሌጁ እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት የግዥ መመሪያውን ተከትሎ መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.36 በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ያልተመዘገበና ያልተፈጸመ የኮንትራክተር ክፍያ፤

5.36.1 ግኝት

የኢንዱስትሪ፣ የማዕድን፣ የአካባቢና ደን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፤ የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት፤ የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃ

ባለሥልጣን ፣ የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን፣ የአማኑኤል ሆስፒታልና የአለርት ማዕከል ለሚያስገነቡት ግንባታ ከተለያዩ ኮንትራክተሮች ጋር ባደረጉት ሥምምነት መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎችና የአመዘጋገብ ሥርዓቱ መመሪያን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ የነበረበት የቅድሚያ ሂሳብ በወጪ በመመዝገቡ፣ የመያዣ ሂሳብ፣ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ እንዲሁም በመስክ ላይ ለሚገኙ ዕቃዎች የተፈጸመው ክፍያ ምዝገባ ሳይከናወን አየር በአየር ከክፍያ ሰርተፊኬቱ ላይ ብቻ እንዲቀናነስ የሚደረግ በመሆኑ፣ የቅድሚያ ግብር በሕጉ መሰረት እንዲቀነስ ባለመደረጉ፣ በተለያዩ የስሌት ስህተቶችና በመሳሰሉት ምክንያቶች ቀጥሎ የተመለከቱት ልዩነቶች ታይተዋል።

- በብልጫ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ብር 37,792,667.88፤
- በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ ብር 89,419,155.80፤
- ያልተሰበሰበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 4,977,146.17፣
- ያልተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ ሂሳብ ብር 457,100.73፤
- በብልጫ የተሰበሰበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 612,447.86፤
- በብልጫ የተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ ብር 243,636.39 ፤
- ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ ብር 16,964,469.94 ፤
- በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,254,319.83 ፤
- ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 989,953.36 ፤
- በብልጫ የተቀነሰ የቅድሚያ ግብር ብር 6,645,668.46 ፤
- ያልተቀነሰ የቅድሚያ ግብር ብር 175,324.75፤
- በተሰብሳቢ መያዝ የሌለበት ሒሳብ ብር 15,011,841.79 ፤
- በተሰብሳቢ ያልተያዘ ሒሳብ ብር 96,696,445.13 ፤
- በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ 3,620,589.56 ፤
- ያልተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ብር 15,494,378.50፤
- በአለርት ሆስፒታል የለውጥ ሥራ ትዕዛዝ ተብሎ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ለተፈጸመው ክፍያ ብር 315,215.25 ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ቀርቦ ለመጽደቁ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከአስራ ሰባት በላይ ኮንትራክተሮች የኢንዱስትሪ መንደር ግንባታን የሚያከናውኑ ሲሆን፣ የእያንዳንዱን የግንባታ ሥራ ክፍያን ለመቆጣጠር የሚያስችል ተቀጽላ ሌጀር እንዲቋቋምላቸው ያልተደረገ መሆኑ፤
- የማዕድን ሚኒስቴር በሳይት ላይ ለሚገኙ ዕቃዎች ክፍያ እንዲፈጸም በህጉ ያልተፈቀደ ሆኖ ሳለ ብር 45,825,426.99 በሳይት ላይ ለሚገኙ ዕቃዎች ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ለኮንስትራክሽን ድርጅቶቹ ከፈጸመው ክፍያ ውስጥ ለብር 1,893,367.77 የክፍያ ደረሰኝ (ማስረጃ) ያልቀረበለት መሆኑ፤

ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በዚሁ ጥራዝ አባሪ- 5 ተያይዟል፡፡/

5.34.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በአመዘጋገብ ላይ ለታዩት ስህተቶች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ መደረግ እንዳለበት፤ መከፈል ያለበት ሂሳብም እንዲከፈል፤ መሰብሰብ ያለበት እንዲሰበሰብ፤ ለወደፊቱም በኮንስትራክሽን ክፍያ አፈጻጸምና አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.37 በሚመለከተው ኃላፊ ያልጸደቁ የወጪ ሂሳቦች፤

5.37.1 ግኝት

የወጪ ሂሳቦች ወጪን ለማጽደቅ ሥልጣን በተሰጣቸው ኃላፊዎች የሚጸድቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የጽዳት ዕቃ (የሽንት ቤት መርዝ) ለተገዛበት የተፈጸመው ክፍያ ብር 296,201.27 እንዲሁም የኮሌጁ ተማሪዎች ለህብረተሰብ ጤና ትምህርት ዓላማ ሞጆ ሲሄዱ ለውሎ አበል የተከፈለው ሂሳብ ብር 41,631.00 በድምሩ ብር 337,832.27 ወጪዎች ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ ያልጸደቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.37.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ወጪዎቹ ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ ካልጸደቁ ወጪዎቹን ተቀባይነት እና ታዓማኒነት ሊያሳጣው ስለሚችል፣ ወጪዎቹ ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ እንዲጸድቁ መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.38 <u>ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ</u> ፤

5.38.1 <u>ግኝት</u>

በበጀት ዓመቱ የተከፈለውን የደመወዝ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ በውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ከሥራ ከለቀቁ በኋላ ለሶስት ሰራተኞች ብር 2,513.00 የደመወዝ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.38.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

አለአግባብ የተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱ እንዲህ ዓይነቱ ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.39 <u>ለመስተንግዶ ተብሎ ለየክፍሉ የታደሉ ለመጠጥ አግልግሎት የሚውሉ ሸቀጦች</u>፤

5.39.1 <u>ግኝት</u>

የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን የመስተንግዶን በጀት የሚጠቀምበትን አግባብ ለማጣራት በናሙና ኦዲት ሲደረግ ለመስተንግዶ ተብሎ ከተያዘዉ በጀት ዉስጥ በብር 18,153.12 ስኳር፤ ሻይ ቅጠል፤ ቡና፤ የታሸገ ዉሃና ቆሎ ግዥ ተፈጽሞ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ከተደረገ በኋላ ለየዳሬክቶሬቶቹና ለየክፍሎቹ በንብረት ወጪ ደረሰኝ ወጪ ተደርጎ የሚታደል መሆኑ ታውቋል፡፡ አፈጻጸሙ በጀቱ ሥራ ላይ እንዲውል የተፈቀደበትን አካሔድ ያልተከተለ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.39.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

አሰራሩ ተገቢ ስላልሆነ በአስቸኳይ እንዲስተካከል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.40 <u>በፋይናንስ አስተዳደር የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ የታዩ ክፍተቶች</u> ፤

5.40.1 <u>ግኝት</u>

1. <u>*የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል*</u>
   - በማዕከሉ በጀትን ለመቆጣጠር የሚያስችል የበጀት ሌጀር ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፤
   - ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
2. <u>**በሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች**</u>፤
   - የአዋሳና የኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬቶች ከዋናው መሥሪያ ቤት ለሥራ ማስኬጃና ለደመወዝ በባንክ በኩል ለሚላከው ገንዘብ የገቢ ደረሰኝ ያልቆረጠላቸው መሆኑ፣
   - የአዋሳና የኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬቶች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለቀነሰው 2% የቅድሚያ ግብር ደረሰኝ ያላዘጋጀላቸው መሆኑ፣
   - የኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬት ቀንሶ ለሚያስቀረው 15% የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ ያላዘጋጀላቸው መሆኑ፣
3. በማሪታይም ጉዳዮች ባለስልጣን የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተደረገና ከመዝገብ (ከሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
4. <u>**በኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በደቡብና በምስራቅ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች**</u>፣
   - በሁለቱም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በየወሩ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፣
   - በሁለቱም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

- በበሁለቱም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ከ2005 በጀት አመት ወደ 2006 በጀት አመት የዞረው የጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ ሒሳብ ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ መሆኑ፤

- በሁለቱም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ከዋናው መሥሪያ ቤት ለስራ ማስኬጃና ለደሞዝ ለሚላከው ገንዘብ የገቢ ደረሰኝ (RV) ያልተቆረጠለት መሆኑ፣

- በሁለቱም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ (መሂ/9)፣ የሒሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (መሂ/23)፣ አጠቃላይ የሂሣብ ቋት (General ledger)፣ የተቀፅላ የሂሳብ ቋት (Subsidiary Ledger) ያልተቋቋመ መሆኑ፣

- በሁለቱም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የበጀት መቆጣጠሪያ ቋት ያልተቋቋመ መሆኑ፣

- በሁለቱም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ከባንክ ሂሳብ ለሚወጡ ሂሳቦች የባንክ ወጪ ማዘዣ (BPV) የማይዘጋጅላቸውና አስፈላጊው ኢንትሪም የማይሰራላቸው መሆኑ፣

- ለሁለቱም ቅ/ጽ/ቤቶች የፒቲ ካሽ የተቋቋመ ቢሆንም የፒቲ ካሽ ጣሪያ ያልተወሰነ መሆኑ፣

5. በማዕድን ሚኒስቴር

- ✓ በአዲሱ የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት ቀርስ፤ ምሳና እራት በተጠቀመበት ቦታ (ከተማ) እንዲሁም የአልጋ ክፍያ በጉዞ ወቅት ባደሩበት አካባቢ በወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት በዝርዝር ታስቦ መሞላትና መከፈል ሲገባው በመንገድ ላይ ቁርስ፣ ምሳና ዕራት የተጠቀሙበት ቦታ የማይሞላ መሆኑ፤

- ✓ በየወሩ የሚከፍለውን ደመወዝ ጠቅላላ ተቀናናሾች የሚያሳይ ዝርዝር የደመወዝ መክፈያ ፔይሮል (Payroll Sheet) ሊያቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤

6. የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬዩ ላባራቶሪ ምርመራ ጥናት አገልግሎት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በፀደቀው የማሻሻያ ታሪፍ/ ተመን መሰረት በትክል መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ሰርቬዩ የሶፍት ኮፒ ሽያጭ ሲያደርግ ለየትኛው አቅርቦት (ሽያጭ) ገቢው እንደሰበሰበ የሚያሳይ ነገር (የገቢው ምክንያት ወይም ሌላ ተያያዥ ሰነድ) ባለመኖሩ የሽያጭ ገቢው በታሪፉ መሰረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

5.35.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መንግሥት ያወጣውን የፋይናንስ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ተከትሎ መፈጸም ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መጠናከር ስለሚረዳ መሥሪያ ቤቶቹ የተጠቀሱትን የአሰራር ክፍተቶች በዚህ አግባብ መፈጸም ወይም ማስተካከል እንደለባቸው አሳስበናል፡፡

6. <u>ንብረት</u>

6.1 ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች ያለው የንብረት አስተዳደር ሥርዓቱ መንግሥት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

6.1.1 <u>ግኝት</u>

1. <u>የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ</u>

- ✓ በቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት 5 የብረት ቁም ሳጥን ውስጥ ምንነታቸው የማይታወቅ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ በዕርዳታ ለሚገቡ ዕቃዎች ምዝገባ ቢካሄድም የዕቃዎቹ ዋጋ የማይጠቀስ መሆኑ፤
- ✓ በተማሪዎች ክሊኒክ ውስጥ በርካታ የህክምና ዕቃዎች ቢኖሩም በሰለጠነ የሰው ሀይል ምክንያት ያለአገልግሎት ታሽጎባቸው የሚገኙ መሆኑ፤

2. <u>የአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

ጳውሎስ ዘለቀ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ለኮሌጁ የውስጥ ለውስጥ የመንገድ ሥራ ብር 785,040.82 የሚገመት 34,078 ሊትር ነዳጅ ከኮሌጁ የነዳጅ ዲፖ በብድር የወሰደ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 11,261.40 ሊትር ነዳጅ በሊትር ብር 17.169 በጠቅላላ ብር 193,346.97 ኮሌጁ ለተቋራጩ ከፈጸመው አጠቃላይ የኮንትራት ክፍያው በተጨማሪ ከውል ውጭ ለተሰሩ ስራዎች በማካካሻነት በሚል እንዲሰጠው የተደረገ መሆኑ፤

3. <u>በሕብረት ሥራ ኤጀንሲ</u>

- ✓ ለቋሚ ንብረቶች በተሟላ መልኩ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣
- ✓ ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ወይም እንዲወገዱ ያልተደረጉ ንብረቶች በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ መሆኑ ፣ (ለምሳሌ ያህል ቁጥራቸው የማይታወቅ ጎማዎች፣ 10 ኮምፒዩተሮች እና 3 ፕሪንተሮች)
- ✓ የ2002፣ የ2003፣ የ2004 እንዲሁም የ2005 እትም በርካታ መጽሄቶች በብዛት ከፍላጎት በላይ ታትመው አገለልግሎት ሳይሰጡ በስቶር ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ ግምቱ ከአንድ ሺ በላይ የሚሆን እስቶክ ካርድ በስቶር ውስጥ ተካማችቶ እያለ ሌላ ብዛቱ ሁለት ሺ እንዲገዛ የተደረገ መሆኑ፣
- ✓ በኤጀንሲው ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያልተዘጋጀላቸው 2 ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፤

4. በኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ልማት ኢንዱስትሪ ኢንስቲትዩት እስቶክ ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም ምዝገባው በተሟላ መልኩ ያልተከናወ መሆኑ፣

5. **<u>በብሔራዊ ሚቲሪዎሎጂ ኤጀንሲና በቅርንጫፍ ጽህፈትቤቶች</u>**

5.1 <u>በኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት</u>፡

- የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠላቸው ዕቃዎች አልፎ አልፎ በእስቶክ ካርድ ላይ ሳይመዘገቡ የተገኙ መሆኑ፣
- የዕቃ ግምጃ ቤቱ ኃላፊ የንብረት ወጪ ደረሰኝ የሚያዘጋጅ መሆኑ፣

5.2 በአዋሳ ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬት ስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣

5.3 **<u>የኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬት</u>**

- ከዋናው መሥሪያ ቤት በሞዴል 22 ወጭ ሆነው ወደ ለተላኩ የሚትዎሮሎጂ ቻርት (መሳሪያዎች) በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ያልተቆረጠላቸው መሆኑ፣
- የንብረት መጠበቅ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ማዘጋጀት በንብረት ሠራተኛው የሚሰሩ መሆኑ፣
- ስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣

6. **በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን** ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፣

7. **<u>በአለርት ማዕከል</u>**

✓ ቋሚ ዕቃዎች ለአገልግሎት ወጪ ሲሆኑ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ለቋሚ ዕቃዎች ባወጣው የንብረት አስተዳደር ማንዋል (ጎፋም) መሰረት በተጠቃሚዎቹ ሥም (User Card) ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

✓ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ያአገልግሎት ከ10 ዓመት በላይ ያስቆጠሩ መሆኑ፤

✓ የጽሕፈት ዕቃዎች ፤የመኪና መለዋወጫ ፤የህትመት ወረቀቶች፤ የህክምና እቃዎች ፤ ካርቦን ፤ የኮምፒውተር ቀለሞች ፤ ቦክስ

ፋሎች የመሳሳሉት ብዛት ያላቸው ዕቃዎች ሳይወገዱ ለረጅም አመታት በኮንቴነር ውስጥ እና በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

- ✓ የልዩ ፋርማሲ የመድሃኒት ቤት ሞዴል 19 ፣ ሞዴል 22 እና ስቶክ ካርድ የማይጠቀም መሆኑ፤
- ✓ በመደበኛ ፋርማሲ ዕቃ ግምጃ ቤት የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች ሳይወገዱ ከአንድ አመት በላይ የቆዩ መሆናቸው፤

8. <u>በገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል</u>

- ✓ በ2006 በጀት አመ ት በብር 25,000.00 ወጪ የተገዛ የዉሃ ማጠራቀሚያ ሮቶ ተገቢ የሆነ ቦታ ሳይዘጋጅለት ተገዝቶ ለብልሽት የተጋለጠ ቦታ በመቀመጡ አገልገሎት ሳይሰጥ ተቀዶ ሜዳ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ንብረቶች የመለያ ኮድ የተሰጣቸው ቢሆንም የመለያ ኮድ አሰጣጡ የመንግሥት የንብረት አስተዳደር ማነዋሉን መሰረት ያላደረገ መሆኑ፤
- ✓ ብር 800,000.00 የሚያወጡ በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ ያልዋሉና ፈሰስ ሊደረጉ የሚገባቸው የነዳጅ ኩፖኖች ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ቁጥር 297103 ከንብረት ክፍል ወጪ ተደርገው በሂሳብ ክፍል የተገኙ መሆኑ፤

9. <u>በብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል</u>

- ✓ በአላቂና ቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት በተወሰኑ ዕቃዎች ላይ በቆጠራ የተገኘውና በቢን ካርድ ላይ የተመለከተው መጠን ተመሳሳይ ቢሆንም ቆጠራው በስቶክ ካርድ ላይ ከተመዘገበው መጠን ጋር የማይጣጣም መሆኑ፤
- ✓ በዕርዳታ ለገቡ ዕቃዎች ምዝገባ የተከናወነ ቢሆንም ዋጋ ያልተተከለላቸው መሆኑ፤

- ✓ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ የገቡ በርካታ ኬሚካሎች የተበላሹና በሠራተኞች ላይ የጤና ችግር እያስከተሉ ቢሆኑም እንዲወገዱ ያልተደረጉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ አገልግሎት ከሚሰጡት ኬሚካሎች ጋር ተቀላቅለው በአንድ መጋዘን የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ የመለዋወጫና የላብራቶር ዕቃዎች በአንድ ግምጃ ቤት የተቀመጡ በመሆኑ ለአሰራር እና ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ መልኩ በሁለት የግምጃ ቤት ኃላፊዎች እጅ ቁልፍ የሚገኝ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎት በሰጡ ዕቃዎች ግምጃ ቤት(salvage store) ውስጥ በርካታ ጎማዎች ፤ ወንበሮች ፤ ጠረጴዛዎች እና ሌሎች በርካታ ዕቃዎች እንዲወገዱ ሲገባቸው ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

10. <u>የቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል</u>

- ✓ ለቡና ናሙና ለሚሰበሰበው ቡና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ የቢሮ ዕቃዎች፣ ሽልፍ ፣ ወንበሮች፣ የመኪና ጎማዎች፣ የብረት ካብኔት፣ ኮምፒዉተር የተሰባበረ ብረት፤ የመኪና አሞርዛተር እና የመሳሰሉት ንብረቶች በመጋዘን ተከማችተዉ የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ በበጀት ዓመቱ የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ ገቢና ወጪ የሆኑ የተለያዩ ንብረቶች በስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ ላይ የማይመዘገቡ መሆኑ፤

11. <u>በፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን</u>

- ✓ በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ያደረገ ቢሆንም የንብረት ትክክለኛነት ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመሳከር ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ንብረቱ ተጠቃሚ ሰዎች የንብረት ምዝገባ ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፣

12. በጤና መድኅን ኤጀንሲ የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፣

13. <u>በአካባቢና ደን ሚኒስቴር</u>

- ✓ በንብረት ክፍሉ ብዛታቸው 51 ዲል (DELL) ኮምፒዩተሮችና 10 ላፕቶፕ ኮምፒተሮች የማያገለግሉትና የሚሰሩት በባለሙያ ሳይታዩ በመሬት ላይ በአንድ ላይ ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ መወገድ የሚገባቸው የተለያዩ በርካታ ዕቃዎች፣ ጠረጴዛዎች፤ ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ የመኪና ጎማዎች የመሳሰሉት ንብረቶች ያልተወገዱ መሆኑ፣
- ✓ ተመላሽ ለሚሆኑ ዕቃዎች ለምሳሌ ላፕቶፖች፤ ኮምፒተሮች፤ ወንበሮች እና ለመሳሰሉት ንብረቶች የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) እንዲሁም ወጪ ሲደረጉ የንብረት ወጪ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው መሆኑ፤
- ✓ መወገድ የሚገባቸዉና በብልሽት የቆሙ 3 መኪኖች ያለአገልግሎት ከ6 እስከ 11 አመት የቆዩ መርቸዲስ የሰሌዳ ቁጥር 4-00855 ፤ ቶዮታ ፒካፕ የሰሌዳ ቁጥር 4-01090 እንዲሁም መርቸዲስ የሰሌዳ ቁጥር 4-28752 የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ ከ2003 በጀት አመት በፊት ብዛታቸው 60 የሚሆን የፎቶ ኮፒ ቀለሞች በወቅቱ በነበረው ዋጋ ብር 19,280.00 የሚያወጣ ያለምንም አገልግሎት በመጋዘን ውስጥ ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ በግለሰብ ስምና በመሥሪያ ቤቱ ስም የተዘጋጁ ብዛታቸው አንድ መቶ አንድ (101) የሚሆኑ ቲተሮች ያለምንም አገልግሎት በንብረት ክፍሉ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፤

14. <u>በዱር እንስሳና ጥበቃ ባለሥልጣን</u>

- ✓ የንብረት ቆጠራ በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው ከመዝገብ ወይም ከስቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ መሆኑ፣
- ✓ ቋሚ ንብረቶች የመለያ ቁጥር ተሚልቶ ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

15. <u>በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል</u>

- ✓ የቋሚና አላቂ ንብረት ክፍልና የምግብ ጥሬ እቃዎች ንብረት ክፍል እንዲሁም በዋናው መድኃኒት ቤት ሠራተኞች የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ የማዘጋጀትና ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት ሥራን ደርበው የሚሰሩ መሆኑ፤
- ✓ በዋናው መድኃኒት ቤት የመድኃኒት ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ) ያልተቋቋመና ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፤
- ✓ በመድኃኒት ስርጭት ክፍሎች የሚሰሩ ሰራተኞች ከዋናው መድኃኒት ቤት በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ወጪ አድርገው የወሰዱትን መድኃኒት ለተጠቃሚው የሚያከፋፍሉበትና የሚቆጣጠሩበት ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤
- ✓ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የተለያዩ መድኃኒቶች ሳይወገዱ ያለአገልግሎት ተቀመጥው የሚገኙ መሆኑ፤

16. <u>በስትራተጂክ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ</u>

- ✓ በኮምቦልቻ እና በአዳማ የእህል መጋዘኖች ተመሳሳይ የሆኑ የስንዴ እህሎች በምድር ሚዛን እና በእጅ ሚዛን ሲመዘኑ የኪሎ ግራም ልዩነት የሚያሳዩ ሲሆን፣ ይህ ሁኔታ ክፍተት ሊፈጥር የሚችል መሆኑ፤ (ለምሳሌ በእጅ ሚዛን የተመዘኑ 48, 49 እና 50 ኪሎ ግራም የሚመዝኑ የስንዴ እህሎች በምድር ሚዛን ሲመዝኑ 40 እና 60 ኪሎ ግራም መሆናቸው፤)

- ✓ በኮምቦልቻ የመገልገያ እቃዎችና ፀረ ተባይ ኬሚካል በአንድ ግምጃ ቤት ውስጥ በተዘበራረቀ ሁኔታ ተቀመጠው የተገኙ መሆኑ ፣

17. **<u>በውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት</u>**

- ✓ የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው ተደርበው የሚሰሩ መሆኑ፤
- ✓ ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት በሞዴል 19 ተመላሽ የተደረጉ ንብረቶች በእስቶክ እና በቢን ካርድ የማይመዘገቡ መሆኑ፤
- ✓ ጽህፈት ቤቱን የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ ለማድረጋቸዉ ወይም ወደ ሌላ ሰዉ ለማስተላለፋቸዉ ማስረጃ ያልቀረበላቸው ንብረቶች መኖራቸው፤

18. **<u>በማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን</u>**

- ✓ ቋሚ ዕቃ ከግምጃ ቤት ወጪ ሲደረግ በሰራተኞች እጅ የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች የሚመዘገቡና የተወሰኑ ቋሚ ዕቃዎች ያልተመዘገቡ ሲሆኑ የንብረቱ ተጠቃሚዎችም የንብረት ምዝገባ ካርድ (User Card) ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
- ✓ ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- ✓ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ንብረቱ እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች የተሟላ መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ የሚሆን ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ እየተሠራበት ያለመሆኑ
- ✓ የንብረት መዝጋቢ ሠራተኛ ያልተመደበ መሆኑ፤
- ✓ ዕቃ ከንብረት ክፍል ወጪ ሲደረግ በአብዛኛው የዕቃ ወጪ ደረሰኝ ላይ ተቀባዩ ንብረቱን ለመዉሰዱ ሳይፈረም ወጪ የተደረጉ ዋጋቸው ብር 20,671.37 የሚያወጡ ንብረቶች መኖራቸው፤

19. በማዕድን ሚኒስቴር ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ተሟልቶ ያልተሰጠ መሆኑ፤

20. በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአሮጌ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ 60 ትልልቅ የመኪና ጎማዎች ፣ 25 ትንንሽ ጎማዎች እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፣

21. በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር እየተሰጠው በቋሚ ንብረቱ ላይ መለጠፍ ወይም መጻፍ ሲገባው ይህ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

22. <u>በኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት</u>

- ✓ በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ንብረቶች በንብረት መቆጣጠሪያ ካርድ ላይ ተመዝግበው ያልተገኙ መሆኑ፤
- ✓ መወገድ የሚገባቸው የተለያዩ በርካታ ዕቃዎች፣ ጠረጴዛዎች፤ ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ የመኪና ጎማዎች፤ ኮምፒተሮች፤ ሁለት ሱዚኪ ሞተር ሳይክሎች፤ አንድ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር እና አንድ ማርቼዲስ መኪና እንዲሁም በርካታ የተለያዩ ንብረቶች ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፤
- ✓ በሞ/19 ገቢ የተደረጉና በሞ/22 ወጪ የተደረጉ ዕቃዎች አልፎ አልፎ በስቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፤
- ✓ በ2005 በጀት ዓመት የተገዙ ቋሚ ዕቃዎች በቋሚ ዕቃ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣

23. <u>በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>

- ✓ በህክምና ኮሌጁ ቋሚ ዕቃዎች ከግምጃ ቤት ወጪ ሲደረጉ በሠራተኞች እጅ የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች የንብረት ተጠቃሚዎች የንብረት ምዝገባ ካርድ (User Card) በተሟላ ሁኔታ አይሰራበትም፡፡

- ✓ በመድሃኒትና የህክምና ዕቃዎች ፣ በምግብ ማደራጃ ፣ በመለዋወጫ ዕቃዎች እንዲሁም በቴክኒክ ዕቃዎች ንብረት ክፍሎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል/19 የሚዘጋጀው በዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኞች (ጠባቂዎች) መሆኑ ታውቋል፡፡

24. በውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተሽከርካሪዎች ጥገናና እድሳት ሰያደርግ በአዲስ የተቀየሩ አሮጌ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች (ለምሳሌ የግጭት መከላከያ፤ ጎማና ለመሳሰሉት) በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል19) ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤

25. <u>በኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን</u>፤

    1. <u>በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ</u>፣

        - ♦ በአሮጌ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ 13 አይነታቸው የተለያየ ኮምፒውተሮች፣ የሰው ሚዛን፣ የወረቀት መብሻ፣ እስቴፕለር መምቻ፣ ማሾ፣ የቤት ቆርቆሮዎች እና የመሳሰሉት የሚገኙ ቢሆንም እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፣
        - ♦ የላቦራቶሪ ኬሚካል ግምጃ ቤት ቬንትሌተር እና የእሳት አደጋ መከላከያ የሌለው መሆኑ፣
        - ♦ ፓስተር በሚገኘው ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በርካታ ከአገልግሎት ወጪ የሆኑ ፈሳሽ ኬሚካሎች ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣ በሌላ መጋዘን ውስጥ ደግሞ የሚያገለግሉ ኬሚካሎች፣ የላቦራቶሪ ዕቃ፣ ግላስ፣ በላይ በላይ ተደራርበው የሚገኙ መሆኑ፣
        - ♦ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደና ማመዛዘኛ ያልተሰራ መሆኑ፣
        - ♦ ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

2. <u>**በደቡብ እና በምሥራቅ ቅ/ጽ/ቤቶች**</u> ፣

- በቅ/ጽ/ቤቶቹ በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ያላደረገ መሆኑ፣
- በቅ/ጽ/ቤቶቹ የንብረት መመዝገብ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞ/22 ማዘጋጀት እና የንብረት መጠበቅ ሥራ በአንድ የንብረት ሰራተኛ ኃላፊነት የሚከናወኑ መሆኑ፣
- በደቡብ ቅ/ጽ/ቤት የቋሚና የአላቂ እቃዎች ከሚያዚያ 2006 ዓ.ም ጀምሮ እንዲሁም በምስራቅ ቅ/ጽ/ቤት ከየካቲት 2006 ዓ.ም አብዛኛው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ እቃዎች በንብረት ገቢ (ሞ/19) ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፣
- በደቡብ ቅ/ጽ/ቤት ለቋሚና አላቂ ንብረት መቆጣጠሪያ የሚሆን መዝገብ ያቋቋመ ቢሆንም ምዝገባው ተሟልቶ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በምስራቅ ቅ/ጽ/ቤት ለቋሚና አላቂ ንብረት መቆጣጠሪያ የሚሆን መዝገብ (እስቶክ ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በሁለቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ለቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር ተሟልቶ ያልተሰጠ መሆኑ፣
- በሁለቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ለንብረቱ ተጠቃሚ ሰዎች የንብረት ምዝገባ ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፣
- በሁለቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች የተሟላ መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ የሚሆን ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በምሥራቅ ቅ/ጽ/ቤት ከዋናው መ/ቤት ለሚላኩ የተለያዩ ደረሰኞች ገቢ ሲደረጉ ሞዴል 19፤ ወጪ ሲደረጉ ደግሞ ሞዴል 22 ያልተቆረጠላቸው መሆኑ፤

- በደቡብ ቅ/ጽ/ቤትአገልግሎት የማይሰጡ 4 ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ 2 ኮምፒውተሮች፣ 1 ኤል ሴፐ ጠረጴዛ እና 1 ዩፒስ ሳይወገዱ በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣

26 በአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን ንብረት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት አሮጌ ጎማዎች ፣ የተለያዩ የመኪናዎች መለዋወጫዎች፣ የተለያዩ ብረታ ብረቶች፣ ኮምፒውተሮች፣ ወንበሮች፣ ስካነሮች፣ የመደመርያ ማሽኖች፣ ታይፐራይተሮች፣ ፐሪንተሮች፣ ሌዝ ማሽን፣ ፓውዛዎች፣ ማባዣ ማሽን፣ ፍሪጂች፣ ዩፒኤስ (UPS)፣ ስታብላይዘሮች፣ መጠረዣ፣ የመኪና ባትሪዎች፣ የውኃ ሞተር፣ የሠነድ መያዣ ቦርሳዎች፣ በርሜሎች፣ የብረትና የእንጨት አልጋዎች፣ ፍራሾች፣ የአየር ማቀዝቀዣዎች (ኤየር ኮንዲሽነሮች) ፣ ካናል ውኃ መጠን መለኪያ፣ የወተት ማስቀመጫ ጋኖች፣ ስሊንደሮች፣ ስቶቮች፣ የእጅ ጋሪዎች፣ የመጽሃፍ መደርደርያዎች፣ የቪድዮ ካሴቶች፣ የፎቶ ኮፒ ማሽን፣ የልብስ ማጠብያ ማሽን፣ የጀልባ ሞተሮች፣ የመገናና ሬድዮዎች እና የመሳሰሉት የሚገኙ ሲሆን በደንቡ መሰረት ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ መጠገን የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤

6.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል ተገቢው ጥረት መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

6.2 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም

6.2.1 ግኝት

በየመሥሪያ ቤቶች ውስጥ ያለው የተሽከርካሪዎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትና መረጃ አያያዝ በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

1. <u>በብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል</u>

- ✓ የሠሌዳ ቁጥር ዩኤን 0557 ቶዮታ መኪና ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ እንዲሁም ሠሌዳ ቁጥር 4-15259 ላንድሮቨር መኪና ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ በማዕከሉ የሚገኙ 5 ተሽከርካሪዎች በቀላልና ከባድ ብልሽት ምክንያት ከ1 ወር እስከ 9 ወር ድረስ ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ የሠሌዳ ቁጥር 4-03768 ሊብሬ የሌለው መሆኑ፣

2. <u>በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ</u>

- ✓ በተሽከርካሪዎቹ ሁለቱም የፊት በሮች ጎን ላይ የኮሌጁን ስም የሚያመለክት መለያ ወይም አርማ ያልተለጠፈ መሆኑ፣
- ✓ 3 ሞተር ሳይክሎች እና 1 ትራክተር የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርና (ሊብሬ) ታርጋ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፣
- ✓ በርካታ አገልገሎት ሊሰጡ የሚችሉ ተሽከርካሪዎች በኮሌጁ ጋራዥ ውስጥ እና በተለያዩ ካምፓኒዎች በከባድና ቀላል ብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ ሊወገዱ የሚገባቸው 2 ትራክተሮች እና 1 ኮምባይነር በኮሌጁ ጋራዥ ውስጥ ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ 3 ትራክተሮች በኮሌጁ ግቢ እና በተለያዩ ካምፓኒዎች ለረጅም ጊዜ ቆመው የሚገኙ መሆኑ፤

3. በኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያልተዘጋጀላቸው 13 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤

4. በአካባቢና ደን ሚኒስቴር መወገድ የሚገባቸዉና በብልሽት የቆሙ 3 መኪኖች ያለአገልግሎት ከ6 እስከ 11 አመት የቆዩ መርቸዲስ የሰሌዳ ቁጥር 4-00855 ፤ ቶዮታ ፒካፕ የሰሌዳ ቁጥር 4-01090 እንዲሁም መርቸዲስ የሰሌዳ ቁጥር 4-28752 የሚገኙ መሆኑ፤

5. <u>**በአማኑኤል ሆስፒታል**</u>

- ✓ ሁለት ላንድ ክሩዘር ተሽከርካሪዎች ከ 4 እስከ 7 ወራት ድረስ በብልሽት አገልግሎት ሳይሰጡ ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ አንድ ላንድ ክሩዘር ተሽከርካሪ ከአለርት ማዕከል የመጣ ሲሆን፣ ከሁለት ዓመት በላይ በብልሽት የቆመ መሆኑ፣
- ✓ ሁለት የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ አውቶቡሶች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸውና ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑ፣
- ✓ ተሽከርካሪዎች መለያ ወይም አርማ ያለጠፉ መሆኑ፣

6. <u>**በውኃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር**</u>

- ✓ ለመሥሪያ ቤቱ ተሽከርካሪዎች አዲሰ መለዋወጫዎች ሲቀየሩ አሮጌዎቹ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ የማይደረጉ መሆኑ፤
- ✓ መሥሪያ ቤቱ የተሽከርካሪዎች ጥገናና እድሳት ሰያደርግ በአዲስ የተቀየሩ አሮጌ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች (ለምሳሌ የግጭት መከላከያ፤ ጎማና ለመሳሰሉት) የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል19) ገቢ የማደረጉ መሆኑ፣
- ✓ ኢንሹራንሰ የተገባላቸዉ ተሽከርካሪዎች የኢንሹራንሰ ፕሪሚየም ክፍያ ብር 121,646.76 የተፈጸመላቸው አስር ተሽከርካሪዎች የመሥሪያ ቤቱ ለመሆናቸው ሊቢሬ ሊቀርብላቸው ያልቻለ መሆኑ

7. በአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን ስምንት የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪዎች ከ1 ወር እስከ 5 ዓመታት፣ ሌሎች የብልሽት ጊዜያቸው የማይታወቅ 8 ተሽከርካሪዎች ደግሞ አገልግሎት ሳይሰጡ ለረጅም ጊዜ የቆሙ መሆኑ፣

8. በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የመኪና ማቆሚያ ውስጥ ለረጅም ዓመታት ተበላሽተው የቆሙ ሰባት ተሽከርካሪዎች የተገኙ መሆኑ፣

9. **<u>በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>**

- ✓ ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 4-03253 ኒሳን የጭነት ተሽከርካሪ መኪና ጳጉሜ 5 ቀን 1999 ዓ.ም በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ ለምስራቅ አዲስ ዲስትሪክት የኢትዮጵያ መድን ደርጅት እንዲጠገን ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ዲስትሪክቱ ወደ ቀድሞ ይዞታው እንዲመለስ የስራ ትዕዛዝ ተከፍቶለት ተሽከርካሪው በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ጋራዥ ለጥገና እንደተሰጠ ታውቋል፡፡ሆኖም ተሽከርካሪው ተጠግኖ ለመሥሪያ ቤቱ እንዲመለስ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ 18 ተሽከርካሪዎች ንብረትነታቸው የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የሆኑ በሞዴል 22 ቁጥር 52960፣ 52971፣ 52957፣ 52958፣ 52959፣ 52984፣ 52986 እና 52992 ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በትውስት ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፐሬሽን በደብዳቤ ተሰጥተው የነበረና ሰርቬዩም ለኮርፐሬሽኑ ተሽከርካሪዎቹ እንዲመለሱለት በደብዳቤ የጠየቀ ቢሆንም ተሽከርካሪዎቹ ተመላሽ ያልተደረጉ መሆኑ፣
- ✓ ከአስራ አምስት ተሽከርካሪዎች በላይ የኪሎ ሜትር ንባባቸው የማይሰራ መሆኑ፣

10. በማዕድን ሚኒስቴር 13 የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪዎች ከ1 ወራት እስከ 20 ዓመታት ድረስ በብልሽት የቆሙ እና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

11. በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል

- ✓ አንድ ላንድ ክሩዘር ተሽከርካሪ (ኮድ 8 ዕ.ድ 036) ከአለርት ማዕከል የመጣ ሲሆን፣ ከሁለት ዓመት በላይ በብልሽት የቆመ መሆኑ፣

✓ ሁለት የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ አውቶቡሶች (የሰሌዳ ቁጥር 4-18729 እና 4-18732) የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸውና ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

6.2.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በንብረት አስተዳደሩ መመሪያው መሰረት ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ተሽከርካሪዎች እንዲጠገኑ መጠገን የማይችሉት ደግሞ በንብረት አስተዳደሩ መመሪያው መሰረት እንዲወገዱ መደረግ እንዳለባቸው እንዲሁም ሊቢሬ ለሌላቸው ተሽከርካሪዎችም ሊቢሬ እንዲወጣላቸው መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

7. <u>በጀት</u>

7.1 <u>ከመደበኛና ከካፒታል በጀት ያልተሰራበት ሂሳብ</u>፤

7.1.1 <u>ግኝት</u>

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2006 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን በሰላሳ አራት ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶችና ለግብርናና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ አራት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ከመደበኛ በጀት ከ10% በላይ ብር **156,728,269.53** እንዲሁም በአስራ ስድስት ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶችና በሁለት ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ ሁለት መሥሪያ ቤቶች ከካፒታል በጀት **582,049,443.90** በድምሩ 738,777,713.43 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡ /አባሪ -33 ተያይዟል/

7.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይችሉ ዘንድ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7.2 ከውስጥ ገቢ በጀት ያልተሰራበት ሂሳብ፤

7.2.1 ግኝት

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2006 በጀት ዓመት ከውስጥ ገቢ የተፈቀደላቸው በጀት አጠቃቀም ሲታይ፡

- ✓ ለግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ከውስጥ ገቢ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የወጪ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር **23,126,158.61** ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- ✓ ለቡና ጥራት ምርምራ ማዕከል ከውስጥ ገቢ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የወጪ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 1,567,521.27 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 24,693,679.88 ከውስጥ ገቢ ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡

7.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይችሉ ዘንድ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7.3 ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ፤

7.3.1 ግኝት

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2006 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን በዘጠኝ ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶች ከመደበኛ በጀት ብር **4,560,082.90** እንዲሁም በሶስት ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶች ከካፒታል በጀት 1,247,341.16 በድምሩ 5,807,424.06 ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ / አባሪ-33 ተያይዟል፡፡/

7.3.1 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ፤ የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸውም በበጀት ሀጉ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

8. ልዩ ልዩ

8.1 በ2005 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች

8.1.1 ግኝት

1. **በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር**

   ✓ በ2004 በጀት ዓመት የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው በመዝገብ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ በመሆኑ እንዲመሳከር አስተያየት የተሰጠ ሲሆን፣ በ2006 በጀት ዓመትም የንብረት ቆጠራው ከዕቃ መዝገብ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ፤

   ✓ በመሥሪያ ቤቱ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ የሚሆን ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፤

2. **በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን**

   ✓ ለመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች ለውሎ አበል ለተከፈለው ብር 409.96 እና ለነዳጅ መግዣ ወጪ ለሆነው ብር 2,813.40 በድምሩ ለብር 3,223.36 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣

   ✓ በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ በመሥሪያ ቤቱ የቋሚና አላቂ እቃ ቆጠራ በተከናወነበት ወቅት፣

   - አንድ ላፕቶፕ ቶሺባ ኮምፒውተር ከነቦርሳው፣

- አንድ ዲጂታል ካሜራ ከ4 ጂቢ ሚሞሪ ካርድ ጋር፣
- አንድ ድንኳን እና አንድ አጉሊ የሜዳ መነፅር፣

በቆጠራ ወቅት ያልተገኙና ያልተቆጠሩ መሆኑ፣

3. <u>በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር</u>

✓ መሥሪያ ቤቶች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባልሥልጣን በተጻፈላቸው ደብዳቤ መሠረት የቀረጥ ሂሣብ ምዝገባ የሚያከናውኑ ሲሆን፣ ቀረጥ የተከፈለባቸው አቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ገቢ ለመደረጋቸው ሲጣራ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ብር 295,102,394.84 ቀረጥ ለተከፈለባቸው አቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) እንዲያያዝ ባለመደረጉ ዕቃዎቹ ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

✓ ብዛት ያላቸው ቀይ እስክሪቢቶዎች ያለ አገልግሎት ለረጅም ጊዜ እንዲቀመጡ የተደረጉ መሆኑ፤

✓ የተለያዩ የማስተማሪያ ፁሁፎች፤ በራሪ ወረቀቶች የህክምና መፅሐፍት፤ እንዲሁም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቀደም ብሎ ይጠቀምባቸው የነበሩ የተለያዩ ፎርሞችና ቅፆች በብዛት የታተሙ ቢሆንም አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

✓ ብዛት ያላቸው የማባዣና የፎቶ ኮፒ ማሽኖች እንዲሁም መለዋወጫ ዕቃዎች የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ ቢታወቅም ንብረቶቹን ለማስወገድ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

✓ በመለዋወጫ መጋዘን ግምጃ ቤት ከፍተኛ ዋጋ እና ብዛት ያላቸው በእርዳታ ከገቡ መኪናዎች ጋር የመጡ የኢቬኮ መኪና

መለዋወጫዎች መኪናዎቹ ለረዥም አመታት ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4. **ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል**

- ✓ በ2005 በጀት ዓመት ያለአግባብ ከተከፈለው ብር 8,554.00 ውስጥ ብር 6,219.75 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን፣ ብር 2,334.25 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ ለሆስፒታሉ ልዩ መድኃኒት ቤት በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ እና የሂሳብ ሪፖርት ያልተዘጋጀ መሆኑ ተገልጾ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመትም ሁኔታው ያልተስተካከለ መሆኑ፤

- ✓ የሆስፒታሉ ልዩ መድሃኒት ቤት የቀድሞው የሂሳብ ባለሙያ የተለያዩ የሂሳብ ሰነዶችን ሳያስረክቡ ሆስፒታሉን የለቀቁ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ ያለመኖሩ፤

- ✓ በውስጥ ኦዲት ክፍሉ ኦዲት ተደርገው ጠፉ ከተባሉት 94 የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ውስጥ 87ቱ የተገኙ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ 7 ደረሰኞች አሁንም ያልተገኙ መሆኑ፤

- ✓ ሆስፒታሉ ለዴንታል ዩኒት ስትሪም ስቴራላዘር ግዥ ለቅድሚያ ክፍያ ከመድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ ጋር በ2003 በጀት ዓመት ውል ተዋውሎ የቅድሚያ ክፍያ ብር 1,141,675.20 ፈጽሞ ንብረቱ ገቢ ሳይሆን በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ማስተካከያ ያልተሰራለት ከመሆኑም በተጨማሪ ንብረቱም በዚህ ኦዲት ወቅትም ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

5. በውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር

የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

1. ቃሊቲ በሚገኘው የኮንስትራክሽን እቃዎች መጋዘን በሚገኝበት ግቢ ውስጥ አገልግሎት ላይ የማይውሉና ያረጁ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎችና ብረታ ብረቶች ለፀሀይና ለዝናብ ተጋልጠው የተቀመጡ ከመሆኑም በተጨማሪ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ የፓምፕ ኬብል ከመጋዘን ውጪ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣ ተገልጾ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
2. አሚቼ በሚገኘው መጋዘን ውስጥ ያሉ ያገለገሉ ፍሪጆች፣ የመኪና ጎማዎች እና የመሳሰሉት ንብረቶች ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

1. አንድ ሰራተኛ ከሥራ ከለቀቀ በኋላ አለአግባብ ብር 1,145.10 ተከፍሏቸው የተገኘ መሆኑ፣
2. አንድ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ በገቡት ውል መሰረት የከፍተኛ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከሥራ የለቀቁ ሲሆን፣ በውሎ መሰረት ሊመልሱ ይገባቸዋል የተባለውን ብር 20,000.00 ተመላሽ ለማድረጋቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
3. አንድ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ ከሥራ ሲለቁ በእጃቸው የሚገኘውን 1 Toshiba laptop computer AR630,Toshiba laptop computer small size Intel dual እና CDMA ለማስረከባቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ተገልጾ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ፤

6. የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

- ✓ ኢኒስቲትዩቱ በወንዶ ገነት ግብርና ምርምር ማዕከል ወርክሾፕ ባካሄደበት ወቅት ያለአግባብ የተፈጸመው ተጨማሪ የውሎ አበል ክፍያ ብር 5,152.50 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ መሥሪያ ቤቶች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተጻፈላቸው ደብዳቤ መሠረት የቀረጥ ሂሣብ ምዝገባ የሚያከናውኑ ሲሆን፣ ቀረጥ የተከፈለባቸው አቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ገቢ ለመደረጋቸው ሲጣራ የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በ2005 በጀት ዓመት ብር 4,153,590.08 ቀረጥ ለተከፈለባቸው አቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) እንዲያያዝ ባለመደረጉ ዕቃዎቹ ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

- ✓ ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

- ✓ በቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ብዛት ያላቸው አገልግሎት የማይሰጡ ልዩ ልዩ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች (ለምሳሌ፤ ፕሪንተር 40 ፤ ታይፕራይተር 10፤ ስልክ ኦልድ ሞዴል 38 ሞኒተር 76 እና ኮምፒውተር 67) የሚገኙ መሆኑ፤

- ✓ በኬሚካልና ላብራቶሪ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ የላብራቶሪ መሳሪያ ኬሚካሎች ሪኤጀንቶችና የተለያዩ አላቂ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

- ✓ በተሽከርካሪ መለዋወጫና ነዳጅ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚወገዱና የማይወገዱ የተለያዩ መለዋወጫዎች በአንድነት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

- ✓ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ 4 ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ ኦዲት ወቅት ሁኔታው ያልተስተካከለ መሆኑ፤

7. <u>የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት</u>

የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

- ✓ ጽህፈት ቤቱ በ6214 የሂሳብ መደብ ለብድር መስጠትና ማስመለስ እንዲውል የተፈቀደለትን በጀት ብር 50,000,000.00 ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ እንዲዞር ያደረገ ሲሆን፣ ጽህፈት ቤቱ ገንዘቡን ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ በማዞር እንዲጠቀም የተፈቀደለት ለመሆኑ ማስረጃ ስላልቀረበ ማስረጃ እስኪቀርብ ድረስ ገንዘቡ በተሰብሳቢ ሒሳብ መያዝ እንዳለበት ተገልጾ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- ✓ ብር 1,883,514.72 ከዓረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት (BADEA) መሸፈን ሲገባው ከፌደራል መንግሥት በጀት ክፍያው የተፈጸመ ሲሆን፣ ገንዘቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ ከዕርዳታው ሰጪ ድርጅት መጠየቅ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤
- ✓ ጽህፈት ቤቱ የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ግንባታ ስትራክቸሮችንና ቁሳቁሶችን ጥበቃ አገልግሎት ለሰጡበት ብር 339,603.20 ክፍያ ሲፈፀም ጥበቃዎቹ አገልግሎት ለሰጡባቸው ቀናቶች ስለመከፈሉና የደመወዝ ገቢ ግብሩ ለግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘቡ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤
- ✓ በሳይት ላይ ለሚገኝ እቃ (Material on Site) በግዥ መመሪያው የማይፈቀድ ቢሆንም ብር 8,234,987.53 ክፍያ ተፈጽሞ ከመገኘቱ በተጨማሪ ሒሳቡ በተሰብሳቢ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤

የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

- ✓ ጽህፈት በ6412 የሂሳብ መደብ ለብድር መስጠትና ማስመለስ እንዲውል ከተፈቀደለት በጀት ብር 15,049,315.03 ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ እንዲዞር የተደረገ ሲሆን፣ ጽህፈት ቤቱ ገንዘቡን ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ በማዞር እንዲጠቀም የተፈቀደለት ለመሆኑ ማስረጃ ስላልቀረበ ገንዘቡ ተመላሽ እስኪደረግ ድረስ የፌዴራል መንግሥት ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ገንዘቡ በተሰብሳቢ ሒሳብ መያዝ እንዳለበት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በተሰጠው አስተያየት መሰረት ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- ✓ ጽህፈት ቤቱ የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ለማቲትዮሊ ጆይንት ቬንቸር (Mattioli Joint Venture) ሥራ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈጸም ብር 328,259.52 የመያዣ ሂሳብ ፤ ብር 4,116,177.47 2% የቅድሚያ ግብር ታክስ ክፍያ፤ ብር 1,989,767.92 የቅድሚያ ክፍያ እና የማቴሪያል ኦን ሳይት ተመላሽ ሂሳብ በቀረበው የክፍያ ምስክር ወረቀት ላይ የተቀነሰ ቢሆንም የሂሳብ ምዝገባው ያልተከናወነ መሆኑ፣

- ✓ የክብረ መንግሥት ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት ለበርሔ ሐጎስ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈጽም ብር 103,533.00 የመያዣ ሂሳብ እና ብር 133,732.20 የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ ሂሳብ በቀረበው የክፍያ ምስክር ወረቀት ላይ የተቀነሰ ቢሆንም የሂሳብ ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፤
- ✓ ጽህፈት ቤቱ የሐረር ከተማ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት የቅድሚያ ክፍያ ብር 209,281.04 እና የመያዣ ሂሳብ ብር 209,281.04 በድምሩ ብር 418,562.08 ሳይቀነስ ለተቋራጩ ለጋሞን ቴቺኖ ፋብ ጆይንት ቬንቸር (GAMMON TECHNO FAB JOINT VENTURE) ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

8. <u>የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

- ✓ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይፈቅድ ለሰራተኞች ማበረታቻ ተብሎ የተፈጸመው ክፍያ ብር 198,783.33 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ በቢሾፍቱ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት በተዘጋጀው ስልጠና ላይ ለሰልጣኞቹ የመኝታ እና የምግብ ወጪ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተሸፈነ ቢሆንም መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ ብር 82,950.00 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- ✓ በሕንድ አገር የሚማሩ ሰራተኞች ለአንድ ወር ለእረፍት ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ወቅት የተፈጸመው የኪስ አበል ክፍያ ብር 124,264.30 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ ከኢትዮጵያ ወጪ በሥልጠና ላይ ለሚገኙ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች ለኪስ አበል እንዲሁም ለመላኪያና ለተለያዩ ወጪዎች ክፍያ ሲፈጸም በባንክ የምንዛሪ ስሌት ስሕተት ምክንያት ብር 18,444.16 በብልጫ ከባንክ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የተደረገ ሲሆን ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

9. <u>በማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን</u>

በ2005 በጀት ዓመት ዓመት ሪፖርት የንብረት ምዝገባ በተሟላ መልኩ እንዲከናወን የተሰጠው አስተያየት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

10. <u>የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን</u>

- ✓ የንብረት መመዝገብ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19፣ የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል 22 ማዘጋጀት እና የንብረት መጠበቅ ሥራ በአንድ ሰው ተደርበው የሚሰሩ መሆኑ፤
- ✓ በንብረት ክፍሉ ውስጥ ለሚገኙ ንብረቶች ቢን ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤

- ✓ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤

11. <u>በማዕድን ሚኒስቴር</u>

- ✓ ከክልል ለስብሰባ የመጡ 23 ሠራተኞች ወደ መኖሪያ አካባቢያቸው ሲመለሱ በብልጫ የተከፈለው ብር 1,963.78 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ ለአውሮፕላን ቲኬት መግዣ ወጪ ተደርጎ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር 541.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

12. <u>የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>

በ2005 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ሲጣራ፡

- ✓ በእርዳታ እና በግዢ የሚመጡ የህክምና መሣሪያዎችና መድሃኒቶች ሳይለዩ በአንድ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሆነው በአንድ የንብረት ወጪ ደረሰኝ ለአገልግሎት ወጪ የሚደረጉ መሆኑ፣
- ✓ በመደበኛ በጀት የሚገዙ የማደንዘዣ መድሃኒቶች፤ ጓንቶች፤ ስሪንጆች እና የላብራቶሪ ኬሚካሎች በዕቃ ወጪ ማድረጊያ (ሞ/22) ወጪ ተደርገው ለግል ህክምና ዘርፍ (Private Wing) አገልግሎት እንዲውሉ የተደረገ መሆኑ፣
- ✓ በልዩ ፋርማሲ ግምጃ ቤት መድሃኒቶች ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ገቢ፣ እንዲሁም ለአገልግሎት በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ወጪ የሚደረጉት ሞዴሎቹ በንብረት ግምጃ ቤቱ ኃላፊው ተዘጋጅተው መሆኑ፣
- ✓ በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ከግል ጤና አገልግሎቱ ገቢ የተጣራ ትርፍ ክፍፍል ሲደረግ የሆስፒታሉ ድርሻ 15% በመደበኛ ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሆኖ ገንዘቡ ለመንግሥት ወደ

ተጠቃለለው ፈንድ ገቢ መደረግ እንዳለበት በሪፖርት የተገለጸ ቢሆንም ምንም አይነት እርምጃ ሳይወሰድ የተገኘ መሆኑ፣

13. <u>የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን</u>

- ✓ ንብረት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት አሮጌ የተለያዩ ንብረቶች በደንቡ መሰረት ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ መጠገን የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ መሰብሰብ ከነበረበት ብር 99,009.87 ያልተሰበሰበ መሆኑ ተገልጾ እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በተሰጠው አስተያየት መሰረት ገንዘቡ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ መሆኑ፣

14. <u>የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>

- ✓ በየወሩ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑና ከመዝገብ (ሌጀር) ወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ ፣
- ✓ ለረጅም ጊዜ የቆሙ 7 ተሽከርካሪዎች 4-03394፣ 4-08147፣ 4-06965፣ 4-07366፣ 4-08423፣ 4-04525 እና 4-04511 መኖራቸው፤
- ✓ በድሪሊንግ መጋዘን አዳዲስ ማሽኖች ያለሥራ ለረጅም ጊዜ የቆሙ መሆኑ፣ የወርክ ሾፕ ማሽኖች ያለ አገልግሎት መቀመጣቸው፣ በመጋዘኑ ውስጥም መወገድ ያለባቸው ኬሚካሎች ለረጅም ጊዜ የተቀመጡና እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤

15. <u>የኢትዮጵያ የምግብ ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን</u>

- ✓ ከቤት አበል ክፍያ ላይ ያልተቀነሰ ሥራ ግብር ብር 23,641.00 ገቢ እንዲሆን በተሰጠው አስተያየት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- ✓ ከደመወዝ ላይ ያልተቀነሰ 1% የነጻ ህክምና አገልግሎት ብር 2,554.08 ተቀናሽ እንዲሆን በተሰጠው አስተያየት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

- ✓ መሥሪያ ቤቱ ብር 5,406.98 ያለምንም የወጪ ማስረጃ በወጪ መዝግቦ የተገኘ መሆኑ ፣

- ✓ ለሥሌዳ ቁጥር 4-03960 መኪና ሊብሬ ያልቀረበ መሆኑ፣

16. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

- ✓ ብር 120,076.68 የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ በአግባቡ ባለመቀነሱ ምክንያት በብልጫ ለተቋራጩ የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ ወይም ከቀጣዩ የክፍያ ሰርተፊኬት ላይ እንዲቀነስ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፣

- ✓ የገ/ኢ/ል/ሚ ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለህንፃ ተቋራጭ ክፍያ ለመፈጸም የክፍያ የምስክር ወረቀት ሲቀርብ ለሚቀነሰው የመያዣ ሂሳብ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለህንፃ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈጽም፡
    - ♦ በ2005 በጀት ዓመት ተቀናሽ ለተደረገውና ላልተመዘገበው የመያዣ ሂሳብ ብር 2,664,608.80 ፤
    - ♦ ከተገጣጣሚ ሕንጻ አቅራቢ ድርጅት በብር 10,900,707.40 የተፈጸመው የግንባታ እቃዎች ግዥ ግንባታው ሳይፈፀም ዕቃዎቹ በወጪ እንደሚመዘገቡ የተደረገ መሆኑ፤
    - ♦ በ2004 በጀት ዓመትም ተቀናሽ ለተደረገውና ላልተመዘገበው የመያዣ ሂሳብ ብር 41,419,848.07 ፤

  በድምሩ ለብር 59,985,164.27 ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፤

17. <u>የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት</u>

- ✓ በሞ/19 ገቢ የተደረጉና በሞ/22 ወጪ የተደረጉ ዕቃዎች ለምሳሌ (Hp toner 80A,JKTH TONER 170) አልፎ አልፎ በስቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፤
- ✓ መወገድ የሚገባቸው የተለያዩ በርካታ ዕቃዎች፣ ጠረጴዛዎች፤ ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ የመኪና ጎማዎች፤ ኮምፒውተሮች፤ ሁለት ሱዚኪ ሞተር ሳይክሎች፤ አንድ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር አንድ ማርቼዲስ መኪና፣ እንዲሁም በርካታ የተለያዩ ንብረቶች ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፤
- ✓ በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ማጭድ፤ መቧጠጫ፤ የብረት ወንበር የመሳሰሉት ንብረቶች የንብረት መቆጣጠሪያ ካርድ ላይ ተመዝግበው ያልተገኙ መሆኑ፤
- ✓ በ2005 በጀት ዓመት የተገዙ ቋሚ ዕቃዎች ለምሳሌ (ዴል ኮምፒዩተር፣ ዩፒኤስ ወዘተ) በቋሚ ዕቃ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፤

በተሰጠው የኦዲት የማሻሻያ አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

8.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

8.2 <u>ዋስትና በሚያስፈልጋቸዉ የስራ መደቦች ላይ የተመደቡ ሰራተኞች ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ ስለመሆኑ</u> ፤

8.2.1 <u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 መሰረት በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት

ያኘነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያኘ እንዲያቀርቡ ያዛል። ሆኖም

- ✓ በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ 7(ሰባት) የግምጃ ቤት ሰራተኞች እና 27 (ሃያ ሰባት) የጥበቃ ሰራተኞች ዋስትና ያልያሳዙ መሆኑ ፤
- ✓ በኤሌክትሪክ ባለሥልጣን ሁለት የጥበቃ ሰራተኞች እና አንድ ገንዘብ ያኘ ዋስትና ያላሲያዙ መሆኑ፤
- ✓ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም በናሙና የግል ማኅደራቸው ከታየው ውስጥ 8 ሰራተኞች ዋስትና ያልያስያዙ መሆኑ፤
- ✓ **የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን** በሁሉም ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች የሚገኙ ገንዘብ ያገሮች እና የግምጃ ቤት ኃላፊዎች እንዲሁም የጥበቃ ሠራተኞች ዋስትና ያላስያዙ መሆኑ፤
- ✓ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በንብረት ያኘነት የተመደቡ ሰራተኞች ዋስትና ያልያስያዙ መሆኑ፤
- ✓ የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በምሥራቅ ቅ/ጽ/ቤት የንብረት ክፍል ሰራተኛዋ ዋስ የሌላቸው መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

8.2.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 መሠረት በገንዘብ ያኘነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያኘነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያኘ እንዲሰጡ ወይም እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

8.3 ከመንግሥት ከፍተኛ ተቋማት ከተመረቁት ላይ የወጪ መጋራት ክፍያ ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

8.3.1 ግኝት

ስለከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/1995 አንቀጽ 7 በንኡስ አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው መሰረት ደንቡን ተግባራዊ እያደረገ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡

- ✓ ከተለያዩ የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች ከተመረቁና በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ቤቱ ከተቀጠሩ አምስት ሰራተኞች ላይ የወጪ መጋራት ክፍያ ያልተሰበሰበ መሆኑ ፣
- ✓ በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለኦዲት ሥራ በናሙና ከተመረጡት የኮሌጁ ሰራተኛ ፋይል ውስጥ በተገኘው መረጃ መሰረት ከ3 ሰራተኞች ላይ የወጪ መጋራት ክፍያ ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

8.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ የወጪ መጋራት የሚመለከታቸውን ሰራተኞች ፋይል አጣርተው እና መረጃ እንዲያቀርቡ ተደርጎ ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግሥት ገቢ እንዲሰበሰብ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

8.4 የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ሆነው ግዴታቸውን ያልተወጡ መምህራንን በተመለከተ ፤

8.4.1 ግኝት

በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በመምህርነት ተቀጥረው ሲያገለግሉ የነበሩ 4 (አራት) መምህራን በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲማሩ የተፈቀደላቸውና ከኮሌጁም ጋር ውል የፈጸሙ ሲሆን፤ በገቡት ውል መሰረት ህጉን ካፈረሱ የወጪው 15 በመቶ ታክሎበት ለመክፈል ወይም ተመጣጣኝ አገልግሎት ለመስጠት ውል የገቡ እና ዋስትና ያስያዙ ቢሆንም መምህራኖቹ የገቡትን

ግዴታ ሳይወጡ ከሥራቸው የለቀቁ ቢሆንም ምንም ዐይነት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

8.4.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መምህራኖቹ በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ካልተወጡ አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት አሳስበናል ፡፡

8.5 የመንግሥት ቋሚ ቅጥር ሆነው በካፌ ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞችን በተመለከተ፤

8.5.1 ግኝት

በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ስምንት የኮሌጁ ቋሚ ቅጥር ሰራተኞች በመንግሥት የተፈቀደ ደመወዝ በየወሩ ብር 9,017.00 እየተከፈላቸው በኮሌጁ ገቢ በሚተዳደረው የኮሌጁ ካፌ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተመድበው እየሰሩ የሚገኙ ሲሆን፣ ሰራተኞቹ በኮሌጁ ካፌ ውስጥ ተመድበው እንዲሰሩ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ያልተፈቀደ መሆኑታውቋል፡፡

8.5.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳፈቀድ በኮሌጁ ካፌ ውስጥ ተመድበው እንዲሰሩ የተደረጉት ሰራተኞቹ ወደ መደበኛ ስራቸው እንዲመለሱ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል ፡፡

8.6 ግዥ ዕቅድ ያላዘጋጁና ቢያዘጋጁም ለኤጀንሲ ያላኩ መሥሪያ ቤቶች ስለመኖራቸው፤

8.6.1 ግኝት

ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 3 አንቀፅ 8 ቁጥር አንድ መሰረት ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤትና በሥሩ የተደራጁ አካላት የታቀዱ የሥራ ፕሮግራሞቻቸዉን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸዉን ግዥ በወቅቱ ለመፈጸም በሚያስችል በመርሃ ግብር

የተደገፈ የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት ዕቅዱ ለግዢ ኤጀንሲ መላክ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ሆኖም፡

- ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በ2006 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ ያዘጋጀ ቢሆንም ዕቅዱ ረቂቅ ሲሆን ለግዥ ኤጀንሲ ያልተላከ መሆኑ፤
- የጂኦሎጂካል ሰርቬይ የ2006 የግዥ እቅድ ያላዘጋጀ ለግዥ ኤጀንሲ ያልተላከ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

8.6.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በግዢ አፈጻጸም መመሪያው መሰረት ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የግዥ ዕቅዱ ከተዘጋጀ በኋላ በበላይ ኃላፊ ጸድቆ ለግዢ ኤጀንሲ መላክቀ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

8.7 መያዣ ገቢና ወጪ ሂሳብን በተመለከተ፤

8.7.1 ግኝት

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የመያዣ ገቢና ወጪ ሂሳብን በተመለከተ በሆስፒታሉ ከሚታከሙ ህሙማን በሞ/85 የሚሰበሰበው እና ህሙማኑ ሕክምናውን ሲጨርሱ በሞ/86 ተመላሽ የሚደረገው የመያዣ ሂሳብ የአሰራር ሥርዓትና አግባብነትን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣

- ✓ ሂሳቡ በፒችትሪ እንዲመዘገብ ተደርጎ ከወጪ ቀሪው ሂሳብ ወደ አይቤክስ እንዲተላለፍ የሚደረግ ቢሆንም የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ምዝገባ የመጋቢት 2006 ሳይጨምር የ11 ወራት ብቻ ተመዝግቦ የተገኘ በመሆኑ በተከፋይ ሂሳብ ላይ የተመለከተውን ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ትክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- ✓ የመያዣ ገቢና ወጪ ደረሰኞች ሞ/85 እና ሞ/86 በተሟላ ሁኔታ ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፣

8.7.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የመያዣ ገቢና ወጪ ደረሰኞች (ሞ/85 እና ሞ/86) የተሰበሰበውና ተመላሽ የተደረገው ሂሳብ ምዝገባ በአግባቡ ሊከናወን እንደሚገባና በፒችትሪ የተመዘገበው የመያዣ ከወጪቀሪ ሂሳብ በየወሩ በሚዘጋጀው በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ መደብ 5053 ሪፖርት ከተደረገው ጋር ተመሣሣይ መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

8.8 በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የግል ህክምና አገልግሎቱ ከመደበኛ በጀት የተጠቀመበት ሂሳብ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

8.8.1 ግኝት

ከሆስፒታሉ በጀት ብር **1,104,481.99** ለግል የህክምና አገልግሎቱ ጥቅም ላይ የዋለ ከመሆኑም በተጨማሪ ገንዘቡ ለሆስፒታሉ ተመላሽ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

8.8.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ከሆስፒታሉ መደበኛ በጀት ለግል ህክምና አገልግሎት ጥቅም ላይ የዋለው ሂሳብ ለሆስፒታሉ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡

አባሪ. 3

<u>የግዥ መመሪያውን ሳይከተል የተፈጸሙ ግዥዎች ዝርዝር</u>

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተፈጸመው ግዥ	ጨረታ ሳይወጣ የተፈጸመ ግዥ	ያለዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ
1	የግብርና ሚኒስቴር	የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሱፐርቪዥንና ኮንትራት አስተዳደር ሥራ	854,162 .50	
1.1	በግብርና ሚኒስቴር የቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል	ለጀንያና ለከረጢት ግዥ		32,305.74
1.2	የአላጌ ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ	የስልክ ኤክስቴንሽን ግዥ		144,419.50
		የመጓጓዣ ትራንስፖርት አገልግሎት ግዥ	252,230.00	
2	የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	ለመኪና መለዋወጫ ግዥ		95,342.48
		የመስተንግዶ የአገልግሎት ግዥ		83,216.86
3	የትራንስፖርት ሚኒስቴር	የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ		20,719.95
4	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ለአልሙኒየም ፓርቲሽን ሥራ	110,586.30	
4.1	የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል	የመድኃኒት እና የእንስሳት መኖ ግዥ	1,129,123.65	
5	የኢትዮጲያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	ለተለያዩ የዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች		688,691.78
6	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	የመስተንግዶና የቋሚ ዕቃዎች ግዥ	3,100,578.68	
		የጽሕፈት መሳሪያዎች፣ የቢሮ ዕቃዎችና የመሳሰሉት ግዥ	1,162,140.40	
		የመስተንግዶ፣ የመኪና መለዋወጫና የውኃ ፓምፕ ግዥ		247,676.17
7	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን	ለመኪና መለዋወጫ ግዥ፣ ለማስጠገኛና ለመኪና ኪራይ		60,776.89
8	የአካባቢና ደን ሚኒስቴር	ያለጨረታ ለሕንጻ ስቲከር ሥራና ለሥልጠና አገልግሎት	239,837.40	
9	የአማኑኤል የአዕምሮ ሰፔሻላይዝድ ሆሰፒታል	ለመድኃኒትና ለፒጃማ ግዥ	635,621.80	
10	የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	የእርሻ መሣሪያዎች ግዥ	693,966.00	
		የሚዞር ድምር	7,324,084.23	1,373,149.37

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተፈጸመው ግዥ	ጨረታ ሳይወጣ የተፈጸመ ግዥ	ያለዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ
			7,324,084.23	**1,373,149.37**
11	የጤና መድህን ኤጀንሲ	ለመኪና ባትሪ ግዥ		**32,095.64**
12	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	የምክር አገልግሎት እና የግንባታ ግዥ	**742,051,501.66**	
		የተለያዩ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥዎች		**231,369.77**
		የፈርኒቸር የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት ግዥ	**349,946.23**	
		የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ		178,282.03
13	የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	ለኬብልና ለወንበር ግዥ	**372,144.60**	
		ለስድስት ጅሊ አውቶሞቢሎች ግዥ	**1,817,644.00**	
		ለህትመት ስልጠናአገልግሎት ግዥ		**26,979.00**
14	የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቱት	ለኦሞ፣ ለቪም፣ ለበረኪና ፣ ለሲዴክስ እና ለአጠና ግዥ		**62,600.00**
15	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	የአገልግሎት ግዥ		**27,928.87**
16	የማዕድን ሚኒስቴር	ለመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ		**377,110.69**
17	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	የዕቃ ግዥዎች		**77,993.00**
18	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	የመለዋወጫና የግድግዳ ቀለም ግዥ		**162,407.38**
	ጠቅላላ ድምር		**751,915,320.72**	**2,549,915.75**

በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ያልተመዘገበና ያልተፈጸመ የኮንትራክተር ክፍያ፤

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	በብልጫ የተመዘገበ ወጪ	ያልተመዘገበ ወጪ	ያልተሰበሰበ የቅድሚያ ክፍያ	ያልተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ	በብልጫ የተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ	]ብልጫ የተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ	ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ
1	የአለርት ማዕከል	25,674.26	457,100.73		457,100.73	50,498.45	28,526.97	
2	የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን			4,837,345.49				87,613.79
3	የአካባቢና ደን ሚኒስቴር							35,384.43
4	የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃ ባለሥልጣን	33,891.14					50,826.82	
5	አማኑኤል ሆስፒታል	2,876,348.08						
6	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	32,712,630.54	86,937,937.07				123,317.20	16,826,024.66
7	የማዕድን ሚኒስቴር		1,960,420.94					
8	የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት	2,144,123.86	63,697.06	139,800.68		561,949.41	40,965.40	15,447.06
	ድምር	37,792,667.88	89,419,155.80	4,977,146.17	457,100.73	612,447.86	243,636.39	16,964,469.94

ተራ ቁጥር	በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ	ያልተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ	በብልጫ የተቀነሰ የቅድሚያ ግብር	ያልተቀነሰ የቅድሚያ ግብር	በብልጫ የተከፈለ ጥሬ ገንዘብ	በወጪ መያዝ ሲገባው በተሰብሳቢ የተያዘ ሂሳብ	በተሰብሳቢ ያልተያዘ ሂሳብ	ያልተከፈለ ጥሬ ገንዘብ
1		6,586.76	21,734.26					68,498.66
2	520,741.74		1,632,695.44		3,022,568.17			242,452.39
3					35,385.25			
4		16,935.70		5,847.49	5,847.51			
5				136,343.49	136,343.45		2,876,348.12	
6	418,702.09	464,018.68	3,172,556.29	32,931.27	172,217.18	15,011,841.79	93,820,097.01	11,110,766.86
7		490,028.07	1,773,742.96					3,244,135.79
8	314,876.00	12,384.15	44,939.51	202.50	248,228.00			828,524.80
ድምር	1,254,319.83	989,953.36	6,645,668.46	175,324.75	3,620,589.56	15,011,841.79	96,696,445.13	15,494,378.50

የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2006 በጀት ዓመት የኦዲት ዕቅድ ክንውንና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች ሪፖርት

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ

1.1 የጥሬ ገንዘብ የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች

ከ2004 በጀት አመት በፊት መኪና ለመግዛት ሌተር ኦፍ ክሬዲት ተከፍቶ በፑል የባንክ ሂሣብ ገቢ ከሆነው ተራፊው እና በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የታገደ የመኪና ግዥ ለማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ በመመሪያው መሠረት ገቢ ያልሆነ፣

- በፌዴራል ማረሚያቤቶች አስተዳደር ብር 1,247,332.17

በሰኔ 30/2006

በኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት ሂሳብ ሪፖርት የተገለጸው ብር 37,041.31 ሲሆን በጥሬ ገንዘብ ተገኝቶ የተቆጠረው ብር 7,864.60 በመሆኑ የብር 29,177.23 በሂሳብ ሪፖርቱ የተገለጸው በመብለጥ ተገኝቷል፡፡

አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የመንግስት ገንዘብ ያለስራ ለረዥም ጊዜ ማስቀመጡ ሌሎች ሥራዎች እንዳይሰሩበት ሊያደርግ እንደሚችል በመግለጽ የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 3 ቁጥር 16 ንዑስ ቁጥር 3 የተዘጉ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ዋጋ ወይም ገንዘብ ወደ ማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ እንዲደረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር መ/ቤቱ በጽሁፍ ማስታወቅ እንዳለበት እንደሚያዝ በመግለጽ አስተዳደሩ ሁኔታውን ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር በጽሁፍ እንዲያሳውቁና እልባት እንዲያገኝ በድጋሚ አሳስበናል፡፡ በኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት በልዩነት የታየው ብር 29,177.23 በቼክ ከባንክ የወጣ ተመላሽ የሚደረግ ሲሆን፣ በ30/10/06 ዓ.ም. Bank System በመቋረጡ ምክንያት ገቢ ሳይደረግ በማደሩ የሂሣብ መደብ 4101 የገንዘብ መጠኑ ከብር 30,000.00 በላይ ሊሆን ችሏል፡፡ ነገር ግን ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ከቆጠራ በፊት ከጠዋቱ 2:30 ገንዘቡ ባንክ ገቢ ተደርጐ በቆጠራ ወቅት Advice የቀረበ በመሆኑ የጥሬ ገንዘቡ መጠን ብር 7,864.60 ብቻ ሊታይ መቻሉንና ይህም የተደረገው

የመንግሥትን መመሪያ በማክበር ከብር 30,000.00 በላይ ላለማስቆጠር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

1.2 የባንክ ሂሳብ

በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዜሮ ባላንስ እና የአደራ የባንክ ሂሳብ /D account/ ባአንድ ላይ በመሆኑ እና የባንክ ሂሳብ ቁጥር ስለሚይዝ የአደራ ሂሳብንና የዜሮ ባላንስ ሂሳብ በጀት ለማጣራት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ለቁጥጥር አመቺ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ለክትትልና ቁጥጥር አመቺ ይሆን ዘንድ የአደራ ሂሳብ ለብቻው ተለይቶ ከዜሮ ባላንስ ሂሳብ ለብቻው ተለይቶ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ሊኖረው እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሣቦች

2.1. ውዝፍ የሠነድ /ተሰብሳቢ/ ሂሣብ

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር

ከ1984 ጀምሮ ከ20 ዓመታት በላይ የቆየ ከዚህ ውስጥ ለብር 11,593,098.48 በሪፖርት ከመገለጹ ውጪ ማስረጃ የሌላቸው፤	ብር 18,708,030.10
በሂሳብ መደብ 4202 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት በሎጅስቲክ ዋና መምሪያ የቀድሞ ገንዘብ ያዥ ያልተተካ	200,187.27
ለግዥ ሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ	7,837,666.54
ለሥራ ተቋራጮች	38,527,406.64
እቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ ከ2003 በጀት አመት በፊት ተከፍሎ ያልተሰበሰበ	33,992,953.51
በሚ/ር መ/ቤቱ ሥር ለሚገኝ አንድ ድርጅት(ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ፋብሪካ) አላግባብ ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ /ያልተከፈለ ደመወዝ / በ2004 በጀት	

አመት በብድር ተሰጥቶ ያልተሰበሰበ፣	45,000,000.00
በጠቅላይ ፍ/ቤት በወቅቱ ያተሰበሰበ ሂሳብ	34,122.11
የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት	14,058.03
የፌዴራል ፖሊስ በአስተዳደር ልማት ዘርፍ	
- የደንብ ልብስ ቅድመ ክፍያ ከ2004 ጀምሮ የሚገኝ	8,005,002.82
- በ2006 በጀት ዓመት ለተለያዩ ድርጅቶች	2,220,966.73
ለሙዚቃ ዕቃ ግዥ ወጪ ሆኖ ያልተወራረደ	
የፌዴራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዘርፍ	
• ለአፋር ፖሊስ በሁርሶ ማሰልጠኛ ለአፋር ምልምል ፖሊሶች ተከፍሎ ከ4 ዓመት በላይ የቆየ	78,905.31
• ለድሬዳዋ ፖሊስ ሁርሶ ማሰልጠኛ ተከፈሎ ከ4 ዓመት በላይ የቆየና እርምጃ ያልተወሰደበትና ለዘርፉ ያልተመለሰ	34,030.90
• በሂሳብ መደብ 4203 ለተለያዩ ሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ ከ4 ወር እስከ 9 ዓመት የቆየ	71,920.12
• ለሰራተኛ የተከፈለ እና በህግ የተያዘ ከ4 ወር እስከ 2 ዓመት የቆየ	408,983.10
• የሬዲዮ መገናኛ ግዥ ከአንድ ዓመት በላይ ሂሳቡ ያልተወራረደ፤	28,474,975.20
በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ከ1 ዓመት እስከ 10 ዓመት	312,527.68
ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከ5-20 ዓመት በላይ የቆየ፤	539,836.64
• የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ለመኪና ግዥ ቅድሚያ ክፍያና ሌሎች	8,028,126.64

* **የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር**

የረዥም ግዜ የደመወዝ ብድር ተሰጥቶ ለዓመታት ሳይሰበሰብ የቆየ	56,192.91
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰብሳቢ ሂሳብ ከ1985 ጀምሮ ለረጅም አመታት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡	9,840,430.59
የብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢኒስቲትዩት	65,587.23
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት	15,672.58
ንግድ ሚኒስቴር	782,792.38
የኢትዮጵያ ጨ/ጨ/ኢ/ል/ኢ	90,027.80
የፍትህ ሚኒስቴር ከ1944-1995 የቆየ	37,766.26

ከላይ ከተመለከቱት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ከፍተኛው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ሲሆን ተሰብሳቢዎቹን የሚገልጽ ዝርዝር ቢቀርብም ደጋፊ ማስረጃዎቹ በአባሪነት አለመቅረባቸውንና ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ እንዲወራረዱም ክትትል ሊደረግባቸው እንደሚገባ፡ እንዲሁም በፋይናንስ ዳይሬክቶሬቱም ሆነ በሌሎች ክፍሎች የሚገኙት ተመሳሳይ ሂሳቦች ማስረጃቸው ተፈልጐ በፋይናንስ ዳይሬክቶሬቱ ሊጠበቁና እነዲሰበሰቡ ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ በተጨማሪም ብዙዎቹ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ለረጅም ዓመታት የቆዩና ባለፉት በጀት ዓመታት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኦዲት ሪፖርቶቸ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው መሆኑንና ሚኒስቴር መ/ቤቱ እርምጃ እወስዳለሁ ከማለት ውጪ በተግባር የተወሰደ እርምጃ ባለመኖሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ በየዓመቱ እየተንከባለሉ መቆየታቸውን በመግለጽ፡ ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ ክትትል በማድረግ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት የታየው የተሰብሳቢ ሂሳቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ጥረት እንዲደረግ ሊሰበሰቡ ያልቻሉትን በማጣራት መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት እንዲፈጸም አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር ስለብር 18,708,030.10 በሰጠው መልስ በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በሂሳብ መደብ 4201 በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ የሚገኘው ብር

11,593,098.46 ከሽሽግር መንግስቱ ጀምሮ በተለያዩ የጦር ክፍሎች በነበሩት አባላት የጠፋና ገንዘቡንም ለማስመለስ ክፍሎቹ በተለያያ ምክንያት የፈረሱ ወይም የታጠፉ ወይም ወደ ሌላ የጦር ክፍል የተቀላቀሉ በመሆናቸውና አባላቱን ይዞ ገንዘቡን ለማስመለስ አብዛኛው በህይወት የሌሉ፣ በተለያየ ምክንያት ከተቋሙ የለቀቁ ወይም የተሰናበቱና አድራሻቸው የማይታወቅ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ በዳይሬክቶሬቱ የሂሳብ ምዝገባ ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ የሚታይና ከመዝገብ ለማሰረዝ በወጣው መመሪያ መሰረት ሂሳቡን ከመዝገብ ለማሰረዝ ደጋፊ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ እንደሆኑ አስፈላጊው ሰነዶች ሲሟሉ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው አካል የሚያቀርቡ መሆኑን፤

- የሂሳብ መደብ 4210 በተመለከተ በማዕከል፣ በዕዞችና በዋና መምሪያዎች በተሰብሳቢ ከሚታየው ገንዘብ ውስጥ ብር 45,000,000.00 በመከላከያ የበላይ አካል ትዕዛዝ ከሰራዊት የደመወዝ ተመላሽ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ላይ ለዝቋላ ስቲል ሮሊን በ2004 በጀት ዓመት የተሰጠና ድርጅቱ እስኪመልስ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ፣ ቀሪው ብር 10,966,546.00 የስራ ክፍሎች ሲፈርሱ ወይም ስታጠፉ ወደ ዳይሬክቶሬቱ በምዝገባ የተላለፈ ሂሳብ ሲሆን ቀሪው ብር 51,974,379.36 በዕዞችና በተለያዩ የመከላከያ የስራ ክፍሎች ለረጅም ዘመናት በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዙና ሌላው ከዕዝ በታች ያሉ የስራ ክፍሎች ለበጀት ዘመኑ ከተላከላቸው የስራ ማስኬጃና የደመወዝ ሂሳብ ውስጥ ሳይከፈል ወይም ሳይጠቀሙበት በጥሬ ገንዘብ ተመላሽ የሆነ ሂሳብ ሆኖ በዚህ በጀት ዓመት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ የተደረገና እየተደረገ ያለ ሂሳብ ነው፤
- በሂሳብ መደብ 4211 ብር 7,837,666.54 ከሚታየው ገንዘብ ውስጥ በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት፣ በዕዞችና በተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አብዛኛው የመከላከያ አስተዳደር ፋይናንስ መምሪያ ለሚያደርጎቸው የውጭ ጉዞ ትክክለኛውን የሂሳብ መደብ ባለመጠቀም በዚህ ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን አብዛኛው አባላትም በህይወት የሌሉ፣ የከዱ፣ በጡረታ የተሰናበቱና አድራሻቸው የማይታወቅ በመሆኑ እስካሁን ያልተወራረደ ሂሳብ በመሆኑ ከመዝገብ ለመሰረዝ በወጣው የመንግስት የፋይናንስ መመሪያ መሰረት ይህን አጣርቶ ለውሳኔ የሚያቀርብ ኮሚቴ በማዋቀር አስፈላጊው የማጣራት እና ማስረጃ የማሰባሰብ ስራ በመሰራት ላይ ያለ ሲሆን ማስረጃ ተሟልቶ

ሲቀርብ ለውሳኔ ሰጪ አካል የሚቀርብ ሲሆን ቀሪው ግን በየጊዜው እየተወራረደ የሚገኝ ሂሳብ ነው፡፡

- በሂሳብ መደብ 4251 የሚታየውን ብር 38,527,406.54 በተመለከተ፣
  - ብር 15,173,225.79 በመከላከያ ቤቶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክቶሬት ለኮንስትራክሽን ስራ ከመከላከያ መሰረተ ልማት ውል በማሰር ለኮንስትራክሽን ስራ በውሉ መሰረት ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ በቀጣይ በጀት ዓመት ስራው ርክክብ በመፈጸም ሂሳቡ በሰነድ እንዲወራረድ የሚጠበቅ መሆኑን፣
  - ብር 512,628.84 በመከላከያ ሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ ለመሰረተ ልማት ሪፈራል ጋራዥ አስፋልት ስራ በቅድሚያ የተከፈለ በቀጣይ በጀት ዓመት ሂሳቡ በሰነድ እንዲወራረድ የሚጠበቅ መሆኑን፣
  - ብር 94,987.48 ከ1997 በጀት ዓመት በፊት በትግራይ ውሃ ስራዎች ድርጅት ስም ተመዝግቦ የሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሲሆን በቀጣይ በሚቀርብለት ማስረጃ መሰረት የሚወራረድ ሂሳብ መሆኑን፣
  - ብር 22,746,564.43 ከአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ በ2006 በጀት ዓመት ለብረታብረትና ኢንጅነሪንግ 30% ቅድሚያ ክፍያ የተፈጸመ በቀጣይ በሚቀርብለት ሰነድ መሰረት የሚወራረድ ሂሳብ መሆኑን፣
- በሂሳብ መደብ 4253 ብር 33,992,953.51 በማዕከል ምዝገባ ከ2003 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመረጃና መረብ ደህንነት የቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ እየተወራረደ በሰኔ ወር 2006 መጨረሻ የሚታይ ከወጭ ቀሪ ሆኖ በመወራረድ ላይ ያለ ሂሳብ መሆኑን፣
  - ብር 1,968,921.02 ከ1998 በጀት ዓመት ጀምሮ በመከላከያ ዕቃ ግዥ ዳይሬክቶሬት ለዕቃ አቅራቢዎች እንዲከፈል የቅድሚያ ክፍያ ተሰጥቶ እስካሁን ያልተወራረደ በጥሬ ገንዘብ ወይም በሰነድ ሊወራረድ የሚገባው ሂሳብ ነው፡፡ ብር 24,367,855.38 የሚለው ከ2005 ወደ 2006 በጀት ዓመት ሲዞር የነበረው ባላንስ ነው አሁን በተጨባጭ ያለው ባላንስ ብር 33,992,953.51 በመሆኑ ይህም ከዚህ በላይ የተሰጠው ማብራሪያ የሚገልጸው መሆኑን፣
  - ብር 2,985,285.63 በተለያዩ የስራ ክፍሎቻችን በሰነድ ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚወራረድ ሂሳብ መሆኑን፣

በአጠቃላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተቀመጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ ቀርቦላቸው እንዲወራረዱ ወይም ማስረጃና ተጠያቂ የሌላቸው ሂሳቦች ከመዝገብ እንዲሰረዝ ተገቢውን ክትትል እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሪፖርቱ ከተላከ በኋላ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ በላከው መልስ ከተጠቀሰው ሒሳብ ብር 848,182.83 መወራረዱን ገልጸዋል፡፡

የንግድ ሚኒስቴር ሪፖርቱ ከተላከ በኋላ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ በላከው መልስ በድምሩ ብር 116,777.05 መወራረዱን ቀሪውን እንዲወራረዱ በአመራሩ በኩል ትኩረት እንደሚሰጠው ገልጧል፡፡

- የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በገባው ውል የሬዲዮ መገናኛ ግዥ ለመፈጸም በ27/10/05 ብር 28,474,975.20 የከፈለ ቢሆንም ከአንድ ዓመት በላይ ሂሳቡ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የደንብ ልብስ ቅድመ ክፍያ ከ2004 ጀምሮ ሳይወራረድ የቆየ ብር 8,005,002.82 እንዲሁም ብር 34,030.90 በ2001 በጀት ዓመት የፌ/ፖ/ወ/መከላከል ዘርፍ ለድሬዳዋ ፖሊስ ማሰልጠኛ ሁርሶ ማሰልጠኛ ከፈሎ ከአሁን ቀደም የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶበት ከ6 ዓመት በላይ የቆየ፤ብር 78,905.31 በ2002 በጀት ዓመት የፌ/ፖ/ወ/መከላከል ዘርፍ በሁርሶ ማሰልጠኛ ለአፋር ፖሊስ ምልምል ፖሊሶች ተከፍሎ ከ4 ዓመት በላይ የቆየና ያልተሰበሰበ ነው፡፡

ኮሚሽን መ/ቤቱ ከኦዲት ሪፖርቱ በኋላ በላከው ምላሽ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን በተመለከተ ንብረቱ ገብቶ በባለሙያዎች ተረጋግጦ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ገቢ መደረጉን ገልጿል፡፡ብር 8,005,002.82 ጉዳዩ በሕግ ተይዞ የቆየና የፍ/ቤት ውሳኔ አግኝቶ ገንዘቡን በማስመለስ ሂደት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

2.2 <u>በተሰብሳቢ ሂሣብ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

➢ <u>የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት</u>

ኤጀንሲው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውል የገቡት መ/ቤቶች ለአገልግሎቱ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ገቢ ሲያደርጉ ሂሳቡን በሂሳብ መደብ 5054 በክሬዲት፣ አገልግሎቱን ከሰጠ በኋላ ወጪ ሲያደርግ በዚሁ የሂሳብ መደብ በዴቢት የሚመዘግብ ሲሆን ኤጀንሲው በበጀት አመቱ ውል የገቡት መ/ቤቶች በቅድሚያ ካስገቡት በላይ ከሌሎች ፕሮጀክቶች ለ34 መ/ቤተች ብር 129,633,744.23

ወጪ አድረጎ ክፍያ ሲፈጽም በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው 5054 ዴቢት በማድረጉ ተሰብሳቢ ሂሳቡን በተጠቀሰው ገንዘብ ዝቅ ማለቱንና ኤጀንሲው ከባለበጀት የመንግሥት መ/ቤቶች ጋር በሚያደርገው ውል መ/ቤቶቹ በየበጀት ዓመቱ መንግሥት በፈቀደላቸው በጀት የሚተዳደሩና ብድር መውሰድ የማይፈቀድላቸው በመሆኑ፤ መ/ቤቶቹ በቅድሚያ ለኤጀንሲው ገቢ ካደረጉት በላይ ወጪ የሚጠይቅ ከሆነ በበጀት ዓመቱ ገቢ እንዲያደርጉ መጠየቅ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

- በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር
  - ከአቅም ግንባታ ሚኒስቴር የሚተካ በሚል በ 2002 በጀት ዓመት ከአደራ ሂሳብ በብድር ወጪ የተደረገ በተሰብሳቢ ሂሳብ ያልተያዘ ብር 700,360.43

ያለአግባብ ከአደራ ገንዘብ ላይ የተፈፀመው ክፍያ ከሚመለከተው አካል ተጠይቆ ለባለመብቱ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ ገንዘቡን ለማስተካት የአቅም ግንባታ ቢፈርስም የእርሱን ሥራ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር እየሰራ ስለሚገኝ ለዚህ ሚ/ር መ/ቤት ጥያቄ በማቅረብ ሂሣቡ እንዲተካ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በድጋሚ አስተያየት ሰጥተናል፡፡

3. <u>ተከፋይ ሂሣቦች</u>

3.1 በሀገር መከላከያ ሚ/ር በሰኔ 30/2005 የሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ መደብ 5004 የደመወዝ ተከፋይ ብር 198,888,924.20 ደመወዛቸውን ባለመውሰዳቸው ለረጅም አመታት በተከፋይ የተያዘ መገኘቱንና የሂሳቡን ትክክለኛነ ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ማስረጃዎቹን ለማቅረብ ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘቱ ፡፡ ይህ ሂሣብ በመንግሥት የሂሣብ አሠራር መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጐ ጥያቄው ሲቀርብ የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴርን በመጠየቅ መከፈል ሲገባው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ለዓመታት ሳይከፈል መቀመጡ ገንዘቡም ለምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደተቀመጠ ለማወቅ የማያስችል በመሆኑና ለብክነት እንዲጋለጥ የሚያደርግ መሆኑን በመጥቀስ ሂሣቡ ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ እንዲደረግ፣ ጥያቄው ሲቀርብ ክፍያ እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

3.2 <u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

• የፍትህ ሚኒስቴር የመያዣ ሂሳብ ከ25 ዓመታት በላይ የቆየ	54,754.50
• ንግድ ሚኒስቴር	3,147,160.53
• የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት	97,700.80
• የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን	20,940.45
• በኢትዩ.የደረጃዎች ኤጀንሲ በሂሳብ መደብ 5061 ሪቴንሽን ከ2002 ጀምሮና ስራው ከተቋረጠ በኂላ (የዋስትና መያዣ) በወቅቱ ያልተከፈለ	470,660.24
• በፌደራል ማረሚያ መ/ቤቶች አስተዳደር	1,262,902.49
• የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማእከል	713,129.24
• የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን	3,356,830.09
• በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	
- በሂሳብ መደብ 5004 ያልተከፈለ ደመወዝ ለረጅም ዓመታት በተከፋይ የተያዘ ለገ/ኢ/ል/ሚ/በደንቡ መሰረት ፈሰስ ያልሆነ፤	247,264,224.87
• ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች	83,541,644.12

በሀገር መከላከያ ሚ/ር ደመወዛቸውን ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በመዝገብ/ሌጀር በተከፋይ የተያዘ የሚገኘው ሂሣብ በመንግሥት የሂሣብ አሠራር መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጐ ጥያቄው ሲቀርብ የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴርን በመጠየቅ መከፈል ሲገባው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ለዓመታት ሳይከፈል መቀመጡ አግባብ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ፡

ቀሪዎቹ ብዙ ዓመታትን ያስቆጠሩና አንዳንዶቹ በሪፖረት ላይ ከመገለጽ ውጪ ማስረጃ የሌላቸውና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ማጣራት በማድረግ ተከፋይ ሂሳቦቹ ላይ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ ሌሎቹም መ/ቤቶች የተከፋይ ሂሳባቸው ላይ እርማጃ እንዲ ወስዱ አሳስበናል፡፡

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል መከላከል ዘርፍ ለትግራይ ክልል አድማ መበተኛ ዕቃ ግዥ ብር2,009,268.91፤ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 568,934.22፤ከተለያዩ ድርጅቶች ለሲፒኦ ማስያዣ ብር 43,094.94፤ ለደቡብ ፖሊስ ጸጥታ 131,894.02፤ለአጉዋ ፎረም ለተለያዩ ጉዳዮች የሥራ ማስኬጃ ብር 603,638.00 በሚል ከጥር/2004 ጀምሮ ከ2 ዓመት በላይ የቆየ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም ዘርፉ ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር ባለው ግንኙነት የተቀበለውን ገንዘብ አገልግሎቱን እንደሰጠ ወዲያው ለባለመብቱ ተመላሽ ካልተደረገ ገንዘቡን ለሌላ ሥራ ሊጠቀምበት ወይም ለጥፋት ሊጋለጥ እንደሚችል ለምሳሌ በ2004 ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር ጋር ባለው የሥራ ግንኙነት የወሰደውን ለ2 ዓመት ያህል ተመላሽ አለማድረጉ አግባብ ሆኖ አለመገኘቱንና የአጉዋ ፎረምም የሌሎቹም እንደዚሁ ስለዚህ ተገቢው ክትትል ተደርጎ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ ወይም በማስረጃ ሊወራረድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር የሰራዊት የደመወዝ ተከፋይ ብር 247,264,224.87 በተመለከተ የመከላከያ ሚ/ር ከተሰጠው ተልኮና ግዳጅ መነሻነት ደመወዛቸውን በወቅቱ ቀርበው ያልወሰዱ የሰራዊት አባላት ከተሰጣቸው ግዳጅ ሲመለሱ ያለእንግልት ደመወዛቸውን እንዲወሰዱ በማሰብ የመከላከያ ከፍተኛ ኃላፊዎች ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጋር በመነጋገር ደመወዛቸውን በግዳጅና በተለያየ ምክንያት ያለወሰዱ የሰራዊት አባላትን ደመወዝ ማሰቀመጫ መደቡ D የሆነ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እንዲከፈት ጠይቀው በቀን 09/10/1995 ዓ.ም. በቁጥር አሂመ1/7/47 ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተጻፈ ደብዳቤ ተፈቅዶ መከፈቱን ገልጸዋል፡፡ይሁን እንጂ ገንዘቡን አላግባብ ለሌላ አካል በማበደር እየተጠቀመበት በመሆኑ ተገቢው ቁጥጥር ካልተደረገ ለግል ጥቅም ሊውል የሚችልበት ሁኔታ የሰፋ ነው፡፡

በሂሳብ መደብ 5021 በተከፋይ ሂሳብ የሚታየው ብር 1,831,070.50 በአየር ሀይል ጠቅላይ መምሪያ ለረጅም ጊዜ በምዝገባ የታየ ሂሳብና ተከፋይ ድርጅቱ ወይም ግለሰቡ ማን እንደሆነ በግልጽ የማያሳይና ገንዘቡም በጠቅላይ መምሪያው የባንክ ሂሳብ ውስጥ የማይገኝ ሲሆን ትክክለኛ የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አወቃቀር (Chart of Accounts) ባለመረዳት

የተፈጠረ የምዝገባ ስህተት መሆኑን በመገንዘብ አስፈላጊውን ማጣራት እያደረግና ወደፊት በማጣራት በሂደቱ የምናገኛቸውን የምናሳውቃቹሁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በሂሳብ መደብ 5028 ብር 2,716,915.38 የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር የሰው ኃይል አስተዳደር መምሪያ መከ 02 ምዕራፍ ስድስት ቁጥር 7.1.3 ሀ የውትድርና ማቋረጥ አፈጻጸም መሰረት አንድ አባል በተለያየ ምክንያት ሲሰዋ የአባሉን የስድስት ወይም የዓመት/የአስራ ሁለት ወር ደመወዝ የወራሽ ቤተሰቡ /ተተኪው/ ቀርቦ እስኪወስድ ድረስ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ የሚታይ ሂሳብ መሆኑን፡

በሂሳብ መደብ 5054 ተመዝግቦ ከሚታየው ውስጥ በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ስም በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ የሚገኘው ብር 10,460,092.58 ከልዩ ልዩ የመከላከያ ክፍሎች በተለያዩ ዓመታት በአደራ ወይም በተከፋይ ሂሳብ ወደ መከላከያ ፋይናንስ በጀታዊ ሂሳብ ገቢ ሆኖ የነበረና ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ገንዘቡ ፈሰስ የሆነ ቢሆንም ለፈሰስ ሂሳብ በወቅቱ አስፈላጊው የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ ባለመደረጉ ለረጅም ዓመታት በምዝገባ ይታያል፡፡ በቀጣይ በጀት ዓመት ከመዝገብ እንዲሰረዝ አስፈላጊ ማስረጃ በማጠናቀር ለውሳኔ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚቀርብ ይሆናል፡፡

- ብር 1,493,974.87 በሰላም ማስከበር ተሰማርተው ለነበሩ አባላት የሚከፈላቸው ከገቢዎች የተገፉ ገንዘብ ሲሆን ገንዘቡ ለሚመለከታቸው የሰራዊት አባላት ተከፍሏል፡፡
- ብር 7,239,497.89 መከላከያ ለሰላም ማስከበር ተልኮ የሚያስፈልገው የተለያዩ ንብረቶችን ለመግዛት ለሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ ለሁለት ድርጅቶች ውል በማሰር ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት አቅራቢ ድርጅቶችም በውላቸው መሰረት ዕቃውን ገቢ ስላደረጉ ሂሳቡ ተወራርዷል፡፡
- ብር 2,021,070.86 ቀሪው ብር አብዛኛው የመከላከያ ሰራዊት አባላት ከኪስ ያዋጡት የቀለብ መግዣ ገንዘብ ሲሆን በየስራ ክፍሉ ፋይናንስ እንዲቀመጥ ተደርጎ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በአደራ ተመዝግቦና ተቀምጦ የሚገኝ ሂሳብ ሲሆን አደራ አስቀማጩ የይመለስልኝ ጥያቄ ሲያቀርብ በየጊዜው እየወጣ እየተከፈለ የሚገኝ ሂሳብና በአየር ኃይል በቻርተር በረራ ገቢና እንዲሁም በአንዳንድ ክፍሎች ገንዘቡ በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ እንዳለ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ ሆኖ ከላይ እንደተገለጸው ወቅታዊ የምዝገባ

ማስተካከያ ባለመደረጉ ምክንያት እስካሁን በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ የሚገኝና ወደፊት አስፈላጊውን ማስረጃዎች በማጠናቀር ከምዝገባ ሊሰረዙ የሚገባ ሂሳብ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

4. የገቢ ሂሳብ

4.1 በገቢ ግብርና ታክስ አዋጅ፤ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ

በሀገር መከላከያ ሚ/ር

- በተለያዩ የሚ/ር መ/ቤቱ ክፍሎች ከቅጣት፤ከሲቪል ሠራተኞች ከህክምና አገልግሎት 50% የተሰበሰበ ከደረሰ የንብረት ጥፋት የተተካ ከጨረታ ሰነድ ሽያጭ የተሰበሰበ በድምሩ ብር 77,834.50 ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መድረግ ሲገባው ለመከላከያ ገቢዎች ዳይሬክቶሬት ገቢ ሆኖ በመገኘቱ አሰራሩ ተስተካክሎ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ እንዲሆን አሳስበናል፡፡ መ/ቤቱ አስተያቱን ተቀብሎታል፡፡

በሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ የትራንስፖርት የስራ ሂደት የተለያዩ ተሽከርካሪዎች በማከራየት የተሰበሰበው ገቢ በህጉ መሰረት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረጉና የሂሳቡ አያያዝ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

- የትራንስፖርት ዋና የስራ ሂደቱ ለተለያዩ ድርጅቶች የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት እንዲሰጥ እና ከኪራዩ የሚገኘውን ገቢ እንዲሰበስብ በህግ የተሰጠው ስልጣን ወይንም መመሪያ አለመኖሩ፤
- ተሽከርካሪ ተከራይ ድርጅቶች ሊከፍሉ የሚገባቸው የገንዘብ መጠን ለመወሰን የትራንስፖርት ዋና የስራ ሂደቱ የሚጠቀምበት የኪራይ ታሪፍ በሚመለከተው አካል የፀደቀ መመሪያ ወይንም ራሱ ያወጣው ታሪፍ የሌለው ሲሆን ክፍያ የሚጠይቀው ከተከራይ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሆኑ፤
- የትራንስፖርት ዋና የስራ ሂደቱ ተሽከርካሪዎች በሚያከራይበት ወቅት ከተከራዮች ጋር ውል ከተገባ በኋላ ተከራዮች አገልግሎቱን ማግኘታቸውን ወይም አለማግኘታቸውን እንዲሁም ከውሉ በላይ ተሽከርካሪዎች አገልግልት እንዳይሰጡ የመከታተያ ስርዓት አለመኖሩ፤

- በ2005 በጀት ዓመት ከናሽናል ኦይል ኢትዮጵያ ብር 194,250.00፣ ከብረታብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ብር 109,500.00፣ ከውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ብር 561,600.00 በድምሩ ብር 865,350.00 በውሉ መሰረት ገንዘቡ ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

- የትራንስፖርት ዋና የስራ ሂደቱ ተሽከርካሪዎች በሚያከራይበት ወቅት የነዳጅ፣ የአበል፣ የዘይትና ቅባት፣ የጎማ፣ የጥገና ወጭዎች እንዲሁም የሹፌሮች ደመወዝ እና አበል ከበጀት የሚሸፈን መሆኑ የታወቀ ቢሆንም በ2006 በጀት ዓመት ከዚሁ አገልግሎት ከተሰበሰበው ብር 5,739,990.48 ውስጥ ብር 5,000,000.00 ለገቢዎች ዳይሬክቶሬት ከህግ ውጭ ገቢ ተደርጎ መገኘቱ፤

- ዋና የስራ ሂደቱ በበጀት ዓመቱ ከሀምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም የሰበሰበውን የአገልግሎት ገቢ በዓመት አንድ ጊዜ ወይንም እንደአስፈላጊነቱ ሲጠየቁ ለገቢዎች ዳይሬክቶሬት ገቢ እንደሚያደርግ እንጂ ወዲያውኑ ወይንም በየወሩ ገቢ የማያደርግ መሆኑ፤

- በትራንስፖርት ዋና የስራ ሂደቱ የሚሰበሰበው የተሽከርካሪ ኪራይ ገቢ ሂሳብ በዋና መምሪያው የፋይናንስ ክፍል ቁጥጥር የማይደረግበት እና የተሰበሰበው ገንዘብም ዋና መምሪያው ሳይውቀው በስራ ሂደቱ በኩል ወደ ገቢዎች ዳይሬክቶሬት ገቢ የሚደረግ መሆኑ፤

- በትራንስፖርት ዋና የስራ ሂደቱ በ2006 በጀት ዓመት ከተሰበሰበው የተሽከርካሪ ኪራይ ገቢ ብር 5,739,990.48 ውስጥ ብር 740,939.35 በዋና መምሪያው ትእዛዝ ወጪ መደረጉ እንዲሁም ከ2003-2005 በጀት ዓመት ድረስ በጀት እስከሚመጣ በሚል ከዚህ ሂሳብ ለተለያዩ ስራዎች ወጪ የተደረገ እና ይተካል በሚል ወጭ ተደርጎ ከበጀት ያልተተካ በወጪ የተመዘገበ ብር 1,730,893.32 መገኘቱ፣

ህጉን ያላግባብ በመተርጎም ከተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት የተገኘው ገቢ ለመንግስት ፈሰስ ባለመደረጉ መንግስትን ገቢ ሊያሳጣ እንደሚችል፤በመመሪያ ያልተደገፈ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የተገኘውን ገቢ ዝቅ ሊያደርገው እና ለግል ጥቅም እንዲውል መንገድ ሊከፍት እንደሚችል፤ የስራ ሂደቱ በገባው ውል መሰረት ገቢዎቹን ለመሰብሰብ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት መዘርጋት እንደሚገባው፤

ለገቢ ሂሳቡም ተገቢው ምዝገባና በዋና መምሪያው በኩል ሪፖርት እየቀረበ የመንግሥትን በጀት ሳይነካ የተገኘው ትርፍ ለገቢ ዳይሬክቶሬት ሌላው ደግሞ ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የተሰበሰበውን ገቢ በሙሉ በአዋጅ በተፈቀደልን መሰረት በሰላም ጊዜ አገልግሎት ሰጥተን የተገኘ ገቢ ነው በሚል ለገቢ ዳይሬክቶሬት ማስተላለፍ አገልግሎቱ ሲሰጥ ከበጀት በተገዛው ተሽከርካሪና ጎማ ላይ የሚደርሰው የእርጅና ቅናሽ (Depreciation)፤ የነዳጅ፤ ዘይት፤ የሰራተኞች ደመወዝና አበል ሌሎቹም ከበጀት ወጪ የተደረጉት ታስበው ከተገኘው ገቢ ላይ ተቀንሶ ለመንግሥት ገቢ ካልተደረገ በአዋጅ የተሰጠውን አንቀጽ በአግባቡ ተተርጉሟል ማለት እንደማስችል አሳስበናል፡፡

- **የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት**
  - ያልተቀነሰ የሥራ ግብር በድምሩ — ብር 13,091.89
- **የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል**
  - ለመንግሥት ፈሰስ ያልሆነ ሥራ ላይ ያልዋለ የውስጥ ገቢ ድርሻ — 627,716.11
- **የንግድ ሚኒስቴር**
  - በሞ/64 ገቢ ያልተደረገና የባንክ ክሬዲት አድቫይስ ያልቀረበለት — 20,306.00

4.2 <u>በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የታዩ የአሰራር ድክመቶች</u>

- በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በየዕለቱ ከዳኝነት፣ ከቅጣት እና ከልዩ ልዩ ገቢ የተሰበሰበውን ገቢ በዕለቱ ወይም በማግስቱ ባንክ ገቢ መደረጉ ሲጣራ በናሙና በተመረጡ የታህሳስና የጥር/2006 ገቢዎች በ37 ሞ/64 ብር 2,235,442.66 ከአንድ ቀን እስከ ስምንት ቀናት ቆይቶ ባንክ ገቢ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡
- በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዳኝነት፣ ከቅጣት እና ከልዩ ልዩ ገቢ የተሰበሰበው በዕለቱ ወይም በማግስቱ ባንክ ገቢ መደረጉ ሲጣራ በጥር ወር 2006 ብር 1,903,090.08 ከአራት ቀን እስከ ሀያ አራት ቀናት ቆይቶ ባንክ ገቢ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

ሆቴሎችና ቱሪዝም በበጀት አመቱ ከውስጥ ገቢው ሥራላይ ሳይውል ተረፈውን በቀጣዩ ዓመት እጠቀምበታለሁ በሚል ለገንዘብና ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ አለማድረጉ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ ፈሰስ እንዲያደርግ አሳስበናል፡፡

ፍ/ቤቶቹ ገንዘብ በገንዘብ ያዥዎች እጅ በመቆየት ለጥፋት የሚጋለጥበትን ሁኔታ ለመቅረፍ በመመሪያው መሠረት የተሰበሰበው በየዕለቱ ገቢ እንዲሆን ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ ንግድ ሚ/ር ሪፖርቱ ወጪ ከተደረገ በኋላ በላከው መልስ ገንዘብ ያዥዋ ገንዘቡን ገቢ ማድረጓንና ለወደፊቱ ተገቢው ቁጥጥርእንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ምላሽ ለወደፊቱ የተሸለ አሠራር በመዘርጋት በየእለቱ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በዕለቱ ወይም በማግሥቱ ገቢ እንዲሆን ጥረት እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡ እንዲሁም ከፍተኛ ፍ/ቤትም በተዘዋዋሪ ችሎት የሚሰበሰበውን ገንዘብ ከየክልልና ዞን ከተሞች በቀጥታ ለማዕከላዊ ግምጃቤት ገቢ ለማድግ የሚቻልበትን ሁኔታ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር መፍተሔ ለመስጠት ጥረት እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡

5. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

5.1. <u>ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ</u>

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማስረጃ ሳይኖር ሂሳቡ የተወራረደና የተመዘገበ ብር 95,089.74 ተገኝቷል፡፡ ቅድሚያ ክፍያው እንዲፈጸም የተፈቀደበት ደብዳቤ ብቻውን በቂ ሊሆን እንደማይችል፤ሀላፊዎቹ መቼ እንደሄዱና እንደመጡ የሚገልጽ በእነርሱ የቀረበ ሪፖርት ሊኖርና በቅርብ አለቃቸው መረጋገጥ እንደሚኖርበት፤ ይህ ሳይቀርብ እንደሚሄዱ የተጻፈበትን ደብዳቤ መሰረት አድርጎ ማስረጃ የማይቀርብበት በሚል ማወራረድ አይገባም፡፡ ስለዚህ ተጓዦቹ ሪፖርት እንዲያቀርቡ፤ ይህንንም የሚደግፍ ማስረጃ ተያይዞ መቅረብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ</u>

- የሀገር መከላከያ ሚ/ር 224,956,468.35
- ሆቴሎችና ቱሪዝም ማ/ማዕከል በተለያዩ ጊዜያት ለመስተንግዶ ወጪ ከሆነው ሂሳብ ውስጥ ለገነት

ሆቴል የትዕዛዝ ደብዳቤ ሳይቀርብ ከ2 ሰው እና ከዚያም በላይ ለተስተናገዱበት ቢል ቀርቦ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ 44,174.92

- የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ 258,241.07
- የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ለተፈፀመው ግዥ የአቅራቢው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይኖር ግዢው ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ 12,013.91
- የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የተለያየ ዕቃ ለተገዛበት የአቅራቢው ደረሰኝ የሌለውና ንብረቱም ገቢ ሳይሆን ተገኝቷል፡፡ 36,680.96
- የግል/ድ/ሠ/መማ/ዋ/ኤጀንሲ ለወጪው ምንም ዓይነት ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ጸድቆ ተገኝቷል፡፡ 483,028.47

<u>ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፤</u>

- ለወጭዎች የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው ብር 370,824.76 ተወራርደው ተገኝተዋል፡፡
- የወረዳ ምርጫ ክልል ጽ/ቤቶች ባቀረቡት የወጪ ማስረጃዎች መሰረት የወረዳው ምርጫ ክልል ጽ/ቤቶች ማህተም የሌላቸው የብር 2,034,485.00 የወጪ ማስረጃዎች በማስረጃነት በመቅረባቸው የወጭውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በወረዳው ምርጫ ጣቢያ የተዘጋጀ የክፍያ ማሳወቂያ ደብዳቤ ሳይቀርብ ብር 880,700.00 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- የየወረዳዎቹ ምርጫ ጽ/ቤት ማህተም ሳይኖረው ብር 421,500.00 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ለምርጫ ታዛቢዎች እና ለምርጫ አስፈጻሚዎች ብር 166,650.00 የተከፈለበት ዝርዝር ላይ ተመሳሳይ የእጅ አጣጣልና የአሻራ ፊርማ ሆኖ መገኘቱ፤
- የተለያዩ ኃላፊዎች ፊርማ ሳይኖር ብር 10,575,596.05 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤
- ብር 7,553.956.83 ለኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር በባንክ እንደተላከ ቢያሳም ፓርቲው ገንዘቡን ስለመቀበሉ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ አልቀረበም፤ እንዲሁም ለፓርቲው ክፍያ እንዲፈጸም የታዘዘበት የማዘዣ ደብዳቤ፤ ለየትኛው ምርጫ የተሰጠ ድጎማ እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር ክፍያው ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በድምሩ ብር 10,179.80 የተከፈለው በውሎ አበል ፎርሙ ላይ ሰራተኞቹ የመጡበትና ለስራ የቆዩበት፤ የተመለሱበት ቀንና ሰአት በሚገባ ሳይሞላ ተከፍሏል፡፡እንዲሁም አመልካቹ የስንት ቀን እንዲከፈላቸው ቀኑ ካለመጥቀሱም በላይ ትዛዝ ሰጪውም ይከፈላቸው ከማለት ውጪ የቀኑን ብዛት አይገልጽም ይህ ደግሞ ክፍተት ስለአለው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የውሎ አበል ክፍያዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ2005 ዓ.ም ለተካሄደው የአካባቢ ምርጫ ማስፈጸሚያ በተለያዩ የወጪ ቫውቸሮች የተከፈለ በድምሩ ብር 44,270 የውሎ አበል ክፍያዎች ላይ የውሎ አበሉን በወሰዱት ሰዎች ብቻ ራሳቸው ጠያቂ የስራ ክፍል አረጋጋጭና ተቀባይ በመሆን በቅጹ ላይ በመፈረም አበል ወስደው ተገኝቷል ፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር የሲግናል መረጃ ሲስተም አቅርቦትና የአገልግሎት ዋጋ ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ 2ኛና 3ኛውን ወይም የመጨረሻ ክፍያ ከፍሎ በወጪ ሲመዘግብ በሞ/19 ገቢ ለተደረገው ዕቃ የዕቃውን ዝርዝርና ዋጋ የሚገልጽ ደረሰኝ እና መ/ቤቱ ለኤጀንሲው ከላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ክፍያ ሲፈጽም ኤጀንሲው

ገንዘቡን ለመቀበሉ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በማስረጃነት አለመቅረቡን በመጥቀስ ማስረጃዎቹ እንዲሚሉ አሳስበናል፡፡

5.3 <u>የሂሳብ መደባቸውን ያልጠበቁ ወጪዎች</u>

- በሀገር መከላከያ ሚ/ር በ6271 ከተከፈለው ብር 178,642.59 ውስጥ ብር 25,843.49 በ7/10 አገልግሎት ከሠራዊቱ ለተሰናቡት አባላት ለትራንስፖርት ከሂሳብ መደቡ ማብራሪያ ውጪ ክፍያ የተፈጸመው አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ ማስተካከያ እንዲሰራለት አሳስበናል፡፡
- በሀገር መከላከያ ሚ/ር በ6271 ከተከፈለው ብር 178,642.59 ውስጥ ብር 25,843.49 በ7/10 አገልግሎት ከሠራዊቱ ለተሰናቡት አባላት ለትርንስፖርት ከሂሳብ መደቡ ማብራሪያ ውጪ ክፍያ የተፈጸመው አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ ማስተካከያ እንዲሰራለት አሳስበናል፡፡
- ባልተፈቀደ በጀት ለውጭ ሀገር ስልጠና ከሀገር ውስጥ ስልጠና ከሂሳብ መደብ (በ6271) ብር 436,075.47 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

5.4. <u>ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ፤</u>

- የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መመሪያው ከሚፈቅደው የገንዘብ መጠን የበላይ ኃላፊ ከተሰጠው ገደብ በላይ ከመዝገብ የተሰረዘ የተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 54,186.62
- በሀገር መከላከያ ሚ/ር ምሥራቅ ዕዝ የውሃ እና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያዎች ለዕዙ አገልግሎት የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በመከላከያ ፋውንዴሽን ስር ለሚተዳደር የሐረር ቤተመንግስት መዝናኛ ክበብ የውሃ አገልግሎት ክፍያ ብር 201,698.00 እንዲሁም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ብር 60,444.97 በድምሩ ብር 262,142.97 ያላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል በማኔጅሜንት በተሰጠ ውሳኔ በሚል ከውስጥ ገቢ በወር ብር 3,500.00 ለዘጠኝ ወሮች ከመመሪያ ውጪ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በድምሩ ብር 31,500.00

5.5. <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸመ ግዥ</u>

➢ የፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር የጨረታ ሰነዱ የታየውና ግዥው እንዲጸድቅ የተደረገው በአንድ ኮሚቴ መሆኑንና በውስን ጨረታ እንዲገዛ የተደረገበት ምክንያት ያልተገለጸ፤	770,900.06
➢ ፌዴራል ፖሊስ	1,472,356.59
➢ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ህንጻ ሲከራይ የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ አስፈላጊው ውድድት ሳይደረግ ቀጥታ ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት አክሲዮን ማህበር ጋር የውል ስምምነት በመፈፀም በበጀት ዓመቱ የ9 ወራት ክፍያ ተገኝቷል	1,796,693.76
➢ የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ልማት ኤጀንሲ ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ፤ ግዥን ከከፋፍሎ በመግዛት	537,218.61
➢ የንግድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዕቃና እና አገልግሎት ግዥ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ውድድር ሳይደረግ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡	278,932.50
➢ የኢትዮጵያ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ፤ ለመስተንግዶ አገልግሎት የግዥ መመሪያ ከሚፈቅደው ውጪ ከአንድ አቅራቢ የምክር አገልግሎት ግዥ	205,239.70
➢ የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ውጪ ከአንድ ድርጅት ብቻ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡	104,650.00
➢ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ድጋሚ ጨረታ ሳይወጣ አስቸኳይ በሚል ግዢው ከሙዳይ ማተሚያ ቤት ከአንድ አቅራቢ ድርጅት ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል	248,975.00

➢ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመረጃ ማጠናከር መተንተንና ሪፖርት ለማዘጋጀት የፈጸመው ክፍያ ብር 94,000 በፌዴራል መንግስት የግዢ አፈፃፀም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም አንቀጽ 24.2 መሰረት በዋጋ ማቅረቢያ የግዢ ዘዴ ግዢ ሲፈፀም ከብር 75,000 በላይ ለሆኑ ግዢዎች ግዢው ለግዢ አጽዳቂ ኮሚቴ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም በግዢ አጽዳቂ ኮሚቴ ሳይጸድቅ ግዢው በግዥ ኮሚቴ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

በግዥ ሕጉ መሠረት ግዥዎች እንዲፈጸሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ለተላከለት ስራ አመራር ሪፖርቱ መልስ ባለመስጠቱ የኦዲት ሪፖርቱ የተላከለት ሲሆን ነገር ግን ዘግይቶ በላከው መልስ፤ - በተለያየ ጊዜ ከአበሻ 2000 ባህላዊ ሬስቶራንት የአገልግሎት ግዥ የተፈጸመው የኢንቨስትመንት ስራዎችን በቆዳው ዘርፍ ለማከናወን የሚመጡ የውጭ ሀገር ባለሃብቶችን ለመሳብ በሚደረገው ጥረት እንግዶቹ በሚመጡበት ጊዜ ያለውን የሀገሪቱን ብሎም የዘርፉን ገጽታ ከመገንባት አንጻር በወቅቱ የዋጋ ማወዳደሪያ አሰባስቦ ለማየት ጊዜ ስለማይሰጥ ፤ ባህላዊ ሬስቶራንቱ በከተማዎቹ መሀል የሚገኝ፤ ለደህንነትም ተመራጭ በመሆኑ አገልግሎቱ እንዲገኝ መደረጉን እንዲሁም ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ ለቢእነስ ፎክስ የማስታወቂያ ክፍያ የተፈጸመው በቆዳው ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመረቱ ፤የቆዳ ውጤቶችን በአውሮፓ፤በኤሽያ በሌሎች አህጉራት ይበልጥ ለማስተዋወቅ ተመረጭነት ያለው የሚዲያ ግኑነት በመሆኑ በበላይ አካል በመታመኑ በፌዴራል የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 18.1 መሠረት መከናወኑን በላኩት ምላሽ ሰጠተዋል፡፡ይሁን እንጂ አንቀጽ 18.1 ለዓለም አቀፍ ግዥዎች የሚገልጸው የውጭ ኩባንያዎች ካልተሳተፉበት በቀር ውጤታማ ሊሆን አይችልም ተብሎ ሲታመን በአዋጁና በዚሁ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ለብሔራዊ ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የተገለጹት ሌሎች አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት መ/ቤቶች የሁለት ደረጃን የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የውስን ጨረታን የዋጋ ማቅረቢያንና ከአንድ አቅራቢ የግዥ ዘዴን በመጠቀም ዓለም ዓቀፍ ግዥን እንደሚፈጽም የሚደነግግ ሲሆን የኢንስቲትዩቱ በበላይ ሃላፊ ለስራ ጉዳ ወደውጭ ሀገር ሲሄዱ እግረመንገዳቸውን ሊሰሩት የሚገብ ሳይሆን በተቋሙ የግዥ ኮሚቴ አሰፈልጊው ሂደት በሀገር ቤት ተካሂዶ አጽዳቂ ኮሚቴው ውሳኔ ከሰጠ በኂላ ሊፈጸም የሚገባው በመሆኑ አሠራሩ ግልጽነት የሌለውና በመረጃ ያልተደገፈ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

5.6 <u>የተለያዩ የመሰረት ልማት ግንባታ ወጪዎችን በተመለከተ ለተለያዩ ለግንባታ የቀረቡ ዕቃዎች በሥራ ላይ ሳልዋሉ (Material on site) ተብሎ የተከፈለ</u>

5.6.1 በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ለግንባታ ሥራ አገልግሎት እንዲውሉ ታቅደው በግንባታ ሥራ ቦታ የሚገኙ (Material on site) ግን ጥቅም ላይ

ያልዋሉ ግብዓቶችን መጠን እና ዋጋ ከመመሪያ ውጪ ብር 3,332,550.00 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ኦዲት አስደራጊዎች በሰጡት ምላሽ ይህ ክፍያ የተፈጸመው ከህንጻ እድሳት አማካሪ ድርጅት ጋር በቂ ውይይት ተደርጐ እንዲሁም የጽህፈት ቤቱ ማናጅመንት ተወያይቶበትና አምኖበት ተመጣጣኝ የሆነ የክፍያ ማስከበሪያ ሲፒኦ ተይዞ መሆኑን፤

ጽህፈት ቤቱ ይህንን አማራጭ የወሰደው በወቅቱ የበጀት መዝጊያ ጊዜ ስለደረሰና ክፍያውን ፈጽመው ህንጻውን በመረከብ ካልገቡ ተከራይተው የነበሩበት ቢሮ ሐምሌ 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሚጠናቀቅ በመሆኑ ፈጥነው ወደ ታደሰው ቢሮአቸው ካልተመለሱ ለተከራዩት ህንጻ ተጨማሪ የአንድ ዓመት ክፍያ ማለትም ወደ ሦስት ሚሊዮን የሚጠጋ ብር መክፈል የሚጠበቅባቸው መሆኑንና ይህንን ወጪ ለማስቀረት ተብሎ የተፈጸመ መሆኑ፣ገልጿል ፡፡

በግንባታ ሥራ ቦታ ለሚገኙ ጥቅም ላይ ላልዋሉ ግብአቶች ሲፒኦ እንደማይያዝ፤ አማካሪ መሀንዲሱም ውሳኔ የሚወስንበት ጉዳይ አለመሆኑን እንዲሁም የጽህፈት ቤቱ ማናጅመንት ተወያይቶበትና አምኖበት ተመጣጣኝ የሆነ የክፍያ ማስከበሪያ ሲፒኦ ተይዞ የሚለው ምላሽ በመንግሥት የወጣውን መመሪያ በአንድ ጽ/ቤት ማናጅመንት ውይይትና አምኖ መቀበልና የበጀት መዝጊያ በመሆኑ የሚለወጥ አለመሆኑን፤እንዲሁም በግዥ ማንዋሉ መሠረትም ለማንኛውም የግንባታ ሥራ የሚዘጋጀው የክፍያ አፈጻጸም ሰርተፊኬት ለግንባታ ሥራው አገልግሎት እንዲውሉ ታቅደው በግንባታ ሥራው ቦታ የሚገኙ ግን ጥቅም ላይ ያልዋሉ ግብዓቶችን መጠን እና ዋጋ ያላካተተ መሆን እንደሚገባው ገልጸናል፡፡ ስለዚህ ጽ/ቤቱ የከፈለው ክፍያ መመሪያን የጣሰ ሆኖ በመገኘቱ ክፍያውን ያፀደቀው አካል ሊጠየቅ እንደሚገባ ለወደፊቱም በመመሪያው የተከለከሉ ክፍያዎች እንዳይፈፀሙ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.6.2 በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የህንጻው እድሳት ከተጠናቀቀ በኂላ የመጨረሻ ርክክብ እስከሚፈጸም ድረስ ተይዞ የሚቆየውን ተከፋይ ሂሳብ ብር 572,121.87 በተመደበለት የሂሳብ መደብ በ5061 ተመዝግቦ ሪፖርት ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

ለሥራ አመራር ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት ተጠይቆ ባልመጣ በጀት ላይ ወጪ ማሳየት በጀት ኔጋቲቭ እንዲያሳይ ስለሚያደርግ

የመያዣው ሂሳብ መክፈያ ጊዜ የተቃረበ በመሆኑ ተጨማሪ በጀቱን ጠይቀን ወጪ ላይ ብናሳይ አማራጭ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል የነበሩ ባለሙያዎች ሂሳቡን በተንከባላይነት ያላሳዩ በመሆኑ የቀድሞው አመዘጋገብ የፈጠረው ችግር መሆኑንና ከዚህ በመማር ቀጣዩን አሰራራቸውን በማስተካከል ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ጽ/ቤቱ የሚቀንሰውን የመያዣ ሂሳብ በመንግሥት የሂሳብ አወቃቀር መሠረት መዝግቦ ሊይዝና ሪፖርት ሊያደርግ እንደሚገባና ያልተመዘገበውም የመያዣ ሂሳብ ምዝገባው ሊከናወን እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.6.3 <u>በብልጫ የተከፈለ የኮንስትራክሽን ክፍያ</u>

በፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን የአስተዳደር ልማት ዘርፍ ለግንባታ ሥራየተፈጸመው ክፍያ በተገባው ውል መሆኑ ሲጣራ በክፍያ ሰርተፍኬቱና በውል መካከል ያለው የነጠላ ዋጋ (unit price) ሲነጻጸር ብር 13,202.50 በብልጫ ክፍያ ተፈጸሞ ተገኝቷል፡፡

ለኮንትራክተሩ የተከፈለው ክፍያም ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባና ለወደፊቱም የኮንስተራክሽን ክፍያዎች ሲፈጸሙ በተገባው ውል መሠረት መሆኑ ክፍያ መፈጸሙ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

ኮሚሽኑ ሪፖርቱ ከተላከለት በኋላ በሰጠው መልስ በአጠቃላይ እየተቀነሰ ስለሚከፈል በውሉ ላይ ከተቀመጠው ዋጋ ለውጥ እንደማያመጣ ገልጧል፡፡

5.7 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ /መ/19/ ያልቀረበ</u>

- በፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር ለመኪና መለዋወጫ እና ለመ/ቤቱ አዳራሽ መጋረጃ ለተገዛበት በድምሩ ብር 270,046.50 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ተገኝቷል፡፡
- በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብር 88,250.00
- በፌዴራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዘርፍ ብር 499,871.83
- የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሄራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት ብር 74,879.12

ለተፈመው ግዥ ሂሳቡ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሊቀርብ እንደሚገባና ለወደፊቱም አሰራሩ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ሲሆን፤ ኦዲት ሪፖርቱ ከተላከለት በኂላ በሰጠው ምላሽ ንብረቱ የተባይ ማጥፊያ መድሃኒት መሆኑን፤ በአንድ ጊዜ ለማስገባት የመጋዘን ጥበት በማጋጠሙና መድሃኒቱን በአንድ ላይ መደራረብ ጉዳት ስለሚያስከትል በሁለት ጊዜ እንዲገባ የተደረገ መሆኑንና የንብረት ገቢ ደረሰኙ መቅረቡን ገልጧል፡፡

የጠቅላይ ፍ/ቤት የኦዲት ሪፖርቱ ከተላከለት በኂላ በሰጠው ምላሽ ማንኛውም ለፍ/ቤቱ አገልግሎት የሚውሉ ንብረቶች ሞ/19ገቢ ሳይሆን ክፍያዎች በፋይናንስ በኩል እንደማይፈጸምና ይህን ግኝት በተመለከተ አልተጠየቅንም የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ የሥራ አመራር ሪፖርት ሲላክ በኦዲቱ ወቅት የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለ ግኝቱ የሰጡትን ምላሽ አካተን የላክን ሲሆን በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው የኦዲት ማስታወሻ የሰጡት መልስ ለደቡብ ክልል የድጓማ በጀት እንደተላከ፤እቃዎች ተገዝተው ሂሳቡ ሲወራረድ ሞ/19ኞች ለፋይናንስ እንደማይመጡ ወደፊት በፋይናንስ በኩል ክትትል እነደሚደረግ ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ የፍ/ቤቱ የዕቃ ግዥ ሂሳብ ሲወራረድ ማስረጃ ሲቀርብ ዕቃው ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገበት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 መቅረቡ እንዲረጋገጥ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባና ይህ ካልሆነ ወጪው ለመ/ቤቱ አገልግሎት መዋሉ የማይረጋገጥና ለጥፋት መንገድ ይከፍታል፡፡ በመሆኑም ንብረቱ ሞ/19 ሊቀርብለት ካልሆነ ከሚመለከተው ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ገንዘቡ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.8 <u>የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

➢ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚሊተሪ ደሞዝና አበል	3,797,151,121.09
- በሀገር መከላከያ ሚ/ር ለመረጅ ግዢ	33,736,693.78
- ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	273,845,378.34
➢ በፌደራል ፖሊስ ለመረጅ ግዢ	667,553.80
➢ የፌዴራል ከፍተኛ ፍቤት	1,779,873.81

- የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልገሎት ከውጭ ሀገር ለገቡለት እህል፣ተሽከርካሪዎች፣ ሞተር ብስክሌቶች፣ ብርድ ልብሶች፣ ወዘተ፣ በተለያየ የሂሣብ መደቦች በወጪ የተመዘገበው ብር 273,845,378.34 ኦዲት ሲደረግ ከእርዳታ ሰጪዎች የተሰጠውን የእቃ አይነት ብዛት የሚገልጽ ማስረጃ ወይም ቢል ኦፍ ሌዲንግ ወይም የአቅራቢው የሽያጭ ኢንቮይስ፡ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን እና ዕቃዎቹ ገቢ የተደረጉበት የንብረት ገቢ ደረሰኞች(GRN) ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻልም፡፡
- በጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍቤት የ16 የክፍያ ቫውቸሮች የወጪ ማስመስከሪያ እና ደጋፊ ማስረጃዎች በተደጋጋሚ ተጠይቆ ባለመቅረባቸው የብር 1,779,873.81 ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ገንዘቡ ሲሰበሰብ የተቆረጡት ደረሰኞች እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ሳይኖር ሂሳቦቹ በወጪ መመዝገባቸው ለፍ/ቤቱ ሥራ ያልዋሉ ወጪዎች ሊሆኑ ስለሚችሉ ፍ/ቤቱ የወጪ ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ ሁኔታው እንዲጣራ ውጤቱም እንዲገለጽልን ካልሆነ ለወጪዎቹ ማስተካከያ ሊሰራ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

  የኦዲት ሪፖርቱ ከተላከ በኂላ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ምላሽ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት በሚል የቀረቡትን የወጪ ማስረጃዎች የባንክ አድቫይዞች ፎቶ ኮፒ አድርጎ አያይዞ ልኳል፡፡
- የፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን የስራ አመራር ሪፖርት መልስ ባለመስጠቱ ኦዲት ሪፖርት ከተላከ በኂላ በሰጠው ምላሽ ማስረጃ ማሰባሰብ እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ የአባሎቹንና የግለሰቦቹን ስም ዝርዝር በማስረጃነት ማቅረብ ማለት የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ደህንነት አደጋ ላይ መጣል መሆኑ፣ ሥራውንም በእጅጉ መጉዳት መሆኑን ገልጿል፡፡

  የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል በማቋቋሚያ አዋጁ ለሚኒስትሩ ስልጣን በተሰጠው መሰረት ሚስጢር የተባሉትን በየሂሳብ መደቡ ለይቶ ስላላሳወቀን በአንዳነድ ክፍሎች ማስረጃዎች ሲቀርቡ በአንዳንድ ክፍሎች ሚስጥር ናቸው በማለት ያልቀረቡ መገኘታቸውን፣ከሠራዊት ደመወዝና አበል ውጪ ለምሳሌ በ6246፣6244፣6325፣6211 እና በመሳሰሉት

ግልጽነት እንዲኖረው መ/ቤቱ ሚስጥር ናቸው የሚላቸውን በየሂሳብ መደቡ ለይቶ እንዲያሳውቀን አሳስበናል፡፡

5.9 <u>ከበጀት ዓመቱ ውጪ የተፈጸመ ክፍያ፤</u>

በካይዘን ኢንስቲትዩት ከበጀት ዓመቱ ውጪ ብር 58,820.63 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

በበጀት ዝግጅት ወቅት በጀት ሊያዝ የሚገባው በበቂ ጥናት ተመሥርቶ ሊሆን የበጀት እንደሚገባና የበጀት ጥረት እንኳን ቢያጋጥምም በወቅቱ ዝውውር በመጠየቅ ወይም ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ የበጀት ዓመት ወጪዎች በተያዘላቸው በጀት ዓመት በወጪ እንዲመዘገቡ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

6. <u>ዕቃና የንብረት አስተዳደር</u>

6.1 የቋሚና አላቂ ዕቃ ምዝገባ ያልተከናወነባቸው መ/ቤቶች

- በጠቅላይ ፍ/ቤት የፎቶ ኮፒ ማሽን መለዋወጫ እቃዎች በመዝገብ ሳይመዘገቡ ተገኝቷል፡፡

  ፍ/ቤቱ ኦዲት ሪፖርት ከተላከ በኋላ በሰጠው ምላሽ የፎቶ ኮፒ ማሽን ከነመለዋወጫው በእርዳታ የተገኘ መሆኑንና ማሽኑ በወቅቱ ወጪ ሆኖ ለአገልግሎት ሲውል ማሽኑ ውስጥ የተገኘው መለዋወጫ ተራፊ ስለነበር አለመመዝገቡን ገልጸዋል፡፡

  በስጦታ የተገኘም ቢሆንም የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት በመዝገብ መመዝገብ ስለአለበት የተጠቀሱት ንብረቶች እንዲመዘገቡ አሳስበናል ፡፡

6.2 <u>የቋሚና አላቂ ዕቃ ቆጠራ ከመዝገብ ወጪ ቀሪ(ከእስቶክ ካርድ) ያልተገናዘበ ሆኖ የተገኘ፤</u>

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሄራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂና የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የጽ/ቤቱ ንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲፈፀም ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

6.3 ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ፤

- በጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት
- በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት
- ኢትዮጵያ የሕዝብ እንባጠባቂ
- ፍትሕ ሚኒስቴር

በፌዴራል መንግሥት የንብረት አያያዝና አጠባበቅ መመሪያ መሠረት ቋሚ ንብረቶች የመለያ ቁጥር ተሰጥቷቸውና ተመዝግበው መያዛቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ የፍትሕ ሚ/ር ከ2003 ዓ.ም. ወዲህ ለተገዙ ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር አለመሰጠቱ፤

6.4 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም

ሊብሬ ያልቀረበላቸው

- ጠቅላይ ፍ/ቤት ሥር የሚገኙ ሰባት ተሽከርካሪ መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ /ሊብሬ/ የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ ፍ/ቤቱ የኦዲት ሪፖርት ከተላከ በኋላ በተሰጠው ምላሽ የሰሌዳ ቁጥር 4-12011፤ 4-15920 4-15921፤ 4-04545 ሊብሬ ፎቶ ኮፒ አድርጎ አያይዞ አቅርቦ የባለቤትነት ደብተር ወይም ሊብሬ የሌላቸው ሶስት ተሽከርካሪዎች ብቻ መሆናቸውንና ለእነርሱም እንዲሰጣቸው ክትትል ላይ መሆናቸውን ገልጿል፡፡ሊብሬ ያልወጣላቸው ተሽከርካሪዎች አስፈላጊው ክትትል ተደርጎ ባለቤትነት መታወቂያ /ሊብሬ/ እንዲወጣላቸው በድጋሚ አሳሰበናል፡፡

6.5 ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመት የታየባቸው

በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

በመጠየቂያው ሞ/20 ላይ የሚመለከተው ኃላፊ ሳያፀድቅ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የመኪና ባትሪ፤ ሽራ ዲስክ፣ የካሚዩ ኩሽኔት፣ CDMA ካርድ 2፣ ምግብና መጠጦች (ቆሎ፣ ውሀ፣ ዳቦ ቆሎ ወዘተ…) የስጦታ ጌጥ፣ የፕሪንተር ቶነር የነዳጅ ኩፖን ወዘተ

በድምሩ ብር 160,442.36 የሚያወጡ ንብረቶች ከመንግሥት የንብረት አስተዳደርና መመሪያ ውጪ ጥያቄው በኃላፊ ሳይፀድቅ ከንብረት ክፍል ወጪ ተደርጐ ተገኝቷል፡፡

ፍ/ቤቱ ኦዲት ሪፖርት ከተላከ በኂላ በሰጠው ምላሽ ልዩ ልዩ ንብረቶች ወጪ በሚሆንበት ወቅት በጣም አስቸኳይ በሚሆንበት ወቅት ኃላፊዎች ሲመጡ ለማስፈረም ወጪ የተደረጉ መሆኑን ገልጿል፡፡

የፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር የሚጠይቀውን ባለመከተል የተለያዩ አሳማኝ ያልሆኑ ምክንያቶችን በማንሣት ንብረቶችን ወጪ ማድረግ ተጠያቂነት መኖሩን አለመረዳትና ኃላፊነትን አለመወጣት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ንብረት ወጪ ከመደረጉ በፊት በሚመለከተው ኃላፊ መፈቀዱ ሊረጋገጥ እንደሚገባና የተጠቀሱትም ወጪ የተደረጉት ንብረቶች ለመ/ቤቱ ሥራ መዋላቸው በውስጥ ኦዲት መረጋገጥ እንዲረጋገጥ አሳስበናል፡፡

7. <u>በጀት</u>

7.1 <u>ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለመረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ6 መ/ቤቶች ብር 5,458,974.33 ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ /ዝረዝራቸው አባሪ- 33 ተመልክቷል/

ለየመ/ቤቶቹ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የበጀት አጠቃቀም ግድፈት እንዳይደርስ ጥንቃቄ እንዲያድርጉ አሳስበናል፡፡

7.2 <u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት</u>

በ2006 በጀት ዓመት የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲገናዘብ ከ10% በላይ ያለውን ብቻ በመውሰድ ያልተሠራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ21 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 140,583,111.57 እና

በ15 መ/ቤቶች ከካፒታል በጀት ብር 33,257,219.18 በድምሩ ብር 173,840,330.75 በስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝረዝራቸው አባሪ- 33 ተመልክቷል/

ስለሆነም አገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ መ/ቤቱ በእቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሰረተ የበጀት ጥያቄ ሊያቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

8. <u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

8.1 <u>ወጪ</u>፤

የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በሶስት ጊዜ ክፍያ በድምሩ ብር 27,350,502.50 ለሰንዓ ፎረም የተከፈለው ለፎረሙ ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በመመሪያ ወይንም በሀገሪቱ በተደረሰው ስምምነት መሰረት የኢትዮጵያ የመዋጮ ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ የሚገልፅ ማስረጃ ባለመቅረቡ የመዋጮውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ፤ የሀገሪቱ ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ ሥልጣን ባለው አካል የተፈቀደበት ማስረጃ ለኦዲት ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል።

መ/ቤቱ በላከው መልስ ከ11 ዓመት በፊት ትእዛዝ የተሰጠበትን ደብዳቤ ከጊዜ መርዘም የተነሳ አለመቻላቸውን ገልጸዋል።

8.2 <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 189,610,276.93 ውስጥ ብር 168,369,827.51 መወራረዱን በኦዲቱ ወቅት የተሰጠውን መግለጫ መሰረት በማድረግ ተወራረደ የተባለው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ

2.1 ብር 27,411,285.24 የተሰብሳቢ ሂሳቦችን ክሬዲት እና የተጣራ ሀብት ዴቢት በማድረግ ከመዝገብ ለተሰረዙት ሂሳቦች መሰረት የሆኑት ሰነዶችና ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው ተወራረደ የተባለውን ሂሣብ አለመቀበላችንን በመግለጽ ትክክለኛነቱን ለማረጋጥ እንዲቻል፤ መዛግብት፤ የወጪ ቫውቸሮች ፤የባንክ ሂሣብ ማስታወቂያዎች፤ የፈሰስ ሰነዶች የገቢ ቫውጨሮች እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠነዶች ስላልቀረቡ የተደረገውን ምዝገባ ወደነበረበት እንዲመለስ(reversing entry) አሳስበናል።

መ/ቤቱ በላከው መልስ የወሰደው ምዝገባ ትክክል መሆኑን፤ ማስረጃ እንዳለው ቢገልጽም ባደረግነው ማጣራት አንድን ሂሣብ በተተቀሰው መልክ ምዝገባ ለማካሄድ መሰረት የሆኑት በሙሉ አልቀረቡም።

- ብር 36,716,650.83 የተሰብሳቢ ሂሳቦችን ክሬዲት እና የተከፋይ ሂሳቦችን ዴቢት በማድረግ ከመዝገብ የተሰረዙት ሂሳቦች ለማጣፋት መሰረት የሆኑት ሰነዶች፣ ማስረጃዎች መዛግብት፤ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠነዶች ባለመቅረባቸው፤ በመ/ቤቱ ሠራተኛ/ሃላፊ ወይም በአንድ ሌላ መ/ቤት ሥም የተመዘገበን ተሰብሳቢና ተከፋ ሂሳብ በማጣጣት ወይም በማገዳደል ሂሳብ ማወራረድ የፋይናንስ ስርአቱ የማይፈቅድ መሆኑን በመግለጽ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉንና የተደረገው ምዝገባ ወደነበረበት እንዲመለስ(reversing entry) አሳስበናል፡፡

  መ/ቤቱ በላከው መልስ የወሰደው ምዝገባ ትክክል መሆኑን፤ ማስረጃ እንዳለው ቢገልጽም ባደረግነው ማጣራት አንድን ሂሣብ በተጠቀሰው መልክ ምዝገባ ለማካሄድ መሰረት የሆኑት ማስረጃዎች በሙሉ አልቀረቡም፡፡

- ብር 8,242.57 ከአቡጃ ዲፕሎማት (ወ/ሮ ሰላም አዳም) የቤት ኪራይ ለመክፈል የተበደሩት እንዲቀነስ ተደርጓል ቢልም ገንዘቡ ለመሰብሰቡ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ መሆኑን በመግለጽ ማስረጃ እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡ መስሪያቤቱ ማስረጃ ማቅረቡን በላከው መልስ ገልጧል፡፡ ይሁን እንጂ ቀረበው ማስረጃ ሲታይ ፎቶኮፒ በመሆኑ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

- በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ በተሰብሳቢ ከተመለከተው ሂሳብ ውስጥ ብር 168,369,827.51 መወራረዱ በተገለጸው መስረት ከፍብሎ በቁጥር 2ሥር በተገለጸው ሁኔታ ተወራረደ ከተባለው ተሰበሰሳቢ ሂሳብ ሲቀነስ ለብር 82,368,644.21 ተሰብሳቢ ሂሳቦች ምንም ማስረጃ ያልቀረበላቸው በመዝገብ የሌሉ በሂሳብ ሪፖርትም ያልተገለፁ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ መ/ቤቱ ለስራ አመራር ሪፖርቱ በላከው መልስ ሠነዶች ለኦዲት እንደቀረቡ ጊዜ የለም በሚል አለመታየታቸውን በመ/ቤቱ ታሪክ በመዝገብ ያልተገለጸ በሪርት ያልታየ እነደሌለ በመግለጽ እንዲታይላቸው ጠይቀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በወቅቱ ማስረጃዎቹ በቅርብ እንደሌሉ በየሚሲዮኖቹ እንደሚገኙ ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው ለቡድኑም ለዳይሬክተሩ ለክቡር ዋና ኦዲተር በመገለጹ ኦዲቱ የሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ስላለው በስምምነት ሰነዶቹ የሚቀርቡበት ቀን የጊዜ ገደብ ተቀምጦ የተሰራ በመሆኑ አቅርበናል የሚለው ተቀባይነት የለውም፡፡ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ማስረጀው ቀርቦ ሲታይ ብር37907311.63 ሚሲዮኖች

በራሳቸው የወራረዱት በሚል የቀረበ ቢሆንም ከዚህሂሳብ ውስጥ በቫውቸር ቁጥር 0290 ብር 10024172.95 ሲታይ ብር 3188603.30 ብቻ እንደሆነ ይህም ሂሳቡን ለመወራረድ የሚያስችል ማስረጃዎች የሉትም ከዚህ ሂሳብ ውጪ ያሉትም በማስረጃ የተደገፉ ሆኖ አልተገኙም፡፡ ልነቱ ብር 44461332.58 ምንም ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ ከመውጫ ስብሰባባ በኋላ በተደረገው ማጣራት ታውቋል ማስረጃ እንደሚቀርብ ሲጠየቁ የፋይናንስ ዳይሬክተሯ በሰጡት መግለጫ በሚቀጥለው በጀት ዓመት ኦዲት እንደሚያቀርቡ ገልጠዋል፡፡ በአጠቃላይ በመ/ቤቱም ሆነ በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሪፖርት ልተገለጸና ከመዝገብ የሰረዘ የሚለው ፉከራ እውነትነት እንደሌለው ታውቋል፡፡

- በኒውዮርክ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን መ/ቤቱ ከቪዛ ገቢ እንዲጠቀም ከተፈቀደው ሂሳብ እንዲተካ ከተደረገው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 663,155.09 በሂሳብ ሰነዱ ላይ የሂሳብ መደቡ ተሰርዞ ተደልዞ መገኘቱን በመግለጽ ሂሳቡ በተመዘገበበት በጀት ዓመት የሂሳብ መዝገቦች ለኦዲት ቀረበው ሂሳቡ ሊጣራ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ መ/ቤቱ በላከው መልስ በቀጣይ ሰነዶቹን ላለመደለዝ ጥረት እነደሚያደርግ ለተፈጠረው ችግር አማራጭ የሌለው መሆኑን ገልጧል፡፡ የመጀመሪያው ምዝገባ ቀርቦ መጣራት ስላለበት አማራጭ የለውም የሚለውን አልተቀበልነውም፡፡
- ከዋናው መ/ቤት ከተተካው ሂሳብ ውስጥ ብር 346,823.67 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ተወራርዶ መገኘቱን በመግለጽ ሂሳቡ በተመዘገበበት በጀት ዓመት ሰነዶችና የሂሳብ መዝገቦች ለኦዲት ቀረበው ሂሳቡ መጣራት እንዳለበት አሳስበናል፡፡ከዚህ ሂሳብ ውስጥ ለብር 291,795.57 ለስራ አመራሩ በሰጡትን መልስ በማድረግ ማስረጃዎች አቅርበው ተቀባትነት ያገኘሲሆን ብር 55,037.10 ማስረጃ የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርት የተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 189,610,276.93 ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2006 ድረስ ያልተወራረደ እና በሪፖርት የተመለከተ ሂሳብ በድምሩ ብር 21,240,449.42 ኦዲት ሲደረግ ፤

- ብር1,846,214.94 በተለያዩ ሚሲዮኖች በቤት ኪራይ እና ሌሎች እንደ መብራት፣ ኢንተርኔት እና ጋራዥ የመሳሰሉ መያዣዎች የተከፈለ መሆኑ የቀረበ ቢሆንም የአገልግሎቱ ውል በየወቅቱ በሚሲዮኖቹ የታደሰ መሆኑን ማስረጃ ያልቀረበ ፤
- በተለያዩ የመ/ቤቱ ሰራተኞች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ተብሎ ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ ብር 1,914,653.81 የተሟላ ማስረጃ የሌለው እና ከማን እንደሚፈለግ ለኦዲት የቀረበው ሰነድ የማያመለክት ፤
- ከ10 ዓመት በላይ የቆዩ እና ሂሳቡን ከመዝገብ ለማሰረዝ በክትትል ላይ ያለ ተብሎ ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ ብር 267,917.65 ገንዘቡ ለማን እንደተከፈለ እና ከማን እንደሚፈለግ ማስረጃ ለኦዲት ያልቀረበ ፤
- ከግብርና ሚኒስቴር ብር 1,468,044.71፣ ከሶማሌ ክልል ብር 1,770,743.25 ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ብር 1,986,671.90 በድምሩ 5,225,459.86 ከመ/ቤቶቹ እንደሚፈለግ እና በተደጋጋሚ መ/ቤቶቹ ተጠይቀው ገንዘቡን ገቢ ባለመድረጋቸው ምክንያት በሚል ለዓመታት የቆየ፤
- ብር 9,805,271.44 ሂሳቡ ከማን እንደሚፈለግ የማይታወቅና እና ማስረጃው ለኦዲት ያልቀረበ ፤ መገኘቱን በመግለጽ

የተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ማስረጃ ተሟልቶ ካልተያዘ እና በወቅቱ እንዲሰበሰብ በቂ ክትትል ካልተደረገ የመንግስት ገንዘብ ላይሰበሰብ እና ለግል ጥቅም ሊውል እንደሚችል አሳስበናል፡፡

መ/ቤቱ በላከው መልስ የቤት ኪራይና ሌሎች አንደ መብራት ኢንተርኔትና ጋራዥ ውሎች ከሁለቱ ወገኖች በአንዳቸው ውሉ ካልፈረሰ በየዓመቱ የሚታደስ አለመሆኑን፤ በመ/ቤቱ ሰራተኞች ስም የተያዙት ማስረጃ የሌላቸውን በተመለከተ ተጣርቶ ውሳኔ እንደሚሰጥበት፤ ከሌሎች መ/ቤቶች የሚፈለገው ለገ/ኢ/ል//ሚ/ር ውሳኔ እንዲሰጥበት መቅረቡን፤ ማስረጃ የሌለውን ብር9,805,271.44 በተመለከተ ማስረጃ ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

8.3 **ተከፋይ ሂሳብ**

በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርት በተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ ብር 179,361,280.26 ብር 165,333,128.20 መወራረዱ በኦዲቱ ወቅት ኦዲት አስደራጊዎች በሰጡን መግለጫ መሰረት ትክክለኝነቱ ሲጣራ፤

ተከፋይና ተሰብሳቢ ሂሣብን በማጣፋት ከመዝገበ የተሰረዘ (የተወራረደ) የተከፋይ ሂሣብ ብር 64,344,349.54 ሚ/ር መ/ቤቱ ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር ባለው የስራ ግንኙነት ሠራተኞች ያለባቸውን ተከፋይ ሂሣብ በስማቸው ከተያዘው ተሰብሳቢ ሂሣብ ጋር አንድ ሚስዮን ከሌላው ሚሲዮን የሚፈለገውንና እዳውን ፣ ሌላው ሚሲዮን በአንዱ ሚሲዮን ሥም በተከፋይ የያዘውንና በበጀትና በቪዛ መካከል የተመዘገበውን ከተከፋይ ሂሳብና ከተሰብሳቢ ወ.ዘ.ተ በማገዳደል ከሂሳብ አሰራር ውጭና በማስረጃ ሳይደገፍ ብር 64,344,349.54 ተወራርዶ መገኘቱን ማስተካከያዎች በበቂ ማስረጃ መደገፋቸው ላያጣራ ይችላል፣ለመ/ቤቱ አገልግሎት ያልዋሉ ተከፋይ ሂሳቦች ሊኖሩ ይችላሉ፣ አሠራሩ ለመ/ቤቱ ከተሰጠው ስልጣን ገደብ ውጭ ሂሳቦችን ከመዝገብ የመሰረዝ ሊሆን እንደሚችል በመግለጽ።

የሂሳብ ማስተካከያ ሲካሄድ ለሂሳቡ (ተከፋዩ) መነሻ የሆኑት የሂሳብ ማስረጃዎች ፣ ደብዳቤዎች ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ቀርበው ከተመረመሩ በኃላ ሲታመንባቸው መሆን እንደሚገባው፤ የማስተካከያዎቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ማስረጃዎች ማቅረብ ሲገባቸው የብዙ ዓመታት ናቸው ከፋይል ውስጥ ፈልጎ ለማገኛት ጊዜ ይወስዳል፣ በየሚሲዮኖቹ ነው የሚገኙት እየተባለ የተሰጡት ምክንያቶች፣ አሳማኝ ባለመሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ፣ እስከዚያ ሂሳቡ ወደ ነበረበት በተከፋይ እንዲመዘገብ (reversing entry) መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል።

መ/ቤቱ በላከው መልስ በበጀትና በቪዛ ሂሣብ መካከል በአንዱ በተሰብሳቢ (በተከፋይ) በሎላው መዝገብ ደግሞ በተከፋይ (በተሰብሳቢ) የተያዙ ሂሣቦች እንዲወራረድ ሲደረግ መነሻ የተየተደረገው የሂሳብ መርህ ሂሳቦቹ በየበጀት ዓመቱ የሚዘጉ በመሆኑና ለሶተኛ ወገን ከአንዱ ሂሳብ(በጀት ወይም ቪዛ) የተከፈለ ወጪ ሲተካ በቀጥታ በውጭ ምንዛሪ ምንዛሪ ወደ ሚሲዮኑ የማይላክ በመሆኑ የበጀት ከወጪ ቀሪ ወይም የቪዛ ገቢ ስም ፈሰስ ተደርጎ ሂሳቡ እንዲወራረድ የሚደረግበት አሰራር በመ/ቤቱ መኖሩን፤በዚህ አሰራር የተገኙ ማስረጃዎችን በመጠቀም እና Professional Judgement በማከል

ማስተካከያ ማድረጉን፤የሂሳብ የማስተካከያው የመቸረሻ ተጽዕኖ(effect) የመንግስትን የተጣራ ሀብት ለማሳደግ በመሆኑ ማስረጃ ያልተገኘላቸው ሂሳቦች ቢኖሩም እነዚህ ሆሳቦች በየበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሳብ ዝርዝር ላይ መታየታቸው ተከፋይ ሂሳቡን ባላንስ ከማሳበጣቸው በተጨማሪ አንድን ሂሳብ በተከፋይ ለመያዝ የሚቻለው መሟላት የሚገባው ዝርዝር መስፈርት ሲኖረው ብቻ በመሆኑ በመ/ቤቱ በአደራ ባንክ ባንክ እና በሌላ ባንክ ላይ በተሰብሳቢና በተከፋይ የተያዘው ሂሳብ inter company የሂሳብ በመሆኑ የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት ሲዘጋጅ እነዚህ ሂሳቦች ሊጣፉ ይገባ ስለነበረ የማስተካከያ ምዝገባ መካሄዱን ገልጸዋል፡፡

የተሰጠው መልስ አሳማኝነት የሌለውና መ/ቤቱ የበጀት መስሪያበ/ት መሆኑን ካለመረዳት የቪዛ፤ የኪራይ ገቢዎች ሰበሰበውን መ/በቱ በበጀት አመቱ እንዲጠቀምበት በመንግስት ከተፈቀደለት ውጪ ሊጠቀምበት እንደማይችል በህግ የተከለከለ በመሆኑ ባለው አሰራር ችግር ሲኖር በብድር ወደበጀት በማዞር እየተጠቀመ ምዝገባው በሰጪው ኤምባሲ በተሰብሳቢ በተበዳሪው ደግሞ በተከፋይ መመዝገቡ የinter company ግኑኝነት አለማለት አያስችልም፤ ተከፋይ ሂሳብ እንዳያብጥ በሚል የለበቂ ማስረጃ የተደረገው የማስተካከያ ምዝገባ ተቀባይነት የለሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

8.4 <u>ማስረጃ የሌለው የተከፋይ ሂሳብ ብር 75,580,355.44</u>

በ2005 በጀት በዓመት መጨረሻ በሰኔ30/2005 በሂሣብ ሪፖርት ከተመለከተው የተከፋይ ሂሣች ብር 179,361,280.26 ውስጥ ብር 165,333,128.20 የተወራረደ መሆኑ በተለገለጸልን መሠረት ሂሳቡ ሲጣራ ብር 75,580,355.44 በሰኔ 30 ቀን 2006 በተዘጋጀው የሂሣብ ሪፖርቶች በተከፋይ ያልተያዘና ለመወራረዱ ምንም አይነት ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ የሚ/ር መ/ቤቱን ትክክለኛ የሂሣብ እንቅስቃሴ እንዳያሳይ ሊያደርግና የመንግሥት ገንዘብ እን<u>ዲባክን</u> ሊያደርግ እንደሚችል በመግለጽ ያለምንም ማስረጃ ከተከፋይ መዝገብ የወጣውና በሪፖርት ሳይካተተ የቀረው የተከፋይ ሂሣብ ምዝገባው ወደነበረበት እንዲመለስ የበጀት ዓመቱ ሪፖርትም በዚህ መጠን እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

መስሪያ ቤቱ ከመውጫ ስብሰባ በሀኋላ ማሽረጃ አለኝ ብሎ ያቀረበውና ይህን እመልክቶ የሰጠው መግለጫ ሲታይ ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ ብር 43675964.02 በሚሲዮኖች መወራረዳቸውን ቀሪው ብር 31904391.42 ማስረጃ እንደሌለው በቀጣይ ኦዲት

እንደሚያቀርቡ ዳይሬክተሯ በሰጡት መግለጫ ገልጠዋል፡፡ ሚሲኖች በራሳቸው አወራረዱ የተባለው እንደሌሎቹ ሂሳቦች የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማስረጃዎች አልቀረቡም፡፡ ብር31904391.42 በቀጣይ እናቀርባለን የሚለው አስተያየት ሂሳቡን ከመዝገብ በመሰረዝና በሪፖርት እንዲገለጽ ባለማድረግ በመሆኑ የተሰጠውን መግለጫ አልተቀበልነውም፡፡

በኒውዮርክ በቀድሞ አንድ የሚሲዮን መሪ ወይም አምባሰደር በፓሪስ ቆይታቸው ለውሎ አበል፣ በቅድሚያ የተከፈለ አበል በመሳሰሉት ምክንያቶች በተሰብሳቢ የተያዘውን ብር 90,005.00 ለምን በተከፋይ እንደተያዘ በሠንጠረዥ ላይ በቂ ማብራሪያ የሌለው ግን አምባሳደሩ ከ2000-2002 በጀት ዓመት በሚል ሀረግ በ5004 የሂሣብ መደብ በተከፋይ የተመዘገበውን ብር 74,247.04 ከተሰብሳቢው ጋር በማገዳደል እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ ተከፋዩ በምን ምክንያት እንደተፈጠረ ምክንያቱ አልተገለጸም፣ ማስረጃ አልቀረበም፣አሰራሩም ከመንግስት ሂሳብ አሰራረ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከሀገር መከላከያ ሚ/ር ጋር መ/ቤቱ ባለው የስራ ግንኙነት በየሚሲዮኖቹ በመከላከያ ሚ/ር ሥም በተከፋይ እና በተሰብሳቢ የተያዙትን ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በማጣፋት/በማገደደል/ ሂሣቦች ከመዝገበ እንዲሰረዙ የተደረገ ሲሆን ይህም ያለ በቂ ማስረጃ መሆኑ ታውቋል፡፡ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በጅዳ ኤምባሲ በተከፋይ የተያዘን ብር 442,876.08 በዚሁ ኤምባሲ በተሰብሳቢ ከተያዘው ብር 2,611,498.60 ጋር እንዲጣፋ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በለንደን ኤምባሴ ብር 909,420.92 ፣በብራስልስ፣ በቴሌአቪቭ፣ በበርሊን፣ በፓሪስ እና በሌሎች ሚሲዮኖች ብር 1,066,556.43 እና በካርቱም ኤምባሲ ብር 15,258.24 በድምሩ ብር 3,023,100.97 በተከፋይ የተያዘው ከተሰብሰቢ ሂሳብ ጋር ተጣፍቶ መገኘቱን በመግለጽ አሰራሩ የመንግስት የሂሳብ አየየዝ ከሚፈቅደው ውጪ መፈጸሙንና ትክክለኛ ማስረጃ ለኦዲት ባለመቅረቡ ምዝገባው ወደ ነበረበት እንዲመለስ አሳስበናል፡፡

የጁቡቲ ኤምባሲ በ1999 በጀት ዓመት የኪራየ ሂሳብ ብር 570,384.47 /29,785.00 የአሜሪካን ዶላር / ወደ በጀት ተዛውሮ እንዲጠቀም ሲደረግ የኪራይ ሂሳብ በተሰብሳቢ በጀት በተከፋይ መመዝገቡን በመጥቀስ ሁለቱ ሂሳቦች እንዲጣፉ ተደርጓል ለዚህም በምክንያት የቀረበው የተጠቀሰውን ገንዘብ በኪራይ ገቢ ስም ቀደም ብሎ ለገ/ሂ/ል/ሚ/ር

ፈሰስ መደረጉ ተገልጿል። ይሁን እንጂ ገንዘቡ ፈሰስ ለመሆኑ ማስረጃው ባለመቅረቡ የተደረገውን ምዝገባ ለማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ ምዝገባው ወደነበረበት እንዲመለስ ወይም የተጠየቀው ማስረጃ እንዲቀርብ አሳስበናል።
በተመሳሳይ ሁኔታ፤

- በካናዳ ቶሮንቶ ኤምባሲ ብር 2,752,130.73
- በቴሌአቪቭ ብር 882,815.57
- በሮም ኢምባሲ ብር 1,046,600.25፤ ዱባይ ብር 3,825,647.26፣ፕሪቶሪያ ብር 2,036,196.17፣ በሰነዓ ብር 1,351,225.53 በኒዮርክ ብር 5,486,857.24 በበጀት፣በቪዛ እና በኪራይ ሂሳቦች በተከፋይ የተያዙት ከተሰብሳቢ ሂሳብ ጋር የተጣፉ
- በጄዳ ኤምባሲ ብር 384,599.91
- ለሞስኮ ሚሲዮን ቀደም ላሉት ዓመታት ለሚሲዮኑ ቢሮ የተላከው ኪራይ በተከፋይ ተይዞ የሚገኘው ብር 11,200,643.50 (የአሜሪካን ዶላር 584,890) ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ እንዲደረግ በተሰጠው ውሳኔ ሂሳቡ ከተከፋይ ሲወጣ ገንዘቡ ፈሰስ ለመደረጉ ማስረጃ ለኦዲት አልቀረበም።
- በዋሽግተን ብር 5,357,164.20
- በፓሪስ አምባሲ ብር 515,000.00
- በጄዳ ኤምባሲ ብር 448,973.83

ተከፋይ ሂሳቦቹን ከተሰብሳቢ ሂሳቦች ጋር ማጣፋት የመንግስትን የሂሳብ አሰራር ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ በማስረጃ ያልተደገፉና ሂሳቦቹን ከመዝገብ እንደመሰረዝ እንደሚቆጠር በመጥቀስ ሂሳቦቹ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ (reversing entry) የምዝገባ ማስተካከያ ሊሰራላቸው እንደሚገባ አሳስበናል።

መስሪያ ቤቱ በላከው መልስ ማስረጃዎች እንዳሉት ገልጧል። በተደረገው የመውጫ ስብሰባ በቀጣዩ ኦዲት ሊረጋገጥ እንደሚችል ስምምነት ላይ ተደርሷል።

- በአራት ሚሲዮኖች በተከፋይ በክሬዲት ተመዝግቦ የነበረውን ብር 688,645.96 በየሀገሩ የውጭ ምንዛሬ ባንክ ሂሳብ ቁጥሮች 4102-03-05 ክሬዲት በማድረግ ለባለጥቅሞቹ እንደተከፈለ ተከፋዩ እንዲጣፉ ለተደረገው ተገቢው ማስረጃ

አልቀረበም፡፡ ዕቃ ማጓጓዣ SEK 18806 የከፈሉበት ደረሰኝ እና የመሳሰሉት ለኦዲት አልቀረቡም፡፡

- ለናይሮቢ ኤምባሲ ሰኔ 15 ቀን 2005 በቁጥር EMR 01/10/9/10 የፋክስ መልዕክት ብር 569,891.17(USD 29,759.33) ለ4ኛው ዙር ስራ ማስኬጃ የሚሆን ከቪዛ ወደ በጀት አዛውረው እንዲጠቀሙ ዋናው መ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በጀት ለቪዛ በተከፋይ የያዘውን ምዝገባ ለማረጋገጥ የመጀመሪያው ሰነድ(የገቢ ደረሰኝ ባለመቅረቡ)፣ በበጀት ሂሳብ ተከፋዩ በትክክል መመዝገቡን ማረጋገጥ አለመቻሉን፡፡
- ብር1,022,152.67 ከቪዛ ገቢ ወደ በጀት አዛውረው እንዲጠቀሙ ከዋናው መ/ቤት በተላላፈ የፋክስ መልዕክት በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 6325 በ21/08/13 የቪዛ ገንዘብ በማለቁ ተከፋዩን ዴቢት ባንክን ክሬዲት በማድረግ የተደረገውን ምዝገባ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ፡፡

በማስረጃ ያልተደገፈ የሂሳብ ማስተካከያ መሥራት በመ/ቤቱ ሀብት ላይ ጉዳትን፣ የሚያስከትል በመሆኑ ማስረጃዎቹ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ለሂሳቡም ቀደም ወደ ነበረበት ምዝገባ እንዲመለስ (reversing) ምዝገባ ሊሰራ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

መስሪያ ቤቱ ማስረጃዎች አሉኝ ቢልም ባለመቅረቡ በመውጫ ስብሰባ ወቅት በቀጣይ ኦዲት እንዲታይላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

- ለአቡጃ ኤምባሲ ከዋናው መ/ቤት በተላለፈ አስቸካይ የፋክስ መልዕክት ብር 824,575.65 (ኔራ 6,814,674.80) በሚስዮን ፕሮጀክት (የቢሮ ግንባታ) በሚሰራበት ጊዜ በሪቴሽን በተከፋይ የተያዘው ለዓመታት በመዝገብ የሚገኝ ሂሳብ መሆኑን የሚንስቴር መ/ቤቱን ሀብት ማፍራትና ህንጻ አስተዳደር ባለሙያዎችን ፋይናስ ዳይሬክቶሬቱ አነጋግሮ በሪቴንሽን በተከፋይ የተያዘውን ገንዘብ ከአሁን በኃላ ለህንጻ ተቋራጩ የሚከፈልበት ሁኔታ እንደማይኖር እንደገለጸላቸው በመጥቀስ ሂሳቡ በሪቴሽን በተከፋይ የተያዘው(5061 ዴቢት ሲደረግ የተጣራ ሀብት (5601)ክሬዲት እንዲደረግ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተከፋዩ አላግባብ ተሰርዞል፡፡ በተሰጠው አስታየት መሰረት የህንጻ ተቋራጩ የሚጠይቅበት ሁኔታ ካለ በልዩ ልዩ ገቢ ወይም በሌላ እርዕስት በገቢ የሂሳብ መደብ ገቢ ሆኖ ክሬዲት

መሆን ያለበት የገቢ ሂሳብ መደብ መሆን እንዳለበት እና ገንዘቡም ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል ። ለተከፋይ ምዝገባ መነሻ (መሰረት)የሆኑትም ሰነዶች ለኦዲት አልቀረበም።

- ህዳር 11 ቀን 2006 በቁጥር EMt 4/10/1/06 ከዋናው መ/ቤት ለቴሌአቪቭ ኤምባሲ በተላለፈ አስቸካይ የፋክስ መልዕክት ብር 511,442.81 (107,403) ተከፋይ 5002 ዴቢት በማድረግ የተጣራ ሀብት(5601) ክሬዲት ተደርጎ የተከፋይ ሂሳብ እንደወራረድ ሲደረግ መጀመሪያ ከቪዛ ሂሳብ ወደ በጀት ገንዘቡ ሲተላለፍ የተደረገውን ምዝገባ ለማጣራት ፣ለምዝገባው መሰረት የሆኑት ሰነዶች ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ማጣራት አልተቻለም።

- መጋቢት 3 ቀን 2006 በቁጥር EMB 2/2/20/06 ዋናው መ/ቤት ለብራሰልስ ኤምባሲ ባስተላለፈው አስችካይ የፋክስ መልዕክት ሰኔ 21 ቀን 2005 ከሚያዝያ 1 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ ያለው የድፕሎማቶች የሎካል ሰራተኞች ደመወዝ የአንደኛው ወር ድርሻ ብር 3,265,552.94(ዩሮ 126,817.59 በድጋሚ መላኩንና በሚስዩኑ የበጀት ሂሳብ በተከፋይ መመዝገቡን በዋናው መ/ቤት በኩል በተሰብሳቢ አለመያዙን በመግለጽ ሚሲዮኑ በተከፋይ በ5002 የሂሳብ መደብ የመዘገቡትን ዴቢት አድረጎ የተጣራ ሀብትን (5601) ክሬዲት እንዲደረግ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ምዝገባው ተካሂዶ ተከፋዩ ተጣፍቷል። ይሁን እንጂ ይህ ገንዘብ በድጋሚ የተላከ ስለሆነ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ የሚገባው በመሆኑ ተከፋይ ዴቢት ባንክን ክሬዲት በማድረግ ለዋናው መ/ቤት ተልኮ ዋናው መ/ቤትም ለሚመለከተው ሚኒስቴር መ/ቤት ፈሰስ ማድረግ ይገባዋል።

የማስተካከያ ምዝገባ ለተደረገለት ማስረጃዎች ሊቀርቡ እንደሚገባ በማስረጃ ሳይደገፍ ማስተካከያ የተሰራለት ሂሳብ ቀድሞ ወደ ነበረበት (reversing) ምዝገባ እንዲመለስ ማስተካከያ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል።

9. ሚሲዮኖች ስለሚጠቀሙበት ሶፍትዌር

በውጭ ጉዳይ ሚ/ር ስር ያሉ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች የፋይናንስ ምዝገባ የሚከናወንበት ሶሊየል ፋይናንሽያል ሶፍትዌር /Soliel Financial Softwear/ ምዝገባውን በሶፍት ኮፒ አግኝቶ ሁሉንም ኢምባሲዎች በንሞና /Sample/ አካቶ በኦዲት አሰራራችን መሰረት በኦዲቱ ለማየት አልተቻለም ባለፉት 4ዓመታት በተደጋጋሚ ይህን ጥያቄ ብናቀርብም ሶፍትዌሩን የሰራው ሰው ዋሽንግተን ነው በሚል ሶፍት ኮፒው ሊሰጠን አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ኋላ ቀር በሆነ አሰራር በብሎክ የንሞና ዘዴ ለመስራት መገደዳችንን፤ በመግጽ የኦዲቱን ስጋት ሊቀንስ በሚችል መልኩ ኦዲቱ እንዲከናወን እና ሁሉንም ኢምባሲዎች እንዲሸፍን ለማስቻል በሶፍትዌሩ የተደረጉ ምዝገባዎች እንዲደርሱን መ/ቤቱ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

መ/ቤቱ በላከው መልስ ይህን አስመልክቶ ጥናት ማስጠናቱን ኢፍሚስ ስራላይ ሲውል ችግሩእንደሚፈታ ከመግለጽ ውጭ እየተጠቀመበት ያለው ሶፍት ዌር ለኦዲቱ የሚቀርብበት ሁኔታን ዝግ አድርጎታል፡፡

10. የክትትል ኦዲት

10.1 ግኝት

- የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች በዋናው መ/ቤት ስም ተይዞ የነበረውን የተሰብሳቢ ሂሳብ በትክክል ያወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 201,904.24 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በበጀት ዓመቱ ውስጥ መ/ቤቱ ከቪዛ ገቢ እንዲጠቀም ከተፈቀደው ሂሳብ እንዲተካ ተደርጎ (ተወራርዶ) ተገኝቷል፡፡
- ብር 1,853,939.53 በነገቲቭ (ክሬዲት) ተመዝግቦ የተገኘ የተሰብሳቢ ሂሳብ በተመለከተ የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን በማብራሪያ ቢገለፅም የማስተካከያ እርምጃ በትክክል የተወሰደ ለመሆኑ ማስረጃ ባለመቅረቡ ማረጋገጥ አልተቻለም፤
- ብር 3,098,228.89 በነገቲቭ (ዴቢት) ተመዝግቦ የተገኘ የተከፋይ ሂሳብ በተመለከተ የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን በማብራሪያ ቢገለፅም የማስተካከያ እርምጃ በትክክል የተወሰደ ለመሆኑ ማስረጃ ባለመቅረቡ ማረጋገጥ አለመቻሉንና በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ

ካልተወሰደ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ባክኖ ሊቀር እንደሚችል በመገረለጽ፡፡

በ2005 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ በድጋሚ አሳስበናል፡፡ መስሪያ ቤቱ በላከው መልስ ማስረጃዎች ቀርበዋልና ተስተካክሏ ከማለት ውጪ ከመውጫ ስብሰባ በፊትም ሆነ በኋላ ማስረጃዎቹ ታይተው የተማሉ ባለመሆናቸው አስተያየታችንን የሚያስቀይር ሆኖ አላገኘነውም፡፡

11. <u>ልዩ ልዩ</u>

11.1 <u>የውስጥ ቁጥጥርን በተመለከተ</u>

- በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ብር 1,070,340.84 ያዘጋጀውም ሆነ ያፀደቀው ስምና ፊርማ ሳይኖረው በኃላፊ ሳይፀድቅ ማስተካከያው ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በወንጀል መከላከል ዘርፍ እንዲቀበሉ በተወከሉ ሰዎች ስም የደመወዝ መክፈያ ፔይሮል ተዘጋጅቶ ብር 116,082.55 በውክልና ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- በብሔራዊ አክረዲቴሽን ጽ/ቤት ለነዳጅ ግዥ ብር 1,371.54 ወጪ ሆኖ ለተከፈለው ወጪው በሚመለከተው ኃላፊ ያልጸደቀ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡
- በታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሄራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት በክፍያ ማስመሰከሪያ ላይ ብር 10,000.00 ለተመዘገበው ወጪውን የፈቀደውና ገንዘቡን የተቀበለው ሰው ፊርማ ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ፈቃጅ እና ገንዘብ ተቀባይ በተመሳሳይ ፊረማ ተፈርሞ መገኘቱ፤

ብሔራዊ መረጃ ደህንነት

የድጋፍና አገልግሎት ዘርፍ በበጀት ዓመት ለኦዲት በቀረቡት የወጪ ማስመስከሪያዎች ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ሠራተኛ/ ኃላፊ በፊርማ የማይረጋገጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በተሟላ የሰው ሃይል እየሰራ አለመሆኑ፤

- ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት

- የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ

በፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን የወንጀል መከላከል ዘርፍን በተመለከተ ደመወዝ በውክልና ሲከፈል በፔሮል ላይ በቋሚነት መመዝገብ ያለበት የወካይ ስም እንጂ የተወካይ ስም ሊሆን እንደማይገባ፤ ተወካይ የደብዳቤው ግልባጭ እንዲደርሰው ተደርጎ ወይም በደመወዝ ከፋይ ክፍል እንዲቀመጥ ሊደረግ እንደማይገባና አሰራሩ ክፍተት የሚፈጥር በመሆኑ ዘርፉ ደመወዝ ሲከፈል ተወካይ ሲፈርም ስለ ብሎ እንዲፈርም በማድረግ እንዲታረም አሳስበናል፡፡ እንዲሁም የወጪ ሂሳብ ምዝገባ ሲከናወን ስለምዝገባውም ሆነ ስለማጽደቁ የሚመለከተው አካል ወይም የሚመለከተው ኃላፊ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

11.2 የክትትል ኦዲት

11.2.1. በኢትዮጵያ ጨ/ጨ/ል/ኢ በ2005 በጀት ዓመት የኢንስቲትዩቱ ቋሚ ንብረቶች አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ በዩኤስ ዶላር 1,306,105 ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ የኢንስቲትዩቱ የሆኑ ቋሚ ንብረቶች ያለአገልግሎት ከአራት አመት በላይ በመጋዘን ተቀምጠው ተገኝተዋል፡፡ ጉዳዩ በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም አገልግሎት ላይ አለመዋሉ ታውቋል፡፡ ንብረቶቹ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው ለንብረቶቹ የወጣውን ወጪ ለኪሳራ የሚዳርግና ከንብረቶቹ የሚገኘውን ጥቅም የሚያሳጣ መሆኑን በመግለጽ ኢንስቲትዩቱ ተከላውን በማከናወን ንብረቶቹ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ በድጋሚ አሳስበናል፡፡

ኢንስቲቲዩቱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት የተከላና ኮሚሽኒንግ የወጣው ጨረታ በአስቸኳይ ተግባራዊ እንዲደረግ ለሚመለከታቸው ለምርምር ላቦራቶሪ እና ለፋይናንስና ሎጀስቲክስ ዳይሬክቶሬት መመሪያ መስጠቱን ገልጿዋል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር

1. በበጀት ዓመቱ የሰሜን ዕዝ ጠቅላይ መምሪያ ከልዩ ልዩ ገቢዎች የሰበሰበው ገንዘብ በገቢ ተመዝግቦ ለመንግስት ገቢ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ከጨረታ ሰነድ ሽያጭ ብር 62,226.33፣ በዕዙ ሆስፒታል ከሚታከሙ የሲቪል ሰራተኞች 50% የህክምና አግልግሎት ብር 38,117.43፣ ከመደሃኒት ሽያጭ ብር

47,495.62፣ የተለያዩ የሰራዊት አባላት በንብረት ላይ ላደረሱት ጥፋት የከፍሉ ምትክ የንብረት ግምት ብር 389,114.55 እንዲሁም በጨረታ ውሉ መሰረት ባለመፈጸማቸው ከአቅራቢዎች የተሰበሰበ ቅጣት ብር 10,408.05 በድምሩ ብር 547,361.98 እንዲሁም በሁርሶ የመሰረታዊ ውትድርና ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ በድምሩ ብር 26,880.86 በገቢ አርዕስት 1485/1489 ሌሎች ልዩ ልዩ ገቢዎች መመዝገብ እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈሰስ መደረግ ሲገባው በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5054 ሌሎች መያዣዎች ተመዝግቦ በሀገር መከላከያ ሚ/ር በኩል ለልዩ ገቢ መምሪያ ገቢ በመደረጉ አሰራሩ እንዲስተካከል በተሰጠው አስተያየት መሠረት ሚ/ር መ/ቤቱ እንዲታረም ለክፍሎች ደብዳቤ በመጻፍ አሳውቋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ መንገድ የተሰበሰበው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ እንዲሆን አልተደረገም፡፡

2. የአየር ሀይል ጠቅላይ መምሪያ የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት አላማ ለማዋሉ ኦዲት ሲደረግ ጠቅላይ መምሪያው ለራሱ የግንባታ ስራ ላልሆነ ለቢሾፍቱ ከተማ የቤተ መጻሐፍት ግንባታ በፒቪ ቁጥር 53710 ብር 149,239.28 እና በፒቪ ቁጥር 54050 ብር 348,224.97 በድምሩ ብር 496,464.25 ወጪ ተደርጎ መገኘቱን በመጥቀስ ተቋሙ ይህን ግንባታ እንዴት ሊገነባ እንደቻለ የሚገልጽ ማስረጃ ለኦዲት ስራ ሊቀርብ ባለመቻሉ ወጪው አግባብነት የሌለው መሆኑ ተጠቅሶ ከሚመለከተው ተመላሽ እንዲሆን አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡

3. ዘርፉ ከመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ጋር በገባው የመቀሌ አፓርትመንት ግንባታ ስራ ብር 34,047,349.38 የተጨማሪ ስራ ውል እንደሆነ በክፍያ የምስክር ወረቀት ቁጥር (14፤15 እና 16) በተገለጸው መሰረት ለብር 5,385,049.56 የተጨማሪ የስራ ውል ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ለብር 28,662,299.82 ለሚሆነው ስራ ተጨማሪ የስራ ውል ማስረጃ ለኦዲት ያልቀረበ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ እንዲጣራ ብናሳስብም የተወሰደ እርምጃ የለም፡፡

4. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቀረበው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

- በሂሳብ መደብ 4201 ቅድሚያ ክፍያ ከብር 18,708,030.10 ውስጥ ብር 11,593,098.46 የፋይናንስ ዳይሬክቶሬት፣ ብር 1,512,851.12 በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ እና ብር 49,335.99 በሰሜን ዕዝ ጠቅላይ መምሪያ ቀሪው ብር 5,844,370.95 በተለያዩ መምሪያዎች እና እዞች በጠፋ እና በወደመ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ በተለይ በፋይናንስ ዳይሬክቶሬቱ ለታየው ብር 11,593,098.48 ደጋፊ ማስረጃዎቹና ዝርዝሩ ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የሂሣቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን፣
- በሂሳብ መደብ 4210 የሌሎች መ/ቤቶች ቅድሚያ ክፍያ ከተያዘው ብር 61,758,074.53 ውስጥ ብር 45,000,000.00 ካልተከፈል የሠራዊት ደመወዝ ለዠቋላ ሰቲል ሮሊንግ ፋብሪካ በ2004 በብድር ተሰጥቶ ያልተተካ፣ በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ብር 5,865,872.05፣ በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ብር 495,102.08 እና በሰሜን ዕዝ ጠቅላይ መምሪያ ብር 419,670.71 ለረጅም ጊዜ በተሰብሳብ ሂሣብ ተይዞ መገኘቱን፣
- በሂሳብ መደብ 4211 የግዥ ሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ ከተያዘው ብር 6,703,891.21 ውስጥ ብር 4,093,372.83 የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ አባላት ወደ ውጭ አገር ሲሄዱ ለውሎ አበል በቅድሚያ ተከፈሎ ያልተወራረደ፣ ብር 336,244.73 በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት፣ ብር 728,662.48 በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ እና ብር 30,006.72 በሰሜን ዕዝ ጠቅላይ መምሪያ ለረጅም ጊዜ በተሰብሳቢ የተያዘ መገኘቱን፣
- በሂሳብ መደብ 4251 የሥራ ተቋራጭ ቅድሚያ ክፍያ ከተያዘው ሂሳብ ውስጥ ብር 2,970,000.00 በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ለረጅም አመታት በተሰብሳቢ የተያዘና ጠቅላይ መምሪያው ከደጀን አቪዬሽን ጋር የግንባታ ውል ገብቶ በቅድሚያ የተከፈለና በ2003 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ተሰጥቶበት እርምጃ ያልተወሰደበት ሆኖ መገኘቱን፣

- በሂሳብ መደብ 4253 ለዕቃ አቀራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ ከብር 26,774,019.73 ውስጥ ብር 24,365,855.88 ከ2003 በጀት አመት ጀምሮ በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በኩል ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ በተሰብሳቢ የተያዘ መገኘቱን፣

በመግለጽ ሂሳቡ እንዲሰበሰብ/እንዲወራረድ ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም የተወሰደ እርምጃ የለም፡፡

5. በሰኔ 30/2005 የሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ መደብ 5004 የደመወዝ ተከፋይ ብር 198,888,924.20 ደመወዛቸውን ባለመውሰዳቸው ለረጅም አመታት በተከፋይ የተያዘ ተገኝቷል፡፡ ይህ ሂሣብ በመንግሥት የሂሣብ አሠራር መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጐ ጥያቄው ሲቀርብ የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴርን በመጠየቅ መከፈል ሲገባው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ለዓመታት ሳይከፈል መቀመጡ አግባብ ሆኖ አለመሆኑን፣

    - በሂሳብ መደብ 5021 ለሠራተኞች ተከፋይ ሂሳቦች ብር 1,831,070.50 በአየር ኃይል ጠቅላያ መምሪያ ለረጅም ጊዜ በተከፋይ የተያዘና ማስረጃ የሌለው መገኘቱን፣
    - በሂሳብ መደብ 5028 በመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ከተያዘው ብር 2,417,120.51 ውስጥ ብር 728,099.61 በአየር ኃይል ጠቅላያ መምሪያ የተያዘና ሲሆን ማስረጃ እንደሌለው እና ቀሪው ብር 1,689,020.90 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ ዕዞችና መምሪያዎች ለረጅም ጊዜ በተከፋይ ተይዞ መገኘቱን፣
    - በሂሳብ መደብ 5054 ሌሎች የመያዣ ሂሳቦች ከተያዘው ብር 40,726,354.99 ውስጥ ብር 10,451,616.94 በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት እና ቀሪው ብር 30,274,738.05 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ ዕዞችና መምሪያዎች ለረጅም ጊዜ በተከፋይ ተይዞ መገኘቱን፣

6. ማንኛውም መስሪያ ቤት በግዥም ሆነ በስጦታ ያገኘውን ንብረት ገቢ ማድረግ ያለበት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባሳተመው የንብረት ገቢ ደረሰኝ(ሞ/19) ወይም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ በሚዘጋጅ የንብረት ገቢ ደረሰኝ

እንደሆነ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር መመሪያ ያዛል፡፡ ነገር ግን የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ የሚኒስቴሩን ስምምነት ሳይጠይቅና ፈቃድ ሳያገኝ መመሪያውን በመተላለፍ በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ስም በታተመ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የሚገለገል መሆኑ መታወቁን፣

በመግለጽ አስተያየት ቢሰጥም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን ለኦዲቱ ትኩረት አለመስጠትና የተጠያቂነት መርህን ባለመገንዘብ ሊሆን እንደሚችል በመጥቀስ በተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ተወስዶ ተሰብሳቢ ሂሳቦች እንዲወራረዱ፣ ማስረጃ የሌላቸው እንዲቀርብላቸው፡፡ አላግባብ ለዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ፋብሪካ የተሰጠው ብድር ላለፉት 3 ዓመታት ሳይመለስ በመገኘቱ እንዲሰበሰብ፣ ተከፋይ ሂሳቦች ላይም እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ አሳስባናል፡፡

<u>**መ/ቤቱ በላከው መልስ**</u>

በ2005 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝት በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት የተወሰደ እርምጃ በተመለከተ፡-

1. የመከላከያ ገቢዎች ዳይሬክቶሬት ገንዘቡን እንዲመልስ በማድረግ ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ/ር በባንክ የወጪ ማዘዣ ቁጥር 004925 ፈሰስ ተደርጓል፡፡

2. ገንዘቡን የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ሰብስቦ በመመለሱ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ ተደርጓል፣

3. ሰነዶችን የማጣራትና የማደራጀት ስራ እየተሰራ ሲሆን ተጣርተው በተወሰነ ደረጃ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ከምዝገባ እንዲሰረዙ ከተላኩ ሰነዶች ውስጥ ደጋፊ ማስረጃዎችንና የህግ ይሁንታን የማግኘት እንድናቀርብ በተሰጠን ትዕዛዝ መሰረት የማጣራት ስራ እየሰራን ቢሆንም ማስረጃዎችንና ሰነዶችን የማጣራትና የማሰባሰብ ስራ ረጅም ጊዜ የሚወስድና አንዳንዶችም የታጠፉ ወይም የፈረሱ ወይም የተዋሃዱ የስራ ክፍሎች ስላሉ ሰነድ የማደራጀት ስራው ጊዜ እንደሚወስድ ገልጸዋል፡፡

   በሰነድ እንዲወራረድ ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲወራረድ ማስረጃ የማሰባሰብ ስራ እየተሰራ መሆኑን፣ አብዛኛው ሂሳቡ እንዲወራረድ የተደረገ ሲሆን ቀሪው እስከ ሰኔ/2007 እንዲወራረድ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

4. በአገር ደህንነት ላይ አደጋ ሊጥሉ የሚችሉ መረጃዎችን በመከላከያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 809/06 በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ክቡር የመከላከያ ሚኒስትር በደብዳቤ ቁጥር መ1/ጠ3/ተ/1/15/06 ባወጡት መመሪያ መሰረት ተቋሙ ለኦዲትና ለሶስተኛ ወገን የማይቀርቡ ሰነዶች ተለይተው ቀርበዋል፡፡

   እስከ ሰኔ/2007 ዓ.ም. በምዝገባው መሰረት ሰነዶችን የማጣራት ስራ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

5. እስከ ታህሳስ/2007 ዓ.ም. ተቋሙ የሚጠቀምባቸውን ሞዴሎች ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ለማስፈቀድና ለማጸደቅ ሞዴሎችን የማጥራትና መገምገም ስራ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	ፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን	26/3/2007	1,136,800,073.00	274,576,834.00	1,411,376,907.00
2	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	22/4/2007	119,092,550.00	42,703,090.67	161,795,641.00
3	የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮምሽን	12/3/2007	42,306,050.48		42,306,050.48
4	ኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት	2/3/2007	15,406,666.67		15,406,666.67
5	የኢትዮጵያ አክርዲቴሽን ጽ/ቤት	5/2/2007	7,929,230.00		7,929,230.00
6	የታላቁ ህዳሴ ግድብ ብሔራዊ ማስተባበሪያ ምክር ቤት ጽ/ቤት	4/1/2007	6‹222‹940.00		6,222,940.00
7	የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት	21/4/2007	8,277,307.50	11,385,622.03	19,662,929.53
8	የፕራይቬይታዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን	23/12/06	24,006,100.00		24,006,100.00
9	በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	13/1/06	17,024,357.00		17,024,357.00
10	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶቸ	30/3/07	318,925,263.20	450,000,000.00	768,925,263.20
11	በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት		101,611,609.76		101,611,609.76
			375,456,378.34		375,456,378.34
12	የፍትህና የሕግ ስርአት ምርምር ኢንስቲትዩት	30/2/07	8,741,100.00		8,741,100.00
13	የኢንፎርሜሽን መረብ ኤጀንሲ	21/2/07	197,756,046.00		197,756,046.00
14	ኢትዮዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	10/4/007	18,298,240.00		18,298,240.00
15	የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር	02/3/007	9,653,330.00		9,653,330.00
16	የኢትዮጵያ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	4/4/2007	105,653,418.27		105,653,418.27

17	የፍተህ አከላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል	7/1/2007	10,383,880.00		10,383,880.00
18	የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን	21/01/07	21,530,511.10		21,530,511.10
19	የፌዴራል መሬትና መሬት ነክ ምዝገባ ኤጀንሲ	10/2/2007	12,006,900.00	-	12,006,900.00
20	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ	17/02/07	106,319,909.00		106,319,909.00
21	የፌዴራል ንግድ ሚኒስቴር	2/3/2007	60,907,502.00	31,645,832.00	91,553,134.00
22	የፌዴራል ፍትሕ ሚ/ር	17/03/07	65,263,463.00	60,727,820.00	125,991,283.0
23	የፌ/ጥ/አ/ኢ/ኤጀንሲ	10/3/2007	35,018,300.00		35,018,300.00
24	የሠነዶች ማ/ም/ጽ/ቤት	7/1/2007	42,907,860.00		42,907,860.00
25	የኢትዮ.ጨ/ጨ/ኢ/ል/ኢኒስቲቲዩት	14/01/07	30,750,060.00	101,911,680..00	132,661,740.00
26	የንግድ ው/ሽ/ጥ/ባለስልጣን	19/12/07	16,275,402.00	-	16,275,402.00
27	የብረታብረት ኢንዱስተሪ ል/ኢ.	16/01/o7	19,247,852.00	23,734,000.00	42,981,852.00
28	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	6/2/2007	18,574,240.00	-	18,574,240.00
29	የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል	22/12/2006	10,380,600.00	-	10,380,600.00
30.00	የሆቴልና ቱሪዝም ማ/ ኢኒስቲቲዩትየሆቴልና	28/12/06	24,505,086.00		24,505,086.00
31	የአትዮ. ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም	27/04/07	32,840,394.00		32,840,394.00
32	የግል ድ/ሠ/ማ/ዋ/ኤጀንሲ	23/12/06	21,001,560.00		21,001,560.00
33	የሀገር መከላከያ ሚ/ር	16/03/07	7,500,000,000.0		7,500,000,000.0
34	የውጭ ጉዳይ ሚ/ር	23/01/07	1,970,121,936.0	84,625,339.00	1,181,747,275.00